ይስማዕከ ወርቁ



# የኦጋዴን ድመቶች

# የኦጋዴን ድመቶች

ይስማዕከ ወርቁ

19/10/2009
At ZEWAY
"I am going to HAWASS before Ariba minch"
page 47

አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ፡ ፪፻፱ ዓ.ም

All Rights Reserved to Yismake worku.
ዘፈሐቆ ወዘሰረቆ በስልጣነ ኪን ወጥበብ
ውጉዝ ለይኩን። © ይስማዕከ ወርቁ-፳፻፲

# OGADEN

## A NOVEL BY YISMAKE WORKU

የመጀመሪያ ዕትም ሐምሌ ፳፻፲ ዓ.ም.

ዲዛይን፦-ዶርቶጋዳ ማተሚያ ድርጅት
Email;- ramatohara@gmail.com
ሽፋን፦- ስንታየሁ ብርሃኑ

# ሐተታ

ከደራሲ ይስማዕከ ወርቁ ሥራዎች ውስጥ ክቡር ድንጋይ ለእኔ ወደር የሌለው ድርሰት ነው። ምልአቱ፣ የኢማጅኔሽን ምጥቀቱና ሽሙጡ…ግሩም ያስብላል። ይህንን ቀደም ሲል በዛው ድርሰት ላይ ሁተታ የመፃፍ እድል ተሰጥቶኝ ለመግለፅ ሞክሬአለሁ። ይስማዕከ ወርቁ የግዕዝና የቅኔ ቤት እውቀቱን ገና ዝቆ እንዳልጨረሰው በዚህ የኦጋዴን ድመቶች በሚል ባበረከተልን ድርሰቱ እንደገና አረጋግጦልናል። በክቡር ድንጋይ የምናውቀው ዲዲሞስ ዶሬ በኦጋዴን ድመቶች ውስጥም የገጠመውን አስደናቂ ታሪክ ይተርክልናል። ሁለቱን ሥራዎች እንደተከታታይ ሥራዎች መቁጠርም አለመቁጠርም የሚቻል ይመስለኛል። ጥቂት ሰበዞች ብቻ ናቸው የሚያያይዟቸው። ጥቂት ክሮች ብቻ ናቸው ከክቡር ድንጋይ ተስበው ኦጋዴን ውስጥ የምናገኛቸው። ከዋናው ባለታሪክ ከዲዲዲሞስ ዶሬ እና ከጥቂት የህይወቱ ቁጢቶች በቀር ኦጋዴን የዘለቀ የለም። እርሱ ራሱም ከእስማት አለሙ ለመውጣት ነበር ወደ ኦጋዴን ራሱን በስራ ለመወጠር የዘለቀው። ይሁን እንጂ እዛ ደግሞ ሌላ ፈተና ያጋጥመውና ወደ እስማት ዓለሙ አዙሪት ሳያስበው ይገባል።

ይስማዕከ ወርቁ በዚህኛው የኦጋዴን ድመቶች ሥራው በአስገራሚ ቴክኒኩ ኦጋዴንን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ባስደናቂ የመግለጽ ችሎታው በረሃው እንዲያቃጥለን፣ ሰቆቃው እንዲሰቀን፣ ባሩዱ እንዲሸተን ያደርገናል። በስነፅሁፋችን ውስጥ ሳይቀር ለዘመናት የተረሳውን የኦጋዴንን ማህበረሰብ ስነ ልቡና፣ ከጎሳው እስከ አበሳው

በጥልቀት ያስቃኘናል፡፡ ለዘመናት የተፈራረቀበት የጦርነት ግሳት ለምን እንደሆነ ከነዳጁ ገደሎቹ እስከ ታላላቅ ሰዎቹ ቁልጭ አድርጎ ስሎልናል፡፡ በረሃው ውስጥ እያስጓዘ አብረን የተራመድን ያህል እያንዳንዷን ጓዳ ጎድጓዳ ያሳየናል፡፡ ችግሩን ብቻ አያሳየንም፤ እንደ ጥናታዊ ፅሁፍ መፍትሄውንም ጭምር ያመላክተናል፡፡ በገጸ ባህርያቱ መካከል የሚደረገው ንግግር በቴሌፓቲ መሆኑም ሌላ አዲስ እይታ ነው፡፡

ይስማዕከ ወርቁ ወደ ኦጋዴን እየተመላለሰ ለዚህ ሥራው ጥናት ሲያካሂድ እስራትን ጨምሮ ለህይወቱ አስጊ የነበሩ ፈተናዎችን አልፏል፡፡ እድለኛ በመሆኑ እንጂ ወደ ኦጋዴን ከዘለቁ አጥኚዎችና ጋዜጠኞች ውስጥ በሰላም የሚመለሱት ጥቂቶቹ ብቻ እንደሆኑ ይነገራል፡፡ ይህ የሚያሳዬን በዚህ ትውልድ ውስጥም ተስፋ ማድረግ እንደምንችል ነው፡፡ ይስማዕከ ወርቁ ይህን ብቻም ሳይሆን ሌሎች የሚወረወሩበትን ጦሮችና ፈተናዎች ሁሉ በጽናት እያለፈ ሥራዎቹ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉን ስመለከት፣ የታላላቆቹ አባቶቻችን ፅኑ መንፈስ እንዳልተለዩን አረጋግጫለሁ፡፡ ይህ የኦጋዴን ድመቶች የተሰኘው ሥራውም የዚህ ፅናቱ ምልክት ነው፡፡ ያንን የተዘነጋ ምድር በጥልቀት ለማዎቅና እንደገና ከይስማዕከ ወርቁ እፁብ ድንቅ አለም ውስጥ ገብቶ ለመሰንበት ለአንባብያን የኦጋዴን ድመቶችን ጋብዤ ላብቃ፡፡

ዶ/ር አድማሱ መሸሻ

በድጋሚ የወጣ ማስጠንቀቂያ

በመፅሐፉ ውስጥ የሚገኙትን የአስማት ቃላት በመሞከር ለሚፈጠረው ችግር ደራሲው ኃላፊነት አይወስድም፡፡

"ከአገሬ አፈር የሚደባልቅ ቤልጅግና ጎራዴ ይዤ እንጂ ጫት ተሸክሜ የምመጣ እንዳይመስልህ!"

ኡመር ሰመተር

# ፩

ለዓመታት ከተዘፈቅኩበት የእስማት ዓለም ውስጥ ለመውጣት ያላደረኩት ጥረት አልነበረም። የዛሬው ጉዞዬም የሙከራዬ አንዱ አካል ሆኖ ሊቆጠር ይችላል። ጭንቅላቴን እንደ አበያ በሬ በሌላ ሥራ ጠምጄ ላቀናው አጋዴን ገብቻለሁ። የሥራን ያህል ፈዋሽ መድኃኒት እስከ አሁን የትኛውም ኬሚስት አልቀመመም። የትኛውም ስር ማሽ የትኛውም ቅጠል በጣሽ ደብተራ፣ እንደ ሥራ ፈዋሽ የሆነ ፍቱን መድኃኒት እስከ አሁን አላገኝም። ሥራ ነው መድኃኒቴ። በሥራ ውስጥ ስላለው ህቡዕ ፈውስ ጡረተኞች ቢያብራሩት ይሻላል። ቤት መዋል ከጀመሩ ጊዜ አንስቶ ስንት ደዌ እንደተፈራረቀባቸው የሚያውቁት እነሱ ብቻ ናቸው።

አጋዴን ውስጥ የሚንቀሳቀስ አንድ የውጭ ድርጅት ለከፍተኛ የመስክ ጥናት ሲጋብዘኝ፣ ያለ አንዳች ማቅማማት የአውሮፕላን ትኬት ቆርጬ የመጣሁት ራሴን በሥራ ጠምጄ ከእስማት ዓለሜ ውስጥ ተመንጥቄ ለመውጣት ካለኝ ፅኑ ፍላጎት የተነሳ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ንብረት የሆነው ቦይንግ አውሮፕላን ጎዴ አውሮፕላን ጣቢያ ለማረፍ ከፍታውን በመቀነስ ላይ ነው፡፡ ከታች ለጥ ያለው በረሃ የአሸዋ ሐይቁን ሠርቶ ብርዥ ብርዥ ይላል፡፡ ሚራገፍ ያጥበረብራል፡፡ አውሎ ንፋሱ እዛም እዚህም ስማይን ለመደገፍ የቆመ ምሰሶ ይመስል እንደ ዘንዶ ሽቅብ ይጥመለመላል፡፡

አውሮፕላኑ በአውሎ ነፋስ ርችት ታጅቦ የጎዴ አውሮፕላን ጣቢያ ማኮብኮቢያ ላይ እንደ ጆፌ አሞራ ጉብ አለና ወደፊት ይንደረደር ጀመር፡፡ ሰላሳ አምስት ሜትር ስፋትና ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሜትር ርዝመት ባለው ማኮብኮቢያ ላይ እየቃሰተ ተንደረደረና ሲቆም፣ በሱማልኛ ቋንቋ ወሬያቸውን እያደሩት የመጡት ተሳፋሪዎች በአንድ ላይ ግር ብለው በመነሳት ለመውረድ ይጋፉ ጀመር፡፡

ከአውሮፕላኑ የወረድኩት የመጨረሻው ተሳፋሪ እኔ ነበርኩ፡፡ ጎዴ በወበቅ እና በአሸዋ ጥፊ ተቀበለችኝ፡፡ በ1959 ዓ.ም በንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተመርቆ የተከፈተው ጎዴ አውሮፕላን ማረፊያ፣ አሁን የሲቪል አውሮፕላኖች ይስተናገዱበት እንጂ አሠራሩ ለወታደራዊ ቤዝ እንደነበር ያስታውቃል፡፡ በኦጋዴን ጦርነት ወቅት የሶማሊያ ወራሪዎች ጎዴን በያዙበት ቅፅበት አርሰውት የነበረው የኢትዮጵያ ጀቶች ለውጊያ እንዳያርፉበት ቢሆንም፣ ከድል በኋላ ታድሷል፡፡

ተርሚናሉን እንዳለፍኩ ዓይኔን እያጨላምስኩ ሰማዩን ቀና ብዬ ለማየት ሞከርኩ፡፡ እሳት የሚተፋ የገሃነም በር መስሏል፡፡ ፀሐይዋ፣ ቂም እንደቋጠረች ባልቴት የዓይኗን

ቂጥ ታንበገቡገዋለች፡፡ የሚሰቀጥጥ ድምፅ የሚያሰማው የበረሃው ነፋስ ሊያንሳፍፈኝ ምንም አልቀረውም፡፡

"ዶክተር ዲዲሞስ ዶሬ እንኳን ደህና መጣህ" የሚል ፅሁፍ ከፍ አድርጋ የያዘች ሴት እየጠበቀችኝ ተመለከትኩ፡፡ በአካል አትወቀኝ እንጂ በሥራዎቼ ታውቀኛለች፡፡ እኔም እስከ ዛሬ በዓይነሥጋ አልያት እንጂ በስልክ ብዙ ጊዜ አጋግሬአታለሁ- አያን ትባላለች፡፡ አያን እኔን የጋበዘኝ የውጪ ድርጅት ቢሮ ባልደረባ ናት፡፡

"ዶክተር" የሚለውን ቅፅል ስመለከት የምሁርነት ስሜት ሊሰማኝ ሞከረ፡፡ በተለያዩ ሀገራት የቀሰምኳቸው የአርኪዎሎጂ፣የፊሎሎጂ እና የአንትሮፖሎጂ ትምህርቶቼ ለዚህ ቅፅል ቢያበቁኝም ውስጤ ግን ከጥንታዊው ዓለም ያልወጣሁ ኋላቀር (ፕሪሚቲቭ) ሰው እንደሆንኩ ይነግረኛል፡፡ ዛሬ ያስጋበዘኝና ዶክትሬት ድግሪ የያዝኩበት የሶሻል አንትሮፖሎጂ ጥናቴ ዓለም አቀፋዊ እውቅና ቢያስገኝልኝም ትክክለኛው እኔነቴ ግን በጥንቱ ዓለም ጥናት የተዘፈቀ ነው፡፡ በአስማቱ ዓለም ውቅያኖስ ውስጥ የሰጠምኩ የሰው መርከብ ነኝ፡፡ የሉቅያኖስ እጆች የሚታዩኝ አስማታዊ ሰው!

እስከ ዛሬዋ ጠዋት ድረስ ከአልጋዬ ሳልወርድ የለመደብኝን አስማት መዳፎቼን ዘርግቼ እደግማለሁ - የጥንት የምስራቅ ፓልሚስቶችን አስማት፡፡

"ኻራግራይ ዋሽታይ ላኽሽሚ
ኻራማዳይ ሻራሽዋት
ኻራሙላይ ቱ ጆቢንዳይ
ራባታይ ኻር ዳርሳናም!"

በዘልማድ፣ ይህንን አስማት ሳልደግም ከአሳጋዬ አልወርድም፤ ሰውም አላናግርም። ከንቱ የአፍ ልማድ ሊባል ይችላል። ይሁን እንጂ ትርጉሙ፣

*"የብልፅግና ኃይል በጣቶቼ ላይ ነህ፤ የጥልቁ እውቀት ኃይል በመዳፌ ላይ ነህ፤ የፈጠራዎች ኃይል በመስመሬ ላይ ነህ፤ ይሄ ቀን የእኔ ነው!..."* እንደ ማለት ነው። ይህን አደግምና በቀኝ መዳፌ ግንባሬን ነክቼ ቀኝ እግሬን አስቀድሜ ቀኔን እጀምራለሁ።

አሁን እንኳ ይህ አመሌ አልለቀኝ ብሎ፣ ከአውሮፕላኑ ስወርድና የኦጋዴን ወበቅ በአሸዋ ጥፊ ሲቀበለኝ፣

*"....ኻራይ*
*ሹራይ*
*ራማይ ...."* አልኩ። ወደ አዲስ ምድር ሲገባ የሚደረግ ድግምት ነው። ትርጉሙን ግን አላውቀውም። በሰጠምኩበት የአስማት አለም ውስጥ ብዙ ትርጉማቸውን የማላውቃቸው ይህን የመሳሰሉ ድግምቶች ያጋጥሙኛል። አደጋው እዚህ ላይ ነው። "አፍ ይዔውዕ ለሞት" ይሏል ይህን ነው- "አፍ ሞትን ይጠራል።"

ይህን ድግምት እያነበነብኩ ስሜ እስከ ማዕረጌ የተፃፈበትን የእንኳን ደህና መጣህ መልእክት ይዛ ወደምትጠብቀኝ ሴት ገሰገስኩ። እቅፍ አበባ ይዛለች። አውሎ ንፋሱ የለበሰችውን ቢጫ መጎናፀፊያ ሊቀማት ይታገላል። የለበሰችውን ሐምራዊ ድሪያ ቀሚስ ወደ ጎን ወጥሮ ሲያውለበልበው የዳሌዋን ቅርፅ ለሁሉም አጉልቶ ለማሳየት ያሰበ መሆኑን ተመለከትኩ። አንዳንድ ድምጻቸው የሚያምር ሴቶች በአካል ሲታዩ ፉንጋ ሲሆኑ ነበር እስከ ዛሬ የሚያጋጥመኝ። አያን ግን ድምጽዋ ብቻ አልነበረም ውብ





ሆኖ ያገኘሁት። ከቅርጽዋ እስከ ደም ግባቷ እንከን አይወጣላትም።

"ዶክተር ዲዲሞስ እንኳን ደህና መጣህ!" አለች እቅፍ አበባውን እያበረከተችልኝ። "ስላዬሁህ መደሰቴን መደበቅ አልፈልግም።"

ከዚህ በፊት ፎቶዬን በዓለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ አይታ ይሆናል እንጂ በድምፅ በቴሌፎን ከመነጋገራችን በቀር በአካል አታውቀኝም። ይሁን እንጂ የአካባቢው ሰዎች ቀልጣፎች መሆናቸውን ሰምቻለሁ፤ ወዘ-ልውጥን ሰው ከመ ቅፅበት የሚለዩበት አንዳች ተአምር አላቸው።

"አመሰግናለሁ! በዚህ አንድ ጠብታ ዝናብ በጠማው በረሃ ውስጥ ይህን የመሰለ አበባ ከወዴት አገኘሽ!?" አልኩ እቅፍ አበባውን ተቀብዬ ሳበቃ። ለስላሳ ጉንጯን ስስማት ጠንከር ያለው ሽቶዋ ከአካባቢው የበረሃ ልዩ መዓዛ ጋር ተቀላቅሎ አወደኝ።

"አይዞህ በኮንትሮባንድ የገባ አይደለም!" አለች እየተፍለቀለቀች። ሀጫ በረዶ የመሳሰሉት ጥርሶቿ በተመጠነ ፈግታዋ ውስጥ ሲፈልቁ ልዩ መስህብ አላቸው።

አያን ተጫዋች መሆኗን ለመረዳት ቀላል ነበር። ራቅ ብሎ ወደ ቆመው የመስክ መኪናዋ እየመራች ስትወስደኝ ያለማቋረጥ እያወራች ነበር። ኮልተፍ ከሚል አንደበቷ የሚወጣው አማርኛ ልዩ ጣዕመ ዕዝን አለው። እኔም እንደ እርሷ መኮላተፍ ሳያምረኝ አልቀረም። መኪናውን የምትነዳው ራሷ ናት።

"ድርጅቱ ሾፌር አልቀጠረልሽም እንዴ?" አልኩ እንዲያው ዝም ላለማለት ያህል -አነስተኛ ሻንጣዬን ከኋላ ጭኜ ሳበቃ ጋቢና ገብቼ እየተመቻቸሁ።

"ስላልፈለኩ ነው" አለች ሞተሩን እያስነሳች። "ብቻዬን ስሆን ደስ ይለኛል።"

"የእኔ አመል ነው ማለት ነው ያለሽ፡፡ ብቻቸውን መሆን የሚችሉ ሰዎች ላቅ ያለ ችሎታ ያላቸው ናቸው።" አልኩ። "የሰው ልጅ እንደ እንስሳ በመንጋ መኳዝ የለበትም፡፡ ከመንጋው መነጠል ላቅ ያሉ ሰዎች ችሎታ ነው።"

ራሷን በአወንታ ነቀነቀችና የበረሃውን አቧራ እያቦነነች መኪናውን ወደ ጎዴ እንደ አባ ጠቅል ፈረስ ታስግረው ጀመር። አውሮፕላን ጣቢያው የሚገኘው ከጎዴ ከተማ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ወጣ ብሎ ነው።

የህሰን አደን ሠመተር "አሽቀ ሀባይን" የሚለው የሶማልኛ ሙዚቃ ከመኪናው የቴፕ ማጫወቻ ይንቆረቆር ጀመር።

*"... ሞግተሃይ ኡርያንክበ*
*አጎሎ መወይኔ*
*አይንካ ወሀሎይዴ*
*ኡዎ አረረዬ ለደን*
*ኢነይ ኡታምሎቃታን*
*ሀሽቀ ሀባይእን..."*

ከቴፑ ማጫወቻ ጋር አብራ እያዜመች እያለ ግጥሙን እንድትተረጉምልኝ ወተወትኳት። ቃል በቃል የተረጎመችልኝን በስንኝ ደርድሬ ባማርኛ አነበነብኩላት።





"...እግሩን ያጣውን ሰው አይተሽዋል ውዴ?
ፈጣሪ እግር አጥቶለት ይመስልሻል እንዴ?
እርሱ ግን እንደዚህ እግር የተኮነነው፣
አጉል ለሚሮጡት ምሳሌ እንዲሆን ነው።
አንቺ ግን ለጫማ ትከራከሪያለሽ
ምን አለህ? ምን አለህ? ምን አለህ ትያለሽ
ፍቅር ግን እንደዚህ ሽቀጥ እንዳይመስልሽ።"

ከት ብላ ሳቀችና፣

"ዶክተር ግዴለህም ጎበዝ ገጣሚም ሳትሆን አትቀርም!" አለች። ሙዚቃውን ደጋግመን እያጣጣምን በዋቢ ሸበሌ ወንዝ ዳርቻ ወደምትገኘው የጎዴ ከተማ ገባንና የበረሃዋን ከተማ የጭቃ ምርግ ቤቶች እያለፍን ወደ አያን ቤት ገሰገስን።

## ፪

ሕያን ወደ ቤቷ በቀጥታ ከወሰደችኝ በኋላ ግሩም የሆነ ምሳ ጋበዘችኝና ጥዑም የሆነ የሐረር ቡና አፈላችልኝ፡፡ አቦል ቡናዋን እያጣጣምኩ ሳሎኑን መቃኘት ጀመርኩ፡፡ ብቻዋን እንደምትኖር መገመት ቀላል ነው፡፡ ቤቷ በጥሩ ሁኔታ የተያዘና የጨካኙን በረሃ ከባድ ወበቅ ለመከላከል "ኤሲ" የተገጠመለት ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ እስካሁን በሙቀቱ ቀልጬ ወደ ፈሳሽነት ላለመለወጤ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡

ቡናዬን በዝግታ እየላፍኩ ግድግዳ ላይ የተሰቃቀሉትን ፎቶዎች እቃኝ ጀመር፡፡ ከፊት ከፊቴ ማዶ ባለው ጥግ ላይ ጥቁርና ነጭ በሆነ የእጅ ሥራ የተቀዳ ፎቶ ይታያል፡፡

"አባትሽ ናቸው?" ስል ጠየኳት ፎቶውን እያየሁ መሆኔን መገንዘቧን እንዳወቅሁ፡፡

"አዎ አባቴ ነው" አለች ቡና የጣደችበትን የከሰል ምድጃ ማርገብገቧን ገታ አድርጋ፡፡ "በሕይወት የለም፡፡"

"ምነዋ?" አልኩ የፊትዋን በቅፅበት መለዋወጥ እየተመለከትኩ፡፡





"በስልሳ ዘጠኝ ዓመተ ምህረት በተቀሰቀሰው የኦጋዴን ጦርነት ጊዜ ነው የሞተው፡፡ የሶማሊያ ወራሪዎች ሰላይ ነው ብለው በግፍ ቀጥቅጠው ነው የገደሉት፡፡ ለኢትዮጵያ መንግሥት እኛን እየሰለልክ መረጃ አቀብለሃል በማለት ጨፍጭፈው ከገደሉት በኋላ በጎዴ ከተማ መንገድ ላይ ለመቀጣጫ ጣሉት፡፡" አለችና ዓይኖቿን ቡዝዝ አድርጋ ዝም አለች፡፡ ከመቀጽበት ፊቷ ላይ ከባድ ሀዘን እንደጨለማ ሲደፋ ተመለከትኩ፡፡ ስሜቷ ቅርብ እንደሆነ ለመገንዘብ ቀላል ነበር፡፡ እንዲህ አይነት ሰዎች ብዙ ጊዜ ያጋጥሙኛል፡፡

"እናትሽስ በሕይወት አሉ?" ስል የቀሰቀስኩባትን ሀዘን በእናቷ ፎቶ አስረሳታለሁ ብዬ በማሰብ ከጎን ወደ ተንጠለጠለው ፎቶ ፊቴን አዙሬ ጠየቅኳት፡፡

"የለችም" አለች እርሷም ወደ እናቷ ፎቶ ዓይኖቿን ወርውራ፡፡ "... ረጅም ነው ታሪኩ ዶክተር፡፡ ... ሌላ ጊዜ አጫውትሃለሁ፡፡ በድካምህ ላይ ሰቆቃ ልጨምርብህ አልፈልግም፡፡"

"ይቅርታ... አዝናለሁ ሀዘንሽን ስለቀሰቀስኩብሽ፡፡"

"ኧረ ግዴለም! ከመንገድ መጥተህ እንዲህ አይነት ወሬ መስማት ተገቢ አይደለም" አለች ሁለተኛውን ቡና እየቀዳችልኝ - ቶናውን፡፡

"ከአዲስ አበባ - ጎዴ በአውሮፕላን መምጣት ይህን ያህል አድካሚ አይደለም፡፡ መኪና እየነዳሁ ብመጣ ኖሮ ምናልባት ሶስት ቀናት መጓዝ ሊጠይቀኝ ይችል ይሆናል፡፡ በዛ ላይ በረሃውን አቋርጦ መምጣት ከባድ ነው፡፡ ያው መቼም ... ካልተለመደ ሁሉም ነገር ከባድ ነው፡፡" ስል ንግግሬን ለማስረዘም ፈለኩ፡፡ ገና ቤቷ ከመግባቴ ወደ

ማትፈልገው የሀዘን ትውስታ ስለከተትኳት ሀፍረት ተሰምቶኛል፡፡ "ቅልብልቡ እንግዳ" ስል ራሴን ፀረፍኩት፡፡ "ምናለ ዝም ብል!"

"መቼም ስለ ስልሳ ዘጠኙ የኦጋዴን ጦርነት የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም" አለች ቡናውን እያቀበለችኝ፡፡ "ያንን አስከፊ ጦርነት ጊዜ ቢረሳው የኦጋዴን መሬት አይረሳውም፡፡"

"ጊዜ የማይጠግነው ቁስል የለም" አልኩ ተመልሳ ወደ ሀዘኗ እንዳትገባ በመስጋቴ፡፡

"እኔ ውስጥ ያለው ቁስል ግን... ሞቼ ተቀብሬ እንደ ሉሲ ሚሊዮን ዓመታትን ባስቆጥር እንኳ፣ አጥንቴ ውስጥ እንደሚገኝ ጥርጥር የለኝም፡፡"

ይህን ስትል ጭንቅላቴ ውስጥ ድማሚት የፈነዳብኝ ይመስል ፀጥ አልኩ፡፡ ወደ ኦጋዴን ከመምጣቴ በፊት ስለዚህ አካባቢ በውል ለማወቅ ያላገላበጥኩት መዝገብና ያላነበብኩት መፅሐፍ ያለ አልመሰለኝም፡፡ ... ግን ... በሰዎች ሕይወት ውስጥ የተቀበሩትን መዛግብት ማን ፈልፍሎ ይጨርሳቸዋል? በሰዎች ልብ ውስጥ የተደረደሩትን መፃሕፍት ማን አንብቦ ይጨርሳቸዋል? ...

አያን ስታወራ፣ በሌላኛው የአእምሮዬ ክፍል፣ ያገላበጥኳቸው መዛግብትና መፃሕፍት፣ ሰነዶችና ክርታሶች እየተዘበራረቁ ይተረማመሱብኝ ጀመር፡፡ አእምሮዬ ወደ ኋላ የዘመን ፈረሱን ገርፎ ሽመጠጠ፡፡ ልመልሰው ታገልኩ፣ አልቻልኩም፡፡ ሁልጊዜም አእምሮዬ የሚያስቸግረኝ በዚህ መልኩ ነው፡፡ አሁን እየሆነ ያለውን ክስተት ወደኋላ ሄዶ ማተት አባዜው ሆኖ ያሰቃዩኛል፡፡





አፍሪካን የተቀራመቷት ጡንቸኛ ሀገራት ብሪታኒያ፣ ኢጣሊያ፣ ፈረንሳይና ጀርመን በኦጋዴን በረሃ ላይ ጥንብ እንዳዩ የሎስ ሲውዘገዘጉ በዓይነ ህሊናዬ ተሳሉብኝ፡፡ ሥጋዊ ዓይኖቼ ግን በአያን ውብ ሽፋሽፍቶች ሥር ከተቋጠሩት ዕንባዎች ውስጥ ፈዘው እየዋኙ ነበር፡፡

ከወልወል ግጭት አስከ ኦጋዴን ጦርነት፣ የሰው ልጅ የአሞራ ቀለብ የሆነበት፣ ሲያዩት የበረሃ ግሳት ላጡት የእግር እሳት የሆነው የኦጋዴንን መሬት... በአያን ሕይወት ተጣድኩበት፡፡ በእንባዋ ፈሰስኩበት፡፡

ኦጋዴን አንድ ሶስተኛውን የኢትዮጵያን ቆዳ የሚሸፍን አካባቢ ነው፡፡ በዚህ ወቅት "የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል" እየተባለ ቢጠራም በብዙዎች ዘንድ ስያሜው ቅቡል አይደለም፡፡ "የኢትዮጵያ አማራ"፣ "የኢትዮጵያ ኦሮሞ"፣ "የኢትዮጵያ ትግራይ"፣ "የኢትዮጵያ አፋር"... ተብሎ ሲጠራ እስካሁን ባንሰማም እንደ ሶማሌዎች ሁሉ እነዚህ ህዝቦችም በጎረቤት ሀገሮች ይገኛሉ- በኬንያ፣ በሱዳን፣ በጅቡቲ፣ በኤርትራ፡፡ ሌላው ይቅርና በዚህ ዘመነ ስደት ወቅት፣ ኢትዮጵያዊ የማይገኝበትን የአለም ጥግ ፈልጎ ማግኘት ያዳግታል፡፡ በአለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድም ኦጋዴን የሚለው ስያሜ የተለመደ ነው፡፡ እኔም ብሆን ይህኛው ስም ይቀናኛል- ኦጋዴን፡፡

አካባቢው 200,000 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ያህል ስፋት ያለው ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ከኬንያ፣ ከሶማሊያና ከጅቡቲ ትዋሰንበታለች፡፡ በአብዛኛው ለዓይን የሚያታክት በረሃ ሲሆን፣ ለዲካ ማረፊያ የሚሆኑ አምባ ተራራዎችም ይታዩበታል፡፡ ከደጋማው የኢትዮጵያ ክፍል ከባሌ ተራሮች የሚነሱት ዋቢ ሸበሌና ገናሌ ወንዞች በረሃውን ሕይወት ዘርተውበት ባያልፉ ኖሮ በዛ አካባቢ የሰው ልጅ ለመኖር

መቻሉ ያጠራጥራል፡፡ የኢትዮጵያን ወሰን አቋርጠው ወደ ሶማሊያ የሚገቡት እነዚህ ወንዞች ለሶማሊያ ህዝብ ሳይቀር ከድንበር ተሻግረው የሕይወቱ መሠረት ናቸው፡፡ ሰማኒያ በመቶ የሚሆነው የሶማሊያ ሀገር ህዝብ በእነዚህ ወንዞች ዳርቻ ነው ተከማችቶ የሚኖረው፡፡

የወንዞቿን ምንጭ ለመያዝ አያሌ ጦርነቶችን በማድረግ ዘመንዋን የጨረሰችው ኢትዮጵያ በሰሜን በአባይ ወንዝ ምክንያት ከግብፅና ከሱዳን፣ በደቡብ በጊቤ ሰበብ ከኬንያ፣ በወዲህ በምስራቅ በኩል ደግሞ በዋቢ ሸበሌና በገናሌ ሳቢያ ከሶማሊያ ተፋጣ መኖሯ ግልፅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ምንጮቿ የጦርነት ምንጭ ሆነውባት ቢኖሩም፣ አቅሟ ቢዳብር፣ ወንዞቿ በሚፈሱባቸው ሀገራት ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር እንደሚጠቅሟትም የውኃ ፖለቲከኞች ይገልፃሉ፡፡

ዋቢ ሸበሌና ገናሌ ሰንጥቀውት በሚያልፉት የኦጋዴን በረሃ ውስጥ በስስት የሚታዩት ረጃጅም ዘንባባዎች፣ ፈጣሪን ለማመስገኛ ደብተራ የሚዘምባቸው የማህሌት መቋሚያዎች ይመስላሉ - የቅዱስ ያሬድ በትሮች፡፡ ከዚህም በቀር እንደ ኪንኪ ፀጉር ችምችም ብሎ በረሃውን የወረረ የእጣን ዛፍ በየአምባው ጥጋትና አናት ላይ ይታያል፡፡ ከቆንጥር ዛፍ ጋር ተቀላቅሎ የተቃጠለ ጭራሮ የሚመስለው የእጣን ዛፍ ላወቀበት ከፍተኛ የእጣን ምርት የሚያስገኝ ሀብት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ አንበሳ፣ ነብር፣ አጋዘን፣ የፍየል ግልገል የምትመስል ኢንሹ የሚሏት ፍጡር፣ የሞተ የማይበላው ጅብ፣ ተኩላና ከከብት ጋር አብሮ የሚግጥ ከርከሮ ይገኛል፡፡ ከዚህም በቀር በዘላን እረኛ ውኃ ፍለጋ የሚርመሰመስ ከፍተኛ የከብት መንጋ ሞልቷል፡፡ ፍየሉ፣ ግመሉና ከብቱ በበረሃው ውስጥ





አልፎው አልፎው የተቆፈሩትን የውኃ ጉድጓዶች በረከት ለመጎንጨት ሲኳትን ይውላል፡፡

ይህን ሁሉ በዓይነ ህሊናዬ እያሰብኩ ከአያን ዓይኖች ሽፋሽፍት አምልጠው እንደ ሜርኩሪ የተንከባለሉትን እንባዎቿን ተከትዬ ነቃሁ፡፡ ኃያላኑን ሀገራት ለዘመናት በዚህ ምድር ላይ አፍጥጠው እንዲኖሩ ያደረጋቸው፣ ምን እንደሆነ የገለፁልኝ፣ የብረት አሎሎ ከመሰሉት የአያን ዓይኖች ላይ እንደ ሜርኩሪ ኩልል ያሉት እንባዎቿ ነበሩ፡፡ አሸዋ ባጠለቀው ረሞጫ በረሃ ውስጥ ሀገራትን ጦር ሲያመዝዝ የኖረውና፣ እንደ እብድ ገላጋይ ድንጋይ ሲያቃብል ዘመናትን ያስቆጠረው አመዳሙ በረሃ ሳይሆን የከርሰ ምድሩ ሃብት ነበር፡፡ ሲያፋጅ የኖረው ነዳጅ ነው፡፡ ሲያስተራርድና ፈንጂ ሲያስቀብር የኖረው፣ በከርሰ ምድሩ ውስጥ ተቀብሮ ያለው ነዳጅ ነው፡፡

የአያንን የእንባ ዘለላዎች ተነስቼ ልጠርግ አሰብኩና የእንግድነት ክብሬ ከለከለኝ፡፡

"እባክሽን ይቅርታ አድርጊልኝ" አልኩ ተቀምጬ እየተመለከትኳት፡፡ "እንዳልሽው ሁሉንም ነገር ሌላ ጊዜ ታጫውችኛለሽ፤ በቂ ጊዜ እንደሚኖረን ተስፋ አለኝ፡፡"

"እኔ ነኝ ይቅርታ መጠየቅ ያለብኝ" አለች አያን እንባዋን ጠራርጋ የግዷን ፈገግ ለማለት እየሞከረች፡፡ "እንግዳ ተቀብሎ እንባ የሚጋብዝ ሰው ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም፡፡"

"እባክሽን ቀለል አድርገሽ እይኝ፡፡ ወግ አጥባቂ የምባል ሰው አይደለሁም፡፡"

"ዶክተር … በአካል ባለውቅህም ብዙ ጊዜ በስልክም አውርቼሃለሁ፡፡… አያሌ ጥናታዊ ፅሁፎችህንም

እንብቤአለሁ፡፡ በውነቱ... ለረጅም ጊዜ የማውቅህ ያህል ይሰማኛል፡፡ ለዛ ነው ስሜቴን መደበቅ ያቃተኝ" አለች በረካውን ቀድታ እያቀበለችኝ፡፡

"እኔም ብሆን ብዙም የእንግድነት ስሜት አልተሰማኝም"

"እንባዬ ሳይቀድም የቤተሰቦቼን ሰቆቃ ባጫውትህ በወደድኩ፡፡ ነገር ግን እነሱን በሳብኩ ቁጥር ስሜታዊ እሆናለሁ፡፡ ለነገሩ ለሌሎች ነገሮችም ስሜቴ ቅርብ ነው፡፡"

"ሌላ ጊዜ ይደርሳል፡፡ ሌላ ጊዜ ሁሉንም ተረጋግተሽ ትነግሪኛ ይሆናል፡፡ ይልቁንስ ፀሐዩ በረድ ሳይል አይቀርም፤ ወጣ ብለን ብንናፈስ ይሻላል፡፡ እኔም ወደ ሆቴል መሄድ ይኖርብኛል፡፡ ስለምሳውና ስለቡናው በእጅጉ አመሰግናለሁ፡፡" ሀሳቧን ሳትቀይር ብድግ አልኩና የእነስተኛ ሻንጣዬን ጆሮ ያዝኩ፡፡ ወዲያው ግን የቤቷ ግቢ በር እስኪያቃስት በኃይል ሲንኳኳ ሰማሁ፡፡ በቆምኩበት ደርቄ ቀረሁ፡፡





# ፫

እያን፣ ያለ እረፍት እስኪያቃስት ድረስ ይንኳኳ የነበረውን የግቢ በር ለመክፈት ሮጣ ከወጣች ቆይታለች፡፡ ከውጪ የሆነ ንግግር እየቀረበ ሲመጣ ይሰማኛል፡፡ የእያን ብቻ ድምፅ ነበር፡፡

"ቀስ አትልም?!" ትለዋለች፡፡ አንኳኪው ወንድ እንደሆነ ተረዳሁ፡፡

'ምናልባት ባለቤቷ ይሆን?' ራሴን ጠየኩ፡፡ 'ከሰው ቤት ዘው ብዬ ... ቢጠረጥራትስ?... ስለ እኔ ያውቅ ይሆን?... ደግሞ ጣቷ ላይ ቀለበት አላየሁም፡፡' በቁሜ ዘጭ ብዬ ተቀመጥኩና ውርደቴን መጠባበቅ ጀመርኩ፡፡ ተጋብገቼ ሳይሆን ተገብገቼ የገባሁ ውሽማ የሆንኩ ያህል ተሰማኝ፡፡ ራሴን በውሽማ አምሳል በመቁጠሬ፣ ክብሬ ሁሉ ተንዶ ሲከዳኝ ታወቀኝ፡፡ ትንሽዬ አይጥ የሆንኩ መሰለኝ፡፡

"ተነግረህ አትሰማም አይደል?! ወይ ጉድ! በሩን እኮ መገንጠል ነው የቀረህ"! የእያን ድምፅና የሌላ ሰው ዳና እየቀረበ መጣ፡፡ በዚህች አፍታ ያላሰብኩት አልነበረም፡፡ ራሴን ለፍልሚያ ማዘጋጀትም ቃጣኝ፡፡ እንደገና ተነስቼ ቆምኩና የቤቱ በር እስኪከፈት ተጠባበቅሁ፡፡

በሩ እንደተከፈተ ያየሁትን ማመን አቃተኝ። አያን አስከትላው የገባችው ግዙፍ ሰውዬ፣ የለበሰው ልብስ የአህያ ቆዳ የመሰለና ከመንተቡ የተነሳ ሽታው አፍንጫን የሚፎንን ነበር። ፀጉሩ እንደ ኦጋዴን የቆንጥር ዛፎች ቅርንጫፍ ተገምዶ የተንጨፈረረ ነው። ገና ከመግባቱ የደም እኻ የተቋጠረባቸው የመሰሉ ትላልቅ ዓይኖቹን እንደ እሳት ነበልባል አንቦገቦገብኝ። ይሁንና የቀትር ጋኔን የመሰለው ይህ ሰውዬ ወደ እኔ አልተጠጋም። ምንም ሳይናገረኝ እዛው በሩ ስር ኩርትም ብሎ ተቀመጠ። ሲቀመጥ ያ የሰማይ ስባሪ የሚያህል ግዝፈቱ እንደ ዘንዶ ተጠቅልሎ ኩርትምትም ባለ አካሉ ውስጥ ገባ። አያን ከጓዳ ገብታ ጥቂት ከቆየች በኋላ በጎድጓዳ ሳሕን ሞልታ የሚበላ ነገር አመጣችና ሰጠችው።

"ዶክተር ተቀመጥ እንጂ ... ሰው አይተናኮልም" አለችኝና በዓይኗ ዝም በል በማለት አይነት ጠቀሰችኝ። ትንፋሼን በረጅሙ ለቅቄ ተቀመጥኩ።

ሰውዬው የጎድጓዳ ሳህኑን ምግብ በአንድ አፍታ በጥድፊያ አሻመደውና ተነሳ። አያን በፎሌ ውኃ ስትሰጠው በከንፈሮቹ ግራና ቀኝ እያዥረበረበ ገረገጨውና፣ ፎሌውን መልሶላት ምንም ሳይናገር ወጥቶ ሄደ።

ትንፋሼን ሰብስቤ እንደተቀመጥኩ ዓይኖቼን በቀስታ ወደ አያን መለስኩ።

"ሊባን ሁልጊዜም እንዲህ ነው" አለች ፎሌውን እያስቀመጠች።

"ምንድን ነው?" ዓይኖቼን የወጣበት በር ላይ ተክዬ ጠየቅኋት።





"ሊባን... ተለክፎ ነው። ማለቴ ንክ ነው። አይናገርም፤ አይጋገርም። ተናግሮ አያውቅም፤ ዲዳ ሆኖ ግን አይደለም።... አስከፊው የኦጋዴን ጦርነት ሰቆቃውን ጥሎባቸው ካለፉት እንደ እኔ ካሉ ሰዎች አንዱ ነው።" ወንበር ስባ ተቀመጠች። "ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት የአምስተኛ ብርጌድ ወታደር ሆኖ ጎዴ ተመድቦ ነበር-ሊባን። በሰላሙ ጊዜ እዚሁ ጎዴ ከተማ ውስጥ ሀቦን የምትባል ፍቅረኛ ነበረችው አሉ። ውበቷ ዓይን ያፈዝ ነበር ይባላል። ስለ ሀቦን ውበት መላ ጎዴ አንስቶ አይጠግብም። እንኳን ወንድን ሴትን ያፈዝ የነበረው ውበቷ ብቻም ሳይሆን የሀቦን እና የሊባን ፍቅር እንደ ዋቢ ሸበሌ ወንዝ ፈስሶ ያልቃል ተብሎ አይታሰብም ነበር። ይህን የፍቅር ኻረት ግን የኦጋዴን ጦርነት እስከ ወዲያኛው ገደበው። ሆኖም ገደበው እንጂ አላስቆመውም። እስከ አሁን በሊባን ልብ ውስጥ ሐይቅ ሆኖ እየኖረ ነው።"

"እንዴት እንዴት?..." አልኩ ይበልጥ ለማዳመጥ እየተመቻቼሁ።

"ጦርነቱ ሲጀመር፣ የዚያድ ባሬ ጦር የጎዴን ከተማ ክፉኛ አጠቃት። በዋቢ ሸበሌ ወንዝ ዳርቻ የኢትዮጵያ ልጆች ደም እንደጎርፍ ፈሰሰ። አስከሬን ከአስከሬን ተቃቀፈ። ይሁን እንጂ በሶቪዬት ህብረት እስከ አፍንጫው ታጥቆ ኢትዮጵያን የወረረው የሶማሊያ ጦር፣ የዋቢ ሸበሌን ወንዝ ተሻግሮ ጎዴን ሲይዝ የኢትዮጵያ ጦር የጦርነት ተፈናቃዮችን ይዞ አፈገፈገ። በዚህ ወቅት ነበር ሊባንና ሀቦን የተጠፋፉት። ሊባን የኢትዮጵያ ጦር ወታደር እንደመሆኑ እሱም ከተማዋን ለቆ መውጣት ነበረበት። ይሁን እንጂ እንደገና ሀቦንን ፍለጋ በሲቪል አለባበስ ጎዴ ገብቶ በፍለጋ እንደባዘነ ይነገራል። እድለ ቢሱ ሊባን ግን

ሀቦንን ሊያገኛት አልቻለም፡፡ ተስዳ ይሆናል ብሎ በመገመት ይመለስና ጓዶቹን ይቀላቀላል፡፡

"ሀቦን ግን በሶማሊያ ወራሪ ጦር ወታደሮች እጅ ወድቃ ነበር፡፡ ይህም የታወቀው በአሰቃቂ ሁኔታ ተደፍራ በመጨረሻም ተገድላ በጎዴ ጎዳና ላይ የሚዘገንን በድኗ ተጥሎ ለመቀጣጫነት በመታየቱ ነው፡፡ ያቺ የዋቢ ወንዝ ዳር አበባ የመሰለችው ውቧ ሀቦን ፈራረሰች፡፡ እስከትፈራርስ ድረስ በድኗን አንስቶ ለመቅበር እንኳ የደፈረ አልነበረም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ለኢትዮጵያ መንግሥት ትሰልል ነበር ተብላ ስለነበር ነው፡፡"

"ያሳዝናል" አልኩ የሀቦንን አሟሟት በአዓይነ ህሊናዬ እየሳልኩ፡፡

"ምስኪኑ ሊባን... የሀቦንን ዘግናኝ አሟሟት የተረዳው በኢትዮጵያ አሸናፊነት ጦርነቱ ከተደመደመ በኋላ ነበር፡፡ የዚያድ ባሬ ጦር እግሬ አውጭኝ ብሎ ሽርጡን ለቆንጥር እያስረከበ ሞቃዲሾ እስኪገባ ከተባረረ በኋላ፣ ሊባን በድል አድራጊነት ጎዴ ይመጣል፡፡ ባዶ ቀርታ የነበረችውን ከተማ እንደገና የጦርነት ተፈናቃዮች ተመልሰው ነፍስ እየዘሩባት ነበር፡፡ ሀቦንን በየመንደሩ እየጠየቀ ሲያፈላልግ ሰነበተ፡፡ ይሁንና ሀቦንን ሊያገኛት አልቻለም፡፡ ይብሱን... የሀቦንን ዘግናኝ አሟሟት ያዩ ሰዎች ይነግሩታል፡፡ በድኗም እስኪፈራርስ ድረስ የወደቀበትን ቦታ ያሳዩታል፡፡ ከዛ በኋላ ነበር በሊባን ላይ ሰማይና ምድሩ የተገለባበጠበት፡፡ የሀቦን አስከሬን የበሰበሰበትን አፈር እየዘገነ፣ እንደተወጋ አውሬ እያጓራ ልብሱን ሲቀድ ፀጉሩን ሲነጭ ከሰነበተ በኋላ በዛው አእምሮው ተነካ፤ ለቀቀ፡፡ የጎዴ እብድ ሆኖ ቀረ፡፡"





"ያንት ያለህ..." ራሴን በሁለት እጆቼ ይገፔ አቀርቅሬ ቀረሁ፡፡ አያን ቀጠለች፡፡

"ወደ እኔ ቤት የሚመጣው የቤተሰቦቼን አሰቃቂ ታሪክ ሲያወሩ ሰምቶ ስለሚመስለኝ አጎርሰዋለሁ፡፡ ውሃም እሰጠዋለሁ፡፡"

ወደ ራሷ ታሪክ እንዳትገባ በማሰብ፣

"እኔ'ኮ ..." አልኩ ካቀረቀርኩበት ቀና ብዬ፡፡ "እኔ'ኮ ሳየው ...አስፈሪ ገፅታ ቢኖረውም፣ የተከበረ ሰው እንደነበር ሁኔታው ያሳብቅ ነበር፡፡... እንዲያውም አግኝቶ ያጣ ደሀም ነው ስል አሳቤ ነበር፡፡ አለ አይደል የከሰረ ሰው... የከሰረ ደሀ..."

"ደሀ ከስሮ አያውቅም" አለች አያን ራሷን እየተቆጣጠረች እንደሆነ በሚያሳይ ሁኔታ፡፡ "ከስሮ የማያውቅ ደሀ ብቻ ነው፡፡ ሊባን ግን የፍቅር ሃብታም ነበር፡፡ ያጣትን ሀቦንን የሚተካለት ምድራዊ ሀብት የትም ሊያገኝ አይችልም፡፡"

"ልክ ብለሻል ... ሶማሊያ የተባለችውን ሀገር በካሳ መልክ ቢሰጡት እንኳ ሊጠገን አይችልም፡፡"

ለአያሌ ደቂቃዎች በየራሳችን አእምሮ ውስጥ ሰጥመን ከቆየን በኋላ ሻንጣዬን ይገፔ ተነሳሁ፡፡ ወደ ሆቴሌ መሄድ አለብኝ፡፡ የተያዘልኝ መኝታ ቤት በጎዴ ከተማ መሀል በሚገኝ "ቀለዲድ" ከተባለ ሆቴል ጎን ነው፡፡ አያን ፔንሲዮኑ ድረስ ሸኝታኝ ስታበቃ መልካም አዳር ተመኝታልኝ ወደ ቤቷ ተመለሰች፡፡

## ፬

በዓይኔ እንቅልፍ ሳይኳል ማደሬን ያወቅሁት ጠዋት የመኝታ ቤቴ በር ሲንኳኳ ነበር። ስለ አያን፣ ስለ ሲባንና ስለ ሀቦን ሳሰላስል ነጋብኝ። የዚህን አካባቢ የጦርነት ቀጠና መሆን ባሰብኩ ቁጥር እንግሊዞችን ስራገም አደርኩ።

እስከ አሁኗ ጠዋት ድረስ በአፍሪካ ውስጥ እንግሊዞች የረገጡት ምድር ሁሉ የጦርነት አውድማ ሆኖ እንደቋያ በመጋየት ላይ ነው። በቅርምቱ ወቅት የወረሯቸው ቦታዎች ሁሉ በማዕድን የበለፀጉ እንደነበሩ ተገለፀልኝ።

ናይጀሪያ በነዳጅ የበለፀገች ሀገር ናት፤ ሆኖም የጦርነት አውድማ ናት። ደቡብ አፍሪካ በአልማዝ የተንቆጠቆጠች ምድር ናት፤ ነገር ግን ፕላኔታችን መሬት እስክትበሳ ድረስ የተቆፈረችውና እየተቆፈረች ያለችው ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ነው። ሱዳንን የረገጠው እግራቸው እስከ ዛሬ ድረስ የዳርፉር ሰቆቃ ሆኖ ቀጥሏል። እግራቸው በደቡብ ሲዳን በኩል የነካው የኢትዮጵያ መሬት ጋምቤላ በነዳጅ የበለፀገ





እንደሆነ ሲገለፅልኝ ምን አይነት መሣሪያ ፈልስፈው መሬትን ያስሱ እንደነበር በአስማት እንኳ ለማወቅ ዳዳኝ። ሌላው ይቅርና አሁን የረገጥኩትን ምድር ኦጋዴንን፣ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ለኢትዮጵያ ያገዙ መስለው ጣሊያንን በማስወጣት እንዴት ይዘው እንወጣም እንዳሉ ይታወቃል። ኢትዮጵያ ነዳጇን ከመቆፈር ይልቅ የእንግሊዞችን ሴራ ቆፍራ ለመንቀል ሀብቷንና ጉልበቷን ጨርሳለች። የኦጋዴን ጦርነት ስር መሠረቱስ ማን ሆነና?

የአውሮፓ ገበሬ እየተባለ የሚዘበትበት ጣልያን ደቡባዊ ሶማሊያን ሲይዝ እንግሊዞች የያዙት ግን በማዕድን የበለፀገውን ሶማሌ ላንድን ነበር። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እንግሊዞች ይዘውት የነበረው ሶማሌ ላንድ እንደ ጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር በ1960 ዓ.ም ነፃ ወጣ። ወር ባልሞላ ጊዜ በዛው ዓመት ደቡብ ሶማሊያም ከባርነት ወደ አርነት ተሸጋገረ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ጣልያን በመሸነፏና ቅኝ ግዛቶቿን እንግሊዝ በመውረሷ ደቡብ ሶማሊያም በእንግሊዝ እጅ ወደቀች።

በ1941 ዓ.ም ንጉሡን አጅበው ኢትዮጵያ የገቡት እንግሊዞች ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ ነጥቀው ከራሳቸው የእንግሊዝ ሶማሌ ላንድና ከጣሊያን የወረሱትን ደቡብ ሶማሊያ፣ ባንድ ላይ ጨፍልቀው "ታላቋ ሶማሊያ" የሚል ግዛት የመፍጠር ህልማቸውን እውን ለማድረግ ተንቀሳቀሱ። ይባስ ብለው ዓይናቸውን በጨው አጥበው ኦጋዴንን በዜይላ ወደብ ለመለወጥ ለኢትዮጵያ ጥያቄ አቀረቡ። ከዚህም በላይ በልዩ ልዩ ጋዜጦች "የታላቋ ሶማሊያ"ን አላማ በማስተዋወቅ ኢትዮጵያን የቅኝ ገዥነት ምስል የሚያላብስ ፕሮፓጋንዳ ጀመሩ። ኢትዮጵያም "ዘኢትዮጵያን ሄራልድ" በሚባለው ጋዜጣዋ የእንግሊዝን "ታላቋ ሶማሊያ" የተባለ ሀሳብ ቅዠት ነው ስትል

አወገዘች። እነ ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድን የመሳሰሉ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ዓለምን ብቻ ለብቻ ባይገጥሙት ኖሮ የእንግሊዞችን ፕሮፓጋንዳ መቋቋም ከባድ ነበር።

ይሁንና የቀዝቃዛው ጦርነት በመተካቱና የዓለም ፖለቲካ በመለወጡ ምክንያት ቅኝ ገዢዎቹ እንደ መኸርገር መነቀል ጀመሩ። ሶማሊያም ነፃ ወጣች። ኦጋዴንም ለኢትዮጵያ ተመለሰች። የእንግሊዞች ቦንብ ግን እንደተቀበረ ነበር። የውስብስቡ ሴራ ክር ቁጢት መመዘዝ የጀመረው ቆይቶ ነበር።

እንግሊዞች ኦጋዴንን ለቀው ሲወጡ በምስጢር ሠርተው የደበቁት መስፈርቱ 1:500,000 የሆነው ካርታና ሌሎች ኦጋዴንን የተመለከቱ ጥብቅ ምስጢራዊ ሰነዶች የውሃ ሽታ እንደሆኑ ቀሩ።

ሶማሊያ ነፃ ከወጣች በኋላ ለዘጠኝ ዓመታት የተዘጋጀችው ኢትዮጵያን ለመውረርና "ታላቋ ሶማሊያ" የተሰኘውን የእንግሊዝ ቦንብ ለማፈንዳት ነበር። ለዚህም ስትል የሶቭየት ህብረት የፖለቲካ የእንጀራ ልጅ በመሆን እስከአፍንጫዋ ታጠቀች። በመፈንቅለ መንግስት ሥልጣን ላይ ፊጥ ያለው ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ "የምዕራብ ሶማሊያ ህዝብ ነፃ አውጭ" የተባለውን ድርጅት በማስታጠቅ እያሰረገ ወደ ኢትዮጵያ ያስገባ ጀመር።

በመቀጠልም ዝግጅቱን ያጠናቀቀው የሶማሊያ ጦር በ1969 ዓ.ም በይፋ ኦጋዴንን ወረረ። በጥቂት ቀናት ውስጥም በዶሎና በባሬ ተረማምዶ ጎዴን ከአምስተኛ ብርጌድ እጅ ነጠቀ። ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬም ለሶማሊያ ወራሪዎቹ በአደባባይ መደስኩሩን ቀጠለ።





"... ወደ ኢትዮጵያ ስትገቡ በጉጉት የሚጠብቃችሁ ብሶት ያናወዘው ፀረ- መንግሥት ኃይል ነው። እፊታችሁ የሚቆም ወታደር የለም። ኢትዮጵያ ስትገቡም ስለምግብ ችግር አይግባችሁ። ሥጋው፣ እህሉ፣ ከብቱ፣ ብርቱካኑ፣ ሙዙና ፓፓያው የተትረፈረፈበት ውብና የጥጋብ ሀገር ነው። ቦንብ እየወረወራችሁ ሳይሆን ሙዝና ብርቱካን እየተወራወራችሁ ነው ኢትዮጵያ የምትገቡት!... ሂዱና ያቺን የጥጋብ ሀገር ያዟት!..." ሲል እንደ አንበሳ አገሳ። የወራሪው ጦር ታላቅ ምት ጎዴ ላይ አረፈ።

የአየር ኃይልና ሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት ስላሉበት፣ ጎዴን መያዝ ከፍተኛ የውጊያ ጠቀሜታ እንዳለው የተገነዘቡት የሶማሊያ ወራሪዎች በመድፍና በሞርታር ከተማዋን ያለ ምህረት ይደበድቡ ጀመር። የሚያስገመግም የከባድ መሳሪያ ተኩስ ሰማይዋን አረሰው። የባሩድ ሽታ የእጣንና የብርጉዷን መዓዛ ሸፈነው። የመትረየስ ፉጨት የሕፃናቷን ሳቅ ፀጥ አደረገው። የልጃገረዶችንና የጎበዞቿን መፈንጠዝ ጎዳና ጥይት አረሰው። ምሽቷን የጥይት ርችት አነደደው። የወዳደቀ አስክሬን አጥሯ ሆነ። በሞት ሽታ ጠረኗ ተቀየረ። የመልዓከ ሞት ክንፍ ጥላ በጎዴ ላይ ወደቀ። አሞራዎቿ የሰው ሥጋ ለመዱ።

የውቧ ሀቦን በድን በጎዴ ጎዳና ላይ ተጣለ። የእያንን አባት ቅዱስ አስክሬን አሞራዎች ተሻጩቁት። ይህንን ቀፋፊ የጦርነት ታሪክ በዓይነ ህሊናዬ ሳዳውር ነበር የመኝታ ቤቱ በር መንኳኳት ወደ አሁኑ ዓለም የመለሰኝ።

## ፫

ፎጣዬን አገልድሜ በሩን ከፈትኩት፡፡ አያን እንደ ጠዋት ጮራ እየተፍለቀለቀች ቆማ ነበር፡፡

"እንደምን አደርክ ዶክተር..."አለች ግንባሯን ቁጥር ፊታ እያደረገች፡፡ "ሙቀቱ እንዴት አደረገህ?"

"ኤሲው ባይኖር ኖሮ እንደ ቂቤ እቀልጥ ነበር፡፡" አልኳት ወደ ውስጥ እንድትገባ እየጋበዝኳት፡፡

"እንቅልፍ በደንብ እንዳልተኛህ ዓይኖችህ ያስታውቃሉ፡፡ ድልህ መስለዋል፡፡"

"አዎ ጥሩ እንቅልፍ አልተኛሁም ማለት ይቻላል፡፡ ስለ ሊባን፤ ስለ ሀቦንና ስለ አንቺ አባትም... የነገርሽኝን ሁሉ ሳመነዥክ ነው የነጋብኝ፡፡"





"የእኔ ጥፋት ነው፡፡ መልካም አቀባበል እንዳላደረኩልህ ግልፅ ነው፣ ይቅርታ ይደረግልኝ፡፡ ለዚህ ጥፋቴ ጥሩ ቁርስና ወፍራም ቡና አዘጋጅቻለሁ፡፡ እንሂድ!" አለች ከደጅ እንደቆመች፡፡

ወደ ውስጥ ተመለስኩና ተለቃልቄ ወጣሁ፡፡ ገና ጠዋት ቢሆንም ሙቀቱን በመፍራቴ ከጥጥ የተሠራውን ነጭ ልብሴን ለብሼ ወጣሁ፡፡

"አውቀህበታል" አለች አያን አለባበሴን አይታ፡፡ "የበዛ ልምድ አለህ ማለት ነው!"

"በትክክል፡፡ ከዚህ በፊት በኑብያና በግብፅ በረሃዎች ውስጥ ሰፊ የአርኪዮሎጂ ምርምር ከሚያደርግ የጥናት ቡድን ጋር ብዙ በመሥራቴ የበረሃን ጠባይ አውቀዋለሁ፡፡"

"ፒራሚዶችን አይተሃቸዋላ!" አለች ወደ ቤቷ እየመራችኝ፡፡ "የመጀመሪያዎቹ ፈርኦኖች ኢትዮጵያውያን ነበሩ የሚባለው እንዴት ነው? ፒራሚዶቹ የተሠሩትም በእነርሱ ትዕዛዝ መሠረት ነው የሚሉ ጥናቶች አሉ፡፡ አሁን ያለችውን ኢትዮጵያ ስናይ ይህ ተረት ተረት አይመስልም?"

"ቢመስል አይገርምም፡፡ ያቺ... የማያ፣ የአዜቴክ፣ የኢንካና የፎኒሺያ ስልጣኔ መነሻ የነበረችው የጥንቷ ኢትዮጵያ አሁን አንገቷን ደፍታለች፡፡ ፔጋሰስን የሠሩት እጆቿ ተጣጥፈዋል፡፡ ውቅያኖስን አቋርጠው ይቀዝፉ የነበሩ መርከቦቿ ሰጥመዋል፡፡"

"ምክንያቱ ምንድን ነው ትላለህ?" ርምጃዋን ገትታ አፈጠጠችብኝ። "ታላቋ ኢትዮጵያ ለምን ፈራረሰች?"

"ለዘመናት በተካሄደ አለም አቀፍ ሴራ ምክንያት መሆኑ ግልፅ ነው። ...እስከዛሬ ኢትዮጵያ ያደረገቻቸውን ጦርነቶች ማን ቆጥሮ ይጨርሳል? በዘመኗ ያለ ጦርነት የመሸ ቀንና የነጋ ሌሊት የለም። ይህ ሁሉ ለምን ይመስልሻል?"

"ድንጋይ የሚወረወረው ፍሬ ወዳለው ዛፍ ነው።" አለችና ርምጃዋን ቀጠለች።

"ልክ ብለሻል። ዛፏ ላይ አንድ ፍሬ እንኳ የቀረ እስከማይመስል ድረስ ተጨፍጭፋለች። ለዘመናት በደረሰው ጭፍጨፋ የተነሳ ዛሬ ያሉት ህዝቦቿ ስላለፈው አኩሪ ታሪክ ማውራት ራሳቸውን እስኪያሳፍራቸው ድረስ አንገታቸውን ደፍተዋል። ታሪኳ በልባቸው ፍርስራሽ ውስጥ ተቀብሯል።" አንድ አነስተኛ አውሎ ነፋስ ጎዳናውን ቀውጢ አደረገውና ንግግሬን አቋረጠኝ። የአያንን ጥቁር እስካርፍ እንደ አሸባሪ ባንዲራ ያውለበልበው ጀመር። ዓይኖቻችንን እያጨላሞስን አንድ ግድግዳ ተከልለን አውሎ ነፋሱን ካሳለፍን በኋላ ስንተያይ፣ ሁለታችንም ወፍጮ ቤት የቆዩን ይመስል የአቧራ ዱቄት ውጦን ነበር። አያን ከት ከት ብላ ሳቀችብኝ።

"ቢያስገሳንኮ አቧራ ነበር የሚወጣን" አለች ሳቋን ሳታቋርጥ። "ቻለው እንግዴህ! ኦጋዴን እንዲህ ነው። ተመልከት! ሰማዩ ላይ የምታየው ደመና እንዳይመስልህ። የኦጋዴን ሰማይ ሁልጊዜም በአውሎ ነፋስ ርችት እንደተንቆጠቆተ ነው።"





"ወድጄ የገባሁበት ነው።"

የአያን ሳቅ እኔንም አሳቀኝ። ስትስቅ የሳቋ ቅላጼ ይቀያየራል።

"...ባንዴ በትቢያ ጥፊ ከግብፅ ስልጣኔ ጎዳ አስገባንኮ አውሎ ነፋሱ።"

"ገና በጠዋቱ እንዲህ አይነት አውሎ ነፋስ አይቼ አላውቅም።"

"ገና ምን አይተህ! የኦጋዴን ነፋስ የጎድን አጥንት ሳይቀር ለመንቀል ይታገላል።"

ከአያን ቤት እንደደረስን ያዘጋጀችውን ቁርስ ከበላን በኋላ፣ ቡና እየጠጣን ስለመጣሁበት የጥናት ጉዳይ መወያየት ጀመርን። በአንዳንድ ቅደም ተከተሎች ላይ ከተስማማን በኋላ ገና ጠዋት በመሆኑ፣ ወደ ዋቢ ሸበሌ ወንዝ ልትወስደኝ ትችል እንደሆን ጠየኳት።

"አይገርምም?... እኔም ወደ ወንዙ ልወስድህ አስቤ ነበር። አንዷት ደስ የምትለኝ ቦታ አለች። እዛች ሥፍራ ተቀምጨ የሚወርደውን ወንዝ ስመለከት መንፈሴ ይታደሳል። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ሰው በአካባቢው አለመኖሩን አይና አወላልቄ እዋኛለሁ። ተደብቀው ያዩኝ ጎረምሶች ወሬውን ወደ ከተማ ስላመጡት የጎዴ ከተማ ሰዎች እንደ ጤነኛ ሰው አይቆጥሩኝም። እንዴት ሴት ልጅ እርቃኗን ወንዝ ውስጥ ትዋኛለች? እያሉ እብድ እንደሆንኩ ያወራሉ። ሻጣን ያለብኝ ይመስላቸዋል" አለች እየተዘገጃጀች። "የአካባቢው ማህበረሰብ ለሴቶች ካለው አመለካከት የተነሳ እንደሆነ ስለምቆጥረው ምንም አይመስለኝም። የሴት ልጅ እርቃኗን መሆን ያለባት ባሏ ፊት ብቻ ነው የሚል አመለካከት አለ።"

ከአያን ቤት ወጣንና ከተማዋን መሃል ለመሃል ሰንጥቆ የሚያልፈውን አውራ ጎዳና ያዝንና ወደ ዋቢ ስንወርድ እግረ መንገዳችን ስለከተማዋም አጫወተችኝ፡፡

የክልሉ ዋና ከተማ ወደ ጅጅጋ ከመሸጋገሩ በፊት ጎዴ የኦጋዴን ዋና ከተማ ነበረች፡፡ አያን እንደነገረችኝ ይህ የሆነው ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ ነው፡፡ ኢህአዴግ ወደ ስልጣን በወጣ ማግስት፣ በዋነኝነት የኦጋዴን ጎሳ ጥርቅም የሆነው ኦብነግ በሽግግሩ ወቅት የተደረገውን ምርጫ በከፍተኛ ድምፅ አሸንፎ ክልሉን ተቆጣጥሮ ነበር፡፡

ከኦጋዴን ውጪ የነበሩ በቁጥር አናሳ የሆኑ ጎሳዎች ፍርሃት ያደረባቸው፣ ኦብነግ "የራስን እድል በራስ መወሰን" የሚለውን ፈሊጥ ይዞ፣ የኦጋዴንን ጎሳ በመያዝ ሌሎቹን የመጨፍለቅና የመገንጠል አላማም እንዳለው ውስጥ ውስጡን በመሰማቱ ነበር፡፡ ኦብነግ አኩርፎ ከሽግግሩ መንግሥት ፓርላማ ሲወጣ፣ ሌሎች ከኦጋዴን ጎሳ ውጪ ያሉ ጎሳዎችን እንወክላለን የሚሉ ሰዎች፣ ኢሶዴሊ የተባለ ድርጅት መሥርተው ኦጋዴንን መምራት ጀመሩ፡፡ ይህኛው ፓርቲም ብቻውን ቀጠናውን መምራት ሲያዳግተው የቀድሞ የኦብነግ ለዘብተኛ አባላትን በማሰባሰብ፣ ሶህዴፓ የተባለ ፓርቲ በማቋቋም ክልሉን መምራት ያዘ፡፡

"ለምን የክልሉን መንግሥት ወደ ጅጅጋ ለማዛወር እንደተፈለገ አይገባኝም" አለች አያን ከተማዋን እያስቃኘችኝ፡፡ "ከተሞች መመሥረት ያለባቸው በወንዝና በኃይቅ ዳርቻዎች ነው፡፡ ያለ ጥቅም የሚፈሰው ዋቢ ሸበሌን ለማልማት ጎዴ አስፈላጊ ነበረች፡፡ በንጉሡም በደርግም ጊዜ የነበሩት ሰፋፊ የእርሻ ቦታዎች አሁን





ወድመዋል፡፡ አሸዋ ሰፍሮባቸዋል፡፡ ወንዙን ወደ በረሃው ይረጩ የነበሩ የውሃ መሳቢያ ሞተሮች አሁን ዝገው ቆመዋል፡፡ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ያሠሯቸው ተቋማት እንኳ አሁን በቅጡ አልተያዙም፡፡ በዛ ባልሰለጠነ ዘመን ባንክ፣ ቴሌ፣ ፖስታ ቤትና መብራት አስገብተው ነበር፡፡ ለሙስሊሙ መስጊድ፣ ለክርስቲያኑ ቤተ ክርስቲያን፣ ትምህርት ቤት፣ ኤርፖርትና ሆስፒታልም አስገንብተው በከተማዋ ዙሪያ ዘላኖችን በማስፈር የተረጋጋ ኑሮ እንዲመሠርቱ ጥረው ነበር፡፡"

ከተማዋን ግራና ቀኝ እየተመለከትን ቁልቁል ወደ ሚጥመለመለው ዋቢ ሸበሌ ወንዝ ወረድን፡፡ ሰማያዊ በርሜል የተሸከሙ አህዮች ብቻቸውን ሲጓዙ ተመለከትኩ፡፡

"ተመልከት ዶክተር!" አለች አያን ወደ አህዮቹ በጣቷ እየጠቆመች፡፡ "ወደ ሰባ ሺህ የሚጠጋውን የጎዴ ህዝብ ውሃ የሚያጠጡት እነዚህ አህዮች ናቸው፡፡"

"ወንዙን ያውቁታል ማለት ነው?" ተገርሜ ጠየቅኳት፡፡ አህዮቹን እንኳን የሚመራቸው የሚነዳቸው ሰው የለም፡፡ ዋቢ ወንዝ ጠብቀው ይጭኗቸዋል፤ ወደቤታቸው ቀጥ ብለው ይመለሳሉ፡፡

"ሌላው ይቅርና አህያ አይታሰርም፡፡ ቤቱን ያውቃል፡፡ ውሃ ቀድተው የሚጭኑት አሽከሮች ወንዝ ይጠብቁትና ያሸክሙታል፡፡ በቀጥታ ወደ ቤቱ ይጓዝና ጭነቱን የሚፈታውን ሰው ይጠባበቃል፡፡"

"ይገርማል!"...አልኩ አህዮቹን እየተመለከትኩ፡፡ "መሰልጠን እንደሚቻል ከዚህ በላይ ማሳያ የለም፡፡

ካሰለጠንከው እንኳን ሰው አህያም ይሰለጥናል፡፡ ይገርማል ሌሊትም አይታሰሩም?"

"አይታሰሩም" አለች አያን፡፡ "ጎዴ ውስጥ ጅብ አህያን በላ ሲባል ሰምቼ አላውቅም፡፡ እንዲያውም አህዮች ጅቡን ያባርሩታል፡፡"

በዚህ እያሳቅን ወደ ዋቢ ወንዝ ደረስን፡፡ በወንዙ ላይ በተሠራው የብረት ድልድይ ላይ ቆመን ቁልቁል የሚጥመለመለውን የዋቢ ሸበሌ ወንዝ መመልከት ጀመርን፡፡

"ይህ ወንዝ ለሰፋፊ የመስኖ እርሻዎች ቢውል እንኳን ኦጋዴንን መላ ምሥራቅ አፍሪካን ይቀልባል፡፡ የኦጋዴን መሬት እንዲህ በረሃ መስሎ ስታዩው የማያበቅል ይመስልህ ይሆናል፡፡ ሆኖም ገርነቱን ለማዩት አንድ ዝናብ እስኪያገኝ መጠበቅ ይኖርብሃል፡፡ በአመት አንድ ዝናብ ብቻ የሚያገኘው ይህ በረሃ ሁለት ጊዜ ዝናብ ሲያገኝ የአመት ቀለብ ያስገኛል፡፡ አስገራሚው ነገር ዝናብ ከዘነበ ከሁለት ቀን በኋላ ይህ ገሃነም የሚመስለው በረሃ አረንጓዴ ሐመልማለሉን ተጎናፅፎ ገነት ይመስላል፡፡ በሁለት ቀን ዝናብ ብቻ ለግጦሽ ያደርሳል፡፡ በዋቢ ወንዝ ዳርቻ የሚገኘው ምዕራብ ጉዴ ሩዝ ሳይቀር ይመረትበታል፡፡ ቀላፎ ነጭ ሩዝ ይሰጣል፡፡ እዚህ ታች..." አለችና ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ በአገጯ አመለከተችኝ፡፡

"እዚህ ታች ደርግ አምስት መንደሮች አቋቁሞ ነበር፡፡ ከኦጋዴን ጦርነት በኋላ፡፡ በሰላም ጊዜ አርሰህ ብላ፤ ሲወሩህ ሲመጡ ተዋጋ ብሎ ደርግ ያሰፈረው ግብረ ኃይል ነበረ፡፡ የዋቢ ሸበሌን ወንዝ ጠልፈው አካባቢውን እሸት በእሸት አድርገውት ነበር፡፡ ኢህአዴግ ከገባ በኋላ የደርግ ጦር ነው ብሎ በታተነው፡፡ ከፊሉን መተማ ዮሐንስ ወስዶ





አስፍሮታል ይባላል፡፡ ቀሪው ግን ወደየመጣበት ተበታትኖአል፡፡ ወደ ከተማ ገብቶ በልመና የተሠማራ እንዳለም ሰምቻለሁ፡፡ ይህ ሁሉ የምታዬው አሸዋ የተኛበት በረሃ በዋቢ ወንዝ መስኖ አረንጓዴ ነበር፡፡ መሬቱ ገር ነው፡፡ ሃምሳ ሳንቲ ሜትር ወደታች ብትቆፍር ለም አፈር ታገኛለህ፡፡"

የወንዙን ዳርቻ ተከትለን ሽቅብ ከተጓዝን በኋላ ብቻዋን ከቆመች የዘንባባ ዛፍ ሥር ተቀመጥን፡፡

"እናቴ ወደዚህ ቦታ አዘውትራ ትመጣ ነበር አሉ" አለች ደፍርሶ ቁልቁል የሚወርደውን የዋቢ ሸበሌን ወንዝ ፈዝዛ ስትመለከት ቀይታ፡፡ ባለፈው ያቋረጠችው ታሪኳን ልታጫውተኝ እንደሆነ ገባኝ፡፡ "ከአባቴ ጋር ጣፋጭ ፍቅር የተቃመሱባት ቦታ፣ ይህች ቦታ እንደሆነች በቅርቡ የሞቱት ጉረቤቴ አጫውተውኛል፡፡"

"በልጅነትሽ ነው ማለት ነው እናትሽንም ያጣሻቸው?"

"አዎ" አለች አሻግራ ከሩቅ ያለውን ድልድይ እየተመለከተች፡፡ "የሶማሊያ ጦር ጎዴን ሲወር ነበር እኔንና ህፃን ወንድሜን በፊትና በጀርባዋ አዝላ የተሰደደችው፡፡"

"ወደ የት?"

"ወደ ሰሜን አቅጣጫ፡፡ ጎዴን የሶማሊያ ወራሪ ጦር ሲቆጣጠረው ከተባራሪ ጥይት የተረፈው ነዋሪ ከተማዋን ለቆ ወደ ደናን፣ ቀብሪ ደሃር፣ ቀብሪ በያህ፣ ደገ ሃቡርና ጅጅጋ ተሰደደ፡፡ እናቴ ግን በዚህ አልቆመችም፡፡ ሐረር ድረስ ገሰገሰች፡፡ እስከ ጦርነቱ ማብቂያ ሐረር ከቆዬች በኋላ የዚያድ ባሬ ጦር ተሸንፎ ሞቃዲሾ ድረስ መፈርጠጡን ስትሰማ ወደ ጎዴ ተመለሰች፡፡

"ጎዴ ፈራርሶ ነበር፡፡ ከተቃጠሉ ታንኮችና ከፈራረሱ ግድግዳዎች በቀር መጠለያ እንኳ አልነበረም፡፡ መንገዶችን የወዳደቁ አስከሬኖች ሞልተዋቸው ከተማዋ ጥንብ ጥንብ ትሸት ነበር፡፡ የጦርነት ተፈናቃዮች ወደ ከተማዋ አንዳንድ እያሉ ተመልሰው ነፍስ እስኪዞሩባት ድረስ ጎዴ ሲኦል መስላ ነበር፡፡ ከስደት የተመለሰው ነዋሪ አስከሬኖችን ቀብሮ ቤቶቹን እንዲነገሩ እየጠገነ መኖር ሲጀምር ግን ሌላ ጦርነት ይጀመራል፡፡"

"ደግሞ የምን ጦርነት?"

"የድመት ጦርነት!"

"አትቀልጂ! ደግሞ የድመት ጦርነት ተብሎ የተሰየመው የትኛው ጦርነት ነው?"

"ያልተፃፈ የጎዴ ጉድ ነው ቀልድ አይደለም፡፡ የጦርነት ተፈናቃዮች በተመለሱ በጥቂት ቀናት ውስጥ አያሌ ህፃናት መጥፋት ጀመሩ፡፡ እምጥ ይግቡ ስምጥ፣ ህፃናቱ የት እንደ ደረሱ ማወቅ ሳይቻል ብዙ ቀናት አለፉ፡፡ የእኔም ወንድም የጠፋው በዚህ ወቅት ነበር፡፡"

"የት ጠፋ?"

"ልነግርህ ነው፡፡ ልጆቻቸው የጠፉባቸው ወላጆች ጓዳ ጎድጓዳውን ሲያስሱ ይሰነብቱና ቢጨንቃቸው በጋራ ልጆቻቸውን ለማፈላለግ ይስማማሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ነው ጉዱ የተሰማው፡፡ አንድ ቀን አንድያ ልጁ የጠፋበት ወላጅ፣ ልጁን እየፈለገ ወደ ቤቱ ታዛ ይሄዳል፡፡ ከታዛው የድመት መንጋ ተከማችቶ የሆነ ነገር ሲቧጨቅ ይደርሳል፡፡ ጠጋ ሲል አንደኛው ድመት ተወንጭፎ አንገቱን ያንቀዋል፡፡ ሌሎችም ድመቶች እየዘለሉ ላዩ ላይ ይወጡና ማንቁርቱን አንቀው ሊጥሉት ይታገሉታል፡፡ ሰውዬው ግን የነፍስ እድን ጩኸቱን እያሰማ የሰፈረበትን የድመት መንጋ





እንደተሸከመ ወደ መንገድ ይወጣል፡፡ መንደርተኛው ሁሉ ይወጣና ከድመቱ መንጋ ያስጥለዋል፡፡ ሰውዬው የሆነውን ሁሉ ያስረዳል፡፡ መንደርተኛው በሰውዬው መሪነት ወደ ቤቱ ታዛ ሄዶ ሲያይ የሆነውን ማመን ያቅተዋል፡፡ ድመቶቹ ሲቧጨቁት የነበሩት የሰውዬዉን ልጅ ነበር፡፡"

"ያንት ያለህ" አፌን በመዳፌ ያዝኩ፡፡

ለረጅም ደቂቃዎች ስትተክዝ ቆይታ ቀጠለች፡፡

"የእኔም እናት ህፃን ልጇ ጠፍቶባት ስትፈልግ ሰንብታ ይህን ወሬ ትሰማና የቤቷን ታዛ ስታስስ ትንንሽ የህፃን አጥንቶች ታገኛለች፡፡ ልጇን ድመቶች ተቀራምተውት ነበር፡፡" ከዚህ በኋላ መናገር አቃታት፡፡ ሳግ ሲተናነቃት ቆዬችና ስቅስቅ ብላ ታለቅስ ጀመር፡፡ እኔም እንባዬን መቆጣጠር አልቻልኩም፡፡

ከአያሌ ደቂቃዎች በኋላ እንባዋን እየጠራረገች ቀጠለች፡፡

"ድመቶች የሰው ሥጋ ለምደው ነበር፡፡ ነዋሪዎች የጦርነት ቀጠና የሆነችውን ከተማ ለቀው ሲወጡ ድመቶች የወዳደቀውን አስከሬን ቀመሱ፡፡ ስደተኞች ሲመለሱ ከተማዋ በድመት መንጋ ተወራ ነበር፡፡ የቤታቸው ድመት ወደ አውሬነት ተቀይሮ ጠበቃቸው ልጆቻቸውን፣ ወተት አጠጥተው ያሳደጓቸው ድመቶቻቸው ነጠቋቸው፡፡ እናቴም ልጇን ድመት እንደበላባት ሲገባት በቁሟ ተዝለፍልፋ ወደቀች፡፡ አልተነሳችም፡፡"

"ያንት ያለህ! ከዚህ የበለጠ የጦርነትን ሰቆቃ ማሳያ የሚሆን ምሳሌ ምን አለ? ...የኦጋዴን ሰቆቃ!....የጎዴ ጉድ!... አንቺስ እንዴት ተረፍሽ?"

"በእድል ብንለው ይሻላል። ይህን ሁሉ ሀዘን ተሸክመሽ ኑሪ ብሎ ፈጣሪ ፈርዶብኝም ይሆናል" አለች ዓይኖቿን ደጋግማ እየጠራረገች።

"ከዛስ ማን አሳደገሽ?"

"እናቴን ለመቅበር የመጣችው አክስቴ ሐረር ወስዳ አሳደገችኝ። ስትወስደኝ ገና የሶስት አመት ህፃን ነበርኩ። ቤተሰቦቼን የማውቃቸው በፎቶ ብቻ ነው። አክስቴ ልጅ አልነበራትም፤ መሀን ናት። እንደ ልጇ ተንከባክባ ነው ያሳደገችኝ።"

"አማርኛሽ የሰላው ለዚህ ነው… ሐረር በማደግሽ።"

"ከሆነ ልክ ነው። …እዛው ሐረር ተምሬ ጥሩ ውጤት ካመጣሁ በኋላ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመግባት የመጀመሪያ ድግሪዬን በሶሾሎጂ ያዝኩ። ሁለተኛ ዲግሪዬን ደግሞ ሆላንድ ሀገር በአንትሮፖሎጂ ሠርቼ ተመልሻለሁ። ይኸው ነው ታሪኬ። በቃ።"

ተነስታ በሚፈሰው የወንዝ ውሃ ፊቷን ታጠበችው። እንባዋን ለዋቢ ሰጠችው።





# ፯

ከምሳ በኋላ፤ ሞቃታማውን ቀን መኝታ ቤቴ ውስጥ ገብቼ አመለጥኩት። ከውጪ መዋል የማይታሰብ ነው። ቤት ገብቶ ኤሲን ከፍቶ መዋል ግድ ይላል። አያን ነፈስፈስ ሲል እንደምትመጣ ነግራኛለች። ሥራችንን በይፋ የምንጀምርበት ምሽት እንደሆነ ተነጋግረናል። ስለ እርሷ ብዙ አውቄአለሁ። ጎዴ ተወልዳ ሐረር ማደጓን፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሶሾሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪዋን እንደያዘች፤ ማስተርስዋን ሆላንድ ሀገር እንደተቀበለችና አሁን እኔን በጋበዘኝ አለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ተቀጥራ እየሰራች እንደሆነ ተርካልኛለች።

ከሁሉም ልቤን የነካው ግን በቤተሰቧ ላይ የወረደው መቅሰፍት ነበር። በሰላይነት ተጠርጥሮ በሶማሊያ ጦረኞች በግፍ የተገደለው አባቷ፣ በድመት መንጋ የተበላው ህፃን ወንድሟና የልጇን ጥቃቅን አፅሞች በማዬቷ በድንጋጤ ወድቃ የሞተች እናቷ …

ዕንባዋ በዓይኔ እየተመላለሰ የመጣሁበትን ሁሉ አስረስቶኛል። ገና ስለ አያን ያላወቅሁት አንድ ነገር አለ። እጮኛ ይኖራት ይሆን?… እጇ ላይ ቀለበት ስለሌላት ባል እንደሌላት ግን ደምድሜአለሁ። ኧረ ለመሆኑ ይህን

ለማዎቅ ለምን ያስፈልጋል? ተነስቼ በቀዝቃዛ ውሃ ተለቃለኩና ክፍሌን ዘግቼ ወጣሁ:: ለአያን ስልክ መደወል ነበረብኝ:: ተንቀሳቃሽ ስልኬ ላይ ስሟን ፈለግሁ::

"ሃሎ ዶክተር... ነቃህ?" አለች ስልኩን በፍጥነት አንስታ:: እየጠበቀችኝ እንደነበር ግልፅ ነበር::

"ወጥቻለሁ::"
"መታወቂያ ወይም ፓስፖርት መያዝህን እንዳትረሳ::"
"መታወቂያ? ...ምን ይሠራልናል?"

ከትከት ብላ ሳቀችና፣
"ፍተሻ መኖሩን አልነገርኩህም ለካ::"
"የምን ፍተሻ ነው? ከሀገሬ ወጥቻለሁ እንዴ?"
"በል ተመለስና ፓስፖርትህን ይዘህ ውጣ:: የቀረውን ስንገናኝ እናወራለን:: ሁሁ!" እየሳቀች ስልኩን ዘጋችው::

ለክፉም ለደጉም ብዬ ወደ ክፍሌ ተመለስኩና ፓስፖርቴን ይዤ ወጣሁ:: አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ደረሰች::

"ለምንድን ነው ፓስፖርት ያዝ ያልሽኝ?" በጥያቄ ተቀበልኳት::

"ከተማው ውስጥ ልንሽራሽር አይደለም?"

"አዎ:: አካባቢዬን በደንብ በመቃኘትና በመልመድ ሥራዬን መጀመር የሁልጊዜም ተግባሬ ነው::"





"ሀሳብህ ጥሩ ነው:: ሆኖም የመጣህበት ክልል ከተቀሩት የኢትዮጵያ ክልሎች የባሰ አደገኛ አካባቢ መሆኑን መርሳት የለብህም::"

"ፓስፖርትም ይጠየቃል ማለት ነው?"

"መታወቂያም ይሁን ፓስፖርት፣ ብቻ አንተን የሚገልፅ ነገር ይዘህ መንቀሳቀስ ግዴታ ነው:: እንኳን አንተ ወዘልውጡ፣ የከተማዋ ታዋቂ ነዋሪዎችም መታወቂያ ይዘው የመንቀሳቀስ ግዴታ አለባቸው::"

"ለምን?"

"ፍተሻ አለ::"

"ለምንድን ነው ፍተሻው?"

"ዶክተር ዲዲሞስ..." አለች አያን ፍጥጥ ብላ እያየችኝ በለሆሳስ:: "የመጣህበት ክልል ሞቀ ስትለው የሚቀዘቅዝ፣ ቀዘቀዘ ስትለው የሚሞቅ፣ ሁኔታውን መተንበይ የማይቻል ቀጠና ነው:: ለበርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማት ዝግ የሆነ፣ ክልሉን ለማጥናት የሚመጣ ተመራማሪ ቀልጠ የሚቀርበትና አለሁ የሚል ጋዜጠኛ የማይደፍረው አካባቢ መምጣትህን በድጋሜ ልነግርህ እወዳለሁ::"

እኔም ዓይኖቿ ላይ ፈጥጬ ቀረሁ::

"ገባህ?"

"ገባኝ:: ግን..."



t.me/BooksandYou

አልመለሰችልኝም፡፡ ዞራ በዝግታ መራመዷን ቀጠለች፡፡ ምንድን ነበር ልጠይቃት የነበረው? በረጂሙ ተንፍሼ ተከተልኳት፡፡

"ፍተሻው ከምን የመጣ ነው?" እጇን ለቀም አደረኳት፡፡ "በደንብ አልመለስሽልኝም፡፡ ፍርሃቱ ከምን የመነጨ ነው?"

"...የመጣሃው ...አንዳንድ ተንታኞች የኢትዮጵያ ዳርፉር እያሉ ወደሚጠሩት አካባቢ ነው፡፡ በአንድ በኩል መንግሥት በቀጠናው የሚፈፀመው የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዲጋለጥበት አይፈልግም፡፡ ታጣቂ ቡድኖችን ለመምታት ሲል የወሰዳቸው እርምጃዎች፣ ያቃጠላቸው መንደሮችና ያደረሳቸው ሰቆቃዎች እንዳይጋለጡ በማለት አለም አቀፍ ድርጅቶችና ጋዜጠኞች በአካባቢው በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ አይፈቀድም፡፡ በሌላ በኩል ይወጣል ተብሎ በጉጉት የሚጠበቀው ነዳጅ ሌላኛው የአካባቢው ስጋት ነው፡፡"

"የነዳጁ መውጣት እንዴት ስጋት ሊሆን ይችላል?"

"የተፈጥሮ ሀብት አንዱና ዋነኛው የግጭት መንስኤ መሆኑን ለአንተ ማስረዳት አይጠበቅብኝም፡፡ እጮኛዬን ያጣሁት..." ርምጃዋን ገታችና ቆማ አጤነችኝ፡፡ "...እጮኛዬን ያጣሁት በነዳጅ አውጪ ሰራተኞች ላይ በተፈፀመ የሽብር ጥቃት ነው፡፡ ጂኦሎጂስት ነበር፡፡"

'በሞት የተከበበች ሞት ሞት የምትሸት ልጅ! የሞት መናኸሪያ!' አልኩ በውስጤ፡፡ ያልሞተችው እሷ ብቻ ናት፡፡

"አያን...አዝናለሁ፡፡" ሁለቱንም ትከሻዎቿን ይዤ ቆሞኩ፡፡ "ብዙ በደል ደርሶብሻል፡፡"





"ያልሞትኩት እኔ ብቻ ነኝ" አለች በዓይኗ እንባ እየተንቆረዘዘ፡፡ "እኔም ብሆን ግማሽ አካሌ እንደሞተ እንደሞተ ይቆጠራል፡፡ ማንም የለኝም፡፡ ብቻውን የቀረ ሰው

የአቤ ጉብኛን ስንኝ አስታወሰችኝ፡፡

"...እናንተ ወገኖቼ አልሞትኩም ሞቻለሁ፡፡" አቤ በዛፈው ዕሁፍ ምክንያት፣ሞቻ በተባለ ተራራ ላይ በግዞት ታስሮ እያለ የቋጠራት ሰምና ወርቅ ስንኝ ናት፡፡

አያን፣ እንባዋን ታግላ መለሰችና መንዛችንን ቀጠልን፡፡ እንዳለችውም በየቅያሱ ቆመው የሚፈትሹ ወታደሮች አላፊ አግዳሚውን ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍር እየፈተሹ ነበር፡፡ ለበርካታ ጊዜ ተፈተሽኩ፡፡ ፓስፖርቴን ባልይዝ አልቆልኝ ነበር፡፡ይህም ሆኖ ፓስፖርቴን አይተው አያበቁም፤ በሶማልኛ ቋንቋ ከአያን ጋር ይነጋገራሉ፡፡

በኋላ ስጠይቃት፣ ከየት እንደመጣሁና ለምን እንደመጣሁ ነበር የሚጠይቁት፡፡ እርሷ የምትሰራበት የውጪ ድርጅት አዲስ አባል እንደሆንኩ አድርጋ ያስናዳችውን መልስ ነበር የምትነግራቸው፡፡

ጎዴ መሸት ሲል ትንሽ ተንፈስ ትላለች፡፡ ከምሳ በኋላ መሥሪያ ቤቶች ሳይቀር ዝግ ናቸው፡፡ አመሻስሽ ላይ እንደገና ሥራ ይጀመራል፡፡

የቀኑ ሀሩርና ገሃነም መሰሉ ሙቀት ጋብ ሲል ነዋሪዎች በየበራቸው ይወጡና ይቀመጣሉ፡፡ ጫት የጨረሰ የቢራ አንገት ያንቃል፡፡

አልመለስችልኝም፡፡ ዞራ በዝግታ መራመዷን ቀጠለች፡፡ ምንድን ነበር ልጠይቃት የነበረው? በረጂሙ ተንፍሼ ተከተልኳት፡፡

"ፍተሻው ከምን የመጣ ነው?" እጇን ለቀም አደረኳት፡፡ "በደንብ አልመለስሽልኝም፡፡ ፍርሃቱ ከምን የመነጨ ነው?"

"...የመጣሄው ...አንዳንድ ተንታኞች የኢትዮጵያ ዳርፉር እያሉ ወደሚጠሩት አካባቢ ነው፡፡ በአንድ በኩል መንግሥት በቀጠናው የሚፈፀመው የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዲጋለጥበት አይፈልግም፡፡ ታጣቂ ቡድኖችን ለመምታት ሲል የወሰዳቸው እርምጃዎች፣ ያቃጠላቸው መንደሮችና ያደረሳቸው ስቆቃዎች እንዳይጋለጡ በማለት አለም አቀፍ ድርጅቶችና ጋዜጠኞች በአካባቢው በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ አይፈቀድም፡፡ በሌላ በኩል ይወጣል ተብሎ በጉጉት የሚጠበቀው ነዳጅ ሌላኛው የአካባቢው ስጋት ነው፡፡"

"የነዳጁ መውጣት እንዴት ስጋት ሊሆን ይችላል?"

"የተፈጥሮ ሀብት አንዱና ዋነኛው የግጭት መንስኤ መሆኑን ለአንተ ማስረዳት አይጠበቅብኝም፡፡ እጮኛዬን ያጣሁት..." ርምጃዋን ገታችና ቆማ አጤነችኝ፡፡ "...እጮኛዬን ያጣሁት በነዳጅ አውጪ ሰራተኞች ላይ በተፈፀመ የሽብር ጥቃት ነው፡፡ ጂኦሎጂስት ነበር፡፡"

'በሞት የተከበበች ሞት ሞት የምትሸት ልጅ! የሞት መናኸሪያ!' አልኩ በውስጤ፡፡ ያልሞተችው እሷ ብቻ ናት፡፡

"አያን...አዝናለሁ፡፡" ሁለቱንም ትከሻዎቿን ይገፎ ቆሞኩ፡፡ "ብዙ በደል ደርሶብሻል፡፡"





"ያልሞትኩት እኔ ብቻ ነኝ" አለች በዓይኗ እንባ እየተንቆረዘዘ፡፡ "እኔም ብሆን ግማሽ አካሌ እንደሞተ የሚቆጠር ነው፡፡ ማንም የለኝም፡፡ ብቻውን የቀረ ሰው እንደሞተ ይቆጠራል፡፡"

የአቤ ጉበኛን ስንኝ አስታወሰችኝ፡፡

"...እናንት ወገኖቼ አልሞትኩም ሞቻለሁ፡፡" አቤ በዓፈው ዕሁፍ ምክንያት፣ሞቻ በተባለ ተራራ ላይ በግዞት ታስሮ እያለ የቋጠራት ሰምና ወርቅ ስንኝ ናት፡፡

አያን፣ እንባዋን ታግላ መለሰችና መጓዛችንን ቀጠልን፡፡ እንዳለችውም በየቅያሱ ቆመው የሚፈትሹ ወታደሮች አላፊ አግዳሚውን ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍር እየፈተሹ ነበር፡፡ ለበርካታ ጊዜ ተፈተሽኩ፡፡ ፓስፖርቴን ባልይዝ አልቆልኝ ነበር፡፡ይህም ሆኖ ፓስፖርቴን አይተው አያበቁም፤ በሶማልኛ ቋንቋ ከአያን ጋር ይነጋገራሉ፡፡

በኋላ ስጠይቃት፣ ከየት እንደመጣሁና ለምን እንደመጣሁ ነበር የሚጠይቁት፡፡ እርሷ የምትሰራበት የውጪ ድርጅት አዲስ አባል እንደሆንኩ አድርጋ ያሰናዳችውን መልስ ነበር የምትነግራቸው፡፡

ጎዴ መሸት ሲል ትንሽ ተንፈስ ትላለች፡፡ ከምሳ በኋላ መሥሪያ ቤቶች ሳይቀር ዝግ ናቸው፡፡ አመሻሸ ላይ እንደገና ሥራ ይጀመራል፡፡

የቀኑ ሀሩርና ገሃነም መሰሉ ሙቀት ጋብ ሲል ነዋሪዎች በየበራቸው ይወጡና ይቀመጣሉ፡፡ ጫት የጨረሰ የቢራ አንገት ያንቃል፡፡

# ፯

የውጪዉ ድርጅት ላቀደው ጥናት ለምን እኔን መምረጥ እንደፈለገ ሳሰላስል አደርኩ። ሁልጊዜም ለአዲስ ፈተና ራሴን ማዘጋጀት ደስታ ቢሰጠኝም፣ ይህኛው ፈተና ግን ከጥናቱ ውጪ ያለ ከባድ ተግዳሮት አለበት። እስራት ወይም ሞት ሊሆን ይችላል። ይህ ከየትኛው ወገን ሊመጣ እንደሚችል አለመታወቁ ደግሞ ሌላው ችግር ነው። ማንን መጠንቀቅ እንዳለበት የማያውቅ ግዳይ፣ ወደ ገዳዩ እየገሰገሰ ላለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አይችልም።

ተነስቼ ከተጣጠብኩ በኋላ፣ ማስታወሻዬን ይዤ ከክፍሌ ወጣሁ። ትናንት አያን ባስጠነቀቀችኝ መሠረት ፓስፖርቴን ኪሴ ወሽቄአለሁ።

ከፔኒሲዮኑ ፊት ለፊት ካለች የክኒን ዛፍ ሥር፣ ቡና የምታፈላ ሴት አየሁና ሄጄ ባርጩማ ላይ ተሰየምኩ።

ቡናው የገለጠልኝ ይመስል የውጪው ድርጅት ሁነኛ ላለው ጥናቱ የጋበዘኝ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሆነ ተረዳሁ። አንደኛው በግብፅ በረሃ ውስጥ ያከናወንኩትና አዓለም አቀፍ እውቅና ያስገኘልኝ ጥናት ይሆናል ስል ገመትኩ። ብዙ ምሁራን ያጣቀሱት ጥናት ነው። ጥናቱ ብቻ ሳይሆን ፈታኝ በነበረው በረሃ ውስጥ የተከናወነ ምርምር በመሆኑ፣ ድርጅቱ የበረሃ ልምዴን





ከግምት አስገብቶ ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ግን የሶሻል አንትሮፖሎጂ ሞያዬን አጢኖ ሊሆን ይችላል የሚል ግምትም አጫረብኝ።

እንደሚታወቀው ሶሾሎጂ የተባለው የእውቀት ዘርፍ ከአንትሮፖሎጂ ጋር ሲጣመር፣ ስለ አንድ ማህበረሰብ በጥልቅ ለማወቅ ምሉዕ የሆነ መሣሪያ ይሆናል። ሶሾሎጂ የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር ሁኔታ፣ ጥቅል በሆነ መልኩ ወይም ጥልቅ በሆነ መንገድ የሚያጠና ሳይንስ ሲሆን፣ ባህሉንና የማህበረሰቡን ስነ ልቡናም በጥልቀት ይመረምራል። በማህበረሰቡ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ፣ ጠፍንገው የያዙትን ችግሮች፣ ግጭቶችን የሚፈታባቸውን ባህላዊ መንገዶች፣ ሊለውጣቸው የሚችሉትን ልማዶች፣ ሊተዋቸው የማይችሉትን ሁኔታዎች፣ ትኩረት የሚሰጣቸውን ኩነቶች እና ሌችንም ሁኔታዎች ይተነትናል። ካርል ማርክስ እንደሚለው ማህበረሰብ የመደብ ግጭት ውጤት ነው፤ የግጭቱ መንስኤ ደግሞ እያለቀ የሚሄደው የተፈጥሮ ሀብት ነው። ይህንን ሁኔታ በውል ለማጥናት ሶሾሎጂ የተባለው የእውቀት ዘርፍ ጥሩ መሣሪያ ሲሆን፣ ከሥሩና ከጥሩ ማህበረሰቡን ለማዎቅ ደግሞ አንትሮፖሎጂ የተሰኘው የጥናት መስክ ሁነኛ ዘርፍ ነው።

ሶሾሎጂ በብዙ መንገድ ከሳይኮሎጂ፣ ከፖለቲካል ሳይንስ፣ ከኢኮኖሚክስ፣ ከታሪክና ከጂኦግራፊ ጋር ቢገናኝም ከአንትሮፖሎጂ ጋር ግን ከሁሉም የበለጠ ትስስር አለው። ሶሾሎጂ የዘመኑ ማህበረሰብ ችግር ላይ ሲያተኩር፣ አንትሮፓሎጂ ግን የሚያተኩረው በጥንቱ ማህበረሰብ ችግር ላይ ነው። አሁን ያለው ማህበረሰብ ችግር ሲንከባለል የመጣ ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ እኔ የተፈለኩበት ዋናው ምክንያት ይኸው ነው ማለት ነው። ድርጅቱ ባቀደው ጥናት ላይ ሁለቱንም እውቀቶቼን እንድጠቀም ተፈልጓል። ጥቅሙ ግልፅ ነው። አንድ ሰርጂን ታካሚውን ከበሽታው ለመፈወስ ቆዳውን እንደሚቀደው አጥንቱን እንደሚሰብረው፣ የአንድን ማህበረሰብ ችግሩን ሰርስሮ ጠልቆ ማዎቅ፣ ፖሊሲ ለመንደፍና ማህበረሰቡን ለማሻሻል ይረዳል። ሀገሬን ለማዎቅ ከመሪዎቿ ይልቅ የውጪ መርማሪዎቿ ለምን እንደሚተጉ ግልፅ ነው። አሁንም ድረስ አይኖቻቸውን ከዚህች ጉደኛ ሀገር ላይ አልነሱም።

በተቃራኒው ማህበረሰቡን ጠልቆ ማዎቅ፣ ለፖለቲከኞች በደካማ ጎኑ ገብቶ ጠፍንጎ ለመግዛትም ያመቻል። ኧረ ለመሆኑ እኔን አሁን የጋበዘኝ የውጪ ድርጅት በጥናቱ መጨረሻ የሚያገኘው ጥቅም ምንድን ነው? ከሰጠምኩበት ሀሳብ ስነቃ የጨበትኩት የቡና ሲኒ ቀዝቅዞ ነበር።

"ምነው ጌታው? ቡናው እጅዎ ላይ ቀዘቀዘ'ኮ!" ቡና ሻጯ በግርምት እያየችኝ ነበር። "ሌላ ልቅዳልዎ?"

"ይሻላል።" ፍንጃሉን ከመስጠቴ በፊት የቀዘቀዘውን ቡና በመንተፍረት ቀመስኩት። የዝሆን ሃሞት የቀመስኩ መሰለኝ። ሁለተኛውን ቡና በትኩሱ ከመቅመሴ አያን እየተፍለቀለቀች መጣች። ትናንት ለቅሶ ዛሬ ሳቅ...

'ዛሬ ደግሞ ምን ሰቆቃ ትነግረኝ ይሆን?'

"እንደምን አደርክ ዶክተር?" አለች እጇን ለሰላምታ እየዘረጋችልኝ። ጊዜ ለማሳለፍ ይመስላል እጇ ላይ ያልሳለችበት ነገር የለም። ጥፍሮቿ በተለያዩ የጥፍር





ቀለሞች ተንቆጥቁጠዋል። "ዛሬ በጠዋት ተነቃቅተሃል። ለሥራውም ዝግጁ የሆንክ ትመስላለህ።"

"በትክክል!" አልኩ በውል ሳላስብበት። "ቡና ጠጪና ወደ ምትፈልጊበት ውሰጂኝ።"

"ሰዎቹ ስላልደረሱ አንድ ተጨማሪ ቀን መጠበቅ አለብን" አለች የተቀዳላትን ቡና እየተጎነጨች።

"ሰዎቹ?!..እነማን ናቸው ሰዎቹ?!...."

"ጥናቱን ለመሥራት የሚያግዙን ሰዎች ናቸው። ምነው ደነገጥክ?"

"አያይ!...አልደነገጥኩም።" ከቡና ሻጯ ፊት ሌላ ጉዳይ ማውራት አልፈለኩም። በዛ ላይ ከመግቢያ መውጫዬ ፊት ለፊት ናት። ሒሳቡን ከፍዬ ተነሳሁ።

"እንግዲያውስ ... ቀትሩ ሳይመጣ ወደ ትናንቱ ቦታ ብንሄድ ደስ ይለኛል" አልኳት የጠዋቷን ጮራ በስተምሥራቅ በኩል እየተመለከትኩ።

"ወደ'ኸዋል ማለት ነው?"

"ውሃ ደስ ይለኛል። በተለይ የሚወርድ ወንዝ መንፈሴን ይማርከዋል። አዲስ አበባ ስለምኖር ንፁህ ወንዝ ሲወርድ ለማዬት ባልታደልም ወደፊት ቀሪ ህይዎቴን ወደ ገጠር ወጣ ብዬ ወንዝ ዳር ቤት ሠርቼ ብኖር እያልኩ እመኛለሁ።"

"የእኔም ምኞት ነበር።" እንዳቀረቀረች ጥቂት 'ርምጃዎችን ተራመደች። የተገደለው እጮኛዋ ትዝ ብሏት መሆን አለበት።

"ለምንድን ነው ስለ እኔ ብቻ የምለፈልፈው? ስለ አንተ ታሪክ ለምን አትነግረኝም?" አለችኝ ቆም ብላ።

"ምን ታሪክ አለኝ ብለሽ ነው?" አልኩ ፈገግ ብዬ የምን ግዴን። ከየት ጀምሬ ልነግራት ነው? ከባዶነቴ ጋር አፋጠጠችኝ።

"ሚስት አለችህ?"

"አሁን የለችኝም" አልኩ ሳቂን አፍኜ ታሪኬን ከሚስቴ መጀመሯ እየገረመኝ። ለነገሩ ልክ ናት። እንዲያውም ትክክል ናት። ከሴት ስለመጣን ታሪካችን ሁሉ ከሴት ይጀምራል። አንዳንዴ ሳስበው ሴት ቀድማ የተፈጠረች ይመስለኛል።

"ምን ማለትህ ነው?" አለች ሳቅ ብላ። "አሁን የለችኝም ማለት ...እዚህ ይዣት አልመጣሁም ማለትህ ነው?"

"ፈታኛለች ማለቴ።"

"ምነው መጥፎ ሰው ነህ እንዴ?" ቆም ብላ አስተዋለችኝ። "በፍፁም መጥፎ ሰው አትመስልም። ግን... መልካም በሚመስሉ ሰዎች ውስጥ የተሸፈነ አደገኛ አውሬ ሊኖር ይችላል።"

"ትክክል ልትሆኚ ትችያለሽ።"

"ውስጤ አውሬው አለ እያልከኝ ነው?"

"የእኔውን አውሬ እንኳ እስካሁን ወጥቶ አላዩሁትም። በሚስቴ ውስጥ የነበረው አውሬ ግን እስከ ሰባት ቀንዶቹ ወጥቶ በዓይኔ በብረቱ ተመልክቼዋለሁ።"

"አልገባኝም።"





"ረጅም ነው ታሪኩ፡" የልጆቼ እናት...መልአክ የምትመስል ውብ ሴት ነበረች። ክንፏ የሳጥናኤል እንደነበር ያወቅሁት በኋላ ነው።...በምድር ላይ የምጠላውን ሰው መርጣ በማግባት ነው የተበቀለችኝ።"

"ምን ብትበድላት ነው?...ያን ያህል..."

"ቀድሞም አብራኝ አልነበረችም። ሥጋዋ እንጂ ነፍሷ ከእኔ ጋር እንዳልነበር የተረዳሁት በኋላ ነው።"

"እንዴት ታዲያ ልጆች ወለደችልህ? ...ወይስ ልጆችም የእርሱ ናቸው?"

"በፍፁም!" ሳይታወቀኝ ድምፄ እንደ በጋ መብረቅ ድንገት ባረቀ። ልጆቼ የእርሱ ቢሆኑ ኖሮ ምን ይውጠኝ ነበር?

"በዲ.ኤን.ኤ አላረጋገጥኩም። ባ... ባላረጋግጥም የእኔ ለመሆናቸው አንዳች ጥርጥር የለኝም። ወንዱ ቁርጥ እኔን ነው የሚመስለው። ሴቷም በህፃንነቷ እናቷን ትምሰል እንጂ ቅንድቧ ሳይቀር የእኔን ነው የሚመስለው። በምድር ላይ ያሉኝ ብቸኛዎቹ ደስታዎቼ እነርሱ ናቸው።"

"ይቅርታ..." አለች አያን እጄን ሳብ አድርጋ መንገድ እያስቀጠለችኝ። "እንዲህ ትሆናለህ ብዬ አላሰብኩም ነበር። ስሜት የሚነካ ጥያቄ በመጠየቄ ይቅርታ። ያሳደገው ልጁ የእርሱ እንዳልሆነ የተነገረውን አባት ያህል ስሜቱ ሊጎዳ የሚችል የለም። እውነቱ ግን የብዙ አባቶች ታሪክ እንዲህ መሆኑ ነው።"

"አያን!... የወሬአችንን ርዕስ መቀየር እንችላለን?"

"ይቅርታ..."

"...እኔ እዚህ በረሃ ውስጥ በዚህ ቅፅበት ድብን ድፍት ብል ግድ የለኝም። ተስፋ መቁረጥ የማልችለው

ልጆቼ ስላሉ ነው። ልጆቼን ሳስብ ስለነሱ ስል ሞትን አጥብቄ እፈራዋለሁ።"

"ርዕስ ቀይሪ... አላልከኝም?" ከት ብላ ሳቀች። "እኔስ ለምን እንደምኖር ታውቃለህ?...በግፍ የተገደለው አባቴና ከልታማዋ እናቴ ቢያንስ በእኔ ውስጥ መኖር አለባቸው ብዬ ስለማስብ ነው። እነርሱ ሞትን የገደሉት በእኔ ውስጥ ነው። ልጅ ማለት ሞትን የምትገድልበት መሣሪያ ነው። መኖር የምትችለው በልጅህ ውስጥ ብቻ ነው።"

"ታዲያ...ይህን ሁሉ እያወቅሽ ምን አይነት ቀልድ ነው የምትቀልጂው?"

"በጥያቄ ውስጥ የተረዳሁትን የማውቀው እኔ ነኝ። ልጆቹን የሚወድ አባት መልካም ሰው ነው ማለት ነው።" ፈገግ ብላ አጥብቃ ተመለከተችኝ።

እኔም በመልሱ ፈገግ ብዬ ተመለከትኳት። የቀድሞዋ ሚስቴ ከከዳችኝ በኋላ፣ ሴትን ልጅ ከልቤ ፈገግ ብዬ ስመለከት የመጀመሪያዬ ነው። ሁሉንም ነገር ላጫውታት ወሰንኩ። የዋቢ ሸበሌን ወንዝ አወራረድ ማጀቢያ ሙዚቃ አድርጌ ታሪኬን በሙሉ ልዘከዝክላት ቆረጥኩ - ሁለተኛ አንዳች የምትጠይቀኝ ነገር እስከማይቀር ድረስ!



፰

ከዋቢ ወንዝ ማዶ ከምትገኘው የአያን ቦታ ተቀምጠን ታሪኬን ባጭሩ እተርክላት ጀመር።

"...አዲስ አበባ ነው የተወለድኩት። ከቀበና ወንዝ ማዶ በምትገኝ መንደር ውስጥ። ቀበና ወንዝ እየዋኘሁ አደኩ። አሁን ሃምሳ ዘጠኝ ዓመት ሆኖኛል።"

"በቃ?!" ዝም ስላት ጊዜ አያን ሳቋን ለቀቀችው።

"አባቴ አለቃ ዶሬ የታወቁና የተከበሩ ሰው ነበሩ። ገና በልጅነቴ ባህላዊውን የኢትዮጵያን ትምህርት አስጠንተውኛል። በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመን የተቋቋመው የቅርስ ምርመራ ቡድን አባል ስለነበሩ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ጥበቦች በየጓዳውና በየጎድጓዳው እየገቡ አስሰዋል። ያልዞሩበት ጥበብ አለበት የተባለ ሀገር የለም። ከፋርስ እስከ ባቢሎን፣ ከሺናሻ እስከ ሱዳን ለጥበብ ዘምተዋል። ከጥንቷ ኑቢያ እስከ ግብፅ እየዞሩ ጥንታዊ ጥበቦችን ቃርመዋል።"

"ምን አይነት ጥበብ?"

"ሌሎች የናቁትን ጥበብ። ሌሎች እንደ ጊላቀርና እንደ ዘበት የሚያዩትን የአስማት ጥበብ ሳይቀር ሰብስበዋል።"

"አስማት?"

"አዎ አስማት፡፡ በአስማት አታምኚም?"

"በፍፁም!"

"አታስቂኝ!...እኔም አላምንም ነበር፡፡ አንትሮፖሎጂ ያጠናሽ ምሁር ሳለሽ እንዴት እንደዚህ ያሉትን ጥበቦች ለመመርመር ዓይኖችሽን አልገለጥሽም?..."

"አኡዝቢሊላሂ!....እንኳን ልመረምረው ይህን የሻጣን ሥራ ስሙ ሲጠራ እንኳ ያስደነግጠኛል፡፡"

ረጂም ሳቄን ለቅቄ ቀጠልኩ፡፡

"በእኔ የደረሰውን ብታይ ኖሮ እንዲህ ባላልሽ!... ለማንኛውም ታሪኬን ልቀጥልልሽ፡፡ ባህላዊዉን ትምህርት በአባቴ እግር ሥር ካጠናሁ በኋላ ወደ ዘመናዊ ትምህርት ገባሁ፡፡ ከልጅነቴ ጀምሬ በጥንቱ እውቀት ላይ ስለተሳብኩ በዘመናዊ ትምህርቴም ወደ ጥንቱ አለም ያጋደሉ ትምህርቶችን ነው የቀሰምኩት፡፡ አርኪዎሎጂን በጀርመን ሀገር፣ አንትቶፖሎጂን በፈረንሳይ ሀገር፣ ፊሎሎጂን በእንግሊዝ ሀገር አጥንቻለሁ፡፡ በመጨረሻም በሶሻል አንትሮፖሎጂ የዶክትሬት ዲግሪዬን በመያዝ ብዙ የምርምር ሥራዎችን ሠርቻለሁ፡፡ ሁሉም ማለት ይቻላል፣ የጥንቱን አለም ምስጢር የሚመረምሩ ናቸው፡፡ ትዳርን በተመለከተ... ወደ ሀገር ቤት ከተመለስኩ በኋላ፣ አንዲት በውበቷ የማረከችኝን ሴት አብግቼ ሁለት ልጆች ወልጃለሁ፡፡"

"ፊትቻለሁ...ምናምን ያልከው ነገርስ?"

"...ከልጅነቴ ጀምሬ ስለማመደው የነበረው አስማት ነው ጉድ የሠራኝ፡፡ ከአራት አመታት በፊት ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ለአንድ ጥናት ሄጄ ነበር፡፡ ...ከይርጋለም ከተማ አለፍ እንዳልኩ በሐመልማል በተሸፈነው ጫካ መመሰጥ ጀመርኩ፡፡ መኪናዬን አቁሜ ወረድኩና ተጉዤ ሳላስበው ጫካው ውስጥ ራሴን አገኘሁት፡፡ የሚጣራ ልዩ መስህብ ያለው ጫካ ውስጥ፣ በተፈጥሮው ውበት ተማርኬ በመደመም አንዳች አስማት ማነብነብ ጀመርኩ፡፡ አስማቱ ወደ ውሻነት የሚለውጥ ኖሯል ለካ!"

አያን አፏን በድንጋጤ ከፈተች፡፡

"ወደ ውሻነት ተለወጥኩ!"

"የፈጣሪ ያለህ!" ዓይኖቿ ፈጠጡ፡፡

"አስቸጋሪው ነገር እንደገና ወደ ሰውነት መመለሻውን አስማት አላጠናሁም ነበር፡፡ 'ከድጡ ወደ ማጡ' እንዲሉ ወደ ሰውነት መመለሻው አስማት አዲስ አበባ ከሚገኘው ቤቴ ውስጥ ሳንዱቅ ከተቆለፈባቸው ጥቅሎች ውስጥ ነበር ይገኛል ብዬ የገመትኩት፡፡"

"አዲስ አበባ ሄድክ? ...ማ...ማለቴ እንዴት ተመለስክ ...ያን ሁሉ መንገድ?..."

"...ከሰውነት ክብሬ ወርጄ ...እንደ ውሻ አጥንት እየጋጥኩ ...ፍፁም ውሻ ሆኜ ... በስንት አሣርና መከራ አዲስ አበባ ለመድረስ አመት ፈጅቶብኛል፡፡ አዲስ አበባ ከደረስኩ በኋላ ግን ሌላ ችግር ገጠመኝ፡፡"

"ምን አይነት ችግር..."

"...እጅግ አፈቅራት የነበረችው ባለቤቴ ኤፍራታ፣ እጅግ በምድር ላይ ጠላቴ የነበረውን የቀድሞ ጓደኛዬን አግብታ ጠበቀችኝ፡፡ ሞቷል ተብዬ ኖሯል፡፡ ሁለተኛ

በምጠላው ሜንጦ በሚባል ገደለችኝ፡፡ ልጆቼ አጥብቁ አጥብቀው ጠበቁኝ፡፡ አንገታቸው እንደ አጋሰስ ሰው እጅ ወድቀው ጠበቁኝ፡፡ እንደ ጅብ ጥላ ተንጠልጥሎ መቃ መንምኖ፣ ራሳቸው እንደ ጅብ ጥላ ተንጠልጥሎ በውሻ ዓይኖቼ ተመለከትኳቸው፡፡ ሚስቴ ግን ከባላንጣዬ ጋር አዲስ አበባን ባንድ እግሯ አቁማት ነበር፡፡ ለአሸሸ ገዳሜው፣ እድሜ ልካቸውን የሚቀልባቸው ሀብቴን፣ ከየባንኩ አውጥታ ቀርቅባለች፡፡ በራሴ መኪና በራሴ ቤት እየተንፈላሰሰ፣ በዛ ላይ በራሴ አልጋ ላይ ሚስቴን እያፈሰ የጠበቀኝ ባላንጣዬ፣ የድሮ ጓደኛዬ ነበር፡፡"

"ታዲያ ምን በጀህ..."

"በውሻነቴ ውስጥ ራሴን አረጋግቼ፣ ወደ ሰውነት የሚመልሰውን አስማት ወደ ቤቴ ገብቼ ለመፈለግ ስልቶችን መንደፍ ጀመርኩ፡፡ አያሌ ቀናትን ፈጀሁ፡፡ በመጨረሻም ጥቅሎቹን አገኘኋቸው፡፡ በጥቅሎቹ ውስጥ ግን በቀጥታ ወደ ሰውነት የሚለውጥ አስማት አልነበረም፡፡"

"ያንትያለህ!"

"...ስመጀመሪያ ወደ ዘንዶነት ተለወጥኩ፡፡ በመቀጠል ወደ ሌላ የማላውቀው ቀጭን መንማና ሰው ተቀየርኩ፡፡ ተስፋ ባለመቁረጥ ስሞክር ወደ ሌላ ባለፀጋ የነበረ ወደሚመስል ሰውዬ ተለወጥኩ፡፡ እንባ እየተናነቀኝ የመጨረሻ እድሌን ሞከርኩ፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር ወደ ገረጣው እኔነቴ የመጣሁት፡፡ መለመላዬን ነበርኩ፡፡ ...ረጂም ነው ታሪኩ፡፡ ሳሳጥርልሽና...በጓሮ በር በኩል ገብቼ ልብስ ለብሼ ወደ ባንክ ቤት ሄድኩ፡፡ ከአንዱ ባንክ በቀር በሌሎች ባንኮች ሁሉ ያለኝን ሀብት በሙሉ ጠራርገው አውጥተውት ነበር፡፡

"ዘመን ከሚባለው ባንክ ያስቀመጥኩት ጠቀም ያለ ሀብት ግን አልተነካም ነበር፡፡ እሱን አውጥቼ ለሰው ልጅ





የሚያስፈልጉትን ነገሮች አደረኩ፡፡ ቆንጆ ቤት ገዝቼ ካስተካከልኩ በኋላ ልጆቼን ይዤ ብቻዬን መኖር ጀመርኩ፡፡"

"...ሚስትህና ውሽማዋ እንደገና ሲያዩህ ምን አሉ?"

"...ከወጥመድ እንደገባች አይጥ ከመቁለጭለጭ በቀር ያሉት ነገር አልነበረም፡፡ ሽጉጤን አቀባብዬ ገብቼ ልገድላቸው ከፊት ለፊታቸው ተቀምጬ ነበር፡፡ ግን...ባዶ እቃ ላይ እንደመተኮስ ቆጠርኩት፡፡ ጥያቼው ወጣሁ፡፡ ባለመግደል ተበቀልኳቸው፡፡ ዘበኛዬን፣ የቤት ሠራተኛዬንና ልጆቼን ይዤ ወደ አዲሱ ቤቴ ተሰደድኩ፡፡"

"የሚገርም ታሪክ ነው፡፡ ልቦለድ ይመስላል፡፡"

"ለእኔም እንደዛ ነው የሚመስለኝ፡፡"

"ከዛ በኋላስ? ...ሚስት ለማግባት አልሞከርክም?"

"በፍፁም!...ከሴት ጋር ይህን ያህል ሳወራ እንኳ ከአራት አመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው፡፡"

"ጥሩ! ...ወደፊትስ..."

"የሚሆን አይመስለኝም፡፡ በልጆቼ ዓይኖች ውስጥ የማገኘው ደስታ በቂ ነው፡፡"

"ልጆችህን የምትወድ ሴት ብትመጣስ?"

"አይመስለኝም፡፡... ይልቁንስ ሥራዬን ጨርሸ ልጆቼን የማይበት ጊዜ ገና ካሁኑ እየናፈቀኝ ነው፡፡"

አያን፣ በዝምታ ለረጂም ደቂቃዎች ራሷን እየነቀነቀች ከቆዩች በኋላ፣ ከተቀመጠችበት ተነስታ፣ ወደ ሚወርደው ወንዝ ጠጠር ትጥል ጀመር፡፡

"ዦር ልትልልኝ ትችላለህ?" አለች ከረጂም ደቂቃዎች በኋላ፡፡ "ልዋኝ እፈልጋለሁ፡፡"

ደንግጬ ተነሳሁ፡፡



# ፱

ጀርባዬን ለወንዙ ሰጥቼ ገንቡን እየወጣሁ እያለ፣ "ቻፍ" የሚል ድምፅ ሰማሁ፡፡ አያን ልብሶቿን አወላልቃ ዘላ ወንዙ ውስጥ ለመዋኘት ስትገባ የተፈጠረው ድምፅ መሆኑን ገመትኩ፡፡ አስቀናችኝ፡፡ ፀሐይዋ እየከረረች በመምጣቷ ሙቀቱን ለማስታገስ ዋቢ ወንዝ ውስጥ ዘሎ ገብቶ መዋኘትን ያህል የተሻለ ነገር የለም፡፡ ሆኖም የአያንን ትዕዛዝ ማክበር ነበረብኝ፡፡ ከእርስዋ ጋር አብሬ ስዋኝ ብታይ የሚፈጠረውን ችግር መገመት ቀላል ነው፡፡

ከወንዙ ገንብ አፋፍ ላይ ባለችው ብቸኛ የክኒን ዛፍ ሥር ተቀምጬ አሻግሬ ቀዬውን ሁሉ መቃኘት ጀመርኩ፡፡ አያን እንደነገረችኝ፣ የጎዴ አካባቢ ነዋሪዎች ክኒን እየተባለ የሚጠራውን ዛፍ ለወባ መድኃኒትነት ይጠቀሙታል፡፡ ቅጠሉ የፓራሲታሞል ምሬት ቢኖረውም ጨቅጭቀው ወባ ለያዘው ሰው እንደሚግቱት ነግራኛለች፡፡

ከክኒኗ ዛፍ ስር ተቀምጬ፣ ቁልቁል ወደ ወንዙ ስመለከት በረባዳው ሸጥ ውስጥ ያለ ቱማታ ፀጥ ብሎ ይፈስ የነበረው ወንዝ ሲንቦጫረቅ አየሁ፡፡ የአያን የደስታ ሲቃ ድምፅ በጥቂቱ ይሰማኛል፡፡ ዋቤን ያለ አንዳች ዋቢ ገብታ እየደነከረችበት ነው፡፡ ከጥብቁ ባህል ያለአንዳች ፍርሃት በማፈንገጧ እኔን ሳይቀር አስቀናችኝ፡፡

'ከነፃነት በላይ የሚያስቀና ነገር የለም' ስል ደመደምኩ፡፡ ሌሎች የሚያስቀኑ ቁሳዊና መንፈሳዊ ነገሮችም በነፃነት ማዕቀፍ ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ …ነፃነት በነፃ አይገኝም፡፡ እንደ አያን መወገዝንና እንደ ስማዕት መወገርን ይጠይቃል፡፡ መወገዙንም መወገሩንም የመቋቋም አቅም ይጠይቃል፡፡ አያን 'ወንጌ' የሚል ቅፅል ወጥቶላታል፡፡ ግን ከቁብ አትጥፈውም፡፡ …ይልቁን በቀሰመችት ትንሽ እውቀት አካባቢዋን አጥንታ ለመለወጥ ትባዝናለች፡፡

ከተቀመጥኩበት ተነስቼ በወንዙ ዳርቻ እየተንሸራሸርኩ፣ ከሩቅ ያሉት ኮረብቶች ዓይኖቼን እስኪጋርዷቸው ድረስ አካባቢውን መቃኘት ጀመርኩ፡፡ ከአድማሱ ጥግ ያሉት ኮረብቶች የዚህን በረሃ ታሪክ ይተርኩልኝ ይመስል በዓይኖቼ ጨረሮች ዳሰስኳቸው፡፡ ወደዚህ ከመምጣቴ በፊት ስለዚህ አካባቢው ነዋሪዎችና ስለዚህ በረሃ የሰቆቃ ታሪክ ያነበብኩት ሁሉ የጆሮ ታንቡር እንደሚበሳው ነፋስ ያፏጭብኝ ጀመር፡፡

ሱማሌዎች በምስራቅ አፍሪካ አካባቢ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ1200 ዓመተ ፍዳ ጀምሮ የዚህን በረሃ ፍዳ እየቀመሱ መኖራቸው በታሪክ የተመዘገበ ነው፡፡

ቀደምት ጥንታወዊ ፅሁፎች እንደሚያስረዱት፣ ይህን በረሃ ይዘውት የነበሩት ነገዶች፣ ከካም ነገድ የወጡ አፋር የተባሉ ህዝቦች ነበሩ፡፡ ኦጋዴን ውስጥ ጥንታዊ ከተማም እንደነበራቸው ጥንታዊ ክታቦች ይገልፃሉ፡፡ ዘመኑ በውል ባይታወቅም እነዚህ ህዝቦች ስልጣኔ እንደነበራቸው ውስን የሆኑ ድርሳናት ይገልፃሉ፡፡ ምናልባት የራሳቸው የፅሁፍ ባህል ስላልነበራቸው ይሆናል ስልጣኔአቸውን የበረሃው





አሸዋ ውጦት ቀርቷል፡፡ እስከዛሬ ድረስ በብዙ ሊቃውንት ዘንድ አወዛጋቢ ሆኖ የቆየው የፑንት ምድርም ይህ በረሃ እንደሆነ በመግለፅ የሚከራከሩ አልጠፉም፡፡

ምሁራኑ ይህ አካባቢ የፑንት ምድር እንደሆነ እንደ ማስረጃ የሚያቀርቡትም የአካባቢውን ኮረብቶች የወረረውን የእጣንና የከርቤ ዛፍ ነው፡፡ የጥንታዊቷ ግብፅ ንግሥት በነበረችው ሃትሸፕሱት ዘመን በፒራሚድ ላይ ተቀርፆ እንደተገኘው፣ የፑንት ምድር ከርቤና እጣን የሚታፈስበት በማዕድናት የበለፀገ የንግድ መናኸሪያ ነበር፡፡ የፑንት ምድር ቀጫጭኖቹ ጥቋቁር ተዋጊዎችም፣ አልመው የማይስቱ ነበሩ፡፡ ምድራቸውንም፣ የግብፅ የፒራሚድ ላይ የሄሮግሊፊክስ ፅሁፎች የአማልክት ምድር ሲሉ ይጠሩታል፡፡ ጥንታዊ ግሪኮች፣ ይህ ምድር ኢትዮጵያ እያሉ የሚጠሩት ሀገር አካል የሆነና የተቃጠለ ፊት ያላቸው የፑንት ህዝቦች የሚኖሩበት እንደሆነ ፅፈዋል፡፡

ከክርስቶስ ልደት ከ1473 እስከ 1488 ዓመተ ዓለም የነገሠችው የግብፅዋ ንግስት ሃትሸፕሱት ወደዚህ ምድር ከፍተኛ ልዑካንን፣ በንግድ ለመተሳሰር ፑንትን ይመራ የነበረው ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ፓሬሑ እንደነበር በዴር አል-ባሪ ቤተመቅደስ ላይ በሄሮግልፊክስ ተቀርፆ ይገኛል፡፡

በኋላ ግን የኤደን ባህረ ሰላጤን እየተሻገሩ የመጡና በልፅጎ የነበረ ንግዳቸውን ለመቆጣጠር የቋመጡ የአረቢያ ምድር ነገዶች ገብተው ተቀየጧቸው፡፡ ምድራችንን አንለቅም ያሉት የመጤዎችን ባህልና ሃይማኖት በመቀበል በረሃውን ሙጥኝ ብለው ሲቀሩ፣ ጥንታዊ ባህላቸውንና ወጋቸውን የያዙት ግን ወደ ደጋማው የኢትዮጵያ ክፍል እንደ ሸሹ የሶማሌ ወንዶች ክታቦች ያስረዳሉ፡፡ አሁንም ድረስ የሶማሌ ወንዶች ራሳቸውን 'እንደ ጎበዝ ጦረኛ መቁጠራቸው ከዚህ የቀደመ

ታሪክ በመነሳት ይሆን?... አሁንም ድረስ የሶማሌ ወንዶች፣ እረኝነትን ለሴቶች በመተው ኢላማ ሲለማመዱ መዋል ልማዳቸው ነው። የሶማሌ ልጃገረዶች የፍዬል መንጋ ሲከተሉ ማየትና ወንዶቹ መሣሪያ አንግተው ሲንጎማለሉ መመልከት አዲስ አይደለም።

ሶማሌዎች፣ ተመሣሣይ ቋንቋ ቢናገሩም፣ ዘጠና ዘጠኝ በመቶ ተመሣሣይ የሆነ የእስልምና ሃይማኖት ቢከተሉም፣ ሁልቆ መሣፍራት በሌለው ጎሳ የተከፋፈሉ ናቸው። ደም አፋሳሽ ለሆነ እልቂት የሚዳርግ የጎሳ ጦርነትም በረሃውን ለዘመናት ሲያምስ የኖረ ነው። ነገር ግን እርስ በእርስ ይጋጩ እንጂ ለሌላ ጠላት ግን አንድ ላይ ይነሳሉ።

የረጋ ህይወት መሥርተው በግብርና እና በእደ ጥበብ የተሠማሩ ጎሳዎች ቢኖሩም፣ በዘላንነት የከብቶቻቸውንና የግመሎቻቸውን ጭራ ተከትለው በረሃውን የሚያካልሉ ጎሳዎችም አሉ። ዘላኖቹ፣ ከእንጨት ቅርንጫፎች ተውተርትረው በተሠሩና ስጋጃ በለበሱ ተንቀሣቃሽ ጎጆቻቸውን ከሴቶቻቸው ሲቼሩ፣ ምግቦቻቸውን ከሚከተሏቸው መንጋዎቻቸው ያገኛሉ። የፍዬልና የግመል ወተት፣ የግመል ሥጋ ሲመገቡ በረሃው ሲቸርም ፍራፍሬ ይለቅማሉ። ከጥንታዊ አረቦች ወይም ህንዶች የወረሱት እንደሆነ የሚነገርለት ሻይ በወተታቸውም ዝነኛ የባህላቸው መገለጫ ነው።

ሶማሌዎች... አጁራን፣ በርሱክ፣ ካለድሬ፣ ዳሮድ፣ ዲር፣ ጋዳቡርሲ፣ ጉርጉራ፣ ሃባር ገደር፣ ሃርቲ፣ ኢሳ፣ ሂራብ፣ ማጂርቲን፣ ሙሴ፣ ማር ሃን፣ ጂድ ዋቅ፣ ሺካል፣ ይብር... የተባሉ አያሌ ጎሳዎች ሲኖሩት፣ ኦጋዴን የተባለው ጎሳ ግን ላቅ ያለውን ቁጥር ይይዛል። እንዲሁም ራዌና ከዲር የተባሉ ጥቋቁር የሶማሌ ጎሣዎች ሲኖሩ፣





ዱቤ እና ኤረርበሬ የተባሉት ደግሞ ለየት ያለ ታሪክ እንዳላቸው የሚነገርላቸው የዋቢ ሸበሌን ወንዝ ተከትለው የሚኖሩ ጎሳዎች ናቸው። እነዚህን የዋቢ ሸበሌ ወንዝ ተከትለው የሚኖሩ ጎሳዎች አፄ ምኒልክ አምጥተው እንዳሰፈሯቸው አንዳንድ አዛውንቶች ይናገራሉ።

በጥልቅ ሀሳብ ውስጥ ገብቼ የወንዙን ዳርቻ በመከተል ረጂም ርቀት እንደተጓዝኩ የተገነዘብኩት ኩንክ ከሚባለው የመስኖ እርሻ ስደርስ ነበር። እንደለመደብኝ በጥንቱ ዓለም ታሪክ ጠልቄበት ኖሯል። የዚህን አሽዋ ያስጠመው በረሃ ጥንታዊ ታሪክ አእምሮዬ ከአካሌ ወጥቶ ይቆፍር እንደነበር የተገነዘብኩት፣ ከሃሳቤ ስነቃ የፀሐይዋን መክረር አይቼ ነበር። በጤናዬ ብሆን ኖሮ ላቤን ለመጥረግ የለበስኩት ልብስ ሁሉ ባልበቃኝም ነበር። ነገር ግን ከራሴ ጋር አብሬ ባለመኖሬ የተነሣ ግንባሬ ችፍፍ ያለ ላብ ቀርቶ ወዝ እንኳ አልነበረውም። በፍጥነት ወደመጣሁበት መመለስ ጀመርኩ።

ብቻዋን ወንዙ ውስጥ ገብታ እየዋኘች የነበረችው አያንን ይህን ያህል ጥያት መምጣት አልነበረብኝም። የሚያጋጥማትን ማን ያውቃል? ልብሷን ለማውለቅ ዞር በልልኝ አለችኝ እንጂ ትተኸኝ ሂድ አላለችኝም። በአእምሮዬ ውስጥ ክፉ ክፉ ሃሳብ እየመጣ ተሰገሰገብኝ። ወደኔ አቅጣጫ የዞረ የራሴን ዱካ ተከትዬ ወደመጣሁበት ገሰገስኩ።

# ፲

እያለከለኩ ወደ ወንዙ ወርጄ ውሃው ዳር ቆምኩ፡፡ ላቤ በጉንጬ እየተንቆረቆረ ነበር፡፡ የኦጋዴን ወበቅ ልብሴን አስወልቆ ሊያሳብደኝ ደርሷል፡፡ ዋቢ ላይ ዓይኖቼን አንከራተትኳቸው፡፡ ሙቀቱ ወንዙን እንደ ሽሮ ያንተከትከው ይመስላል፡፡ የአያንን ልብሶች ነፋሱ ወስዶ በየቆንጥሩ ሰቅሏቸዋል፡፡ አያን ግን የትም አትታይም፡፡ ዓይኖቼን ፀጥ ረጭ ብሎ በሚፈሰው የዋቢ ወንዝ ላይ አቅበዘበዝኳቸው፡፡ አያንን ግን ማዬት አልቻልኩም፡፡ የት ገባች?

"አያን!" ተጣራሁ፡፡ የራሴ ድምፅ፣ በወንዙ የገደል ማሚቶ መላልሶ አስተጋባብኝ፡፡ ደጋግሜ ተጣራሁ፡፡

"አያን!...አያን!...አያን!..."የገደል ማሚቶው ደጋግሞ አስተጋባ፡፡

የት ገባች? ልብሶቿ ከወንዙ ማዶ ባሉት የቆንጥር ዛፎች ላይ እንደ ባንዲራ ተሰቅለው በፈጣኑ ነፋስ ይርገበገባሉ፡፡ በወንዙ ዳርቻ ከወዲያ ወዲህ በፍጥነት እየተመላለስኩ ተጣራሁ፡፡ መልስ የለም፡፡ በአእምሮዬ ያሰብኳቸው ሰቅጣጭ ቅዠቶች ምስል ሠርተው ተንቀሳቀሱብኝ፡፡ የወንዙ ዳር የበረሃ ዘንዶ ተወርውሮ የተጠመጠመባት መሰለኝ፡፡ ግዙፉ ዘንዶ ወገቧን ጨምቆ ካደቀቃት በኋላ





በኃይል አፉን መልግዶ ሲውጣት በዓይነ ህሊናዬ ተሳለብኝ፡፡

ዓይኖቼን አርገብግቤ አሁንም ተጣራሁ፡፡...ከራሴ የድምፅ ማሚቶ በቀር አሁንም መልስ አላገኘሁም፡፡ ‹ደራሽ ውሃ ወስዷት ይሆን?› ስልም አሰብኩ፡፡ የዋቢ ሸበሌ ወንዝ ከታላላቆቹ የኢትዮጵያ ተራሮች ስለሚነሳ ምናልባት እዛ ዘንቦ ሊሆን ይችላል ስል ገመትኩ፡፡ እዚህ በረሃ ውስጥ እንዴት የዝናብ ጠብታ ሳትኖር የዋቢ ሸበሌ ወንዝ እስከ አፍጢሙ ግጥም ብሎ እንደሚሞላ ሰምቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ወንዙ ምንም ለውጥ አላሳዬም፤ ጠዋት ስመጣ እንዳዬሁት ነው፡፡ በወንዙ ዳርቻ ምንም አይነት አዲስ የመጣ ግፋፎ የለም፡፡

አጥብቄ በመመልከቴ ብቻ በፀሐዩ ጨረሮች የሚያንፀርቀው ወንዝ አያንን ይተፋት ይመስል፣ የራሴን ምስል እስካይ ድረስ አፍጥጬ ከቆዬሁ በኋላ አንድ ውሳኔ ላይ ደረስኩ፡፡ ገብቼ ልፈልጋት ቆረጥኩ፡፡

የዛሬን አያድርገውና በልጅነቴ ቀበና ወንዝ ውስጥ ከሰፈር ጓደኞቼ ጋር እዋኝ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ቀበና ወንዝ ውስጥ ገብቶ የሚዋኝ ልጅ ያለ አይመስለኝም፡፡ ቀበናን የአዲስ አበባ የቆሻሻ ጉድ ይኾነኾደኾድበታል፡፡ በድልድዩ ላይ ሳልፍ እንደተመለከትኩት የየሸንት ቤቱን ቆሻሻ ይዞ የሚጓዘው የቀበና ወንዝ፣ ያልወጣውን የኦጋዴንን ነዳጅ ድፍድፍ እንጂ ውሃ አይመስልም፡፡ እዚህ ቆሜ አዲስ አበባን ሳስብ ገብቶ ለመዋኘት ቀርቶ አይቶ ለማለፍ የሚያስጠይፉት ወንዞቿ በዓይኖቼ ላይ ተሳሉብኝ፡፡ የአዲስ አበባን ጥንባት እንጂ የህዝቡን ብሶት ይዘው የማይወርዱት ወንዞቿ ሲፈሱ ታዩኝ፡፡ በልጅነቴ የለመድኩት ዋና፣ እንኳን ሌላን ሰው ለማዳን፣ ለራሴም የማያወላዳ ቢሆንም ልብሶቼን

አወላልቄ ልገባ ተሰናዳሁ፡፡ አያንን ባላድናት እንኳ ሳልፈልጋት ትቻት መሄድ አይቻለኝም፡፡

መለመላዬን ቆሜ እጆቼን ወደ ወንዙ ዘረጋሁና አመነታሁ፡፡ በመስጠምና በመንሳፈፍ መሃል ያለውን ልዩነት ለምን ማሰብ እንዳስፈለገኝ አልገባኝም፡፡ ሰዎችን የሚያስጥመን ፍርሃታችን እንደሆነ ሰምቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ስለዚህም ማሰብ አያስፈልገኝም ነበር፡፡ የሰው ልጅ ትልቁ የሽንፈቱ ምስጢር ፍርሃቱ ነው፡፡ ፍርሃት በራሱ ያስፈራል፡፡ ሆኖም… ፍርሃት የሚመጣው ለመኖር ካለ ጉጉት ነው፡፡ መኖር እንዳለብኝ ግልፅ ነው፡፡ ሰው ከወለደ በኋላ ፍርሃቱ በእልፍ ይጨምራል፡፡ ሰው ከወለደ በኋላ መኖር ምርጫው አይደለም፤ ግዴታው ነው፡፡ የመኖርና ያለመኖር መብቱን በልጁ ይነጠቃል፡፡ አዲስ አበባ ጥያቼው የመጣኋቸው ልጆቼ ውልብ አሉብኝ፡፡ አባታቸውም እናታቸውም እኔ ነኝ፡፡ እናታቸው ወልዳ እንደ እበት ጥላቸዋለች፡፡

የልብ ምቴ ይሰማኛል፡፡ በመስጠምና በመንሳፈፍ መሃል ቆምኩ፡፡ በመላምት መዋኘት ቢቻል ኖሮ ይህን ያህል ባላንበቀበቀኝ ነበር፡፡ ዋና ስለማመድ የትኛው የአእምሮአችን ክፍል ለመንሳፈፍ እንደሚያስችለን አውቃለሁ፡፡ የፊተኛው የአእምሮአችን ክፍል ፍርሃታችን ተቆጣጥሮ እንደ አስከሬን ያንሳፍፈናል፡፡ አስከሬን የማይሰጥመው ስለማይፈራ ነው፡፡ ነፍስ ያላወቁ ህፃናትም አይሰጥሙም፡፡ ይኸውም ፍርሃት ስለሌላቸው ነው፡፡ ዋና የማይለማመዱት እንስሳት ብቻ ናቸው፡፡ ወደ ወንዙ ልገባ ስንደረደር እሳትና ውሃ ሲበዙ እንደሚያስፈሩ እያሰብኩ ነበር፡፡

እንደምንም ጥርሴን ነክሼ ወንዙ ውስጥ ተደነቦቅሁ፡፡ ለሰኮንዶች ራሴን ስቼ ነበር፡፡ በደመ ነፍስ እየተንሳፈፍኩ





ነቃሁ፡፡ በልጅነቴ የለመድኩት ዋና አልጠፋብኝም፡፡ በሲቃ ጮህኩ፡፡

"ሁሁ!" የልብ ልብ ተሰምቶኝ በወንዙ ላይ ከወዲያ ወዲህ እየተንቦራጨኩ አያንን መጣራቴን ቀጠልኩ፡፡ ነገር ግን አሁንም ደምፅዋ የውሃ ሽታ እንደሆነ ነው፡፡

ጠልቄ ለማዩት ሞከርኩ፡፡ ውሃው የጠራ ባለመሆኑ ጉም ከመሰለ ነገር በቀር የሚታዬኝ ነገር የለም፡፡ ይባሱን አንድ ትልቅ ቋጥኝ ግንባሬን ሊቦረቅሰኝ ለጥቂት ተረፍኩ፡፡

ለአያሌ ደቂቃዎች በወንዙ ላይ እየጠለኩና እየተንሣፈፍኩ ፈልጌ ከአጣኋት በኋላ ተስፋ ቆርጬ ዋናዬን ለማቋረጥ ወሰንኩ፡፡ ወደ ከተማ ሄጄ ለፖሊስ ማመልከት ይኖርብኛል፡፡ በወንዙ ዳርቻ ላይ ነፋስ ወስዶ የሰቀላቸውን ልብሶቿን ባዬሁ ቁጥር የበለጠ አንጀቴ ይላወስ ጀመር፡፡ ጉሮሮዬን አንዳች ነገር እያነቀኝ ያጫወተችኝን ታሪኳን ሁሉ አስታወስኩ፡፡ የአባት የእናቷ አሰቃቂ አሟሟት የጫነባትን የሀዘን ካባ ሳታወልቀው ወደ መጣችበት መመለሷን ሳስብ እንባ ተናነቀኝ፡፡ ሆደ ቡቡ ያልነበርኩት ሰውዬ ባር ባር እያለኝ ወደ ወንዙ ዳርቻ ዋኘሁ፡፡ ነገር ግን ከኋላዬ ባለው የወንዙ ዳርቻ የሆነ ነገር የወንዙን ፀጥታ ሲያደፈርሰው ሰማሁ፡፡ ሽዋ! ካለው የውሃ ድምፅ ጋር የተቀላቀለ ሳቅ ስሰማ ከመቅፅበት ድምፁን ተከትዬ ዞርኩ፡፡ አያን ከወዲያኛው አቅጣጫ እየዋኘች ወደ እኔ እየመጣች ነበር፡፡

"የፈጣሪ ያለህ!" አልኩ በተዘበራረቀ ስሜት፡፡

"ምን ነካሽ?!...የሞትሽ መስሎኝ ነበር፡፡"

እየሳቀች ብቻ ከጥጌ ደረሰችና በዝምታ ተመለከተችኝ፡፡

"እዛ ማዶ ካለው ቋጥኝ ውስጥ ተወሽቄ የምታደርገውን ሁሉ እየተመለከትኩኝ ነበር፡፡ አለች ትንፋሽዋ እስኪገርፈኝ ተጠግታ፡፡

"በጣም ነው ያስደነገጥሽኝ።"

"ባለፈው በነገርከኝ የአስማት ችሎታህ በውሃው ላይ እየተረማመድክ ትፈልገኛለህ ብዬ ገምቼ ነበር።" ከጥጊ ስትዋኝ እግሮቿ እግሮቼን እየነኩኝ እንደሆነ ተሰማኝ።

"እንዴ! ምን ነካሽ? እኔ እኮ አስማተኛ አይደለሁም።"

"ስለ አስማት አጥብቀህ ከማጥናትህ የተነሳ ከአስማተኞች ሳትበልጥ አልቀረህም። ወደ ውሃው ከመግባትህ በፊት እጆችህን ዘርግተህ ለረጅም ደቂቃዎች ስትቆይ አንዳች ነገር ሊከሰት እንደሆነ እየገመትኩ ነበር። አስማት እየሠራህ መስሎኝ ነበር።"

"በፍፁም እንደዛ አልነበረም። ዋና ያቆምኩት በልጅነቴ ነበር። ተረስቶኛል ወይስ አልተረሳኝም? እስጥማለሁ ወይስ አልሰጥምም ብዬ በመጨነቅ ላይ ነበርኩ።"

"ህይወቴን ለማዳን ደፍረህ እዚህ የማታውቀው ወንዝ ውስጥ ስለገባህ አመሰግናለሁ!" አለችና ይበልጥ ተጠግታ ዓይኖቿን ዓይኖቼ ላይ አንከባለለችብኝ። አንዳች ልዩ ስሜት የሚፈጥሩ ጨረሮች የረጨችብኝ መሰለኝ። ከራሴ ጋር እየታገልኩ ዝም አልኳት። በነገረችኝ ግለ ታሪኳ መሠረት በ1969ዓ.ም ከተወለደች በዚህ ሰዓት እድሜዋ 39 አካባቢ ይሆናል። ይሁን እንጂ ገና የሃያዎቹ አካባቢ ልጃገረዶች ትመስላለች። ሰውነቷ ጥርት ያለና ልዩ መስህብ ያለው ነው። የዋና ልብስ ባለመልበሷ ምክንያት መላ አካሏን አለማየት አልቻልኩም። ከሾሉት ጡቶቿ ላይ ዓይኖቼን ለማሸሽ ጥረት ባደርግም፣ እርሷ ግን እንዳያቸው ፍላጎት ያላት ይመስል ከፊት ለፊቴ እየተስተካከለች መዋኘቷን ቀጠለች። ህይወቷን ለማዳን





ህይወቴን አደጋ ላይ ጥዬ መግባቴን እየደጋገመች በማንሳትና በማመስገን በዙሪያዬ እየተሽከረከረች ስትዋኝ፣ ልዩ ቅርፅ ያለው ዳሌዋንና የዘንባባ ፍሬ የመሰሉ ጭኖቿን ማዬቴን አላቆምኩም። እውነት ለመናገር ካለፉት አራት አመታት ወዲህ የሴት ልጅ ሙሉ እርቃን ገላ ሳይ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር። በበደል አርጩሜ የገረፈችኝ የቀድሞዋ ሚስቴ በልቤ ላይ ለሴቶች የጥላቻ አመዳይ እንዲወድቅ አድርጋለች።

"ሚስትህ ያሳደረችህብህ ጥላቻ ሁሉንም ሴቶች በጥቅል አስፈርጆሃል። አይደለም?" አለች አያን እንደገና ከአጠገቤ እየዋኘች።

"ውስጤን ማንበብ እንዴት ቻልሽ?...እኔም ይህንኑ እያሰብኩ ነበር።" ስሜቴ እንዳይነበብብኝ እየታገልኩ መለስኩላት። "አዎ...ሴቶች ሁሉ የአንድ ዛፍ ቅጠሎች ይመስሉኛል።"

"ስህተት ነው" አለች ከት ብላ ስታበቃ። "...እኔ የማስበው ግን ተቃራኒውን ነው። ፌሚኒስት ሆኜ ግን አይደለም። እንዲያውም ለወንዶች ሳላዳላ አልቀርም። ጭራሽ ሰዎች ሁሉ እኩል ናቸው ብዬ አላምንም። ሰዎች እኩል መሆን ያለባቸው በህግ ፊት ብቻ ነው። ከዛ ውጪ ባለው ሁሉ ግን መነፃፀር እንኳ የለባቸውም። ጠባያቸውና አመለካከታቸው ሁሉ እንደተቀዱበት ማህበረሰብ፣ እንደቀሰሙት እውቀትና ልምድ ይለያያል። ኤፍራታን ባዬህበት ዓይን አያንን ማዬት ፍፁም ስህተት ነው።"

መልስ ሳልሰጣት ለአያሌ ደቂቃዎች ተመለከትኳት። ሳቀችብኝ። ደጋግማ ሳቀችብኝ። እያላገጠችብኝ ነው ብዬ እስካስብ ድረስ ሳቀችብኝ። ጠፍንጎ ያሰረኝ አመለካከ

ሊያስጥመኝ እየታገለ፣ ዋኝተን ከወንዙ ዳርቻ ስንደርስ፣ የሚቀባበል የክላሽንኮቭ ቃታ ሰምቼ በደመ ነፍስ ቀና አልኩ። ስድስት ያህል፣ ጭንብል ያጠለቁና አውቶማቲክ መሣሪያ የታጠቁ ሰዎች፣ የተቀባበሉ መሣሪያዎቻቸውን ወድረው ከወንዙ እንድንወጣ አዘዙን።



# ፲፩

መሳሪያ ያቀባበሉት ሰዎች ባንክ ሲዘርፍ እንደተያዘ ወሮበላ በኃይል ተጯጯሁብን። ቋንቋቸው ሶማልኛ እንደሆነ ተረድቻለሁ። አዛገሮቸው ይመስለኛል አንዳንድ የአረብኛ ቋንቋ ይቀላቅላል።

"ቢሱር አህ! ...ቢሱር አህ!" ይላል እየደጋገመ። "ቶሎ በል! ...ቶሎ በል!"

አንደኛው ተንደርድሮ መጣና ጭንቅላቴ ላይ የክላሻንኮቩን አፈሙዝ ደቀነብኝ።

"ወሪያ! ሶአ!" አለ ወደፊት እየገፈተረኝ። "አንተ! ቀጥል!" የጫማው ቁጥር መቀመጫዬ ላይ እስኪቀረፅ ድረስ ረገጠኝ። ሌላኛው አፋኝ፣ ልብሶቼን አይነ ምድር የነካቸው ይመስል ተጠይፎ በጠመንጃው አፈሙዝ አንስቶ ሲያበቃ፣ ለሌላኛው አቀበለው።

አለቃቸው እንደሆነ የገመትኩት አስፈሪ ሰውዬ፣ አረብኛና ሱማልኛ እየቀላቀለ ሲለፈልፍ ከቆዬ በኋላ ልብሶቼን የወሰዳቸው ሰውዬ ሸርጥ አምጥቶ ሰጠኝ። እየተንዘፈዘፍኩ በወገቤ ዙሪያ አሸረጥኩ። ከወገቤ በላይ እርቃኔን ነኝ።

"ሶአ!" አለኝ ለብሼ እንደጨረስኩ በጠመንጃው አፈሙዝ ጭንቅላቴ እስኪበሳ ጎስሞኝ። "ቀጥል!" እያጣደፈ ዳገቱን በአፍታ አስወጣኝ።

ዳገቱን ጨርሼ ወደኋላ በቅፅበት ስመለከት፣ አንደኛው ወንበዴ የሚያብለጨልጭ ጩቤውን ከአያን አንገት ሥር ወሽቆ ፀጉሯን ጨምድዶ ወደ ዳገቱ እያንደረደራት ነበር። እርሷም እንደ እኔ አሽርጣለች። ጭንቅላቱ በአንገቴ ዙሪያ እስኪሽከረከር ከባድ ጥፊ መንገጭላዬ ላይ ሲያሳርፍብኝ አያንን ማየቱን አቁሜ ጉዞዬን ቀጠልኩ።

"ሚን ፋድላክ?!" ስትል ብቻ ይሰማኛል በአረብኛ- "እባክህ!?" ፀጉሯን እየነጫት ወይም ሳንጃው አንገቷ ሥር ቀዷት ይሆናል።

"ዋሲኽ!" ይላታል ድምፁን ከፍ አድርጎ- "ቆሻሻ!"። ሌሎቹ ጭንብል ያጠለቁ ወንበዴዎች በግራና በቀኝ በፍጥነት እየተራመዱ አካባቢውን በጥንቃቄ ይቃኛሉ። የቀትሩ ጊዜ ስለተተካ በአካባቢው ዝር የሚል የሰው ዘር የለም።

በግምት ለሃያ ደቂቃ ያህል እንደጋለ ብረት ምጣድ እግርን በሚጠብሰው የበረሃ አሸዋ ላይ ከተጓዝን በኋላ በረሃው ውስጥ ወደ ቆመ ክፍት የመስክ መኪና ደረስን። የእኔንና የአያንን እግርና እጆች ጠፍንገው ካሰሩ በኋላ፣ ዓይኖቻችንንም በጥቁር ሻሽ ግጥም አድርገው ጠፍረው ሲያበቁ፣ እየተሸከሙ ወደ ክፍቱ መኪና እንደ እቃ ወረወሩን። ሁለታችንም በክፍቱ መኪና ወለል ላይ እያቃሰትን ወደቅን። ወንበዴዎቹ በፍጥነት ከወጡ በኋላ መኪናው ሞተሩን አስጓርቶ ሲያስነሳ ተሰማኝ። ትንሽ ቆዬና በበረሃው ወጣ ገባ መንገድ ላይ ገጭ ጓ እያለ እንደ የሎስ ይከንፍ ጀመር።





# ፲፪

በግምት ለሶስት ሰዓታት ያህል፣ በረሃው ውስጥ በክፍቱ መኪና ነፍሳችን እስክትወጣ እየተንገጫገጭን ከተጓዝን በኋላ፣ መኪናው በድንገት ቆመ። ወንበዴዎቹ እንደ እቃ ተሸክመው ወደ ታች ለቀቁን። ወደ ገደል ሊጥሉን መስሎኝ ነበር። ጀርባዬን የሚከፍለኝን ቋጥኝ ስጠባበቅ፣ በድቡሽቱ አሸዋ ላይ ሳርፍ ከዚህ በፊት አውጥቸው የማላውቀውን ድምፅ አወጣሁ። ድቡሽቱ አሸዋ ባፍ ባፍንጫዬ ገብቶ ትንፋሼን አሳጠሮት ትን ብሎኝ አሳልኩ።

አያንም አጓርታ ስትወድቅ ሰማሁ። እግሮቻችንን ተራ በተራ ከፈቱልን በኋላ፣ እየረገጡ አስነሱንና እንደገና በእግር ይነዱን ጀመር። የምንወርደው ቁልቁለት እንደሆነ ተረዳሁ። የመንገዱ ጎንና ጎን የሾሉ ድንጋዮች እንዳሉበት የገባኝ በተደጋጋሚ ሲጎስሙኝና አጥንቴ እስኪሰበር ጎን አጥንቴን ሲወጉኝ ነበር። አያን ከፊት ለፊቴ እንደሆነች የተረዳሁት የቋጥኞቹ ውግ ሲያስቃስታት ነበር።

ቁልቁለቱን ለሃያ ደቂቃ ያህል ወርድን ስናበቃ በሚዋጉ ጠጠሮች ላይ መጓዝ ቀጠልን። ከሾሉት ጠጠሮች ጉዞ በኋላ ደግሞ እግሮቼ ከውሃ ውስጥ ሲገቡ ታወቀኝ። ውሃው ቀስ እያለ እስከ ወገቤ ድረስ እያሰጠመኝ ሲመጣ ታወቀኝ። ወንዝ ውሃው ከወገቤ ሳያልፍ እየቀነሰ መጣና አበቃ።

እንደተሻገርን ተረዳሁ፡፡ ምናልባት ዋቢ ሸበሌን በሌላ አቅጣጫ መልሰን እየተሻገርነው ይሆናል፡፡

እንደገና በወንዙ ዳር ጠጠሮች ላይ ካለፍን በኋላ ዳገት እየወጣን መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ ንግግር የለም፡፡ የአያን ድምፅም ወንዙን ከተሻገርን በኋላ አልተሰማኝም፡፡ በግምት ለአሥር ደቂቃ ያህል ዳገቱን ከወጣን በኋላ አስቆሙን፡፡

በሶማልኛ ቋንቋ እየተጯጯሁ ሲያወሩ ከቆዩ በኋላ ወደ ሆነ ሸለቆ ወደሚመስል ነገር ታጠፍን፡፡

ከጥቂት ደቂቃዎች ጉዞ በኋላ የሆነ በር ተንገጫግጮ ሲከፈት ሰማሁ፡፡ ወዲያው አንድ ፈርጣማ ሰውዬ አንገቴ እስኪሰበር ወደታች ጭንቅላቴን ደፋና እንደረደረኝ፡፡ እንደጎበጥኩ ተንደርድሬ ባፍ ጢሜ ተደፋሁ፡፡ ድቡሽቱ አፈር ሲውጠኝ ምንም አልቀረውም፡፡

የወረወረኝ ሰውዬ ምንም ሳይናገር በሩን ከኋላዬ በኃይል ዘግቶት ሲሄድ ተሰማኝ፡፡ ከወዲያኛው ጥግ አያን ስታቃስት ተሰማኝ፡፡

"አያን!" ተጣራሁ፡፡ ያለንበት ቦታ ያስተጋባል፡፡ ዋሻ እንደሆነ ተረዳሁ፡፡

"ዲዲሞስ!"

"ተጎዳሽ?!

"አንተስ?!"

"ደህና ነኝ!"

"እነማን ናቸው?!....ምን ፈልገው ነው?!...."

"አላውቅም!...አላውቃቸውም፡፡"

"የትነው ያለነው? ዓይኖችሽን አልፈቱልሽም?!"





"አላወቅሁም፡፡ አልፈቱልኝም፡፡ ያንተንስ?!"

"አልፈቱልኝም፡፡ ያለንበት ዋሻ ውስጥ ሌላ እንደኛ የተጣለ ይኖራል!?" ስል ጠየኳት፡፡

"የለም መሰለኝ፡፡ ... ስጠይቅ ጥያቄዬን የመለሰልኝ ድምፅ የለም፡፡"

አቧራ ባጠለቀው ዋሻ ውስጥ እንደወደቅን፣ በፍርሃት የሚሆነውን መጠባበቅ ጀመርን፡፡ ሞታችንን ከመጠባበቅ በቀር ሌላ አማራጭ አልታዩኝ አለ፡፡ ግንድ ላይ አንተርሰው አንገቶቻችን ሲቀሉን በዓይነ ህሊናዬ ተሳለብኝ፡፡

'በምን አይነት ጥፋት ይጠይቁን ይሆን?' ስልም በቅዱሳት መፃህፍት ውስጥ ያነበብኳቸውንና ፈጣሪን የማስደሰቻ መንገዶች ለማስታወስ ሞከርኩ፡፡ ለደፃ መፅውቼ አውቅ ይሆናል፡፡ እሱንም ለመፅደቅ ብዬ ሳይሆን ህሊናዬ ስለሚያስገድደኝ ነው፡፡

የአያንን ባላውቅም እኔ በብኩሌ ሃይማኖቴ ላይ ጥሩ የምባል ሰው አይደለሁም፡፡ የስልጣኔን መነሻ እንጂ የፈጣሪን እጅ መንሻ ስፈልግ አልኖርኩም፡፡ እንዲያውም ሃይማኖቶችን በአደባባይ አይሁን እንጂ በውስጤ እነቅፋለሁ፡፡ የሰውን ልጅ መጨቆኛ የፖለቲካ መሣሪያዎች መስለው ይታዩኛል፡፡ በታሪክ እንደምንረዳውም ሃይማኖቶች የሰውን ልጅ ስልጣኔ አውድመዋል፡፡ ይህ ማለት ግን ሃይማኖቶች በራሳቸው ያመጡት ስልጣኔ የለም ማለት አይደለም፡፡ የተረገምኩ ሰው እንደሆንኩ የምቆጥረው ለዚህ ነው፡፡ የሙሴን አስርቱ ትእዛዛት ሳነብ በግብፅ ፒራሚዶች ላይ ከተፃፉት ቀደምት ህጎች ጋር ይመሳሰልብኛል፡፡

"አያን ...በፈጣሪ መኖር ታምኛለሽ?" ስል ፈራ ተባ እያልኩ ጠየቅኳት፡፡

"እንዴ! ...ይቅር ይበልህ! ...እንዴታ! ሁሁ!" ከመዛሏ የተነሳ እንደተስነጠቀ ዋሽንት ይነፋነፍ የነበረ ድምፅዋ ተሳለ፡፡ "ያንት ያለህ! አንተስ አታምንም ማለት ነው?"

"በልጅነቴ አምን ነበር፡፡ ፈጣሪን ከመፍራቴ የተነሳ ...ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በስህተት በመፍሳቴ እንኳ፣ ፈጣሪ ይቅር እንዲለኝ ሶስት ቀን መጾሜን አስታውሳለሁ፡፡"

የግዷን ከት ብላ ሳቀች፡፡ "ይቅር ይበልህ!"

"አሜን!... ዛሬ እንደዛ ጊዜ ብሆን እንዴት ደስ ባለኝ! የልጅነቴ ልብ ለፈጣሪ ቅርብ ነበር፡፡...ሰማዩን ቀና ብዬ ባዬሁ ቁጥር ፈጣሪን የማየው ይመስለኝ ነበር፡፡"

"በእርግጥ በፈጣሪ መኖር አታምንም ማለት ነው?"

"እምኜ አልጨረስኩም፡፡" አልኳት ጥቂት ሳስብ ቆይቼ፡፡

"ያንት ያለህ? ሞትን እየተጠባበቅን ሳለን እንዴት እንዲህ ትላለህ?...፡፡ እነዚህ ሰዎች በምን መንገድ መገደል እንዳለብን እየመከሩ እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ፡፡ አብቅቶልናል፡፡ ፈጣሪን ልናዬው የቀረን ደቂቃ የለም፡፡"

"ምን አጠፋን?...ምን አጥፍተን ነው የሚገድሉን?!"

"ዶክተር ዲዲሞስ ...ያለነው እኮ ኦጋዴን ውስጥ ነው፡፡ ማን እንደሚያስርህ አታውቅም፡፡ የፌድራሉ መንግሥት ወታደሮች ይሁኑ፣ ወይም የክልሉ መንግሥት ልዩ ኃይሎች... ማንኛው በዓይነ ቁራኛ ሲከታተለን እንደነበር መገመት አይቻልም፡፡ በሽምቅ ተዋጊዎች እጅም ወድቀን ሊሆን ይችላል፡፡"





"በቋንቋቸው ልትለያቸው አልቻልሽም? ማለቴ..."

"ሶማልኛና አረብኛ እየቀላቀሉ ነበር ሲናገሩ የነበሩት፡፡ ሶማልኛ ተናገሩ ማለት የየትኛው ቡድን ሰዎች እንደሆኑ ይለያሉ ማለት አይደለም፡፡"

"እሺ. እኔንስ ወዘልውጥ ነው ብለው በሰላይነት ጠርጥረው ይያዙኝ፡፡ አንቺ የዚህ አካባቢ ተወላጅ ነሽ፡፡ በዛ ላይ ቋንቋሽ ቋንቋቸው ነው፡፡ አንቺን ለምን ያዙሽ?"

"ኦጋዴን ውስጥ የሚታሰረው፣ የሚንገላታውም ሆነ የሚገደለው፣ ለጥናትና ምርምር የመጣ ወዘ ልውጥ ብቻ አይደለም፤ ነዋሪዉም ጭምር ነው፡፡ እንዲያውም መረጃ በሚያቀብለው የቀዬው ሰው ላይ በትሩ ይበረታል፡፡ በባንዳነት ተፈርጆ ፍዳውን የሚበላው የዚሁ በረሃ አሳረኛ ነዋሪ ጭምር ነው፡፡ ተገድሎ ለበረሃ አሞራ ሲሳይ የተሰጠውን የሚያውቀው የአሞራዎች ሆድ ብቻ ነው፡፡ ...እኔም እጣ ፈንታዬ ደርሷል፡፡ አንድ ቀን ይህ መከራ ሊመጣ እንደሚችል እገምት ነበር፡፡ ሆኖም ይህ በረሃ እንዲለወጥ በመጣሬ አልቆጭም!..."ሳግ እየተናነቃት እንደሆነ ገባኝ፡፡ ድምፅዋ መቆራረጥ ጀመረ፡፡ "አንተንም ጨምሬ የገደልኩህ እኔ ነኝ፡፡ አብቆቶልናል፡፡"

# ፲፫

ሌሊት ይሁን ቀን አይታወቅም። አያሌ ሰዓታት ተቆጠሩ። ወደ ተጣልንበት ዋሻ መጥቶ ያነጋገረን አልነበረም። እህል አልቀመስንም። በዛ ላይ እስክንያዝ ድረስ፣ ውሃው ውስጥ እየዋኘን ስለነበር ረሃብ ለቆብናል። አያንን ብጠይቃት በረሃብ ጠኔ ከመያዟ የተነሳ ጥያቄዎቼን መመለስ እንኳ እንደማትችል ነገረችኝ። አልፈረድኩባትም።

"ይቅርታ..." አለችኝ በዛለ ድምፅ። "ይቅርታ ዶክተር ዲዲሞስ ...የዚህን የተረገመ በረሃ ኑሮና ህዝቡን ማጥናት እንደምትችል ለውጪው ድርጅት የጠቆምኩት እኔ ነኝ። ይህን በብዙ አሳርና ሰቆቃ የሚማቅቅ ህዝብ አጥንቶ መላ የሚያበጅለት ካንተ የተሻለ ምሁር እንደሌለ በኩራት ነበር የተናገርኩት። ...ያነበብኳቸውና ከዚህ ቀደም የሠራሃቸው ጥናቶችህ እስካመልክህ ድረስ አጃኢብ አሰኝተውኝ ነበር።...አንተን በአካል ማዬት በራሱ ለኔ ተአምር ነው። ...እውነቱን ልንገርህ? ...ገና ሳላገኝህ በሥራዎችህ ፍቅር ወድቄ ነበር። በረባ ባልረባው እየደወልኩ አነጋግርህ የነበረው ለዛ ነበር።...ይቅር በለኝ! ...እንደተቀየምከኝ መሞት የለብኝም..."

"አይዞሽ አትሞቺም!" አልኩ ቢጨንቀኝ ራሴን እንደ ነቢይ ቆጥሬ። "አይዞሽ!"





"የደም ጥሙ የማይቆርጥለት የተረገመ በረሃ! የሚያቃጥል ፀሐይ እንጂ ቀን የማይወጣለት ርጉም በረሃ!..." አያን በምሬት ስትራገም ዋሻው ያስተጋባ ነበር።

ሞቴንና ሞቷን በሰመመን እየተጠባበኩ ስለምትረግመው በረሃ አስብ ጀመር! የመከረኛው በረሃ የመከራ ታሪክ ወደ አእምሮዬ እንደ ደም ይንቆረቆር ጀመር።

የአሚሮችና የሱልጣኖች ምህረት የለሽ ሰይፍ የተቅዘመዘመበት የደም በረሃ! አያሌ የሰው አንገቶች የተቀሉበት፣ ጭንቅላቶች እንደቅል በቆሙ ሰዎች ደረቶች ላይ የተንከባለሉበት የደም ምድር! ውሃ እንጂ፣ ደም የጠገበው አኬልዳማዊዉ ግራጋዴምስ!

ይህ ምድር፣ ሰው ባልረከሰበት ዘመን ይኖሩበት የነበሩትን ጎሳዎች፣ በንግድ ምክንያት ባህር እየተሻገሩና በረሃውን እያቋረጡ የመጡ ነገዶች ባህላቸውንና ወጋቸውን በርዘው አላበቁም። ጥንታዊ እምነታቸውን አስጥለው ሲያበቁ በግድም በውድም እንዲሰልሙ አድርገዋቸዋል።

ከስምንተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ፣ የንግድ መስመሩን ተከትሎ የእስልምና ሃይማኖት የበረሃውን ምድር ያጥለቀልቀው ጀመር። ኦጋዴኖቹ፣ እጣን፣ ከርቤና ዝባድ ሲሸጡላቸው፣ የአረብ ነጋዴዎች ደግሞ እስልምናን በነፃ አደሏቸው። እስከ ምሥራቅ ሸዋ የቆላ ኮረብታዎች ዘልቆ እስልምና መስፋፋቱን ተያያዘው። ሃይማኖቱን እንደመሣሪያ በመጠቀም አረቦቹ የኢትዮጵያን ወደቦች በሙሉ መቆጣጠር ጀመሩ። ከዚህም በላይ በርካታ ሥርዎ መንግሥታትና ሱልጣኖች ተመሥርተው የበረሃውን ዘላን ማስገበርም ጀመሩ።



t.me/BooksandYou

ያልሰለመ ዘላን እንደ አውራሪስ ቀንድ ተቆጥሮ በባርነት ተሸጠ። የመጤ አረቦችን ሃይማኖት አልቀበልም ያለ ቋንቋው ተቆርጦ ለግመል እረኝነት ተጋዘ።

በሌላ በኩል፣ ከ1108ዓ.ም ጀምሮ የተመሠረተው የሸዋ ሱልጣን፣ የሸዋን ምሥራቃዊ ኮረብቶች ተቆጣጠሮ ነበር። እስከ ኦጋዴን የበረሃ መከረኞች እየወረደ ከብቶቻቸውን ነድቶ ይመለስ ነበር።

በኢማሞች ይመራ የነበረው የአጁራ ሱልጣን፣ በ13ኛው ክፍለ ዘመን ምሥራቅ አፍሪካን ተቆጣጥሮ፣ ወቅቱን በመከተል በቀላፎና በመርሳ በእስልምና ስም አስተዳደሩን እየተከለ ኦጋዴንን አንገፍግፎ ገዝቷል።

መናገሻውን ዘይላ ላይ ያደረገው የይፋት ሱልጣን፣ ከ1285 ዓ.ም ጀምሮ አፋርና ሐረርን ጨምሮ በኦጋዴን ላይ 18 ሱልጣኖቹን አፈራርቋል።

በይፋት ሱልጣን እግር የተተካው የአዳል ሱልጣን፣ ከ1415 ደክቶ የኦጋዴንን መንጋ ነድቷል። የይፋትንም የአዳልንም ግዛቶች ያስተዳደረው የወላስማ ሥርዎ መንግሥትም፣ ምሥራቅ አፍሪካን ሲያምስ የኦጋዴን በረሃ ብረት ምጣዱ ነበር።

በኦጋዴን ላይ ያልተቅዘመዘመ ሰይፍ ያልተሰበቀ ጦር አልነበረም። አሚር ከአሚር፣ ሱልጣን ከሱልጣን፣ ጎሳ ከጎሳ፣...ሌላው ይቅርና አውሮፓ ውስጥ ይፋለሙ የነበሩት የመስቀል ጦረኞች፣ ኦጋዴን ድረስ ወርደው ሰይፋቸው እስኪቀላ ደም አፋስሰዋል- ኦቶማን ቱርክና ፓርቱጋል። ቱርኮቹ ለሙስሊሙ ፖርቱጋሎቹ ለክርስቲያኑ ሰይፍ አቀብለዋል።





የአንደኛው የዓለም ጦርነት ተፋላሚዎችም እዚህ ምድር ላይ ተፋጠዋል። ይህ በረሃ የሁለተኛው የአለም ጦርነት ገፈትንም ቀምሷል። እንዲያውም የሁለተኛው የአለም ጦርነት ጀርመን ሀንጋሪን ወርራ ተቀሰቀሰ ይባል እንጂ፣ ጣሊያን እዚሁ በረሃ ውስጥ ወልወል በተባለው ቦታ ኢትዮጵያን ስትወር ነው የተጀመረው ማለት ይቻላል።

በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜም፣ ዓለም በርእዮተ ዓለም ጎራ ለይቶ በቃላት ሲፋለም፣ ይህ ምድረ በዳ ግን ቃላት ሳይሆን ጥይት ነበር ይዘንብበት የነበረው። ኢትዮጵያ እያሌ ጀግኖቿን እዚህ ገሃነማዊ በረሃ ውስጥ የቀበረችው፣ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ነበር- በኦጋዴን ጦርነት።

የኦጋዴን ጦርነት ካበቃ በኋላ የወጡ ሰነዶች እንዳረጋገጡት፣ ኢትዮጵያ፣ ወደ አሥራ ዘጠኝ ሺህ የሚጠጉ ልጆቿን እዚህ በረሃ ውስጥ ቀብራለች። ከሃያ ሺህ በላይ ቁስለኞቿን አንስታለች። ወደ መቶ ሃምሳ የሚጠጉ ልዩ ልዩ አይነት ታንኮቿ ወድመውበታል። ከመቶ በላይ የሆኑ የተያዩ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎቿ ጋይተውባታል። የወደሙባትን የጦር አውሮፕላኖች ቁጥር አላውቅም።

ይህ ሁሉ ውድመት በሀብት ወይም በገንዘብ ቢተመን፣ ኦጋዴንን ገነት ማድረግ የሚችል ሀብት እንደነበ መገመት አያዳግትም። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን በመ ሺዎች የሚቆጠሩ የኦጋዴን ምድር መከረኞች በጦር ምንክንያት ህይዎታቸው ተመሰቃቅሏል። ህፃና በጦርነቱ የወደቀን አስከሬን ሥጋ የለመዱ ድመ በልተዋቸዋል። እናቶችንና አዛውንቶችን ተባራሪ ጥ ከኋላቸው ጥሏቸዋል።

በዚህ ሳይበቃ አሁንም ድረስ በኦጋዴን ሰማይ ላይ ጥይት ሳያፏጭ አያድርም። ድርቅና ቸነፈር ረሃብና ጥይት የዚህ በረሃ ቀለቦች ናቸው። ይህን ሁሉ ሳስብ መምጣቴ ትክክል እንደሆነ ተረዳሁ። አያንም ትክክል ናት። እንኳንም ጋበዘችኝ ወይም አስጋበዘችኝ።

አም በእርግጥ ታስረን ወደ እንጦርጦስ ተጥለናል። ግን ለምን ሳይገድሉን እንሞታለን? ሼክስፒር እንዳለው ሳይሞቱ የሚሞቱት ፈሪዎች ናቸው። ሳልገደል አልሞትም። ራሴን በውስጤ አጀግኜ ሳልጨርስ የዋሻውን በር በኃይል በርግደው ሁለት ወንበዴዎች ገቡ።





# ፲

ሁለቱ ወንበዴዎች እኔን አልፈው አያንን ከወደቀችበት አነሷት።

“ምን ፈልጋችሁ ነው?!” በኃይል ጮኸች። “አማርኛ ትችሉ አደለም እንዴ?! በአማርኛ አናግሩኝ!”

እኔ እንድሰማ ስለፈለገች መሰለኝ፣ በሶማልኛ ቋንቋ ብዙ ቢለፈልፉም ልታናግራቸው አልፈለገችም።

“እኛ ንፁህ ሰዎች ነን! በዛ ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው የውጪ ድርጅት ባልደረቦች ነን። ስለእኛ ከፈለጋችሁ ድርጅቱን መጠየቅ ትችላላችሁ። ምን አድርጉ ነው የምትሉን?” አማርኛዋ ከእኔም ይሻል ነበር። በዛ ላይ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋዋ ተፅእኖ ሊሆን ይችላል እያንዳንዱን ፊደል እየረገጠችና እያንዳንዱን ቃል እያስረገጠች ጮሃ ነው የምትናገረው።

አንጀቴን አራሰችው። ‘ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ’ የሚባለው ብሂል ሃሰት የለውም። ግመልን ደጋ ላይ መጥመድ አይቻልም። አያን ዓይኖቿ እንዳያዩ በዓይነ ርግብ ቢታሰሩም፣ ለግዞት የዳረጉንን ሰዎች በንግግራቸው ለመለዩት ስትል በራሳቸው ቋንቋ ታስለፈልፋቸው ጀመር።

"ዚም በል ቲካላ!" አለ አንደኛው ኃይለኛ ጥፊ አሳርፎባት ሲያበቃ። የጥፊውን ጮኸት ስሰማ ሰቆጥጠኝ መንጋጋዎቼን ከረቼምኩ።

"ሚን አባኪ ቲከላምጂያሌሽ! ኪትረኛ!" አለ ሁለተኛው። "ፈረንጂ ሚንዲን ኖ?! ሀበሺ ሚንዲን ኖ?! ...ሹርሙታ!" እሱም በጥፊ አጋላት።

"ኪንቲራም! አንቲን ቢሎ ተመራማር?! ቱ! ኢኛ ያንቴ መቻወቻ ኖ?!"

"ቢገባህ እኔም እንዳንተው ሶማሌ ነኝ! እንዲያውም ካንተ የተሻልኩ ኦጋዴን ..."

"ዚም በል! ባንዳ ኖ!"

"አይደለሁም! ባንዳው አንተ ነህ!... የማይማር የማይለውጥ ወገኖቹን የማይለውጥ ነው ባንዳ! ...እስኪ ምን አደረክ አንተ?! እኔን መምታት ነው ያንተ ጀግንነት?! ...እስኪ ንገረኝ! እ?! ... ኦጋዴን ውስጥ አንድ የውሃ ጉድጓድ ቆፍረሃል?! በውሃ ጥም የሚሞት አንድ ግመል አትርፈሃል? ...አፉ በረሃብ ደርቆ አንቋሮ የሚሞት አንድ ህፃን አድነሃል?! ....ጥላው ከሀሩር ከማያድን ቆንጥር ሥር ተቀምጠው፣ በረሃብ ምክንያት መነሳት ያቃታቸውን አዛውንት አንስተሃል?!"

"ዚም በል!" ሁለተኛው ዋሻውን ሳይቀር የሚያነጋ ጥፊ አሳረፈባት።

"ቱ!..." ስትተፋበት ተሰማኝ። "...ከስክስ ጫማ ሲሰጡህና ጠመንጃ ሲያስታጥቁህ ንጉሥ የሆንክ





ይመስልሃል! ...አንተ ነህ ባንዳ! አንተ ነህ የኦጋዴን ፍዳ!..."

"ዚም ባል አንቴ ቲርቲር ሽርሙታ!"

ደረቷ ላይ የተመታች መሰለኝ።

"ህእ!..." የሚል ድምፅ አሰምታ ፀጥ አለች።

እየጎተቱ ይዘዋት ሲወጡ ተሰማኝ። የዋሻው በር ተከረቸመ። ደረቷን ሲመቷት ሞተች ይሆን? ወይስ ሊደፍሯት ይሆን? የጭንቀት መርግ ተጫነብኝ። ጨለማ በዋጠው ዋሻ ውስጥ ጨለማ ተደፍቶብኝ ብቻዬን ቀረሁ። ጆሮዬ ይጮህብኝ ጀመር።

በሰቀቀን ተራዬን መጠባበቅ ጀመርኩ። እኔ ነኝ ተረኛው ቀጣዮን ፅዋ የምቀበለው እኔ ነኝ። የፀጋዬ ገብረ መድህንን ስንኞች ቀጣዩን ፅዋዬን እየጠበኩ አስታወስኳቸው።

"...ይድረስ ወገን ከእኛው ለእኛ፤
አበቅቴ ውሉን አልሳተም፤ ፅዋህን ተቀበለኛ!...
ሕዝብ መርተን ያለ ዓላማ፣ ያለ ማተብ ያለ ሃይማኖት፣
በአምባ ገነንነት እብሪት፣ ያለ ዴሞክራሲ ፍኖት፣
ጠመንጃ ነክሰን በመግደል፣ ጠመንጃ ነክሰን በመሞት፣
ፍቅር ፈርተን፣ ሰላም ፈርተን፣
አንድነታችንን ቀብረን፣ እምቡጥ ህልማቸውን በልተን፣
ሳይነጋ እየጨለመብን፣ ሳንጎለምስ እያረጀን፣
የሥጋችንን ጨርሰን፣ በመንፈስ እየሞትን ነን።..."

# ፲፫

የሥቃይ ዕዋዬን እየተጠባበኩ፣ ጨለማ በዋጠው ዋሻ ውስጥ ወድቄአለሁ። ለነገሩ፣ ጨለማ ይሁን ብርሃናማ፣ ሳውቀው አልችልም፤ ዓይኖቼ እንዳያዩ ሆነው በጥቁር ዓይነ ርግብ ታስረዋል። ቢሆንም ያለሁት ዋሻ ውስጥ እንደሆነ መገመት አላዳገተኝም። በዛ ላይ በሩ ተከርችሟል። ብርሃን በዬትም በኩል ሊገባ አይችልም። ያለምንም ጥርጥር ያለሁበት ሥፍራ፣ እንደ ኦጋዴን ህይዎት ጨለማ ነው። ደኀኀን። ድቅድቅ ጨለማ።

ዓይኔ ከእይታ ቢጋረድም አእምሮዬ ማሰቡን አላቆመም። ስለ ሌላ ስለምንም ማሰብ አልቻልኩም። የማሰላስለው ሁሉ ስለ ኦጋዴን ብቻ ነው። ስለ እድለ ቢሱ በረሃና እድለ ቢስ ስላደረጉት ኃይሎች ማሰላሰሌን መግታት አልተቻለኝም። እያንዳንዱን ክር ስመዝ የምደርሰው አሁን ላለው አሣረኛ ምድር ሴረኞች ታሪክ ላይ ነው። ሱልጣኖች ለስልጣን እንደተፋጁበት፣ እንግሊዞች ለከርሰ ምድር ሀብት እስካሁን የማያባራ የጦርነት ሴራ ጎንጉነውበታል።

እንግሊዞች በረቀቀ ሴራቸው “የታላቋ ሶማሌን” ፅንሰ ሀሳብ ለማራገብ እንዲያመቻቸው የሶማሌ ወጣቶችን ለማነሳሳት፣ “የሶማሌ ዩዝ ሊግ” የተባለ ድርጅት ሀርጌሣ ላይ መሥርተው፣ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት በ1937 ዓ.ም አካባቢ ነበር።





“የታላቋ ሶማሌን” ፅንሰ ሀሳብ ከጫፍ ጫፍ ለማስረፅ፣ እንግሊዞች ኦጋዴንን ለእናት ሀገሯ ኢትዮጵያ ከብዙ ስጣ ገባ በኋላ ከመመለስዋ በፊት፣ ይኸው “የሶማሌ ዩዝ ሊግ” የተባለው ቡድን ጅጅጋ ላይ ሳይቀር ባንዲራውን ሰቅሎ ይቀሰቅስ ነበር። እንግሊዞች ኦጋዴንን ለቀው ከወጡ በኋላ ወደ ሽምቅ ተዋጊነት ተቀይሮ፣ የኮምኒዝም ርዕዮት ዓለምን በማቀንቀን፣ የሶቭዬት ህብረት ጥገኛ ሆኖ፣ ከቅኝ ግዛት አርነት በወጣችው ሶማሊያ ውስጥ ስብከቱን ቀጠለ።

በ1955 ዓ.ም፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተርን ለማፅደቅ በተጠራው ስብሰባ ላይ ነበር፣ አዲሲቷ ሀገር ሶማሊያ፣ ኦጋዴን ይገባኛል ስትል ኢትዮጵያን በአደባባይ መክሰስ የጀመረችው። በወቅቱ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩትና፣ ስለኢትዮጵያ ሀገራቸው በዓለም አደባባይ በመከራከር አንቱ የተባሉት አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ለሶማሊያው መሪ የሰጡት መልስ የተሰበሰቡትን የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ሁሉ ያስደመመ ነበር።

“የተሰነዘረብን ክስ ፍሬ ቢስ ነው። ኢትዮጵያ ለብዙ ዓመታት ነፃ መንግሥት ሆኖ የኖረች ናት። ከሶስት ሺህ አመታት በላይ በታሪክ የታወቀች ሀገር ሆና የኖረች ናት። የሶማሊያ መንግሥት የሚባል ወይም ሶማሊያ ሪፐብሊክ የሚባል ሀገር የትም ተመዝግቦ አይገኝም። አዲሱ የሶማሊያ ሪፐብሊክ መንግሥት የ1908 ዓመተ ምህረቱን ስምምነት የማይቀበል ከሆነ ከነጭራሹ የሶማሊያ ሪፐብሊክ የሚባል ሀገር አይኖርም። በአሁኑ ወቅት ቅኚ ገዥዎች በካርታ ላይ ያሰመሩትን ወሰን ጥሩም ሆነ መጥፎ አፍሪካውያን እንዲቀበሉ ሁኔታው ያስገድዳቸዋል። ለሶማሊያ የሚበጃትም ይኸው ነው።...” በማለት የሶማሊያውን መሪ ፀጥ አሰኙት።

ይሁን እንጂ፣ "የሶማሌ ዩዝ ሊግ" የተለያዩ ፀረ ኢትዮጵያ ቅስቀሳዎች ማድረጉን አላቆመም። ሰርጎ እየገባም የኦጋዴንን ምድር የጦርነት ቀጠና አደረገው። በ1955 ዓ.ም በሻምበል ደምሴ ቡልቶ የሚመራ አንድ ሻምበል የአየር ወለድ ጦር ደገሃቡር ላይ ከአውሮፕላን በጃንጥላ ወርዶ ሰርጎ ገቡን ቡድን አይቀጡ ቅጣት ቀጥቶ አባርቶ ነበር።

በ1957 ዓ.ም "ሶማሌ-አቦ" የተባለ አማፂ ቡድን በሶማሊያ አጋፋሪነት ተመሠረተ። አነሳሱ፣ ዋቆ ጉቱ፣ ኦሮሞ ቢሆንም፣ ከባሌ ሹማምንት ጋር በፈጠረው አለመግባባት፣ አኩርፎ በመሸፈቱ ቢሆንም፣ ይህን ወርቃማ እድል ለመጠቀም የቋመጠችው ሶማሊያ፣ ራዕዩን ከኩርፊያ ከፍ አድርጋ ሶማሌዎችንና የባሌ ኦሮሞዎችን በእስልምና ጥላ ሥር በማሰባሰብ አዲስ ራስ ምታት ለኢትዮጵያ ፈጠረችላት። ከሌሎች ሰርጎ ገብ ቡድኖች ጋር በማጣመር ጉልበቱን አፈረጠመችው።

በ1958 ዓ.ም ኢትዮጵያ በ"አቦ" ላይ አንድ የአየር ወለድ ጦር ብትልክም፣ ዋቆ ጉቱ እንደተራ ሽፍታ የዋዛ ሆኖ አላገኙትም። ጥቅጥቅ ባለው የባሌ ጫካ ውስጥ ገብቶ የሰለጠነውን የአየር ወለድ ጦር ገትሮ ተፋለመው። የአየር ወለዱ ጦር የአየር ድጋፍ ቢጠይቅም፣ የመጣው የጦር አውሮፕላን በስህተት በአየር ወለዱ ጦር ላይ የታጠቀውን ቦንብና ጥይት አራግፎበት ተመለሰ። የኢትዮጵያ መንግሥት ዋቆ ጉቱ በሰላም እጁን እንዲሰጥ አዋጅ ቢያስነግርም እርሱ ግን የተመናመነ ኃይሉን ይዞ እጁን ባለመስጠት ቀጠለ።





ጉዳዩ ያሳሰበው የኢትዮጵያ መንግሥት በሜጀር ጀነራል ጃገማ ኬሎ የሚመራ ኃይል ዋቆ ጉቱን እንዲይዝ ላከ። በመጨረሻም ጃገማ ኬሎ ተሳካለትና ዋቆ ጉቱን በማግባባት እጁን እንዲሰጥ አደረገው። ዋቆ ጉቱ አዲስ አበባ መጥቶ ንጉሡ ፊት በመቅረብ ምህረት ከተደረገለት በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ ተሰጠው። ለዋቆ ጉቱ ሽንገላው አልተዋጠለትም ነበር። ባልታሰበ ሰዓት ጠፍቶ ሶማሊያ ገባ። የሶማሊያ መንግስት ዋቆ ጉቱ ሞቃዲሾ ሲገባ የጀግና አቀባበል ነበር ያደረገለት። ራሱን ጀነራል ብሎ በመሰየምም ኃይሉን እያደራጀ አመቺ ጊዜ እስኪገኝ እዛው ሞቃዲሾ አቆየው።

"በሶማሌ ዩዝ ሊግ" የተጀመረው የአማፂ ቡድኖች ጥንስስ በ"አቦ" አላበቃም። "የሸበሌ ነፃ አውጪ ድርጅት"፣ "የኦጋዴን ነፃነት ድርጅት" እና "የምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጪ ድርጅት" የተባሉ የደፈጣ ተዋጊዎች በኦጋዴን ምድር ላይ መፈልፈል ጀመሩ።

"የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ድርጅት"፣ ከ1969 ዓመተ ምህረቱ "የኦጋዴን ጦርነት" በፊት ጀምሮ፣ "የሶማሌ ዩዝ ሊግን" አላማ በማንገብ፣ ኦጋዴን ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት ተቋማት ላይ ከፍተኛ ውድመት አድርሷል። የኦጋዴን ጦርነቱን ርችት የለኮሰውም በሶማሊያ መንግሥት ስንቅና ትጥቅ ጉልበቱን በኃይል አፈርጥሞ ሲያበቃ ነበር። በጦርነቱ ወቅት የኦጋዴንን ጓዳ ጎድጓዳ እንደ መዳፉ መስመር የሚያውቀው የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር፣ በየኩርባው ቆረጣ እየገባ የኢትዮጵያ ጦር የእግር እሳት ሆኖ ነበር።

የኦጋዴን ጦርነት ሲያበቃና የሶማሊያ ወራሪ ጦር ሲመታ የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባርም ደጀኑን አጥቶ

ተብታትኖ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በ1984 ዓ.ም "የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር" በእግሩ ተተካ፡፡

ምንም እንኳ የሶማሌ ብሔር፣ የአብሳም፣ የጌሪ እና የመርሐን ነገዶችን ያቀፈ ቢሆንም፣ ኦብነግ ግን በዋናነት ከዳሩድ ነገድ የሚመዘዘው የኦጋዴን ጎሳ ስብስብ ነበር፡፡ ሲመሠረት የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር አመራር በነበሩ ስድስት ሰዎች ቢሆንም ቀስ በቀስ ብዙ የኦጋዴን ጎሳዎችን ከጎኑ አሰልፏል፡፡

በወቅቱ የደርግ መንግሥት በሰሜኑ ጦርነት ተጠምዶ ስለነበር፣ የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር ማሊያውን ቀይሮ ኦብነግ ሆኖ ሲመጣ በእንቁላሉ ለመቅጣት እድል አልነበረውም፡፡ የደርግ መንግሥት ተገርሥሦ ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ ኦብነግም የሽግግሩ መንግሥት አባል ሆነ፡፡

ኢህአዴግ የደነገጠው፣ በሽግግሩ መንግሥት ወቅት በተደረገው ምርጫ ኦብነግ የሶማሌን ክልል ሰማኒያ በመቶ ድምፅ ሲሰበስብ ነበር፡፡ በክልሉ መንግስት የፓርላማ ወንበሮች ውስጥም የኦብነግ ሰዎች ያልተቀመጡባቸው እጅግ ጥቂቶቹ ብቻ ሆነው ታዩ፡፡

ኢህአዴግም "እሾህን በእሾህ" በሚለው ፈሊጡ፣ በሶማሌ ክልል ሌላ አጋር ሁርሶ ላይ አስመሠረተ - "የኢትዮጵያ ሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ሊግ"ን፡፡ ቀጥሎ በተደረገ አጠቃላይ ምርጫም ኦብነግ በኃይል ተገፍቼ ከምርጫው እንድወጣ ተደርጌአለሁ በሚል ጩኸቱን ማሰማት ቀጠለ፡፡ አባላቶቼ ተገድለውብኛል ሲልም ክሱን አሰማ፡፡





ጩኸቱን አሰምቶ አልቀረም፤ ጠበንጃውን አንስቶ ወደ ኦጋዴን በረሃዎች ወርዶ የጥይቱን ጩኸት አሰማ፡፡ ራሱ ኃላፊነት የወሰደባቸውን ጥቃቶችም መሠንዘሩን ቀጠለ፡፡ ኦጋዴን ውስጥ በነዳጅ ፍለጋ ላይ የተሠማሩና ለመስማራትም እቅድ የነበራቸው ካምፒኒዎችም ሥጋታቸውን መግለፅ ጀመሩ፡፡ ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላም ኦጋዴን እንደገና የጦርነት አውድማ ሆነች፡፡

እኔ እዚህ ዋሻ ውስጥ ታስሬ እስከተጣልኩበት ሰዓት ድረስ የኦጋዴን ሰማይ ባሩድ እንጂ ደመና አይዞርበትም፡፡ የኦጋዴን ምድርም የተቀበረ ፈንጂ እንጂ ድንች አይቆፈርበትም፡፡ "አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ" የተባለው ብሂልም፣ በኦጋዴን ንፁሃን ላይ እውን መሆኑ እንደቀጠለ ነው፡፡ ኦብነግን ለማፅዳት የገባው የኢትዮጵያ ጦር በአንድ በኩል "አጋልጥ" በሚል ሰበብ፣ ብዙዎችን በእሥርና በቶርቼር ወገባቸውን ይልጣል፡፡ በሌላ በኩል የአማፂው ቡድን የጦር አበጋዞች "ባንዳ" በሚል ፈሊጥ የኦጋዴንን ህዝብ ፍዳ ያወርዱበታል፡፡ ከዚህም በላይ ዓለም ያላወቃቸው በየጊዜው የሚነሱ አማፂ ቡድኖችን ቆጥሮ መዝለቅ አይቻልም፡፡

እኔንና አያንን ወደዚህ እንጦርጦስ ያወረደን ቡድን የትኛው ወይም በማን የታዘዘ እንደሆነ እስካሁን አላወቅሁም፡፡ አያንም እስካሁን ምን እንደደረሰባት አላውቅም፡፡ እየተደፈረች ይሁን ወይም እየተቀላች ጨለማው ዋሻ አልነገረኝም፡፡ ክፉ ሀሳቦች አእምሮዬን ወረውታል፡፡ ማንም ሊደርስልን አይችልም፡፡ ማንም፡፡

# ፲፯

ሳላውቀው ከወሰደኝ ጥልቅ እንቅልፍ የቀሰቀሰኝ የዋሻው በር መበርገድ ነበር። በጠኔ ከመያዜ የተነሳ ይሁን አልያ በሀሳብ በመናወዜ ምክንያት እንቅልፍ ሲያሸልበኝ አላስታውስም። ለምን ያህል ሰዓታት እንደተኛሁም አላውቅም። እንቅልፍን ያህል እረፍት ከወዴት ይገኛል? ...ከረሃቤና ከሀሳቤ እንቅልፍ ባይገላግለኝ ኖሮ እስካሁን በህይዎት መቆየቴን እጠራጠራለሁ።

የዋሻው በር እንደተከፈተ ሁለት ሰዎች አያንን ወደ ውስጥ ወርውረዋት ሲያበቁ ዋሻውን እንደገና ዘግተውት ሄዱ።

"አያን!?" እውር ድንበሬን ወድቃ ወደምቃስትበት አቅጣጫ ተንከባለልኩ። "ጎዳሽ?"

"አ...አይነገርም!" መናገር አቅቷት ጫን ጫን መተንፈስ ያዘች። "እህ!.እህ!"

በእጄ ዳብሼ የተጎዳችውን ማዎቅ አልችልም። ሁለቱም እጆቼ የፊጢኝ ተጠፍንገው ታስረዋል።

"እ...እርቃኔን አቁመው እጆቻቸው እስኪዝሉ ገረፉኝ!..." አለችና ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች።

"...ም...ምን ፈልገው ነው?...እነማን ናቸው?"
"...ከ ...ከጥያቄዎቻቸው እንደ ተረዳሁት... በሰላይነት ጠርጥረውናል።..."





"ምን ለመሰለል የመጣን መስለናቸው ነው?..."
"ኢጋዴን ውስጥ ከነዳጅ ምስጢር በቀር ሌላ የሚደበቅ ምን ምስጢር ይኖራል?"

"ነዳጅ..."
"ከእንግዴህ ዋጋ የለኝም!" ብላ እንደገና መንሰቅሰቅ ጀመረች።
"አያን ምነው? እንዲህማ በቶሎ ተስፋ ትቆርጫለሽ ብዬ ማሰብ ይከብደኛል።"

"ተፈራረቁብኝ!" ለቅሶዋን መቆጣጠር አቃታት።

"ምን ማለትሽ ነው?" አፌ ደረቀብኝ። "ይህን ማመን አልችልም። ሊሆን አይችልም!"

"ሆኗል! ...ስንት እንደሆኑ እንኳ ማስታወስ አልችልም!... ተፈራረቁብኝ! ...እንደ አውሬ እያጓሩ ደፈሩኝ ...ለእንግዴህ ተስፋ የለኝም።...በቁሜ ቀብረውኛል..."

መናገር አቃተኝ። እርሷን ማፅናናት ቀርቶ ራሴ መፅናናት ተሳነኝ። አፌን ደም ደም አለኝ። ጭንቅላቴ ዞረብኝ።

# ፲፯

የእኔ ተራ መድረሱን ያወቅኩት የዋሻው በር ሲከፈት ነበር። ፈርጣማ እጆች ክንድና ክንዴን አንጠልጠለው እየጎተቱ ከዋሻው አወጡኝ። ከዋሻው እስክርቅ ድረስ የአያን ድምፅ ከውስጥ እየተሰማኝ ነበር።

"ተውት! ተውት! ...ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። የምትሉት ሁሉ ቅዠት ነው። ንፁህ ሰው ነው። ተውት..."

የሰማት የለም። ወደ ሆነ ክፍል አስገቡኝና ከቆመ ምሰሶ ጋር አሰሩኝ። ይህኛውም ዋሻ ነገር ሳይሆን አይቀርም፤ እያንዳንዱ ኮቴ ያስተጋባል። ምንም አይነት ጥያቄ ሳያቀርቡልኝ የመጀመሪያው ቆመጥ ከጀርባዬ አረፈብኝ። ገና ካሁኑ አጥንቴ የተሰበረ መሰለኝ። ከዚህ በፊት አውጥቼው የማላውቀውን የማቃስት ድምፅ አወጣሁ። ያለ አንዳች ርህራሄ እየተንጠራራ ይመሽልቀኝ ጀመር። የመጀመሪያው ሲደክመው ሁለተኛው ተተካ።

"አፈቲ ማረብታ?!" ይለኛል በሱማልኛ እየተንጠራራ ዱላ ባሳረፈብኝ ቁጥር። ምን እያለ እንደሆነ





አላውቅም። ሌላም ብዙ ቃላት ተናግሯል። የአንዱንም ትርጉም አላውቅም። "ማረብታ!"

የጀርባ አጥንቴ እስኪሰባበር ተረባርበው እርቃኔን አቁመው ከገረፉኝ በኋላ ከቆመው ግንድ ላይ ፈቱኝ። እንደ ልጥ ተጣጥፌ ወለሉ ላይ ጥቅልል አልኩ።

ቁስሉ እንዲለበልበኝ መሰለኝ ሁለቱም በወደቅኩበት ሸኑብኝ። ለመጮህ እንኳ አቅም አልነበረኝም። ወድቄ ቀረሁ። በምፀት እየተሳሳቁ ሸንተውብኝ ካበቁ በኋላ አንድ ሌላ ሰው ከውጭ ሲገባ ሰማሁ። እሱን ተከትሎ ደግሞ ሌላ ሰው ገባ።

"አቲካ መቃ?!" ሲል ተናገረ መጀመሪያ የገባው።

"ሲም ማኖ?" አለ ሁለተኛው። አስተርጓሚ መሆኑ ነው። "አንቴ ኖ...ከ! ማቲመልስ ካሆና ያካፋ ናጋር ይካታላል።"

"ዶክተር ዲዲሞስ ደሬ እባላለሁ" አልኩ እንደምንም አቅሜን አሰባስቤ። እስካሁን ያለምንም ጥያቄ የገረፉኝ ሞራሌ እንዲላሽቅና በፍርሃት ተስፋ በመቁረጥ ምስጢር እንድዘረግፍ መሆኑ ገብቶኛል። ይሁን እንጂ ምንም ምስጢር የለኝም። ወደዚህ በረሃ የመጣሁበት ጉዳይ ምስጢር አይደለም።

"አፈቲ ማረብታ?!" አለ ጠያቂዬ ሙክ ባለ ድምፀት።

"እዚህ ላምን ማታህ?!" ሲል አስተርጓሚው ቀጠለ።

"እዚህ የመጣሁት ለምርምር ሥራ ነው።"

"ሚንዲ ኖ ሚትማራምራው?"

"የማህበረሰብ አጥኚ ነኝ።ሶሻል አንትሮፖሎጂስት ነኝ።"

"አታችባርቢሬ! ወናቱን ማናጋር ቢቻ ኖ ሚያዋተው!"

"የምናገረው እውነቱን ብቻ ነው።"

"ይህ ጋና ማጃማራ ኖ! ...ካታዩን ናጋር ሲቲማላካት ያግድህን ቲናጋራላህ!"

"ምንም የተደበቀ ነገር የለኝም። እውነቱ ይህ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የሚጠቅመው የአካባቢውን ነዋሪ ነው።"

"ለኛ ቲክም አንቴን ማን ፋላጋ? ኢኛ ሲላራሳችን ኣናውክም ብሎ ያላካህ ማኖ?!"

"ስለራሳችሁ አታውቁም ማለት አይደለም። ከእናንተ የበለጠ ስለ እናንተ ማንም ሊያውቅ አይችልም። ግን... ይህን ለዘመናት የተረሳን ምድር በሳይንሳዊ ዘዴ አጥንቶ ለዓለም ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። የኦጋዴንን ችግር መፍታት የሚቻለው የአካባቢውን ሳንካዎች ጠለቅ ብሎ በማዎቅ ነው።"

"ሚንዲ ኖ ሳንካዎች?"

በውስጤ'ሳንካዎቹማ እናንተ ናችሁ!' አልኩ።

"ችግሮች ማለቴ ነው።" አልኩ ጥቂት አስብ አድርጌ። "የችግር የመፍቻ ቁልፍ የሚገኘው ራሱ ችግር ውስጥ ነው።"

"አታችባርብር! ...ሳላይ ናህ!.... እውነቱን በኋላ ቲናጋራላህ!"





ሁለቱ ሰዎች ጥለውኝ ሲወጡ፣ ገራፊዎቹ እየጎተቱ፣ ቀድሞ ወደ ነበርኩበት ዋሻ ወስደው ወረወሩኝ። እያን አሁንም ድረስ እያቃሰተች ነበር።

# ፲፰

የሚያንገበግበው የጀርባ ቁስላችንን ማስታመም አልቻልንም። እጆቻችን የፊጥኝ እንደተጠፈነጉ ናቸው። ለምን እስካሁን እጆቻችንን እንደማይፈቱልን አልገባኝም። ከውጭ እሳት የሚተፋ ነፍጥ ያነገበ ወንበዴ አለ። የትም ማምለጥ አንችልም። "የፈሪ ዱላ አስራ ሁለት ነው" የሚባለው እንዲህ አይነቱ ነገር ነው። ደም የጎረሰውን የጀርባ ቁስል መፈወስ ባይቻል እንኳ እንዲያው መዳበስ ቢቻል ምን ነበረበት?!

ከሰዓታት ቆይታ በኋላ የዋሻው በር ተከፈተና የሚገባ ሰው ኮቴ ሰማን። ወደ ወደቅንበት ቀረብ አለና፣

"ቴናሱ!" አለ።

መነሳት የሚያስችል አቅም አልነበረንም። ለመነሳት ይቅርና አንገት ቀና የሚያስደርግ ጡንቻ የለንም። አጥንታችን እንደ ጭራሮ ተሰባብሯል። ጡንቻዎቻችን እንደ ክር ተበጣጥሰዋል።

"አቲናሱም?!" አለ እንደገና። "ማብላት አቲፋልጉም?" የሚበላ ነገር ይዟል ማለት ነው።





"አያን!..." አልኩ የሞትሞቴን ካንገቴ ቀና ብዬ። "...ቀና በይ ነፍሳችንን እንያዛት።"

"እጆቻችን ሳይፈቱ በምን እንመገባለን?!" አልኩት ካንገቴ ቀና እንዳልኩ። እጆቻችን ፈታልን። የደም ሥሬ አብጦ ነበር። ጣቶቼ ዝለዋል። በእርግጠኛነት የአያንም የደም ሥሮች ከእኔ በከፋ ሁኔታ ተጎድተዋል።

ጣሳ መሰል ነገር አስጨበጠኝ። ተስገብግቤ ወደ አፌ አስጠጋሁት። የስጋ ሾርባ ነው። የምን ሥጋ እንሆነ ግን አላውቅም። የዛው መከረኛ ግመል ሥጋ ሊሆን ይችላል። ኦጋዴን ውስጥ ግመል የማይሆነው የለም። ይጫናል፤ ይታረስበታል፤ ይታለባል፤ ይታረዳል። ለአንድ ኦጋዴናዊ ግመል ከሰው ሳይቀር ሳይበልጥበት አይቀርም። ሁሉ ነገሩ ነው።

በዚህ ሰዓት ምግብ መምረጥ ቅብጠት ነው። በሞት ሽረት መሃል ያለ ሰው እንኳ ሥጋ አግኝቶ ይቅርና ድንጋይ ቢነክስ አይፈረድበትም። ለም አፈር ባገኝ ያለ አንዳች ማመንታት ተጎንብሼ እሸመሽመው ነበር። በናዚ ማጎሪያ ጣቢያዎች ውስጥ የነበሩ እስራኤላውያን የሰው ሥጋ መብላታቸውን አንብቤአለሁ። የበሉት ሰውዬ በቁመቱ ልክ በተሰራ ብረት ድስት ውስጥ ሆኖ ከአሽዊትዝ ማስቃያ ጣቢያ መሃል እየተንፈቀፈቀ ነበር። ሰውዬው እንዲቀቀል የተደረገው ሥጋው ከአንጥንቱ ሲላቀቅ ለመዋቅረ አጥንት (አናቶሚ) ጥናት ለማዋል ነበር። የናዚ ዶክተሮች ከሚንፈቀፈቀው ብረት ድስት ርቀው አስከሬኑ ሙክክ ብሎ በስሎ ከአጥንቱ እስኪላቀቅ እየተጠባበቁ ነበር። በረሃብ የተጎዱት እስራኤላውያኑ ትልቁን ብረት ድስት በመመልከት የእለቱ ምግብ ሾርባ መሆኑን በማመን ፈጣሪያቸውን አመስግነው እየተጠባበቁ ነበር። ሾርባው

ዘገዬ:: ወደ እነርሱ ሊመጣ አልቻለም:: እነሱ ወደ ሾርባው መሄድ ነበረባቸው:: ወደሚንፈቀፈቀው ብረት ድስት ተንጋጉ:: ቡድስ ቡድስ ያለ ሥጋ በአራት ማዕዘኑ ገንዳ መሰል ብረት ድስት የሚንፈቀፈቅ ውሃ ላይ እየተንሳፈፈ ተመለከቱ:: አንዱ በአንዱ ትከሻ ላይ እጁን እያሳለፈ የገሃነብ ያህል የፈላውን ውሃ ከምንም ሳይቆጥር ሥጋውን ተሻማ:: የራሱ እጅ እስኪበስል ብረት ድስቱ ውስጥ ገብቶ ሥጋ የፈለገም አልታጣም:: ከረጂሙ የብረት ድስት ሥር ዘግጠ የነበረው ግን የሰው አፅም ነበር:: ሥጋውም የወገናቸው ሥጋ ነበር:: ከረሃብ በላይ የከፋ ነገር የለም:: ተረት ይሁን ታሪክ ባይታወቅም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በተከሰተ ረሃብ እናት ልጇን በልታለች ይባላል::

ባዶውን ጣሳ መለስኩለት:: አያንም ሾርባውን ጨርሳው ነበር:: ሰውዬው ጣሳዎቹን ይዞ ዋሻውን ዘግቶብን ሄደ:: እጆቻችን መልሶ አላሰረንም ነበር:: ተመስገን ነው:: የጀርባዬን ቁስል ዳበስኩት:: ይዘገንናል::

የአያንንም ቀስሎች ዳበስኳቸው:: ሰቀጠጠኝ:: እርሷም ሳግ እየተናነቃት የእኔን ቁስሎች ዳበሰቻቸው::

"አዝናለሁ" አለች አንገቴ ሥር ተወሽቃ:: ትኩስ እንባዋ ሞቀኝ::

"ለምን ይመስልሻል ሾርባ የሰጡን?"

"እንዳንሞት ነዋ:: ገና ይመረምሩናል:: ብዙ ምስጢር እንደያዝን ነው የሚያስቡት:: አላመኑንም:: የፈለጉትን ምስጢር ሳያገኙ ብንሞት፣ ኪሳራ እንደሆነ አምነዋል ማለት ነው:: ቀጣዩ ምርመራ ከዚህ እንደሚከፋ መገመት ቀላል ነው::"

"ምን አይነት ምስጢር?..."





ጥያቄዬን ሳትመልስልኝ የዋሻው በር ተበረገደ:: ሾርባ ያመጣልን ሰውዬ ስህተቱን ለማስተካከል መመለሱ ነበር:: እጆቻችን እንደገና የፈጥኝ አስሮን ሄደ:: በተፈታንበት ቅፅበት የታሰሩ ዓይኖቻችን መፈታታትና ከመሞታችን በፊት መተያዬት እንችል ነበር:: እስረኛ ራሱም ራሱን እንደሚያስር የገባኝ ያኔ ነው:: ሁለታችንም ቆጨን:: ከሄደ በኋላ ንግግራችንን ቀጠልን::

"ሾርባውን መርዘውት ይሆን?"

ወደየኋላችን ተዘረርን::

# ፲፱

የቀመስናት ሾርባ ነፍሳችንን ይዛልን ቆዬች። በጥርጣሬያችን መሠረት ሾርባው እስካሁን አልገደለንም። ደም የጎረሰው ቁስላችን ግን እረፍት የሚነሳ ጥዝጣዜ ለቆብን ውሏል ወይም አድሯል። ዓይኖቻችን ታስረው ዋሻ ውስጥ ስለተወረወርን ቀንና ሌሊቱን ለይተን ማወቅ አንችልም። የወፍ ድምፅ እንኳ የማይሰማበት እልም ያለ በረሃ ውስጥ እንደሆንን ገምተናል። ይሁን እንጂ ወደዚህ ሲያመጡን የተሻገርነውን ወንዝ እንደምልክት በመቁጠር ዋቢ ሸበሌ አካባቢ እንዳለን ገምተናል።

አያን እንቀላፍታለች እኔ ግን ጭልጥ ካለ ሀሳብ ውስጥ ገብቻለሁ። አያን ከመተኛቷ በፊት ለዚህ ሁሉ ፍዳ የዳረገን ነገር ምን እንደሆነ ብጠይቃት፣

"ይህ በረሃ ከነዳጅ በቀር ሌላ ምንም ምስጢር የለውም።" ስትል ነበር የጀመረችልኝ።

"ነዳጅ ቢኖር ኖሮ እስካሁን ለምን አልወጣም? ወይስ ነዳጅም እንደፍልፈል ውስጥ ለውስጥ እየቆፈረ ከአሳዳጁ ያመልጣል?" ነዳጅ ኦጋዴን ውስጥ የለም የሚሉትን ሰዎች መላ ምት እየደረደርኩ ተከራከርኳት።





አያን ስለኢትዮጵያ አታካች የነዳጅ ፍለጋ ታሪክ ጥልቅ እውቀት እንዳላት የተረዳሁት ከዚህ በኋላ ነበር። 'ለምን ያለሞያዋ ስለነዳጅ ይህ ሁሉ እውቀት ሊኖራት ቻለ?' ስል፣ እኔ ራሴ እስክጠራጠራት ድረስ ነበር አንድ በአንድ የተረከችልኝ።

ታሪኩ የሚጀምረው የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ መሠረት ከነበሩት ከአጤ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ ነው። እንደ ጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር ከ1860 ዓ.ም አካባቢ ጀምሮ፣ በኦጋዴን ሸለቆ ውስጥ "ነዳጅ ገነፈለ" የሚል ወሬ መሰማት ጀምሮ ነበር።

በጅጅጋ አቅራቢያ በፋፋን እና በገርገር ወንዞች ሸለቆ አካባቢም ነዳጅ ከከርሰ ምድር ሰርጎ የመውጣቱ ዜና ይሰማ ጀመር። ከዚህም አልፎ በጋራሙለታ ተራሮች ግርጌም እንደተበጣ ደም ሥር ነዳጅ ተንፎለፎለ ይባል ጀመር። አንዳንድ የውሃ ጉድጓዶች ሳይቀር የነዳጅ ሰፈፍ ታየባቸው ተባለ። ከዚህ በኋላ ነበር ኢትዮጵያ የሃይድሮ ካርቦን እምቅ ኃይል እንዳላት የታወቀው።

ይህንን ታሪክ፣ "በሬ ወለደ" አይነት እንደሆነብኝ ለአያን ስነግራት፣

"እሳት በሌለበት ጭስ የለም።" በማለት ነበር ትረካዋን የቀጠለችልኝ። "…'ግመል ባለበት ነዳጅ አለ' የሚባለውንስ አለሰማህም?"

የኦጋዴን በረሃ አስር ሺህ ያህል ውፍረት ያለው ሴዲሜንታሪ ሮክ (ዝቅጤ አለት) የተነጠፈበት ነው። ጂኦሎጂስቶች እንዳጠኑት ይህ የአለት ንጣፍ፣ እስከ አራት



t.me/BooksandYou

መቶ ስኩዌር ኪሎ ሜትር ይሸፍናል። ይህም በረሃው ድፍድፍ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ እንዳረገዘ ምልክት ነው።

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የእንስሳትና ከእፅዋት ቅሪት አካል በመዝቀጥ ጠንክሮ ወደ ቋጥኝነት የተቀየረበት ይህ አካባቢ በሃይድሮ ካርቦን ብልፅግናው ከመካከለኛው ምሥራቅ ምድር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ስነ ምድር እንደሆነ ጂኦሎጂስቶች ደርሰውበታል።

አጥኚዎቹ፣ ኢትዮጵያ አምስት የዝቅጤ ድንጋይ (ሴዲመንታሪ ሮክ) ሸለቆዎች እንዳሏት ደርሰውበታል። በዋነኛነት ኦጋዴን ባዚን፣ አባይ ሸለቆ፣ የኦሞ ሸለቆ፣ ጋምቤላ እና መተማ እንደሆኑም ተለይተዋል። በእነዚህ በማዕድን የበለፀጉ የኢትዮጵያ ሸለቆዎች፣ የነዳጅ ፍለጋው የተጀመረው ከ1920ዎቹ ጀምሮ ነው።

በየጊዜው በሚነሱ ግጭቶችና ጦርነቶች የነዳጅ ቁፋሮው እየቆመ ኩባንያዎቹም እያቋረጡ ባይወጡ ኖሮ፣ እስካሁን ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብቷ መበልፀግ የምትችልበት ተስፋ ነበረ።

ሲንክሌር የተባለ የነዳጅ አሳሽ ኩባንያ፣ በጅፕሰም፣ በመዳብና በቤንዚን የከበረ ነው የተባለውን የኦጋዴን ሸለቆ ከንጉሥታቱ ዘመን ጀምሮ ያስሰው ነበር። ነገር ግን ሳይታሰብ በ1950ዎቹ ውስጥ እቃውን ሸክፎ ወጣ። የሲንክሌር ኩባንያ ኦጋዴንን ለቆ በወጣበት ወቅት ብጣቂ ወረቀት እንኳ (የነዳጅ ካርታ) አልተወም ነበር። ፍለጋ ያካሄደበትን ወይም ያላካሄደበትን ሥፍራ የሚጠቁም ካርታም አልተገኘም።





ሆኖም በኋላ እንደ ጎርጎርሳውያን አቆጣጠር በ1970ዎቹ፣ ቴንኮ የተባለ የአሜሪካ ኩባንያ ኦጋዴን ገብቶ ባደረገው ሀሰሳ ሁለት ጉድጓዶች ውስጥ ነዳጅ እንዳገኘ ገልፆ ነበር። ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ነዳጁ ከመፈንዳቱ በፊት ኮሚኒስቶች አብዮት አፈነዱ። መሠረቱ ከካፒታሊስት ርዕዮተ ዓለም አቀንቃኟ አሜሪካ የሆነው ቴንኮ ኩባንያም ነዳጅ ሳይወጣ እግሬ አውጭኝ ብሎ ከኦጋዴን ወጣ።

በቴንኮ እግር ከኮሚኒስት ርዕዮተ ዓለም አራማጇ ሶቭዬት ህብረት የተነሳው ነዳጅ አዳኝ ኩባንያ በኦጋዴን ረሞጫ በረሃ ላይ እግሮቹን ተከለ። የአሜሪካኑ ኩባንያ የጀመራቸውን ገደሎችም ይቆፍር ጀመር። በኢላላና በካሉብ የነዳጅ ጉድጓዶች ተስፋ ሰጪ ፍንጮች እንዳገኘ ቢገልፅም፣ የደርግን መውደቅ ተከትሎ ከኦጋዴን ምድረ ገፅ ላይ ተስፋውን ሰርዞ ወጣ።

ከ1980ዎቹ በኋላ የኢህአዴግን መግባት ተከትሎ፣ እንደገና ሁለት የአሜሪካ ኩባንያዎች ወደ ኦጋዴን በረሃ ብቅ አሉ። እነዚህ ሃንት እና ማክሲስ ኢነርጂ የተባሉ የአሜሪካ ኩባንያዎች የኦጋዴንን ምድር ሲቆፍሩ ከቆዩ በኋላ ማክሲስ ሁለት አመታት ብቻ ሞክሮ ሲወጣ ሃንት ግን ለስምንት አመታት አደኑን ቀጥሎ እጁን አዝሎ ወጣ።

ከዚህ በኋላ ነበር ገዢው ፓርቲ አቀራረቡን የቀየረው። ለነዳጅ አሳሽ ኩባንያዎች ብሎኮቹን ከማከራዬት ይልቅ ከሚገኘው ነዳጅ የጥቅም ተጋሪ እንዲሆኑ ወሰነ። ይህንን ተከትሎ በርካታ ኩባንያዎቹ የፊርማ ክፍያ ሳይቀር ራሳቸው እየከፈሉ የሴድመንታሪ ሮክ (ቅዝጤ አለት) ባዩባቸው የኢትዮጵያ ሸለቆዎች ሁሉ ለቁፋሮ አኰበሱ። የፊርማው ክፍያ አላማ ነዳጅ በሚቆፈርባቸው አካባቢዎች ለሚገኙ ህዝቦች የጤና፣ የትምህርትና የንፁህ ውሃ

አገልግሎት እንዲውል ቢሆንም፣ በዚህ ተጠቀምኩ ያለ አካባቢ ግን አልተገኘም፡፡ ለነዳጅ አዳኞች አካባቢዎቹ ምቹ አለመሆናቸውም፣ 'ተጠቃሚ አይደለንም ወደፊትም ተጠቃሚ አንሆንም' ብለው ከማሰባቸው የተነሳ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ጆሮ ዳባ ልብስ ያሉት ኩባንያዎች ገብተው ማሰሳቸው አልቀረም፡፡ የዩናይትድ ኪንግደሙ ጎደት ናይል፣ የዩናይትድ ስቴቱ ኢንተር ግሎባል፣ የስዊድኑ ሉንዲን፣ የማሌዢያ ሁለት ኩባንያዎች ፔትሮናስ እና ፔኮ፣ የሆንግ ኮንጉ ሳውዝ ዌስት፣ የአሜሪካው አፍር ኤክስፕሎረር፣ የቻይና ሁለቱ ኩባንያዎች ዥንግያን እና ፖሊግሩፕ ኮርፖሬሽን እንዲሁም ሌሎች ኩባንያዎች፣ በኢትዮጵያ የዝቅጤ አለት ሸለቆዎች ተሰማሩ፡፡ ለእያንዳንዳቸውም አካባቢዎች ተለይተው ተሰጡዋቸው፡፡

የአፋር አካባቢ ለአፋር ኤክስፕሎረር፣ አዲጋላ እና ሪፍት ቫሊ ለአፍሪካ አይል ኮርፖሬሽን፣ መተማ ለኩሊቫሊ ፔትሮል፣ ደቡብ ኦሞ -ለቱሎው አይል፣ የአባይ ሸለቆ . ለፋልካን ፔትሮሊዩም፣ ጋምቤላ እና ጅማ ለሳውዝዌስት ኢነርጂ፣ እንዲሁም ፍፁም ተስፋ የተጣለበት ኦጋዴን ለተለያዩ በርካታ ድርጅቶች መታደሉን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ኦጋዴን ውስጥ በነዳጅ ቁፋሮ ላይ የተሰማሩት ፔኮ፣ ኒው ኤጅ፣ ሳውዝዌስት ኢነርጂ፣ ፖሊግሩፕ ኮርፖሬሽን እና ዥንግያን የተባሉት ኩባንያዎች ቢሆኑም፣ ዥንግያን የተባለው የቻይና ኩባንያ ግን በተፈፀመበት አሰቃቂ ጥቃት ጥሎ ወጥቶ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ኦጋዴን ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ኦብነግ የተባለው አማፂ ቡድን ጥቃቱን እንዳደረሰ በተጠቀሰው በዚህ ጭፍጭፋ፣ አደሌ በተባለው ቦታ ስድሳ አምስት ኢትዮጵያውያንና ሰባት ቻይናውያን እንደተገደሉ በወቅቱ ተገልፆ ነበር፡፡





አያን ይህንን ሁሉ ነግራኝ ስታበቃ ነበር ጥቃቱ ላይ ስትደርስ ያቆመችብኝ፡፡ ምናልባት በየትኛው ጥቃት እሙኛዋ እንደተገደለ ባላውቅም ነገሩን ላለማባባስ ብዬ ከመጠየቅ ተቆጠብኩ፡፡ በዚህ ሰዓት ሁለታችንም በቂ ጥቃት ደርሶብናል፡፡ ምናልባት የቀረን መቀላት ብቻ ይሆናል፡፡ ጨለማ ውስጥ የወረወረን አካል ማንነቱ ባይታወቅም በቀላሉ ሊለቀን እንደማይችል ግልፅ ነው፡፡

በዚህ ሰዓት ሁለታችንም የምናስበው አሟሟታችን እንዴት እንደሆነ ነው፡፡ በዓይነ ህሊናችን የሚሳለው፣ ወፍራም ግንድ ላይ አንተርሰው አንገታችን ሲቀሉት ነው፡፡ ከአንገታችን በላይ ያለውና የተቀላው ጭንቅላታችን፣ ህይወቱ እስኪያከትም ድረስ፣ ከወዲያ ወዲህ እየተራወጠ ሲቃኝ ነው፡፡

# ፳

ጥቂት የሰቆቃ ሰዓታትን በእንቅልፍ ገፍቼ ነቃሁ። አያን ቀድማ ነቅታ ነበር።

ገና ከመንቃቴ ነበር ከማንቀላፋታችን በፊት ጀምራልኝ የነበረውን ታሪክ እንድትቀጥልልኝ የወተወትኳት።

"ለመሆኑ ነዳጅ ተገኝቷል? ወይስ ዝም ብለው ነው አሳራችን የሚያበሉን?" ስል ጠየኳት። "ይህ ሁሉ ግርግር ከምን የመጣ ነው?"

"በኢላላና በካሉብ ባሉ ብሎኮች ውስጥ ነዳጅ መገኘቱ ተረጋግጧል።" ስትል ቀጠለች። "ች..ችግሩ ከዚህ በኋላ ነው የሚከተለው።"

"ምንድን ነው ችግሩ?"

"...በደርግ ዘመነ መንግሥትም፣ በአካባቢው መረጋጋት ስላልነበር በምስጢር ተይዞ እንጂ፣ ነዳጅ ተገኝቶ እንደነበር የሚናገሩ የዓይን እማኞች አሉ። ነገር ግን ኦጋዴን የጦርነት ቀጣና ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ኢትዮጵያ ለነዳጅ ማጣሪያነት ሊያገለግሉ የሚችሉት የቀይ ባህር ወደቦቿም፣ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት አስተማማኝ አልነበሩም። የደርግ መንግሥት ከኦጋዴን አሰብ ወደብ ድረስ የነዳጅ መስመር ለመዘርጋት እቅድ ነበረው። ነገር





ግን በምሥራቅና በሰሜን በጦርነት በመወጠሩ ምክንያት አልቻለም። ነዳጅ መገኘቱ ብቻውን ዋጋ የለውም። ነዳጁን ማጣሪያ መስመር ወደ ወደብ መዘርጋት ያስፈልጋል። የነዳጅ ቱቦው የሚያልፍበት ቀጠናም ከአደጋ ጣዮች የፀዳ መሆን ያስፈልገዋል።"

"ስለዚህ ነዳጁ መገኘቱ ምን ዋጋ አለው? ለዚህ ሁኔታ በኦጋዴን ምድር ላይ የነዳጅ ቧንቧ መዘርጋት እንዴት ይቻላል? ወደየትስ ነው ቱቦው የሚዘረጋው? ኢትዮጵያ ወደብ የላትም።"

"ችግሩ ይኸው ነው። ይኸም ሆኖ ፖሊግሩፕ የተባለው የቻይና ኩባንያ ከኢትዮጵያ ጅቡቲ የሚዘረጋውን የነዳጅ ቱቦ መስመር ለመዘርጋት ከገዢው ፓርቲ ጋር ተስማምቷል። በዚህም መሠረት ከካሉብ እና ከኢላላ የነዳጅ ጉድጓዶች የተገኘው የተፈጥሮ ጋዝ ጅቡቲ ወደብ ላይ ተጣርቶ ወደ ኢትዮጵያ ይመለሳል ማለት ነው። ከኦጋዴን ልብ የሚነሳው ይህ የነዳጅ መስመር፣ ከጅቡቲ ወደብ ለመድረስ አንድ ሺህ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ማቋረጥ አለበት። ኢላላና ካሉብ የነዳጅ ጉድጓዶች አምስት ትሪሊዮን ጫማ የተፈጥሮ ጋዝ እንደሚያመርቱ ቢገመትም ይህን ምርት አጓጉዞ ለማጣራት የሚዘረጋው መስመር ግን አራት ቢሊዮን ዶላር ይፈጃል። ከዚህ ውስጥ ደግሞ ሶስት ቢሊዮን ያህሉ ገንዘብ የሚፈሰው ጅቡቲ ውስጥ ነው። ከዚህም ሌላ ለዚህ ትብብሯ፣ ጅቡቲ ሁለት ኤርፖርቶች እንደሚገነቡላት ቃል ተገብቶላታል።"

"ከተጣራ በኋላስ..." አልኩ አያን እንደ ፀሎት ባጠናችው መረጃ እየተገረምኩ።

"ወሳጁ የቻይና ድርጅት ሲሆን መላሹ የአሜሪካ ድርጅት ነው። ብላክ ርኪኖ የተባለው የአሜሪካ ኩባንያ

ሃያ ኢንች ዲያሜትር ያለው የቧንቧ መስመር ከጅቡቲ ወደብ እስከ አዋሽ ማዞሪያ ድረስ ለመዘርጋት ተስማምቷል። አምስት መቶ ሃምሳ ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ይህ መስመር ወደ ሁለት ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ይፈጃል። ባንቧው በቀን እስከ ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ በርሜል የሚጠጋ ነዳጅ ያጓጉዛል ተብሎ ይገመታል።"

"ከአፍ የወደቀች ጥሬ የምታክለው ሀገር ጅቡቲ ኢትዮጵያ ወደብ ቢኖራት ኖሮ በምን ትተዳደር ነበር?!" በማለት ተገርሜ ሳበቃ፣ "ጅቡቲ ምን ያህል ብትታመን ነው ኢትዮጵያ እጣ ፋንታዋን ሁሉ ይህን ያህል ያጣበቀችባት?" ስል ጠየቅኳት።

"በነዳጁ መስመር ትገረማለህ እንዴ? ጅቡቲ ወደብ ላይ በአመት ከሚራገፈው አምስት መቶ ቶን ያህል ካርጎ ውስጥ ከሰማኒያ በመቶ በላይ የሚሆነውን የምታነሳው ኢትዮጵያ ናት። ኢትዮጵያ በአመት ከሁለት ቢሊዬን ብር በላይ ጅቡቲ ለምትሰጣት የወደብ አገልግሎት ትከፍላለች ማለት ነው። ባጠቃላይ ዘጠና በመቶ የሆነው የኢትዮጵያ ኢምፖርትና ኤክስፖርት የጅቡቲ ጥገኛ ነው። አሁንም ቢሆን በቀን እስከ ሃምሳ ሺህ በርሜል የሚሆን ነዳጅ ተጠቃሚ የሆነችው ኢትዮጵያ በጅቡቱ ወደብ በኩል ነው የሚራገፍላት። ከዘጠኝ መቶ ኪሎ ሜትር በላይ ተጓጉዞ አዲስ አበባ ሲገባ ዋጋው ምን ያህል እንደሚንር መገመት ቀላል ነው።"

"ማኩረፊያ የሚሆን እንኳ ሌላ ጣባ የሚያክል ወደብ ቢገኝ ምን ነበረበት?"

"እርሱ ህልም ነው። ገዢው ፓርቲ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጥህ ምላሽ፣ የሶማሌ ላንድ ንብረት የሆነውን





በርበራን፣ ፖርት ሱዳንን፣ ወይም የኬንያውን ሞምባሳን በአማራጭነት መጠቀም እንችላለን የሚል ነው።"

ለረጂም ደቂቃዎች ዝም አለችና፣ ቀጠለች።

"ከሁሉም በላይ፣ በድርቅ፣ በረሃብና በጦርነት የሚታመሰው የኦጋዴን ምድር ቀን ሳይወጣለት መሞቱ ያሳዝነኛል። አንድ ቀን፣ የምታቃጥለው ፀሐይ ስትወጣ የምትናፈቅበት ጊዜ ይመጣል የሚል ህልም ነበረኝ። ነገር ግን ይህ የደም ምድር አሁንም ድረስ ሁቡቱ በደም ይለወስበታል። ነዳጅ ሳይሆን ደም ይንፎለፎልበታል። በሽላቦ፣ በደናን፣ በጎዴና በፊቅ ሽለቆዎች ወታደር ይርመሰመስበታል። በዶሎ፣ በቡርኡር፣ በገላዲ ኮረብታዎች ወንበዴ ያደፍጥበታል።

"የኦጋዴን ሸለቆዎች ተቃጥለው የቆሙ ታንኮች እንጂ በተስፋ የቆሙ ሰዎች አይታዩባቸውም። በወገኖቻችን ደም ከጨቀየው ምድር አንዲት ጠብታ ነዳጅ እናስነካም የሚሉ ኃይሎች አሁንም ድረስ አሸዋ ከለበሰው ጎን ነፍጣቸውን ደግነው አሸዋ ለብሰው አድፍጠዋል።" ደምፅዋ እየጨመረ መጣ።

"ምንድን ነው መፍትሄው?!" አልኩ ቢጨንቀኝ።

"የለውም።"

"መፍትሄ የሌለው ነገር የለም።"

"...'የቼገረ ነገር የጠፋ ለመላ፣

አስታራቂው በዛ እኛ ሳንጣላ።'... የሚለው ያዝማሪ ግጥም ነው መልሱ" አለችና በብሽቀት አክላላች።

# ፳፩

እያንዳንዱ ሰከንድ የዘለአለምን ያህል ረዝሞብናል። ከአስጨናቂው ትንፋሻችን በቀር የሚሰማን ነገር የለም። ጭንቅላታችን ቁሟል። ባዶ...። እንደ ባዶ ጭንቅላት የሚከብድ ነገር የለም።

ጥልቅ በሆነው ድንዛዜ ውስጥ እንዳለን፣

"ለምን ስለማምለጥ አናስብም?" ኢያን ድንገት ጠየቀችኝ።

"እንዴት ሊሆን ይችላል?!"

"ተቀምጠን ሞታችንን ለምን እንጠብቃለን?! እጅ ሰጥቶ ከመሞት እየሮጡ መሞት ይሻላል።"

"አብደሻል?!..." አልኳት ባመጣችው ሃሳብ እየተገረምኩ። "መታሰራችንን ረሳሽው እንዴ?"

"ጭንቅላታችን አልታሰረም።"

እያበደች እንደሆነ ገመትኩ። ደም ሥራችን እስኪያብጥ ታስረናል። ዓይኖቻችን ድብን ባለ ጥቁር ዓይነ ርግብ ታጅለዋል። እንዴት ማምለጥ ይቻለናል?...ጭንቅላታችን ብቻ ከአካላችን ተለይቶ አይሮጥ ነገር! ምን ማለቷ ነው?





"ምንም የሞከርነው ነገር የለም። ቢያንስ እንኳ ስለማምለጥ አላሰብንም።" አለች ኢያን እንደገና።

"...ለመሞከር አለማሰብን ያህል ድክመት የለም።" የተናገረችውን ማሰብ ጀመርኩ። "...ከሞከርነው ነገር ይልቅ፣ ያልሞከርነው ነው 'ሚቆጨኝ!" ያለውን ፀሐፊ አስታወስኩት። ኢያን ትክክል ናት።

አለመሞከርን ያህል ደዌ የለም። እርግጥ ነው ማጥ ውስጥ ገብተናል። ችግር ውስጥ ነን። የባሰው ችግር ችግሩን ተቀብለን መቀመጣችን ነው። እስክንሞት መጠበቅ ሳይሆን እስክንሞት መሞከር ነበረብን። ችግሩን ለማለፍ አንዳች ጥረት የማያደርግ ሰው ከአስከሬን አይሻልም። አንዳንድ ችግሮች ፅናትን ለማጎናፀፍ ይፈጠራሉ። ችግርን ያህል ታለቅ ዩኒቨርስቲ የለም። ታላላቅ ሰዎች የተመረቁት ችግር ከሚባል ታላቅ ትምህርት ቤት ነው። የሆነ የመነቃቃት መንፈስ ወረረኝ።

"እንዴት ማምለጥ እንደምንችል ያሰብሽው ነገር አለ?" ጠየቅኳት።

"እርስ በእርስ እንፈታታ።"

"እንፈታታ ስትይ..."፣

"በጥርሴ ያንተን እስር ለመፍታት ልሞክር ካቃተኝ አንተ የእኔን ትፈታልኛለህ።"

"በደንብ አስበሽበታል?"

"አስቤበታለሁ።"

"ስንሞክር ብንገኝስ? ...የባሰ ችግር ውስጥ መግባታችን እንደሆነ አስበሽዋል?"

"አው... ስንሞክር ቢያገኙን የባሰ መከራ ያደርሱብንና ነጣጥለው ያስሩናል።" ፀጥ ረጭ አለች።

"እስሮቻችን ፈታተን ከዚህ ዋሻ ወጥተን ስመርጥ ብንሞክር እንኳ ከጀርባችን በጥይት ይጥሉናል።"

"...እርሱ እንኳ ይሻላል። አንገትን ከመቀላት በጥይት መሞት ይሻላል።"

"ግዴለሽም...ተረጋግተን እናስብበት..."

"ሌላ ምን ማድረግ እንችላለን? ሌላ ምን የማምለጫ መላ ይኖረናል?"

"እስማት..." አልኩ ሳላስበው።
"እ?!" አለች በድንጋጤ። ዝም ስላት ጊዜ ምጸት የሚመስል ሳቋን ትስቀው ጀመር።





# ፳፬

"ስለ እስማት እውቀት ያለሽ አይመስለኝም" አልኳት ስለ እስማት ረዢም ጊዜ ካወራን በኋላ። "ወይም ላለማወቅ አእምሮሽን ዘግተሽዋል።"

"አታስቀኝ!" አለች እያን ደረቅ ሳቅ ስቃብኝ ስታብቃ። "በእስማት ከዚህ ዋሻ መውጣት እንችላለን ነው ምትለኝ?"
"አዎ!"

"እሺ የእኔ ክርስቶስ! ምክረህ አሳየኝ! ሁሁ! ...ሲባል እንደሰማሁት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በተዘጋ በር መግባትና መውጣት የሚችለው።"

"እያን! ...አድምጪኝ! ...ባለፈው በእስማት ምክንያት ህይወቱ መትና እንዳሳ አሜውቼሽ ነበር። አላመንሽኝም ነበር ማለት ነው?"

"ምርጥ የልብ ወለድ ድርሰት የምታወራኝ ነበር የመሰለኝ። ወደ ውሸት በእስማት ተሰወጥህ። ወደ

ሰውነት እንደገና መመለሻውን አስማት አላጠናህም ነበር። በዚህ የተነሳ ለአንድ አመት ያህል ከደቡብ ኢትዮጵያ እስከ አዲስ አበባ ተንዝክ። ቤትህ ስትደርስ ሚስትህ ሌላ ባል አግብታ ጠበቀችህ።"

"እጥብቄ የምጠላውን ባላንጣዬን!..."

"አየህ? በደንብ ሰምቼሃለሁ ማለት ነው። ኀበዝ ደራሲ የፃፈው ድርሰት የመሰለውን ታሪክህን ግን ለማመን ይቸግረኛል።"

"የነገርኩሽ ስለ እኔ ማወቅ ስለፈለግሽ እንጂ እንድታምኚኝ፣ ወይም እንደ ህፃን ልጅ ተረት ተረት እያጫወትኩ ላስተኛሽ አልነበረም። ካልሽስ እኔ ራሴ ወደ አስማቱ ዓለም መመለስ አልፈልግም።"

"ለምን?"

"ህይወቴን ያዘበራረቀው አስማት ነው። ከልጅነቴ ጀምሬ ሳጠናው የኖርኩት የአስማት ጥበብ ከዓለም ነጥሎኛል። ወደዚህ በረሃ ለጥናት ሲጋበዝ ያለ አንዳች ማቅማማት የመጣሁት ከገባሁበት የአስማት ዓለም ለመውጣት ካለኝ ጉጉት የተነሳ ነበር።"

"ኦጋዴን የአስማት ዓለም ሆና ጠበቀችህ።"

"ያው ነው። እንዲያውም ሳይብስ ይቀራል?...."

"እስኪ በደንብ አስረዳኝ ...ከልብህ ነው አስማት የምትለው? ታምንበታለህ?"

"በደንብ! ...ሳይንቲስቶች ሙከራ የሚያደርጉት በልዩ ልዩ እንስሳት ላይ ነው። እኔ ግን አስማትን ያህል አስፈሪ ነገር የሞከርኩት በራሴ ላይ ነው። ከራሴ በላይ ማረጋገጫ የለኝም።"





"ለምን ታዲያ አሁን ወደ ሆነ ነገር አትለወጥምና ከዚህ ዋሻ አታመልጥም። መለወጥን ያህል ጥበብ እያለህ ለምን ሞትን ትጠባበቃህ?"

"እንደገና ወደ ውሻነት አልለወጥም። ውሻ ሆኜ የደረሰብኝን የማውቀው እኔ ነኝ።"

"ወደ ድመት ተለወጣ ታዲያ!"

"እንደገና ወደ ሰውነት መመለሻውን አላውቅም እንጂ ወደ ድመት መለወጫ አስማት አለኝ።"

"እባክህ አታስቀኝ። ወደ ድመት ብትቀየር አንቄ ነበር የምገድልህ። ድመትን ያህል ጠላት የለኝም። ህፃን ወንድሜን የበላው ድመት ነው። ድመት ባዩሁ ቁጥር በጦርነት ያጣኋቸው ቤተሰቦቼ ናቸው የሚታወሱኝ። እስከ አሁን ለቁጥር የሚያዳግት ድመት ፈጅቻለሁ። ብዙ ድመት አሰቃይቼ ገድያለሁ። ሰዎች 'ተይ ድመት የገደለ ሰው ሽባ ይሆናል' ሲሉኝ አልሰማቸውም። እስካሁንም ሽባ አልሆንኩም። ...ወደ ድመት እለወጣለሁ ብለህ እንዳትሞክር። ሰምሮህል ከተቀየርክ ገዳይህ እኔ ነኝ።"

"ካልሽስ ወደ ድመት መለወጫው አስማት ቀላል ነው።" አልኳት በለሆሳስ። "ለአንቺም አስማቱ የሚቀልሽ ወደ ድመት መለወጫው ነው።"

"እኡዝቢሊላህ! አንተ ዝም በል!" ጮኸችብኝ። "ጭራሽ እኔ ወደ ድመት?!"

"መቼም በከንቱ አንገትን ተቀልቶ ከመሞት የማይሻል ነገር የለም። ብዙ ህልም፣ ብዙ ተስፋ ያለው

ሰው ሞትን ዝም ብሎ መቀበል የለበትም። ክፉ ቀን እሾህ ያስጨብጣል። ጎደሎ ቀን ከሰውነት ክብር ዝቅ ያደርጋል። ምንም ይሁን ምን፣ በየትኛውም መንገድ ጎደሎ ቀኖችን ማለፍ ነው ቁም ነገሩ። ለእኔ ጀግና ሰው ማለት አንበሳን ታግሎ የሚጥል አይደለም፤ ክፉ ቀንን በጥበብ የሚያልፍ ነው። ሁሉም ሰው ማሰብ እስከቻለ ድረስ፣ ክፉ ቀኖቹን የሚያልፍበት መንገድ እጁ ላይ አያጣም። ዘጠና ዘጠኝ በሮች ሲዘጉ መቶ በሮች ይከፈታሉ። ለእኛ ለጊዜው የተከፈተው በር፣ በእጃችን ያለው የአስማት ጥበብ ነው። አስማትን አጥብቄ እጠላለሁ። ነገር ግን በዚህ ሰዓት ሌላ ምርጫ ስለሌለኝ እጠቀመዋለሁ። ማንም ሰው መጀመሪያ መጠቀም ያለበት በእጁ ላይ ያለን መፍትሄ ነው።"

"አስረዳኝ!" አለች አያን ድምፅዋን ቀዝቀዝ አድርጋ። "አስረዳኝ… አሁንም ድረስ በአስማት ለማመን አዕምሮዬ አልተዘጋጀም።"

"እንቺን ስለ አስማት ለማስረዳት ሰዓታትን ሊፈጅብኝ ይችላል። በዚህ መሀል አሳሪዎቻችን መጥተው አንገቶቻችን ሊቀሏቸው ይችላሉ።"

"አስረዳኝ! ካላመንኩበት አይሠራ ይሆናል።"





# ፳፫

ለአያን ስለ አስማት ለማስረዳት ሰዓታትን ፈጀሁ። ከጥንት ዘመን ጀምሮ ስላለው የአስማት ጥበብ አመለካከት ቅዱሳን መፃህፍትንና ርኩሳን መጥቁሎችን ጭምር እያጣቀስኩ ተረኩላት። በመሃል በመሃል ለምትጠይቀኝ ጥያቄዎችም ከበቂ በላይ መልስ ነበረኝ። ከልጅነቴ ደክቼ ያጠናሁት የአስማት ዓለም ጥበብ፣ በሰዓታት ብቻ ተተርኮ የሚያበቃ አልነበረም። አያሌ መፃህፍት የሚወጣውን ታሪክ ጨምቄ የነገርኳት ጨለማ ውስጥ የወረወሩን ወንበዴዎች አንገታችንን ሳይቀሉን ለማምለጥ ካለን ጭንቀት የተነሳ ነው።

ብዙ ሰዎች አስማት፣ መተት፣ ድግምት፤ ምትሐት ለይተው አያውቁም፤ የሳይኪክ ጥበብና የቴሌፓቲ (ስድስታኛው ስሜት) ተስጥኦ ይምታቱባቸዋል። ለአያን እነዚህን ሁሉ ፀየፈርጁ አስረዳኋት።

አስማት፣ በጥቅሉ ልዕለ ተፈጥሮ (ሱፐር ናቹራል) የሆነውን ኃይል የመጠቀም ጥበብ ነው። ይህ ጥበብ ቅደም ተከተሎችን (ሪቹዋልስ)፣ ጠልሰሞችን (ሲምቦልስ) እና ቃላትን (ስፔል) የመጠቀም ጥበብ ነው። በጥንታዊ ጥቅሎች ላይ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጠልስሞች

(ሲምቦልስ) ተመልክቻለሁ። የወከሉትን ነገር ለመረዳትም አያሌ ጥናቶችን አድርጌአለሁ። ይሁን እንጂ በውል ያተኮርኩት በቃላት በሚገልፀው የአስማት ጥበብ (ማጂክ ስፔል) ላይ ነው። በዚህም የቃላትን ኃይል ተምሬአለሁ።

አስማት ("ማጂክ") የሚለው ቃል ከክርስቶስ ልደት በፊት ከስድተኛው ክፍለ ዘመን ቀደም ብሎ በፔርሺያ ምድር "ማጉ" በመባል ይታወቅ ነበር። ቃሉ ወደ ግሪክ ሲገባ አስፈሪ ትርጓሜ ያዘ። ከክርስቶስ ልደት በኋላ በአንደኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ በክርስቲያን ቲዎሎጂ ውስጥ፣ በላቲን ትርጓሜው ከሃይማኖት ተፃራሪ የሆነ ትርጓሜ ከተሰጠው በኋላ፣ ከሰይጣን ጋር በማያያዝ፣ አያሌ የአስማት መፃህፍት ይቃጠሉ ጀመር።

ከእሳት የተረፉት የአስማት መፃህፍትም በጥቂት ሰዎች እጆች ስለገቡ፣ በተለይ በምዕራቡ ዓለም ሰዎችን ማስፈራሪያና መበዝበዣ ሆኑ። አዋቂዎቹ ተሳደው ስለተገደሉ አባይ ጠንቋዮቹ የአስማት ጥቅሎቹን መጫዎቻ አደረጓቸው።

ከቀኝ ግዛት በፊት በአፍሪካ አያሌ አዋቂዎች እንደነበሩ ጥናቶች ያሳያሉ። ዘመናዊ ህክምና ከመስፋፋቱ በፊት፣ አፍሪካውያን ይታከሙ የነበሩት በእነዚህ አዋቂዎች የቅጠላቅጠልና የሥራሥር ጥበብ ነበር። ከተፈጥሮ ጋር ጥብቅ ቁርኝት የነበራቸው አዋቂዎች ቅጠላ ቅጠልን ብቻ ሳይሆን ልዕለ ተፈጥሮ (ሱፐር ናቹራል) ኃይልንም ይጠቀሙ ነበር። ነገር ግን ለሀብት ቅርምት በሃይ[illegible] ስብከት የገቡ ወራሪዎች፣ አዋቂዎችን በህዝብ ፊ[illegible] ጥቅሎቻቸው በእሳት አቃጠሏቸው። በየዋሻው ተ[illegible] የተገኙት ጥቂት ጥቅሎች ብቻ ናቸው ለጥናት[illegible] የተረፉት።



በሀገራችን ኢትዮጵያም ከጥንት ዘመን ጀምሮ አንቱ የተባሉ አዋቂዎች እንደነበሩ ይታወቃል። ሕዝቡን በቅጠላ ቅጠልና በሥራሥር ከመፈወስ አልፈው፣ የውስጥ ደዌን በመስታዉት ቁልጭ አድርገው የሚያዩ፣ በልዕለ ተፈጥሯዊውን ኃይል በመጠቀም በውሃ ላይ የሚራመዱና በደመና የሚጫኑ የአስማት ሊቃናት እንደነበሩ ይነገራል። ሆኖም ከሃይማኖት ምሁራን ጋር ባለመስማማታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ተወግዘው ከህዝቡ በመለየታቸው ቀስ በቀስ እንዲጠፉ ተደርገዋል።

በሃይማኖት መፃህፍት ውስጥም እነዚህ የአስማት ሊቃውንት መኖራቸው ተመዝግቧል። በጥንታዊቷ ግብፅ ፈርኦኖች ፊት ልዩ ልዩ ጥበቦችን ያሳዩ እንደነበርም በመፅሐፍ ቅዱስ ሳይቀር ተጠቅሷል።

ከምድያም ምድር ጥበብን ተክኖ፣ ፈርኦን ህዝቦቹን እንዲለቅ ተአምር ያሳይ የነበረውን ሙሴን፣ በአስማት ጥበባቸው ተገዳድረውታል። የፈርኦን ጥበበኞችም በትራቸውን ወደ እባብ በመለወጥ ጥበብ አሳይተዋል።

በዘፀአት መፅሐፍ እንደተጠቀሰው። ሙሴና አሮን፣ ፈርኦንን በተአምራት ለማስፈራራት ወደ ንጉሡ ይገባሉ። አሮንም በትሩን በፈርኦንና በባሮቹ ፊት ይጥላል። እባብ ትሆናለች። ፈርኦንም የግብፅን ጠቢባን ፈጥኖ ይጠራል። በአስማታቸው በትሮቻቸውን ወደ እባብነት ይለውጣሉ። በዚህ ጊዜ ግን ወደ እባብ የተለወጠችው የአሮን በትር የግብፆቹን በትር ትውጣለች።

በትንቢተ ዳንኤል ላይ፣ ስለ ባቢሎን ጠቢባን አያሌ ጊዜ ተጠቅሷል። የባቢሎኑ ንጉሥ ምስጢር አዋቂዎች፣ ህልም ፈቺዎችና ቃላተኞች እንደነበሩት በስፋት ተጠቅሷል።

በዘፍጥረት መፅሐፍ ላይ እንደተጠቀሰው፣ ልዩ ልዩ ጥበቦችን ያደርጉ የነበሩት ኔፍሊም የተባሉ የሰውና የመላእክት ዲቃላዎች ናቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ፍጡራን፣ እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ እስኪፀፀት ድረስ አማረውታል።

በዘፀዓት ላይም፣ "መተተኛይቱ በህይዎት እንድትኖር አትፍቀድላት" ሲል ያወግዛል።

የዘሌዋውያን መፅሐፍ "አስማት አታድርጉ፣ ሞራ ገላጭም አትኹኑ።" ሲል ይመክራል።

ዘኍልቁ፣ "በዕያቆብ ላይ አስማት የለም፤ በእስራኤል ላይም ሟርት የለም።" ሲል ያውጃል።

ዘዳግም ላይ፣ "ወንድ ልጁን ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ፣ ሟርተኛ፣ ሞራ ገላጭም፣ አስማተኛም፣ መተተኛም፣ በድግምት የሚጠነቁልም፣ መናፍስትንም የሚጠራ ጠንቋይም፣ ሳቢም ባንተ ዘንድ አይገኝ" ይልና፣ አስማት በዛ ኋላ ቀር ህዝብ ውስጥ ምን ያህል ተስፋፍቶ እንደነበር ያሳያል። መናፍስትን መጥራት የሚችሉ፣ ምንም ሳይቃጠሉ በእሳት ላይ የሚረማመዱና የሞቱ ሰዎችን እንኳ ስበው በመጥራት የሚያናግሩ ጥበበኞች እንደነበሩ ያስረዳል።

በመፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ላይ ግርምት የሚፈጥር የሙታን መጥራት ጥበብ ይታያል። በዚህ ትረካ ላይ፣





ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ሊወጉ ይመጣሉ። በወቅቱ ሳሙኤል ሞቶ ነበር። በዚህ ጦርነት የሚፈጠረውን ነገርና ምን ማድረግ እንዳለበት (የጦርነት ትንበያ) ሳሙኤል ሞቶ ስለነበር የሚነገር ይጠፋል። ቀደም ብሎ ሳኦል መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ከምድር አጥፍቶ ነበር። ያለው ብቸኛ አማራጭ ሳሙኤልን በአስማት ከሙታን ጠሪዎች ዘንድ አስጠርቶ ማነጋገር ነበር። በዚህ ጊዜ ባሪያዎቹ አይንዶር በተባለ ምድር አንዲት መናፍስትን የምትጠራ ሴት እንዳለች ለሳኦል ይነግሩታል። ሊገድላት የሄደ መስሏት እንዳትሸሽ ሳኦል እንደተራ ሰው ተሸፋፍኖና መልኩን ለውጦ ወደ አይንዶሯ አስማተኛ ይሄዳል። ይለምናታል። እርሷ ግን በሳኦል ታስገድለኛለህ ብላ ለሶኦል እንደማይናገር በእግዚአብሔር ይምልላትና አስማተኛዋ በድግምቷ ሳሙኤልን ከተፍ አደረገችለት። "የምትፈልገውን ጠይቀው!"

በትንቢተ ኢሳይያስ መፅሐፍ ላይ ደግሞ፣ እግዚአብሔር በአስማተኞች በመማረር በኃይል ሲዝት ያሳያል።

"የሐሰተኛዎችን ምልክት ከንቱ አደርጋለሁ፤ ሟርተኞችንም አሳብዳለሁ፤ ጥበበኞችንም ወደ ኋላ እመልሳለሁ። እውቀታቸውንም ስንፍና አደርጋለሁ።" ይላል። ፈጣሪን የሚገዳደሩ አስማተኞች እንደነበሩ ዛቻው በደንብ ያስረዳል።

ዳዊትም አስማተኞች እንዳያጠፉት አምላኩን ሲማፀን እንደነበር የሚያስረዳ መዝሙር አለው። በብሉይ ብቻ ሳይሆን በሐዲስም ላይ ስለአስማተኞች ብዙ ቦታ ላይ ተጠቅሷል። በሐዋርያት ሥራ ላይ ስለ ጉደኛው አስማተኛ ሲሞን ተተርኳል። የሰማርያ ከተማ በእርሱ ክህሎት ትደነቅ ነበር። በሲሞን ተአምራዊ የአስማት ችሎታ ውስጥ የፈጣሪ ኃይል እንዳለበት የሚያምኑም ነበሩ። ሐዋርያው

ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ገብቶ ህዝቡን ሰብኮ ከጣመቀ በኋላ ግን ራሱ አስማተኛው ሲሞንም ሲጠመቅ ይመጣል፡፡ ከተጠመቀ በኋላ ግን መንፈስ ቅዱስን በገንዘብ ይሸጡለት እንደሆን ጠየቀ፡፡ በዚሁ መፅሐፍ ላይ ብዙ አስማተኞች መፃሕፍቶቻቸውን ሰብስበው እንዳቃጠሉና ዋጋውም ሐምሳ ሺህ ዲናር እንደሆነ ተዘግቦአል፡፡አንዳንድ ተመራማሪዎች፣ "መፅሐፈ ጠቢባን" የተባለና ከብዙ ታዋቂ አስማተኞች ጥበብ ተጨምቆ የተፃፈ ድጉስ በዚህ ወቅት እንደተቃጠለ ይናገራሉ፡፡ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በፃፈው መልእክትም አስማትን አውግዞአል፡፡ ይሁን እንጂ በዮሐንስ ራዕይ መፅሐፍ ላይ አስማተኞቹ ጨርሰው እንዳልጠፉ ይናገራል፡፡ ይህ ማለት ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ ባለው የመፅሐፍ ቅዱስ ትረካ ላይ እንደተገለፀው አስማት በቀደምት ህዝቦች ዘንድ የታወቀ ጥበብ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ ስለ አስማት ሥረ መሠረትና የት መጤነት በደንብ ትንትን ብሎ የተገለፀው በመፅሐፈ ሔኖክ ላይ ነው፡፡ በአያሌ የአስተሮሎጂ ጥበቦችና በህዋ ምስጢሮች የተሞላው መፅሐፈ ሔኖክ፣ እስካሁን ድረስ ሳይንስ ያልደረሰበትን ጥበብ እንደያዘ ይገመታል፡፡ በርካታ ሳይንቲስቶችም ጥናት እያካሄዱበት ይገኛሉ፡፡ የአውሮጳ አሳሾች መፅሐፈ ሔኖክን ለማግኘት ከጥንት ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ እየገቡ ያላደረጉት ጥረት አልነበረም፡፡ በሃይማኖት ስብከት መልክ የገቡ የካቶሊክ ቄሶች ሳይቀር ዋና ግባቸው መፅሐፈ ሔኖክን ማግኘት እንደነበር ይታመናል፡፡

በመካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈልጉት በነዳጅ የበለፀጉት ጉድጓዶች ሳይሆኑ ሁለት ቅርሶች ነበሩ፤ መፅሐፈ ሔኖክና ፅላተ ሙሴ፡፡ በተለይ ራሳቸውን





የኤሊያን ዘሮች ነን ብለው የሚቆጥሩ ህዝቦች ታሪካቸው በውል የተከተበበትን መፅሐፍ ለመፈለግ ኢትዮጵያ ውስጥ እየገቡ ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም፡፡ ነገር ግን መፅሐፈ ሔኖክን በማግኘት የተሳካለት አንድ ሰው ብቻ ነው- ጀምስ ብሩስ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ተገኝቶም ምስጢሩ ያልተገኘው መፅሐፍ፣ ስለ ስነ ፈለክና ስለ ዩኒቨርስ ምስጢራት ብቻ ሳይሆን ስለ አስማት ጥበብም ትንትን አድርጎ ያስረዳል፡፡

መፅሐፈ ሔኖክ ስለ ስነ እፅዋት ከዘረዘረ በኋላ፣ ስለ ስነ ሰብዕ ይተርካል፡፡ በገዳዩ ቃኤልና የሟቹ አቤል ምትክ በሆነው የሴት ልጆች መካከል ስለተደረገ ጋብቻ በመተረክ የሰው ልጅን ታሪክ ይጀምራል፡፡ የሴት ልጆች በቃኤል ልጆች መልከ መልካምነትና ደመ ግቡነት ይማረካሉ፡፡ እርስ በእርስ ይጠራሩና ከመኖሪያቸው ከደብር ቅዱስ ተነስተው የአርሞንኤም ተራራ ራስ ወደሆነው ወደ አርዲስ ወጥተው የቃኤልን ሴት ልጆች ለማግባት ይሄዳሉ፡፡ ወደ አርሞንኤም ተራራ የወጡትን የሴት ልጆች የጎበዝ አለቆች መፅሐፈ ሔኖክ በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡

አሥራ ስምንት ናቸው፡፡ ሰማዝያ፣ ዑራኪበራምኤል፣ አኪቢኤል፣ ጣምኤል፣ ራሙኤል፣ ዳንኤል፣ ኢዚቃኤል፣ ሱሩቃኤል፣ አስኤል፣ አርሞርስ፣ በጥርኤል፣ አናንኤል፣ ዘቂቢ፣ ሳምሳፒኤል፣ ሰርትኤል፣ ጡሩኤልያም፣ ያኤልና እራዝያል ይባላሉ፡፡ እነዚህና ሌሎች የተከተሏቸው የሴት ልጆች ቃኤልን ዘር የተወለዱትን ቆነጃጅት ሴቶች ከአርሞንኤም ተራራ ቁንጮ ድረስ ወጥተው ጠልፈው ተዳሯቸው አገቧቸው፡፡ ከተጠለፉት የቃኤል ዘሮችም፣ ሥር መማስንና ቅጠል መበጠስን ተማሩ፡፡ አስማትና ድግምትን አጠኑ፡፡

የፀነሱት ሴቶችም ከዚህ ቀደም ታይተው የማይታወቁ ረጃጅም ልጆችን ወለዱ። ቁመታቸው ሦስት ሺህ ክንድ ያህላል። እናትና አባቶቻቸው እነሱን መቀለብ እስኪሳናቸው ድረስ የሰበሰቡትን ሁሉ አሟጠው በሉት። ጭራሽ እናትና አባቶቻቸውን አንቀው ይበሏቸው ጀመር። አእዋፍንና አራዊትን አሳደው ይዘው እስከነፍሳቸው ይዘለግዷቸው ገቡ። መጥገብ ተሳናቸውና እርስ በእርሳቸውም መበላላት ቀጠሉ። አንዱ አንዱን ይዞ ደሙን መጥጦ ይጥለዋል። ሻምፓዬር የሚባሉት የዘመናችን የፈጠራ ገፀ ባህርያት መነሻ ይህ ታሪክ ሳይሆን አይቀርም።

ከነዚህ መሀል የላቀ ጥበብ የነበራቸው ሰዎችም ነበሩ። ፈረስና በቅሎን ከሰው ጋር አዳቅለዋል። አዛዝኤል የተባለው በዚህ የተካነ ነበር። ለወንዶች ሰይፍ መስራት፣ ጋሻ መሰጎድንና ሽለላን፣ ለሴቶች እንሶስላ መሞቅን፣ መኳኳልንና መቀንደብን አስተምሯል።

ጋኔን መሳብን፣ አስማትንና ምትሃት ማሳየትን አሚዛራክ፣ ኮከብ ቆጠራን- በረቅእልም፣ ምልክት ማሳየትን- ኮከብኤልም፣ የጨረቃ ምህዋርን- አስራድኤልም እንደስተማሩ መፅሐፈ ሔኖክ ያትታል።

እያን በበኩሏ እንዳስረዳችኝ በቁርዓንም ስለ አስማት ብዙ ሐተታዎች አሉ። ዘመናዊዎቹ ምሁራን አስማትን ለሃይማኖትና ለሳይንስ ማንፀሪያነት ያቀርቡታል። ሶሾሎጂስቶቹ አስማት የሃይማኖት ተቃራኒ እንደሆነ ሲገልፁ፣ አንትሮፖሎጂስቶቹ የሰውን ልጅ እድገት ቅደም ተከተል በማጥናት አስማት፣ ሃይማኖትና ሳይንስ የአእምሮ እድገት ማሳያ ቅደም ተከተሎች እንደሆኑ በማስቀመጥ አስማትን የኋላ ቀሩ የሰው ልጅ ማሳያ አድርገው ያቀርቡታል።





ሲግመን ፍሩድ አስማትን ከስነ ልቡና ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው አስረድቷል። አስማትን የሰው ልጅ ፅኑዕ ተምኔት ውጤት አድርጎ ያቀርበዋል። አስማት የሰው ልጅ የምኞት ውጤት እንደሆነ በማስረዳት ፈቃዱን ለመፈፀም ሲል መሠረት የሌላቸውን ነገሮች በሀሳቡ የሚስማበትና የሚያይበት መሣሪያ ነው ሲል ይከራከራል።

ይሁን እንጂ፣ በጥንቱ እና በመካከለኛው ዘመን የታሪክ ፀሐፍት፣ አንዳንዴ ከሰይጣን አሠራር ጋር አንዳንዴም ከሰው ልጅ የአእምሮ እድገት ጋር እየተያያዘ ሲገለፅ የኖረው የአስማት ጥበብ፣ በጥቅሉ ሶስት ዋና ዋና ክፍሎችን ይዟል። ጥቁር አስማት፣ ነጭ አስማትና ተፈጥሯዊ አስማት በሚል ተከፍሎ ይታያል።

ጥቁር አስማት ተብሎ የሚታወቀው፣ ልዕለ ተፈጥሯዊዉን ኃይል ለጎጂ ተግባራት አገልግሎት እንዲውል የሚያደርገው ክህሎት ነው። ፓራሳይኮሎጂስቶች ይህንን የአስማት ጥበብ ከግለሰብ እስከ ሀገር ድረስ በህይወትና በንብረት ላይ ከሚደረግ ጉዳት ጋር ያይዙታል። በምዕራቡ ዓለም ሙሴ እንደፃፈው ባይረጋገጥም፣ "የሙሴ መፅሐፍ" የሚባል የድግምት መጥቁል አለ። ሙሴ የአስማት ጥበብ ችሎታ እንደነበረው በመግለፅ መፅሐፉ ገብቶት የተጠቀመ ሰው ሉሲፈርን አስሮ የፈለገውን ሊያሠራው እንደሚችል ለማሳመን ይሞክራሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥም ከዚህ ሊመደቡ የሚችሉ፣ እንደርቢ፣ አፍዝ አደንግዝ፣ ጥላ ወጊ፣ ምስሐበ ንዋይ የተባሉ ጥቋቁር አስማቶች እንዳሉ ይታመናል። እንደርቢ ወርዶባቸው በማያዩት መንፈስ ቤታቸው ላይ ድንጋይ ወርዶ ጣራቸው የደቀቀባቸውና የቤት እቃቸው ሁሉ

ዱቂት የሆነባቸው፣ ሰዎች አስማተኞች እንዲያቆሙላቸው ድንጋይ ተሸክመው እንደስመኑ እንደርቡን ሆነው የቀረቡ ማስረጃዎች አሉ:: በረድ የሚያዘንቡ፣ ተባይ የሚያዘንቡ አስማተኞች እንዳሉ ይነገራል:: አውደ ነገሥትና ሐተታ መናፍስት የተባሉ የታተሙ መፃህፍት ቢኖሩም፣ አደገኛው የአስማት ጥበብ የተከተበባቸው መፃህፍት ግን በብራና ተፅፈው በጥቂት ሰዎች እጆች ላይ ብቻ እንደሚገኙ ይታመናል::

ሁለተኛው የአስማት ክፍል "ነጭ አስማት" የሚባለውና ልዕለ ተፈጥሯዊዉን ኃይል ለበጎ ተግባር የማዋል ጥበብ ነው:: የጥቁር አስማት ተቃራኒ ነው:: በኢትዮጵያ ለዚህ ዋቢ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ አስማቶች እንዳሉ ይታወቃል:: መፍትሔ ሥራይ፣ አቃቤ ርዕስ፣ ሌባ ገትር፣ ዘኢያገድፍ (መስተፋቅር?) ወዘተረፈ በዚህ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ናቸው::

ሶስተኛው የአስማት ክፍል በዘመናዊ አጥንኚዎች ዘንድ "ተፈጥራዊ አስማት" በመባል ይታወቃል:: ከአስማተኞች ልዩ ተፈጥሯዊ ችሎታ ጋር ይያያዛል:: ከተመስጦ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ሲኖረው የሳይኪክ ጥበብን ይጠይቃል::

በሣይኪክ ጥበብ፣ በቁስ አካሉች ላይ በመመስጥ ብረቶችን ማጣመም፣ እቃዎችን አየር ላይ ማንሳፈፍ፣ የሚበሩ ነገሮችን ቀጥ ማድረግ ወዘተርፈ በዚህ ክፍል የሚመደቡ ናቸው:: በሀገራችን ከዚህ ክፍል የሚመደቡ "መሰውርን" የመሳሰሉ ጥበቦች እንዳሉ ይታወቃል:: ግዑዙን አካል ከዓይን እይታ መሰወር ወይም ቦታ ቀይሮ እንዲገኝ የሚያደርግ ኃይል የመጠቀም ጥበብ ነው:: ግድግዳ ሳይከለክለው የሚያልፍ፣ በውሃ ላይ የሚራመድ፣ ናቡከደነፆር በእቶን ውስጥ እንዳስጣላቸው ሲድራቅ





ሚሳቅና አብደናጎ በእሳት ውስጥ የሚመላለስ የሳይኪክ ጠቢብ በእኛም ሀገር እንደነበርና አሁንም እንዳለ የሚገልፁ አሉ::

የተፈጥሮ አስማት (ናቹራል ማጂክ) እየተባለ በምሁራን ዘንድ የሚታወቀው ይህ የሣይኪክ ጥበብ፣ ለፈውስም ያገለግላል:: በምሁራኑ ዘንድ ይህ ጥበብ ለህክምና ሲውል "ፖዚያኪስማቲክ" እየተባለ ይጠራል:: የፈውስ ሥርዓቱ በእይታ ብቻ ወይም የተመረጡ ቁሶችን በበሽተኛው ላይ በማስቀመጥ ይከናወናል::....

"ኸረ ለመሆኑ የሣይኪክ ጥበብ ምንድን ነው? ይህኛው ጥቂት የተሻለ ይመስለኛል" አለች አያን ስለ አስማት ለሰዓታት ያዘነበከባትን ገለፃ ባለመስልቼት አዳምጣ ስታበቃ::

"ሳይኪክ ማለት የሰው ልጅ ካሉት አምስት የስሜት ህዋሳት ሌላ በረቂቅ ሁኔታ ካልታወቀ ኃይል፣ ክህሎት የሚቀበል ሰው ማለት ነው::" ስል ትንታኔዬን ቀጠልኩላት:: "ሣይኪክ ኃይል ያለው ሰው በሌላ ሰው አእምሮ ውስጥ የሚመላሰውን ሀሳብ ልክ እንደተገለጠ መፅሐፍ ማንበብ ይችላል:: በሌለበት ቦታ የሚከናወኑ ድርጊቶችን አድማስ በማይገድበው ዓይኑ መመልከት ይችላል:: ወደፊት ስላለው ጊዜም መተንበይ ይችላል:: ባጠቃላይ ሣይኪክ ማለት የስውር እውቀት ባለቤት የሆነ ሰው ማለት ነው:: ለምሳሌ በሃገራችን እንደ ሼህ ሁሴን ጅብሪል አይነት ሰዎችና ሌሎችም አሁን እስካለንበት ያለውን ዘመን ጥንቅቅ አድርገው ተንብየዋል:: የወደፊቱንም ተንብየዋል:: ይህ አንዱ ማረጋገጫ ነው::"

አያን ሌላም አያሌ ጥያቄዎችን አንስታ ነበር::

"ጊዜ የለንም!" አልኳት አንገታችን የሚቀላበት ጊዜ ዳናው እየቀረበ የመጣብኝ ያህል እየተጨነቅሁ።

"መለወጥ ባንችልስ? ማለቴ ድመት መሆን ባንችልስ? ድመት ከሆንን በኋላ እንደገና ሰው መሆን ባንችልስ?"

አሁንም ሌላ የጥያቄ መዓት አዥጎደጎደችብኝ።





# ፳፩

አያን በነገርኳት አስፈሪ ታሪክ ስትርበተበት ቆየች።

"የጥብቅ ጥያቄ መልሱም ጥብቅ ነው" አልኳት መደንገጧ እያስገረመኝ።

"እስካሁን ያስረዳኸኝ ስለ አስማት ነው" አለች በሚሰባበር ድምፅ። "በአስማት ወደሌላ ፍጡርነት ስለመለወጥ ግን አልነገርከኝም።"

"ልብ አላልሽኝም እንጂ ነግሬሻለሁ። የአሮን በትር ወደ እባብነት መለወጧን መፅሐፍ ቅዱስን አጣቅሼ ነግሬሽ ነበር። ‹ከሰዎች ተለይተህ ትሰደዳለህ፤ መኖሪያህም ከምድር አራዊት ጋር ይሆናል፤ እንደ በሬም ሣር ትበላ ዘንድ ትገደዳለህ› የተባለው ናቡከነፆር፣ ጠጉሩ እንደ ንስር ጥፍሩ እንደ ወፍ እስኪረዝም የምድረ በዳ አውሬ ሆኗል። እንደ በሬም ሣር ግጧል። በግሪክ ሚቶሎጂ ውስጥም አያሌ ወደ ሌላ ፍጡርነት የመለጥ ትረካዎች አሉ። አንዱን ለምሳሌ ልጥቀስልሽ።" አልኳትና ለማዳመጥ ዝግጁ መሆኗን ለመገንዘብ ለጥቂት ሰከንዶች ዝም አልኳት።

"ይገርማል!... እሺ ቀጥል።"

"በግሪክ ሚቶሎጂ ውስጥ ...የመንገደኞች ጠባቂ የሚባለው የሐሜስ ዘመን ትንግርት ነው። አባቱ

የአማልክት አባት ዜውስ ይባላል፡፡ እናቱ ኤራ ትባላለች፡፡ ነገር ግን ዜውስ፣ ኢዮ የምትባል ሴት በሚስቱ ላይ ይወሽምባታል፡፡ ኤራ በንዴት አብዳ ወደ ኢዮ ትሄድና በረቂቅ ጥበቧ ወደ ላም ትለውጣታለች፡፡ በዚህ አላበቃችም፣ ለአርጎ መቶ ዓይኖች ትሰጠውና እንዲጠብቃት ታዘዋለች፡፡

"አርጎ ሲተኛ እንኳ አምሳወቹ አይኖቹ ሲከደኑ ሃምሳዎቹ ቁልጭ ቁልጭ ይሉ ነበር፡፡ ዜውስ ይህን ይሰማና ሐሜስ አርጎን ገድሎ ወደ ላም የተለወጠችው ኢዮን ነፃ እንዲያወጣት ያዝዘዋል፡፡ ሐሜስ ወደ አርጎ ሄዶ ለመግደል ሲጠባበቅ አርጎ ባለመቶ ዓይን በመሆኑ በሃምሳው ሲያንቀላፋ በሃምሳው እየነቃ ያስቸግረዋል፡፡ አንድ መላ መጣለት፡፡ ጥዑም የሆነ የሙዚቃ ቃና እያጫወተው ሁሉም ዓይኖቹ እንዲከደኑ ያደርገውና በድንጋይ ቀጥቅጦ ይገድለዋል፡፡"

"ኢዮን አስፈታት?" አለች አያን፡፡ "ከላምነት ወደ ሰውነት እንደገና መለሳት?"

"በአፈ ታሪኩ መሠረት ሐሜስ ኢዮን አስፈትቷታል፡፡ ነገር ግን ከላምነት እንደ ገና ወደ ሰውነት እንደለወጣት የሚገልፅ ነገር አላነበብኩም፡፡"

"ይህን ነው መፍራት!...." አለች አያን እየተርበተበተች፡፡ "ድመት አድርገህ ልታስቀረኝ ሃሳብ አለህ ማለት ነው፡፡ አልሞክረውም፡፡"

"ወደ ድመትነት መለወጥ እንደምትችይ ግን አምነሻል ማለት ነው፡፡"





"ሰው ሆኖ ሰው መሆን ባልተቻለበት ዘመን፣ እንዴት አውሬ ሆኖ ሰው መሆን እንደሚቻል ልታስረዳኝ ትሞክራለህ?! እ?!... ደፋር! "

"ሰው መሆን እንጂ አውሬ መሆን ቀላል ነው፡፡ ትክክል ነሽ፡፡ ወደፊት ተስፋ ያለው ሰው ግን ክፉ ቀኑን ከሰውነት ክብር በታች ሊያስቀምጠው ይችላል፡፡ እያልኩሽ ያለሁት ይህንን ነው፡፡ እኔ በአንድ ወቅት ውሻ ነበርኩ፡፡ ሰው ለመሆን የበላሁትን አሳር አውቀዋለሁ፡፡ ተስፋ ብቆርጥ ኖሮ ውሻ ሆኜ እሞት ነበር፡፡ አሁን ሰው ነኝ፡፡ ነገር ግን በየትኛው ሰከንድ አንገቴ እንደሚቀላ አላውቅም፡፡ ወደ በድንነት ከመለወጤ በፊት ወደ አውሬነት ተለውጬ ህይወቴን ባቆያት እመርጣለሁ፡፡ አንዳች ጥረት ሳናደርግ እንዴት ህይወታችን ታከትማለች?"

"እሺ..." አለች አያን ሳቋ እያፈናት፡፡ ይሄ ነው የሚገርመኝ ጠባይዋ፡፡ በዚህ ጭንቅ ጊዜ ሳቋ ከየት ነው የሚፈልቅ?

"ምን ያስቅሻል?"

"ላብድ ነው መሰለኝ፡፡ ጭንቅላቴ ዞረብኝ፡፡ ድመት ሆኜ... ጅራቴን ስቆላ፣ ስናዝር፣ አይጥ ሳሯሩጥ... በአእምሮዬ ስስለው አጥወለወለኝ፡፡ ...ኤክ! ...ውይ ውይ...! ድመት ከመሆን ውሻ መሆን ይሻላል፡፡ ድመት መሆን አልፈልግም፡፡"

"እኔ ደግሞ ውሻ መሆን አልፈልግም፡፡"

“ለምን?!.. .እባክህ ውሻ ብንሆን ይሻላል! …ውሻ ብንሆን ከዚህ ቀደም ሆነህ ስለምታውቅ እንደገና ወደ ሰውነት ለመለወጥ አንቸገርም። በዛ ላይ… ‘ድመት አልወድም’ ብዬ ሺህ ጊዜ ነግሬሃለሁ።”

“ሁልጊዜም የወደድሽውን መሆን አትችይም።”

“ድመት ሆነን ብንቀርስ እሺ?!”

“ይልቁንስ አስማቱን ማጥናት ጀምሪ!”

“ፈራሁ።… የልቤ ምት አይሰማህም? ዋሻውን ሊንደው ደርሷል እኮ። ተንፈቃ ተጠጋችኝና ደረቴ ላይ ተለጠፈችብኝ።

እንደወደደችኝ አውቄባታለሁ። እንደወደድኩዋት አውቃብኝ ይሆን? … ከዓመታት በኋላ ልቤ የፍቅር ደም ሲረጭ ታወቀኝ። ወደ እውሬነት ከመለወጣችን በፊት ትኩስ የሰው ከንፈሯን ግመጠው ግመጠው አለኝ። ቀደመችኝ።





# ፳፫

አስማቱን አለማምዳት ጀመር። አያን እየተኮላተፈች የአስማቱን ቃላት ትጠራና መልሳ አሻፈረኝ ትላለች። በመሃል ደግሞ ያችን ሳቋን ታመጣለች።

“ውሻ ብንሆን ይሻላል” ትላለች።

“ስሚኝ!… ያለነው ኦጋዴን ውስጥ ነው። ዘጠና ዘጠኝ በመቶ የአካባቢው ህዝብ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ነው።”

“ቢሆንስ…”

“ውሻ ነጃሳ መሆኑን አታውቂም ማለት ነው?”

“ነው! አዎ በእስልምና ሃይማኖት መሠረት ውሻ ነጃሳ ነው።”

“ውሾች ሆነን ኦጋዴንን ስናቋርጥ ከስንት ቅዝምዝም ማምለጥ እንዳለብን ገባሽ? አንዱ በደቦል ድንጋይ ወግሮ ቢገድለንስ?”

“ድ…. ድመት ብንሆንስ ምንም ችግር እንደ ማያጋጥመን በምን እርግጠኛ ሆንህ?….”

"ሰው ሆነንም እኮ ችግር አጋጥሞናል። ድመት ብንሆን ችግር አይገጥመንም ማለቴ አይደለም። አውሬ መሆን በራሱ ችግር ነው። ውሻ ከመሆን ግን ድመት መሆን ችግሩን ይቀንሰዋል። በቀላሉ ለመሽሎክሎክም የድመት መጠን አነስተኛ በመሆኑ ከጠላት ለመደበቅ ያመቻል።"

ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ እንደገና የአስማት ጥናቱን ትቀጥላለች። ትኮላተፋለች። ትስቃለች። ትቀጥላለች።

"...ኢኮስ፣ ኮሞስ፣ አዝዮስ
ፓፓር፣ አንበር፣ ፓፓር
ሙራኤል፣ ሙራኤል፣ ሙራኤል
አግዮስ፣ አግዮስ፣ አግዮስ፣
ዶርጋሞን፣ ዶርጋሞን፣ ዶርጋሞን
ሄሴሜት፣ ካዮን፣
ሄሴሜት፣ ፔጋሉን፣
ሄሴሜት፣ ኡራዮን
ጅምጀርታን፣ ጅምጀርታን፣ጅምጀርታን፣
አፍዛሪዎን፣ አፍዛሪዎን፣ አፍዛሪዎን፣
አውቃስ፣ አውቃስ፣ አውቃስ፣
መሲፌልጠን፣ መሲፌልጠን፣ መሲፌልጠን፣
አፅቢን፣ አፅቢን፣ አፅቢን፣
ሻላክሮስ፣ ሻላክሮስ፣ ሻላክሮስ፣
አናስዮስ፣ አናስዮስ፣ አናስዮስ፣
ፓፓሮስ፣ ፓፓሮስ፣ ፓፓሮስ፣
ሄኖኤል፣ ሄኖኤል፣ ሄኖኤል
ሸድቃኤል፣ ሸድቃኤል፣ ሸድቃኤል፣
ጀማጅኤል፣ ጀማጅኤል፣ ጀማጅኤል፣
ኢኮስ፣ ካማስ፣ አክዮስ፣
ኢላማዋጢነኪን፣ኢላማዋጢነኪን፣





አያን፣ አስማቱን በደጋገመችው ቁጥር መንዘፍዘፍ ጀመረች።

"ፈራሁ... ፈራሁ... ፈራሁ... ልቤን ንካው!" አለች ድምፅዋ እየተቆራረጠ።

"እጇ መታሰሩን ረሳሽ?... ሰው ሆነን ታስረናል። አውሬ ሆነን ነፃ እንወጣለን። ....አናስዮስ አናስዮስ አናስዮስ አጥኚው!" ባረኩባት። "ፓፓሮስ! ፓፓሮስ፣ ፓፓሮስ፣ አካስ፣ ዝያስ፣ አክያስ ድገሚው!... አዛሪምስ! አዛሪምስ! አዛሪምስ! ጠበቅ አድርገሽ በይው! ... ሰው ሆነን ታስረናል፤ አውሬ ሆነን ነፃ እንወጣለን። ...ፓራሜስ! ታራሜስ! ሓራሜስ" ሳላስበው እየጮኩ ነበር።

'እሷን ሳልለውጣት ራሴ ልለወጥ ነው እንዴ?!... አይደረግም! አይሆንም!'

# ጃጄ

ከውጪ የብዙ ሰው ኮቴ ይሰማል፡፡ ሊቀሉን እየመጡ መሆን አለበት፡፡ አክትሞልናል፡፡ ለአያን አስማቱን ለማስጠናት ካለኝ ጉጉት የተነሳ ከጫፍ ጫፍ ደገምኩት፡፡ አያንም በሂደትና በድግግሞሽ ረቂቆቹን ቃላት ታንበለብላቸው ጀምራለች፡፡ መርበትበቷ ግን እያየለ መጥቷል፡፡

ለአያን መለወጥ ያለኝ ጉጉት እየጨመረ ከመምጣቱ የተነሳ አስማቱን በከፍተኛ ተመስጦ ሙሉውን መድገሜ ትክክል አልነበረም፡፡ ትቻት ላለመለወጥ ታገልኩ፡፡

'አይደረግም!'

አስማቱን ከመጨረሴ ዋሻው ይንቀጠቀጥ ጀመር፡፡ ንውፅውፅታ …እሳተ ገሞራ ይንጠው ይመስል ታስረን የተጣልንበት ዋሻ ድብልቅልቁ ወጣ፡፡ ከውጭ የብዙዎቹ ሰዎች ርምጃ ይበልጥ እየቀረበ ሲመጣ ይሰማኛል፡፡ የተፈጠረውን ትንግርት ለማዬት ይሁን ወይም ሊቀሉን ወስነውብን እንደሆነ ባላውቅም ወንበዴዎቹ እየመጡ እንደሆነ ግን እርግጠኛ ነኝ፡፡





"ፍጠኚ! ድገሚው!... አያን!.." ደነፋሁባት፡፡ "...ሻላሮስ፣ ሻላሮስ፣ ሻላሮስ... አናስዮስ፣ አናስዮስ፣ አናስዮስ፣ ጀማጅኤል፣ ጀማጅኤል፣ ጀማጅኤል፣ ኢኮስ፣ ካማስ፣ አክዮስ!...."

ከዚህ በኋላ የተፈጠረውን ሳላውቅ ከአካሌና ከመንፈሴ ተለያዩሁ፡፡ በማላውቀው ቅዥብርብር ባለ ዓለም ውስጥ ራሴን አገኘሁት፡፡ ብዙ አይነት ህብረ ቀለማት ያላቸው የብርሃን ጨረሮች ብቻ ናቸው የሚታዩኝ፡፡ ቀጥሎ... ከዚህ ቀደም የማላውቃቸው ፍጡራን ይታዩኝ ጀመር፡፡ በልጅነቴ በቤተ መቅደስ ላይ ተስሎ ያየሁት ሶበድአት አይነት እንስሳ ያለበት ዓለም ውስጥ ያለሁ መሰለኝ፡፡

ሶበድአት ከወገቡ በላይ የሰው አካላዊ ቅርፅ ሲኖረው ከወገቡ በታች የእንስሳ ቅርፅ ያለው ቅጥ ያጣ ፍጡር ነው፡፡ ጅራቱ ምላሶቻቸው እንደ ጮለታ የረዘሙ እባቦች ናቸው፡፡ ይህ አይነት ፍጡር ያለበት ዓለም ውስጥ የገባሁ ይመስለኛል፡፡ መነሻ የሌለው እሳት ይጥመለመላል፡፡ ረጃጅሞቹን ተራሮች ሲዞር ቆዬና ወደ እኔ እየተጥመለመለ መጣ፡፡ ቁመቶቻቸው ከተራሮች ጫፍ ለመድረስ የቀረቡ ሰዎች፣ እሳቱን ለማምለጥ ወደ እኔ አቅጣጫ ሲሮጡ ተመለከትኩ፡፡ የእኔ አካላዊ ቅርፅ ባይታየኝም ይህን የሚመምዘገዘግ የእሳት ላንቃ ማምለጥ እንደማልችል በመገመት ተስፋ ቆርጬ ጠበቅኩት፡፡ እሳቱ ተውጀምጅሞ መጥቶ ከዋጠኝ በኋላ የማስታውሰው አንዳች ነገር አጣሁ፡፡

# ፳፫

ምን ያህል ጊዜ እንዳለፈ አላውቅም፡፡ ከድብልቅልቁ ዓለም ስነቃ ራሴን ያገኘሁት በከባድ አውሎ ነፋስ ውስጥ ነው፡፡ አካባቢው ሁሉ የምፅዓት ቀን የደረሰበት መስሏል፡፡ የጥይት ድምፅ ሁሉ ይሰማኛል፡፡ ምንም ነገር ለማዬት አልቻልኩም፡፡ የተፈጠረውን ነገር ሙሉ በሙሉ ለመገንዘብ በርካታ ደቂቃዎች የፈጀውን አውሎ ነፋስ መጠበቅ ነበረብኝ፡፡

እስከ ሰማዬ ሰማያት የሚጥመለመለው አውሎ ነፋስ አካባቢውን አተራምሶት ካለፈ በኋላ፣ ራሴን በአካለ ድመት አገኘሁት፡፡ የት ነው ያለሁት? ራሴን ጠየኩ፡፡

ከአያን ጋር በታሰርኩበት ኮረብታ ወገብ ላይ እንደሆንኩ ተገነዘብኩት፡፡ የወታደሮች ካምፕ የመሰለው ኮረብታ ከከባዱ አውሎ ነፋስ ተጠልለው ያመለጡት ወታደሮች ከወዲያ ወዲህ ይራወጣሉ፡፡ አሁንም ወታሮቹ የሆነ የአማፂ ቡድን አባላት ይሁኑ ወይም የኢትዮጵያ ጦር አባላት መለዬት አዳገተኝ፡፡ በካምፑ ውስጥ የተሰቀለ ሰንደቅ አላማ የለም፡፡

‹ከዋሻው እንዴት ወጣሁ?› ራሴን ጠየኩ፡፡ አካባቢውን እየቃኘሁ ራሴን መጠየቄን ቀጠልኩ፡፡ ወደ ኋላ



ዞሬ ስመለከት ታስረንበት የነበረው ይሁን ወይም ሌላ ዋሻ በሩ ክፍት ሆኖ ተመለከትኩ፡፡

'አያን የት ገባች? ሰቀሏት? በአውሎ ነፋሱ ውስጥ የሰማሁት የተኩስ ድምፅ አያንን የገደሉበት ጥይት ድምፅ ይሆን?' እንደ ሶብዬት ሠራሽ ሚሳዬል ተወንጭፌ ዋሻው ውስጥ ገባሁ፡፡

አያን በዋሻው ውስጥ የለችም፡፡

'እርሷም እንደኔ ወደ ድመት ተለውጣ ይሆን?' የዋሻው ግድግዳ አያንን ይተፋ ይመስል በሾሉት የድመት ጥፍሮቼ እየቧጨርኩ አጓራ ጀመር፡፡ ድምፄ ራሴን ሳይቀር አስደነገጠኝ፡፡

እንደገና ከዋሻው ተፈትልኬ ወጣሁና አካባቢውን እራወጥበት ጀመር፡፡ ከሩቅ ካለ የቆንጥር ጥላ ሥር እንደ አቦሸማኔ ክምችት ያሉ ወታደሮች ታዩኝ፡፡ እንደ አቦሸማኔ ተወንጭፌ ሄድኩ፡፡

በእግራቸው ሥር ተሹሎክሉኬ ገባሁ፡፡

‹ያንት ያለህ!›

እመሃላቸው ወፍራም ግንድ ተጋድሟል፡፡ በግንዱ ላይ ደግሞ የአያን አንገት አርፏል፡፡ የሚያብለጨልጭ ፋስ የያዘ ፈርጣማ ወንበዴ መፍለጫውን አንገቷ ላይ ለማሳረፍ ከፊት ለፊቷ ተንቆርጥጦ የሚያናዝዛት አለቃውን ትዕዛዝ በመጠባበቅ ላይ ነው፡፡

# ጿጿ

እያን ከሞት ጋር ተፋጣ ተመለከትኳት፡፡

‹አስማቱን ሞክሪው! አስማቱን ሞክሪው!› የድመት ቋንቋዬን ታውቅልኝ ይመስል ጥቁር ጅራቱን እያወነጨፍኩ ተንጨረጨርኩ፡፡ ዓይኖቼን ፍስጋ፣ የወንበዴ ጫማ እንዳይረግጠኝ እየተጠነቀኩ ከወዲያ ወዲህ ዛበርኩ፡፡

"የቲ ኖ ያሄዶው?" ከፊት ለፊቷ የተንቆረጠጠው ሰውዬ በጥያቄ ያጣድፋታል፡፡ እኔ እምጥ ልግባ ስምጥ ልግባ ባለመታወቄ ትተፋኝ ይመስል ወጥሮ ይዟታል፡፡ ፋሱ ካንገቷ በላይ ይብለጨለጫል፡፡

"አላውቅም!" አለች እያን እልህ እየተናነቃት፡፡ ከመት ጋር ተፋጣ እንኳን ፍርሃት የሚባል ነገር አይታይባትም፡፡ "የት እንደሄደ አላውቅም! ዓይኖቼ ታስረው ነበር፡፡ እንዴት አድርጌ የሄደበትን ላውቅ እችላለሁ? የዋሻውን በር የከፈታችሁት እናንተ ናችሁ፡፡"

"ማሬት ገባ ታዳ?!"
"አላውቅም!"
"ሲብሱ ታጋኝቷል! እዛው!"



እያን መልስ መስጠቷን አቆመች፡፡ ወደ ሌላ ፍጡር መለወጤን ሳትረዳ አልቀረችም፡፡

‹ሞክሪው! አስማቱን ሞክሪው!› በድመት ድምፄ ቃተትኩ፡፡ ድንገት ከእያን ዓይኖች ጋር የድመት ዓይኖቼ ተገናኙ፡፡ አፈጠጠችብኝ…

በዚሁ ቅፅበት እያን አስማቱን ታንበለብለው ጀመር፡፡ ወደ ድመት መለወጤ ገብቷታል ማለት ነው፡፡

"…ኢኮስ! ካሞስ! አዝዮስ!
ፓፓር! አንበር፣ ፓፓር!
ሙራኤል! ሙራኤል! ሙራኤል!
ጼርጋሞን! ጼርጋሞን! ጼርጋሞን!…" እያን ጮኸች፡፡ አስማቱን አልተሳሰተችም፡፡ ፈነጠዝኩ…

"ሚንዲኖ ሚታምራው?!" አለ ጠያቂዋ አስተርጓሚው ላይ ሳይቀር አፈጠጠ፡፡ "ሚን ኳንኳ ኖ?!"

ሁሉም በድንጋጤ እርስ በእርስ ከመተያየት በቀር መልስ የሰጠ የለም፡፡

"…ሄሴሜት! ካዩን!
ሄሴሜት! ፒጋሉን!
ሄሴሜት! ኡራዮን!…" እያን ቀጠለች፡፡ እስከ አሁን አንዳችም የሳተችው የአስማት ቃል የለም፡፡ ጅራቱ እስኪበጠስ ድረስ እያወናጨፍኩት ተቁነጠነጥኩ፡፡

"…ጅምጀርታን! ጀምጀርታን! ጀምጀርታን!
…እፍዛሪዎን! እፍዛሪዎን! እፍዛሪዎን!…"

በድንገተኛ አውሎ ነፋስ አካባቢው ተናወጠ፡፡ ማንም ማንንም ለማየት አልቻለም፡፡ የሚጅመለመለው አውሎ



t.me/BooksandYou

ነፋስ የአቧራ ምሶሶውን እስከ ሰማይ ተክሎ ይጥመለመል ጀመር፡፡ የቆንጥር ዛፎች ሾሃቸውን እስኪጥሉና እስኪነቃቀሉ ድረስ ምድሩ ቀውጢ ሆነ፡፡

ከአያሌ ደቂቃዎች በኋላ፣ ከባዱ አውሎ ነፋስ ሽቅብ ኮረብታውን ዞሮ ሄደ፡፡ ቀስ በቀስ አካባቢው ሲጠራ የወዳደቀው ወንበዴ ሁሉ አቧራውን እያራገፈና እያሳለ ከወዳደቀበት ተነሳ፡፡

እኔ ከአንድ ቋጥኝ ጥግ ተወሽቄ ሳበቃ፣ መሬቱን በጥፍሬ ሰፍቼ በመያዝ በከባዱ አውሎ ነፋስ ከመወሰድ አምልጫለሁ፡፡

ከተወሸቅኩበት ቋጥኝ ጥግ ወጥቼ አካባቢውን ቃኘሁ፡፡ አንዲት ነጭ ፀአዳ ድመት አቧራዋን እያራገፈች ብቅ አለች፡፡ ከፍተኛ ጩኸት ካሰማች በኋላ እያጉረመረመች ወደ እኔ መጣች፡፡ አያን ወደ ድመትነት ተለውጣ መሆን አለበት፡፡

ወንበዴው ሁሉ ግራ በመጋባት ይንጫጫ ጀመር፡፡ እንገቷ ሊቀላ የነበረችው አያን ከግንዱ ላይ የለችም፡፡ በግንዱ ጥግ ወድቆ የሚታየው ሰው እያለች ለብሳው የነበረው ልብሷ ነው፡፡

ነጯ ውርዬ ወደ እኔ እንደደረሰች በድመትኛ ተንጫጭተን ከኮረብታው ወገብ ቁልቁል ተፈተለክን፡፡





# ፳፱

ቁልቁል ኮረብታውን ተንደርድረን ወርደን ስናበቃ ከወንዙ ዳር ስንደርስ ድንገት ቀጥ አልን፡፡

በውሃው መስታውትነት ራሴን ተመለከትኩት፡፡ የኑግ ልጥልጥ የመሰልኩ ጥቁር ድመት ሆኛለሁ፡፡ አስፈሪ ጥልማሞት ድመት፡፡ ረጃጅሞቹ አንቴና የመሰሉት የአፌ ዳር ጢሞች ሳይቀሩ ጥቋቁር ናቸው -ጨለማ፡፡ የኦጋዴን ሰቆቃ ያጠለሸኝ ይመስል፣ ወደ ጥልማሞትነት ተለውጬ አርፌዋለሁ፡፡

ከጎኔ የቆመችው ነጯ ድመት አያን ምስልም በውሃው ውስጥ ብዥ ብዥ እያለ ይታየኛል፡፡ ሀጫ በረዶ የመሰለች ድመት ሆና ተለውጣለች- ወተት የመሰለች ድመት፡፡

ከሰውነት ክብር አውርዶ፣ ወደ አውሬነት የቀየረን ችግር፣ ወርዶ በማያልቀው ወንዝ ውስጥ ገብቶ ይፈስ ይመስል ያሳለፍነው መከራ ሁሉ አንድ በአንድ ተሳለብኝ፡፡ ሁሉንም ችግር አሰብኩት፡፡ የእኔን የግሌን ችግር፣ የኦጋዴንን ችግር፣ የሀገሬን ችግር… ከሰውነት በታች የጣለንን ሰቆቃ ሁሉ ሳስበው፣ "Rivers of Babylon" የሚለውን የቦኒን መዝሙር መሰል እንጉርጉሮ አዚም አዚም አለኝ፡፡

"By the rivers of Babylon, there
We sat down, yea we wept,
When we remembered Zion…"

በግዕዝ ቋንቋ ሳይቀር፣ በዳዊት መዝሙር ውስጥ ግጥሙን አውቀዋለሁ፡፡

"ውስተ አፍላገ ባቢሎን ህየ ነበርነ ወበከይነ
ሶቦ ተዘከርናሃ ለፅዮን እምነ...
...በባቢሎን ወንዞች ማዶ ተቀምጠን
ጽዮንን ብናስብ አምርረን አለቀስን፡፡"

ይህ ዜማ የሀገሬ ፍዳ ማሳያ ስለሆነው ለኦጋዴን የተዜመ ይመስለኛል፡፡

"ውስተ አፍላገ ዋቢ ህዬ ነበርነ ወበከይነ
ሶቦ ተዘከርናሃ ለኢትዮጵያ እምነ
ወለ ኦጋዴን ስቃይነ...

... በዋቢ ወንዝ ማዶ፣ ተቀምጠን ሳለን
ኢትዮጵያን ብናስብ፣ አምርረን አለቀስን
ኦጋዴን ቁስላችን፣ እጅግ ጠዘጠዘን"

የሰው ሥጋ ለምደው ህጻናትን ወደበሉት ድመትነት የለወጠንን ፈተና የሚገልፀውን ግጥም ማዜም ብንችል እንዴት ጥሩ ነበር? በኩሩን ወደሚበላው ድመት የለወጠን የሀገራችን ችግር እንደ ባቢሎን ግንብ የሚናድበት ቀን መቼ ነው?

እኔና አያን ከእንግዴህ በአካለ ድመት ውስጥ የታፈንን ፍጡራን ነን፡፡ በኩሩን ወደ ሚበላ ድመትነት ያስለወጠን ችግራችን መቼ አብቅቶ ወደ ሰውነት እንደምንለወጥ ማሰብ የጀመርነው ገና ከአሁኑ ነው፡፡ አውሬ መሆን ቀላል ነው- ሰው መሆን ግን አሳር ነው፡፡ በምን እንደተግባባን ሳይገባን እርስ በእርስ ተያየን፡፡





# ፴

ሰው የሆንኩት ሰው ምን እንደሆነ ሳላውቅ ነው፡፡ የሰው ልጅ አሁንም ድረስ ራሱን ፍለጋ ላይ ነው፡፡ ድመት መሆን ግን ራስን መሆንን አይጠይቅም፡፡ ድመት ሲፈጠር ያው ድመት ሆኖ ነው የተፈጠረው፡፡ ሰው ግን ሙሉ ሰው ሆኖ አይፈጠርም፡፡ ሙሉ ሰው ለመሆን ወደ መጣበት እስኪመለስ ድረስ ይታትራል፡፡ ይህም ሆኖ ሙሉ ሰው ሆኖ የተቀበረ የለም፡ ድመት ወደ ዚህ ምድር ሲመጣ ግን ሙሉ ድመት ሆኖ ነው የሚመጣው፡፡ ሲሄድም ድመትነቱን ጠብቆ ነው፡፡ የሰው ልጅ እንደሰው መጥቶ እንደ እንስሳ ኖሮ ወደመጣበት ሊመለስ ይችላል፡፡ እንዲያውም የብዙ ሰዎች እጣ ፈንታ ሰው ሆኖ መጥቶ እንደ እንስሳ ታይቶ ማለፍ ሆኗል፡፡

ድመት ስለሆንኩ ብዙም ስለድመት ማወቅ አይጠበቅብኝም ነበር፡፡ ስለ ድመት ለማወቅ ጉጉት ያደረብኝ የሰውነት አመሌ ገፋፍቶኝ ነው፡፡ ሆኖም ድመትን የማውቃት ውሻ እያለሁ ነው፡፡ የሴቶች ጠባይ ወኪል ነበረች- ድመት፡፡ እያለሁ ሰው እያለሁ አምርሬ ሴቶችን በመጥላቴ ምክንያት ወደ ውሻነት የተለወጥኩ ስሞን በድመት መስያቼው ድመት መስለው ይታዩኝ ነበር፡፡ ድመት ወተት ካሳያት ከማንም ጭን ላይ ፊጥ

እንደምትል ሴትም ካለው ጋር መንከውከው ጠባይዋ ነው- እልነበር፤ ውሸ እያለሁ፡፡ ሁሉንም ሴት ጨፍልቆ በድመት መመሰል ግን ትክክል አልነበረም፡፡ ሁሉንም ወንድ ጨፍልቆ በውሻ መመሰልም አይቻልም፡፡ እንደ ድመት ባዬበት ጅራቱን የሚቆላ ወንድም ሞልቷል፡፡ ዓለማችን በሰው ኑባሬ ውስጥ ያለን ሰው ጠባዩን ያውሬ እንዲያደርግ ትገፋፋለች፡፡ ከዚህ አዙሪት ራሳቸውን ጠብቀው ለመኖር የታደሉት እጅግ ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡

ወደ ድመትነት የሚለውጠውን አስማት ባጠናሁበት ወቅት እንደገና ወደ ሰውነት የሚመልሰውን ድግምት ያላጠናሁት አንድ ቀን ድመት እሆናለሁ ብዬ አስቤ ስለማላውቅ ነው፡፡ ሰው ሆኖ ተፈጥሮ ሳለ ድንገት ወደ አውሬነት የሚቀይር ሁናቴ የገጠመው ሰው ሞልቷል፡፡ ይሆን እንጂ ከአውሬነቱ አምልጦ ወደ ሰውነቱ ለመመለስ አይሞክርም፤ በአራዊት መንጋ ውስጥ ሰው ሆኖ ለመገኘት መሞከር ትርፉ መበላት እንደሆነ ስለሚገባው፣ የነገደ አራዊት ኑባሬውን ይቀጥላል፡፡ የሚያፈነግጡትና ከኑባሬ አራዊት የሚያመልጡት እጅግ በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው፡፡

ስለ ድመት የማውቀው እጅግ ጥቂት ነው፡፡ ይህንኑም ጥቂት እውቀት የቀሰምኩት ሰው ሳለሁ ወደ ድመትነት የሚቀይረውን አስማት ባጠናሁበት ወቅት ነው፡፡ በዛ ወቅት ወደ ድመትነት አለመለወጤ እድለኛነቴን ያሳያል፡፡ ቢሆንም እንደ ገና ወደ ሰው የሚለውጠው ጥቅል እጄ ላይ ነበር፡፡ እሱን ለማጥናት ያልሞከርኩት ሰው ሆኜ ለመቀጠል እድልና ጊዜ እንዳለኝ በመገመቴ





ነበር፡፡ ትክክል አልነበርኩም፡፡ ዛሬ እንጂ ነገ በእጄ አለመሆኑን ተረድቻለሁ፡፡

አሁን ከድመትነቴ ወደ ሰውነቴ የሚመልሰኝ አስማት የሚገኘው በመቶ የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን ርቆ ነው- አዲስ አበባ፡፡ ከኦጋዴን አዲስ አበባ ድረስ በድመትነቴ የመቀጠል ግዴታ አለብኝ፡፡ በድመት ህላዌ፣ በድመት ኑባሬ፣ በድመት ቀኖና እና ደግማ ውድማ ለውድማ መዳከር ግዴታዬ ነው፡፡ ምግቤ እንጀራ በወጥ ሳይሆን የገደል አይጥ ነው፡፡ ጉዳይ ለማስፈፀም ቢሮ ለቢሮ መዳከሬ ቀርቶ፣ የዕለት እንጀራዬ በሹል ጥፍሬ ላይ ሆኗል፡፡ ጥፍሬ እስካለች ድረስ ደጅ መፅናት አይጠበቅብኝም፡፡ ቢሮዬ የኦጋዴን በረሃ ሆኗል፡፡ አለቃ የለኝም፡፡ ድመት ነኝ፡፡ አይጥም አይጥ ነው፡፡ አይጥ በመሆኑ ሊኮራ ይችላል፡፡ አይጥ ለመያዝ ምንም አይነት የብቃት ማረጋገጫ ማውጣት አያስፈልግም፡፡ የብቃት ማረጋገጫዎቼ በመዳፌ ላይ የተቆለመሙት የገዛ ጥፍሮቼ ናቸው፡፡ አድፍጨ የማለም መብቴን ከማንም አልጠይቅም፡፡ የማምለጥ መብቱ ደግሞ የአይጡ ነው - አቅም ካለው፡፡ ኬላ ላይ እንዲያዝ ስልክ አይደወልም፡፡

ከዚህ በኋላ ባልንጀራዬ ሴቷ ኤፍራታ ሳትሆን ድመቷ አያን ናት፡፡ ውርዬ የበረሃ ጓዴ፣ ነጭ ጅራቷን እንደ መኪና ዋይፐር እያወናወነች ካጠገቤ ቆማ ሽቅብ ወደ ተራራው እየተመለከተች ነው፡፡ የጉዞ መስመራችን እየነደፈች መሆን አለበት፡፡ ሰው እያለች የምታውቀው የኦጋዴን ምድር ድመት ሆና ሊጠፋባት አይችልም፡፡ ኧረ ለመሆኑ የት ነን? ወደ እርሷ ዞሬ ተቁለጨለጭኩ፡፡ አየችኝና ሽቅብ ወደ ዳገቱ ተፈተለከች፡፡

"ሚያው" እያልኩ ተከተልኳት፡፡

# ፴፩

የተራራውን ጫፍ ወጥተን እናቱ ላይ ቆምንና ቁልቁል ተመለከትን የኢላላ ኮረብታዎች የምድር ቡጉር መስለው ከታች ይታያሉ። የነዳጅ ፍለጋ የሚጧጧፍባቸው አካባቢዎች እነዚህ መሆናቸውን አያን ነገረችኝ። ውርዬ አያን የምታወራኝ በሰው ልጅ ቋንቋ አይደለም። እኔም ውሮ ዶክተር ዲዲሞስ ዶሬ የምረዳት በአፊ ሰብ ቋንቋ አይደለም። የምንጋባባው "በቴሌፓቲ" ነው። በውስጧ የሚመላለሰውን ሀሳብ ለማዎቅ የቻልኩት ወደ ድመት ከተለወጠችና ከተለወጥኩ በኋላ ነው። የሰው ልጅ በቋንቋው እንኳ አይግባባም፤ ሰው እያለሁ ይህን አውቃለሁ። የሰው ልጅ ተነጋግሮ፣ ተነታርኮ፣ ተከራክሮና ተነዛንዞ ሳይግባባ ይለያያል። አንዱ የአንዱን ሀሳብ አይረዳውም።

ምድር ላይ ያለው ቋንቋ መብዛት የሚያሳዬው ይህንኑ ነው። ሊቃውንት ቅዱስ መፅሐፍን አጣቅሰው ቋንቋ እንዴት እንደተቀያየረ ያስረዳሉ። በዘፍጥረት መፅሐፍ መሠረት ሲያብራሩት፣ ምድር ሁሉ ባንድ ቋንቋ ነበረች። ነገር ግን በሰናዖር ምድር የአዳም ልጆች ከተማ ይገነባሉ። ፈጣሪም እንደ ተፈታተኑት ሲያውቅ ይወርድና ቋንቋቸውን ይደባልቀዋል። በዚህም ምክንያት የሰናዖር ምድር ባቢሎን ተብሏል። ባቢሎን የመለያየት መገለጫ ሆነ- የመበታተን ፍቺ ሆነ። ባቢሎን፣ የመለያየቱ መንፈስ ሀገሬ ላይ ዛሬም ድረስ እየፈነጨባት ነው። ዘመናዊ ምሁራን ደግሞ የሰውን





ልጅ ቋንቋ መለያየት ከጂኦግራፊ መራራቅ ጋር ያያይዙታል።

ይሁን እንጂ የሰው ልጅ አሁንም ባቢሎን ውስጥ ነው- አንድ ቋንቋ እየተናገረም አይግባባም። ባልና ሚስት አንድ ላይ ተቃቅፈው ቋንቋቸው ለየቅል ነው- አልጋቸው ባቢሎን ነው። እኔና አያን ግን ለመግባባት ቋንቋ አያስፈልገንም። በቴሌፓቲ ሀሳቤን ልቅም አድርጋ ታውቀዋለች። እኔም እንደዛው።

"ቴሌፓቲ" ስድስተኛው የስሜት ህዋስ ነው። ይህ ፀጋ ለሰው ልጅ በሙሉ አልተሰጠም። እንኳን ስድስተኛውን ስሜት አምስቱን ህዋሳቱን እንኳ በትክክል የማይጠቀም ሰው ሞልቷል። የሰው ልጅ አካባቢውን ሁሉ በአምስቱ አካላዊ ህዋሳቱ ዳብሶ፣ ዳሶና ተጨላምሶ ለመረዳት ይሞክራል።

ስድስተኛው ስሜት ወይም ቴሌፓቲ ግን ከአምስቱ ህዋሳት ተግባር በላይ የሆነና ልዩ በሆነ ስውር ኃይል ሌላው አእምሮ ምን እያሰበ እንደሆነ የመረዳት ክህሎት ነው። ርቀት ሳይገድበው ያለምንም መሣሪያ የማየት ጥበብ ደግሞ "ክሊርቪውናንስ" ይባላል።

"የክሊርቪውናንስ" ችሎታ ያለው ፍጡር ከእርሱ በብዙ ሺህ ማይል ርቆ ያለን ድርጊት በዓይኖቹ ያዬ በጆሮው የሰማ ያህል ይረዳዋል። ይህ ችሎታ ያላቸው ሰዎች በምድር ላይ ተከስተው እንደነበር ፓራሳይኮሎጂስቶች በጥናት ደርሰውበታል። በትንሹም ቢሆን ይህ ተሰጥኦ በእጅጉ በሚዋደዱና በሚፋቀሩ ሰዎች መካከል መኖሩ ተደርሶበታል። ንፁህ ፍቅር ያላቸው ሰዎች ሳይነጋገሩ ይግባባሉ። በተለያዬ ቦታ ሆነው እንኳ ማን ምን እያደረገ

እንደሆነች ችግር ደርሶበት እንደሆነ ህሊና ተብሎ በሚገለፀው አካላቸው ላይ በግዘፍ የማይገኝ አካላቸው ይረዱታል። በእናትና በልጅ መካከልም ይህ ስሜት እንዳለ ተደርሶበታል።

ይህ የሚያሳየው ግርግርና ኳኳታ ባንኮታኮተው ዓለም ውስጥ የጠፋው የሰው ልጅ ብዙ ያልተጠቀመባቸው ችሎታዎች እንደነበሩት ነው። አሁን ግን እንኳን ስድስተኛ ህዋሱን ይቅርና አምስቱን ህዋሳቱን እንኳ መጠቀም የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱ በግልፅ የሚታይ ነው። በተመስጦ ውስጥ ያሉ በየገዳሙ ያሉ አባቶች፣ "ይህ ታይቶኛል፤ እንዲህ ሊሆን ነው" እያሉ የሚናገሩት በቅዠት ተተርጎሞባቸዋል። ወይም እፀ ሰጠጢራ ነፍተው ነው ሊባሉም ይችላሉ- ሀሽሾሞች።

እኔና ውርዬ ግን ሀሽሽም ሆነ ስጠጢራ ሰንነፋ ይኸው እየተግባባን ነው። ሳንነጋገር እንግባባለን። አንድም ቃል ሳንለዋወጥ ሀሳቧን መረዳት ችያለሁ። እርሷም እንደዛው። ማን ያውቃል? ከሰው ልጅ በልጠንም ሊሆን ይችላል። ጦጣና ዝንጀሮን እንዳልሰለጠኑ የሚቆጥረው ስልጡን ነኝ ባይ ፍጡር ጦጣና ዝንጀሮ እየሳቀበት መሆኑን ቢረዳ ኖሮ በራሱ ያፍር ነበር።

ሽለቆዎችን እያቋረጥን፣ ኮረብቶችን እየወጣንና እየወረድን የነዳጅ ቁፋሮ ወደ ሚጧጧፍበት የኢላላ ምድር ስንጓዝ አንድ ሀሳብ በድመት አእምሮዬ ውስጥ ተሰነቀረ። በድንጋጤ ክው ብዬ ቆምኩ። ውርዬ እያንም ቀጥ አለች። የመጣብኝ ሀሳብ እርሷም ጋር ከመቅፅበት ነበር የደረሰው። አንዱ ድመት መንገድ ላይ አግኝቶ ቢያስረግዛትስ?

‹ያንት ያለህ!› በርሬ ሄጄ አጠገቧ ቆምኩ።





# ፴፪

ሰው እያለሁ ስለድመት ብዙ አለማምቁ ይበልጥ ስጋቱን ጨመረው። ሰው እያለሁ ይህ ወቅት የድመቶች የሥሪያ ወቅት ይሁን አይሁን አላውቅም። ጭራሽ ድመቶች የሥሪያ ወቅት ይኑራቸው አይኑራቸው አላውቅም።

ሰው እያለሁ ስለ ድመቶች ከማውቀው ውስጥ ከሰባ በላይ የድመት ዝርያ አይነት መኖሩ ይገኝበታል። የሰው አመሌ ገፋፍቶኝ ስለድመት ዘርና፣ እኔና እያንም ከየትኛው የድመት ዘር እንደምንመደብ አስብ ጀመር።

እንደሰው ልጅ አንዱ የድመት ዘር ከሌላው የድመት ዘር እበልጣለሁ የሚል እብሪት ይኑረው፣ ወይም አንሳለሁ የሚል የበታችነት ዝቅጠት ይኑርበት አላውቅም። ይሁን እንጂ ሁለቱም በሽታ ነው። እብሪት የኀበረው የበላይነት ስሜትንና፣ ዝቅጠት የቆፈረው የበታችነት ስሜትን ያህል ደዌ የለም። በሁለቱ መሃል ያለው መመሸለቅ የሰውን ልጅ ቁልቁል ሲገፋ የኖረ ሀቅ ነው። የበታቹም የበላይ የሆነ ጊዜ በቀሉ አይቻልም። በድመትስ እንዲህ አይነት የዘር ዛር ይኖር ይሆን?

.... ከድመት መንጋ ውስጥ ካልተቀላቀልኩ በቀር ይህን ጉዳይ ሳውቅ አልችልም፡፡ መሆን የማዎቅ ማህለቅ ነው፡፡ ሰው እያለሁ፣ ፌሊስ ካተስ ተብለው የተለዩት የቤት ድመቶች፣ ከሌሎች ፌሊንስ ተብለው ከሚጠሩት ነገዶቻቸው የሚለዩት ከሰው ልጅ በቀላሉ መላመዳቸው ብቻ ይመስለኝ ነበር፡፡ የሰው ልጅ ፀረ አይጥ መሣሪያዎቹ አድርጎ በወጥመድና በመርዝ ፋንታ ይጠቀማቸዋል፡፡

ድመቶች የተሻለ የማሽተት አቅምና ዝቅተኛ የሆነ ቀለምን የመለየት ችሎታ አላቸው (ይቅርታ አለን)፡፡ ድመት ከሆንኩ በኋላ እንደሰው ማሰቤን ማቆም አለብኝ፡፡ ከሆኑ ወዲያ ሆኑ ነው፡፡ "ሚያው" የሚለው ቋንቋችን በተለያዩ ድምፀት እልፍ ትርጉም አለው፡፡ ከፍተኛ የሆነ የ"ፐርጅ" ችሎታ አለን- ተቀናቃኝን አሳዶ ቅታውን የማጥፋት ኃይል፡፡ ይህን የድመቶችን ችሎታ ሳስብ ድንጋጤ ወረረኝ፡፡

ዘራቸውን የበረዘውን የሰው ነፍስ፣ ከገባንበት የድመት አካል ለማባረር ከፍተኛ የሆነ የ"ፐርጅ" አዋጅ ሊያዉጁብን ይችላሉ፡፡ ምናልባት እኛ በአካለ ድመት ውስጥ የገባን ርኩሳን-መናፍስት ልንመስላቸው ይችላል፡፡ ...መጠንቀቅ ነው፡፡ ከድመት መንጋ መቀላቀል የለብንም፡፡

ድመቶች ከፍተኛ የማሽተት አቅማቸውን ተጠቅመው፣ የሰው ርኩስ መንፈስ ድመትነታቸውን ለማቆሸሽ እንደገባ ከተረዱ፣ የ"ፐርጁን" አዋጅ ለመላው የድመት ዘር ያውጃሉ- ልክ አንድ ገዢ ፓርቲ በተቃዋሚው ላይ የ "አሳደህ በለው" አዋጅ እንደ ሚያውጀው፡፡ የድመት ፐርጅ ደግሞ በጨበጣ ውጊያ ነው- እጅ በእጅ፡፡ እኛ እንደሆንን ልምዱ የለንም፡፡





የፐርጁ አዋጅ ሳይነገር አዲስ አበባ ገብተን ወደ ሰውነታችን መመለስ አለብን፡፡ የምናውቀው የሰው ልጅ "ፐርጅ" ይሻል ይሆናል፡፡

የሰው ልጅ ፐርጅ ሲታወጅ በስለላ ሞያ የተካኑ የሥርዓቱ ሰዎች መንደር ለመንደር አሰሳ ያካሂዳሉ፤ በየካፌው ያደፍጣሉ፤ አብረው ከተቃዋሚ ጋር ብርጭቆ ጨብጠው ካቲካላ ይጎነጫሉ፤ ወሬ ያውጣጣሉ፡፡ የሥርዓቱ ተቃዋሚ መሆኑን ካረጋገጡ ጀርባውን አጥንተው "ፐርጅ" ያውጁበታል -የአሳደህ በለው ፐርጅ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እስርቤቶችን ያጣበቡት እስረኞች ማንቆርቆሪያ የሰረቁ ሌቦች ብቻ ያልሆኑት ለዚህ ነው፡፡ የፐርጁ ሰለባ የሆኑት የፓለቲካ ሰዎች፣ ተቃዋሚዎች፣ ጋዜጠኞችና ደራስያን ናቸው፡፡

የድመት ፐርጅ (ፀርን የማጥፋት ዘመቻ) ከዚህ የሚለየው ፐርጅ የሚታወጅበት ድመት ያለበት ቦታ በቴሌፓቲ መታወቁ ነው፡፡ የዘመናችን ገዢዎች ግን ተቃራኒያቸውን የሚደርሱበት በቴሌኮምኒኬሽ በኩል ነው፡፡ ልዩነቱ ፍጥነቱ ብቻ ነው፡፡ ድመት ቴሌፓቲን ተጠቅሞ የጨበጣ ውጊያ ሲሰነዝርብህ፣ መንግሥት ቴሌኮምኒኬሽንን ተጠቅሞ ካለህበት ከች ይልና ከችክቾ ከርቼሌ ይልክሃል፡፡

እኔና ውርዬ አያን፣ ለረጅም ሰዓት ቆመን በዚህ ሀሳብ ከናወዝን በኋላ በጭንቀት ተወጥረን ማጉረምረም ጀመርን፡፡

"ኧረ ዝም በይ ይደርሱብናል!" አልኩ አያን በከፍተኛ ድምፅ ስታጉረመርም ጊዜ፡፡ "ናዘርሽ እንዴ?" ንግግራችን በቴሌፓቲ ቀጠለ፡፡

‹ወደናዘረች ድመትነት ተለውጣ ይሆን?› ስል በውስጤ ከማሰቤ ወዲያው ሀሳቤን ቀለብ አድርጋ፣

"እንጃልኝ!" አለች- አሁንም እየተቁነጠነጠች። "ለሥሪያ ወደ ደረሰች ድመትነት መሰለኝ የተቀየርኩት ለዛ መሰለኝ ድምጼ የጎረነነው!...."

እየናዘረች ከሆነ አንዱ የቴሌፓቲ መልእክቱ የደረሰው የዱር ድመት መጥቶ ሊሰራት ይችላል።

'ያንት ያለህ!'

በሁለቱ የፐርጅና የሥሪያ ስጋቶች ተወጥረን ሩጫችን እናስነካው ጀመር።





## ፴፫

በሁለቱ ሥጋቶች ተወጥረን ኢላላ ደረሰን። ኢላላ የነዳጅ ቁፋሮ የሚጧጧፍበት የኦጋዴን በረሃ ክፍል ነው። ቻይናዎች ከወዲያ ወዲህ ይራወጣሉ። ኢትዮጵያውያኑ የደረቁ ቅጠሎች መስለው ይንጠራወዛሉ። የቻይናዎቹን ጩኸት ከመጤፍ አይቆጥሩትም። አካባቢውን የኢትዮጵያ ጦር ነፍጡን ለጉሞ ይቆጣጠራል። ዱር ገደሉ መሣሪያ ባቀባበለ ወታደር ታጥሯል። ለወታደሩ እኔና እያን ተራ ድመቶች እንጂ ሰዎች አይደለንም።

ተሹለክልከን ወደ ብሎኮቹ ተጠጋን። ነዳጁ ወጥቷል ወይስ ዝም ብሎ ወሬ ብቻ ነው?... ከብሎክ ብሎክ በጥንቃቄ ተራወጥን። ሰዎች በዚህ አካባቢ የሚራመዱት በጥንቃቄ ነው። የተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ ስቦ በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው። የተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ ስቦ ሊያፈርጣቸው ይችላል። እኛም ወጉ ደርሶን ይሁን ወይም ሰው እንደነበርን ትዝ ብሎን የማናውቀው ሁኔታ ስንራመድ በጥንቃቄ ነው።

እዚህ ማንም ሰማይ ሰማይ አያይም። ለነገሩ የኦጋዴንን ሰማይ ማዬት አያስፈልግም፤ ዘወትር ያው ነው- ጥርት ያለ በድመት ምላስ የተሳለ ሳሃን የመሰለ ሰማይ። ኦጋዴን

ምድሩም ተመሳሳይ ነው- አሸዋና እሾህ። የቆንጥር፣ የእጣንና የሰው አጥንት እሾህ።

ኦጋዴን ምድሩና ሰማዩ ሳይሆን ከርሰ ምድሩ ነው ለምለም። እዚህ "አባባዬሁሽ" ሊዘፈን አይችልም- "ቆፍሬ አየሁሽ" የሚል ዘፈን ሊዘጋጅለት ይገባል። ኦጋዴን እንደ በለስ ላዩ እሾህ ውስጡ ወተት ነው። ኦጋዴን ላዩ ግለት ውስጡ ዘይት ነው። ኢላላ ደግሞ ብዙ "ቆፍሬ አየሁሽ" የተዘፈነባቸው ብሎኮች የተሠሩባት የነዳጅ ገደሎች ማህፀን ናት። አንዳንዶቹ በብዙ ጥረት ተቆፍረው ሲያበቁ፣ ክው ያሉ ተስፋ ቢስ ገደሎች ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ግን የተፈጥሮ ጋዝ አረፋ የሚደፍቁ ጉድጓዶች ናቸው።

የነዳጁ ጠበል የፈለቀላቸው ብሎኮች ሠራተኞችና "ቆፍሬ አየሁሽን" ዘፍነው አጨብጭበው የቀሩ ተስፈኞች፣ አረማመዳቸው እንኳ ለየቅል ነው። እኔና አያን ይህን እየታዘብን ከአንዱ ብሎክ ወደ ሌላው በመራመጥ፣ የሚበላ ነር ፍለጋ ኳተንን። ሰው ብንሆን ኖሮ ልናገኘው የማንችለውን ምስጢርም እስኪበቃን በመቃረም ላይ ነን። ብሎክ ስምንት ጥግ አንድ ወደል አይጥ ለጥቂት አመለጠን። ገና ልምድ አለማዳበራችን ብቻ ሳይሆን የሰው አእምሮአችን እንደ እርኩስ ስለቆጠረው ይሆናል አይጡ እንዲያመልጥ ያደረገው።

ቁጥሩን ወዳላወቅሁት ብሎክ ሄድንና ወደ መጠለያው ሥፍራ ገባን። ከምሳ በኋላ ነበር የደረስነው። ሠራተኞቹ በልተው ጨርሰው ያወራሉ። መሬቱን ቆፍረው ፍሪጅ ሠርተዋል። ከውስጡ በፕላስቲክ የታሸገ ውሃ እያወጡ ሲጠጡ ገረመን። ሙቀቱ በጃፓኒ ብቻ እንዲቀመጡ አስገድዷቸዋል።እርቃናቸውን አለመቀመጣቸውም የሰውነት ክብራቸው አስገድዷቸው ነው።



እኔና አያን የበሉባቸው ሰሀኖችን ማለስ ጀመርን። እንደ ድመት የላሷቸው ይመስል፣ ሰሃኖቻቸው እንደ ኦጋዴን ሰማይ ክው ያሉ ናቸው። ተስፋ ቆርጠን ልንመለስ ስንል የአንደኛው ወዛደር ወሬ ጆሮዎቻችን ቆንጥጦ አስቀረን። ስለ ነዳጅ ነው ወሬው።

እዚህ ወሬዉ ሁሉ ጋዝ ጋዝ ይሸታል። ከዚህ ቀደም ሰው ባንሆን ኖሮ ለድመቶቹ ለእኔና ለአያን፣ ከነዳጅ ድፍድፍ መገኘት ይልቅ ሰበር ዜና የሚሆንብን የሰባራ ገል ወተት ነበር።

"ይህ ነዳጅ የወጣ ቀን…" ሲል ነበር ወሬውን የጀመረው ወዛደሩ- በፕላስቲክ የታሸገ ውሃውን እንቆርቁሮ ሲያበቃ። "ፍጅት ነው መቼም… ፍጅት!"

"አታሟርት ባክህ!" አለው ሌላኛው እጁን አወናጭፎ ሲያበቃ። "…አንተ ሁልጊዜም የምታስበው ሁሉ አወንታዊ አይደለም። ምህረቱ ሳይሆን መዓቱ ነው ሚታይህ!"

"ምናለ በለኝ የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በእርሱ ባይባላ!"

"ዝም በል ባክህ!"

"ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና አንድነት በሌለበት ሀገር፣ እንዲህ አይነቱ የከርሰ ምድር ሃብት በገፍ ከወጣ የግጭት መንስኤ መሆኑ የማይቀር ነው። በሌላ በኩል የግጭት መንስኤ መሆኑ የማይቀር ነው። በሌላ በኩል ግንባሮች ከዚህ ምድር ሀብት ሲዛቅ የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባሮች ከዚህ ምድር ሀብት ሲዛቅ እጃቸውን አጣጥፈው አይመለከቱም።"

"ዝም በል!"… ‹ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም› ሲባል አልሰማህም?!"

"ከዚህ ቀደምም ነጻ አውጭዎቹ ሲያስጠነቅቁ ቆይተዋል።" ቀጠለ የመጀመሪያው። "ደማችን ሳይፈስ ነዳጃችን አይፈስም፤ ሲሉ ዝተዋል። ነፃ አውጪዎቹ ነዳጁን በነጻ አይሰጡም!..."

"ደም ሲፈስበት የኖረ ምድር ነው" አለ ሁለተኛው ቱግ ብሎ።

"አሁንም ይቀጥላል።"

"ያምሃል እንዴ አንተ ሰው?!"

"ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በሌለበት ሀገር የግጭት መንስኤው የሚሆነው ያው ሃብት ነው።"

"ነዳጁም ይወጣል! ደሙም ይፈሳል!..." አለ ሶስተኛው ሰው በዝምታ ሲያደምጥ ቆይቶ። "ኢትዮጵያ የምድሯ ሀብት ተጠቃሚ መሆን አለባት። በልመና እስከመቼ ትቀጥላለች?!... ነዳጁ ይውጣና ይዋጣልን። ይህ ምድር ከጥንት ጀምሮ አባቶቻችን ደማቸውን ሲያፈሱበት የኖረ ነው። ደም መጠጣቱ ይበቃዋል። ይትፋው!... በነዳጁ መልኩ የአባቶቻችንን ደም ይትፋው። ካሳችን ይሄ ብቻ ነው።"

"ክርክራችን የገባህ አልመሰለኝም..." አለ የመጀመሪያው።

"ገብቶኛል!" ሶስተኛው ውሃ ተጎንጭቶ መለሰ። "ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በሌለበት ሀገር፣ ሀብት በራሱ የግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል፣ የሚለውን ሀሳብህን ሰምቻለሁ። የትኛው መቅደም እንዳለበት ግልፅ አይደለም። ፍትሑ ነው ሀብቱ መቅደም ያለበት? ፍትፍት ነው ፍትህ የሚቀድመው? ይህች ሀገር ፍትህ የተጠማች እንደሆነች የአደባባይ ምስጢር ነው። ሆኖም... ፍትህን በሀብት ለማምጣት መሞከር አደጋ አለው። ሀብቱ ጥንትም በከርሰ





ምድራችን ውስጥ እንዳለ ይታወቃል። ከፍትሑም ከሀብቱም ለመቋደስ ግን መስዋዕትነት የማይቀር ነገር ነው። ለሁለቱም በቁርጠኝነት መፋለም ግድ ይላል። ሀገራችን ጥቅም ላይ ያልዋለ የከርሰ ምድር ሀብት ብቻ አይደለም ያላት። ሀብቷ ጥቅም ላይ ያልዋለው መቶ ሚሊዮን ህዝብ ጭምር ነው። የሰው ሀብታችንን በስደት ከመበተን በማስተዋል ሀብተችን አውጥተነ መጠቀም አለብን።"

"ብጥብጡን ለማን ተውከው?" አለ አሁንም የመጀመሪያው።

"ብጥብጡ ከኢፍትሃዊ የሃብት ክፍፍሉ የሚመጣ ነው። አይደለም እንዴ? ለፍትሁም መፋለም ይጠይቃል። ኮንፍሊክት እኮ..."

"በአማርኛ አውራ!... እንዷት ዲብሉም ያዘኩ ብለህ አትበጥብጠን!"

"...ግጭትን በአግባቡ ማኔጅ የሚያደርግ መሪ ካለ ግጭት በራሱ ለማህበረሰብ እድገት ጠቃሚ ነው። ግጭት ከራስ ይጀምራል። ከራስህ ጋር በቀን ሺህ ጊዜ ትጋጫለህ። ግጥትክን በአወንታዊ መልኩ ካልተረጎምከው ራስህን ልትሰቅል ትችላለህ። በሰዎች መካከል የሚከሰተው ግጭት ሙቅና ቀዝቃዛ ተብሎ ሊከፈል ይችላል። ሙቁ ግጭት በጠንካራ ስሜትና በሚታይ ውጥረት ሲገለፅ፣ ቀዝቃዛው ግን በታመቀ ዝምታና በማይታይ ቁጭት ይንፀባረቃል። ይህኛው ነው አደገኛው። እምቁ ዝምታ የፈነዳለት ግጭቱን ማብረድ ከባድ ነው። ይህን ለመቆጣጠር በአመራር ጥበብ የተካነ መሪ ያስፈልጋል።"

"እሱ ከየት ይመጣል?"

"... `when the student is ready the master will arrive` ...ሲባል አልሰማህም?"

"አትበጥብጠን ባማርኛ አውራ።"

"ብጥብጥና ግጭት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ግጭት ውስጥ ጥቅም አለ። ብጥብጥ የሚመጣው ግጭቱን በአግባቡ ማስተናገድ ካልቻልክ ነው። የጎሪጥ እየተያዩን ዘለአለም በድህነት ከምንኖር የከርስ ምድር ሃብታችን በፍትሐዊ መልኩ ለመጠቀም እንጋጭ... ሁ ኬርስ!"

"ኧረ እባክህ!"
"ያበጠው ይፈንዳ ያመጣል ክፉ እዳ"

"ሄይ ወሪያ! ሰዓት ደርሷል ወደ ሥራ!..." አለ አንድ ሰው ወደ መጠለያቸው እየገባ። ሶስቱም ተከራካሪዎች ጭጭ ምጭጭ ብለው መሰስ አሉ።





# ፴፬

ብሎክ ስድስት አጠገብ በሚገኝ የቆሻሻ ክምር ሥር አንድ የወደቀ አጥንት አግኝተን አፈጠጥንበት። በሁለታችንም ውስጥ አጉሉ የሰውነት አመል እየተመላለሰ እንድንጠየፍ ሊያደርገን ሞከረ። በሞሸለቀን የረሃብ ስሜትና ባቅለሸለሸን ጠባይ መካከል ሆነን ክብ ዓይኖቻችን አንቀዋለልንበት።

አጥንቱ ረዥም ነው። የግመል ጉልጥምት ሊሆን ይችላል። ጥቂት ፍቅፋቂ አለው እንጂ ለማገዶነት ከሚውል ፍልጥ አይለይም፤ ተፈቅፍቋል። የቆዩ ግን አይደለም። ጥቂት ዝንቦች ሰፍረውበታል። ቢቀርብን ይሻላል። ትተነው እንደገና ወደ ብሎክ ስድስት መጠለያ አመራን።

ብሎክ ስድስት እስከ አርባ የሚደርሱ ወዛደሮች ይኖሩበታል። ነዳጁ መገኘቱ ከተረጋገጠ ወዲህ ሽርጉዱ ይብዛ እንጂ የጥጋብ ምልክት አይታይም። ጥጋብ ቢኖር ኖሮ ትርፍራፊ ይበዛ ነበር። ሃሰሳ ሥጋችን ቀጠለ።

የብሎክ ስድስትን ጥጋጥግ ስናስስ ቆይተን በቆራጥነት ወደ ማብሰያ ቤቱ ዘው ብለን ገባን። ከመግባታችን ነበር በአንድ መዘፍዘፊያ ውስጥ የተቆለለ ሥጋ የተመለከትነው። እያን ‹ሚያው› እንዳትል ፀለይኩ። ድምፅ ሳናሰማ አንዱን ሙዳ ሥጋ ይዘን ከዚህ ካምፕ መሸሽ አሰብን።

እያን ‹ሚያው› ለማለት ጊዜ አልነበራትም። ከአንዱ ሙዳ ሥጋ ሳይ ተወርውራ አረፈችበት። የሸንጥ ሥጋ መሆን

አለበት፡፡ እንደስካርፍ እየጎተተችው ሥትወጣ አንዱ ሼፍ ተመለከታት፡፡

"ወሰደችው! ወሰደችው!" ሁለት ቢላዋ አከታትሎ ወረወረባት፡፡ አያን ዞራ አላዬችም ቁልቁለቱ አካባቢ ወደ ሚገኘው ጥሻ ተፈተለከች፡፡ እኔ ባዶ አፌን ተከተልኳት፡፡

ሼፉ ተስፋ ቆርጦ እየተራገመ ሲመለስ መንገድ ላይ ተገጣጠምን፡፡

"አሁን ማን በላው ሊባል ነው?! የተረገመች! ልታሳማኝ ነው፡፡ ድሮም ደሜ መራራ ነው፡፡..." በእርሷ ቁጭት እኔን በደቦል ድንጋይ ደጋግሞ ሳተኝ፡፡ "...ሰይጣኖች!"

አያን ቁልቁለቱ ላይ የሚገኝ ቆንጥር ዛፍ ጥግ ይዛ እያግተመተመች ጠበቀችኝ፡፡

"ለምን ሌላ አላመጣህም?" አለች በተለመደው የቴሌፓቲ መንገድ፡፡

"ይበቃናል ብዬ ነው፡፡"

"ሥጋ አይቶ ያለፈ የመጀመሪያው ድመት መሆን አለብህ!" አለች ውርዬ አፏን እያቀላጠፈች፡፡ "በል ያገ! ረጂም ጉዞ አለብን፡፡"

በወዲህኛው ጫፍ መጉመድ ጀመርኩ፡፡ ጣፋጭ የሽንጥ ሥጋ... ለረጅሙና አድካሚው ጉዟችን ጥሩ ስንቅ ነው፡፡ ዋናውን አስፋልት ይዘን ለመጓዝ ተስማምተናል፡፡ ይህ ሽንጥ ብዙ ሽጥ አቋርጠን ዋናውን አውራ ጉዳና እስክንደገ ሊበቃን ይችላል፡፡





# ፴፫

ከኢላላ ኮረብታዎች ተነስተን ለሰዓታት ከተጓዝን በኋላ አደዌ ገባን፡፡ አደዌ፣ ከጎዴ ከተማ ሰላሳ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ በዋናው አስፋልት ላይ የምትገኝ ከተማ ቀመስ መንደር ናት፡፡

አደዌ ስንደርስ ከየአቅጣጫው የመጣ የግመል መንጋ ተመለከትን፡፡ አደዌ የግመል ከተማ ናት፡፡ ብዙ የውሃ ጉድጓዶች ቢኖሩባትም ውሃው ጨዋማ በመሆኑ ለእኛ ለድመቶቹ አልተመቼንም፡፡ በሚጋፋው የግመል መንጋ እግር ሥር ተሹሎክሉከን ገብተን፣ ከውሃው ሞጭለፍ ሞጭለፍ አድርገን ምላሶቻችን ከአራስን በኋላ ወጣን፡፡ እዚህ እንደ ውሃ ውድ ነገር አለመኖሩን ተመለከትን፡፡

የግመሎቹ እረኞች ግመላቸውን ለማጠጣት እኔ እቀድም እኔ እቀድም ይንጫጫሉ፡፡ ትንቅንቅ፡፡ ውሃ እንጂ ነዳጅ ለእነርሱ ዋጋ የለውም፡፡ ከበርሜል ሙሉ ነዳጅ ይልቅ ለእነዚህ እረኞች ጥርኝ ውሃ ይበልጥባቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ በአካባቢው ጉድጓዶች ለራሳቸው ውሃ ጠምሟቸዋል፡፡ ህፃን ልጅ ጉድጓዶች ንቃቃት ምክንያት የውሃ ጉድጓዶች በመግባቱ ድርቅ ይውጣል፡፡

እኔና አያን ብዙ ከተመካከርን በኋላ አደዌ ለማደር ወሰንን፡፡ ወደሚቀጥለው ከተማ ደናን ጉዟችንን ለመቀጠል ብናስብም፣ መድረስ ለመቻላችን እርግጠኞች አይደለንም፡፡

መንገድ ላይ ደግሞ የሚያጋጥመን አናውቅም። የምድረ በዳ አውሬ ሲሳይ ልንሆን እንችላለን።

አንድ ጤነኛ ድመት በቀን መጓዝ የሚችለው እስከ አሥር ማይል ብቻ ነው። በታሪክ ረጂሙን ጉዞ ተጉዞ የተገኘው ድመት የተጓዘው ርቀት ሶስት መቶ ሃያ ሁለት ኪሎ ሜትር ብቻ ነው። ይህ ግን በጤነኛ አረማመድ እንጂ እንደኛ ሰው ለመሆን በቸኮለ ድመት ላይ በተደረገ ጥናት መሠረት አይደለም። እኛ የዚህን ጥናት ብዙ እጥፍ በቀን ካልተጓዝን በቀር አዲስ አበባ መግባታችን ያጠራጥራል። ይሁን እንጂ ለዛሬው፣ ከዚህ በላይ ጉዟችንን ከቀጠልን ደናን ሳንደርስ መንገድ ላይ ሊመሽብን ይችላል። ትልቁ ሥጋታችን ጤንነታችን ነው። ሰው እያለን እንደምናውቀው ድመቶች አምስት ገዳይ በሽታዎች አሉባቸው። እኛንም እንደ ሰው ልጅ ኤፍ. አይ. ቪ.. የተባለ ቫይረስ ያጠቃናል። ፌላይን ኢሚኖዲፊሸንሲ ቫይረስ ይባላል። በድመቶች መካከል በሚነሳ ቡጭሪያና ንክሻ ከመተላለፉ በተጨማሪ በሥሪያም ይተላለፋል።

በግብረ ድመት ከሚተላለፈው ኤፍ አይ ቪ በተጨማሪ በንክሻና በቡጭሪያ የሚተላለፉ ፌላይን ሉኬሚያን የመሳሰሉ በሽታዎች ያጠቁናል። የተበላሸ አይጥ በመመገብ የሚመጣ ነው። የኩላሊት በሽታ ሳይቀር ይይዘናል።

የበሽታ መከላከል አቅማችን ከተዳከመ፣ ቶክሶፕላዝሞሲስ የተባለው በሽታችን ይነሳብናል። ቶክሶፕላዝሞሲስ ቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ በተባለ ፓራሳይት የሚመጣ በሽታ ነው። በተፈጥሮ በእኛ በድመቶች ሰገራ ውስጥ መኖር ይመቸዋል። ሰገራችን የምንቀብረው ለሰው ልጅ ሽንት ቤት መጠቀምን ለማስተማር አይደለም። ፈጣሪ ሲፈጥረን ይህንን ቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ የተባለ ተህዋስ ቅበሩ ብሎን





ነው። የበሽታ መከላከል አቅማችን ከወረደ ይህ ተህዋስ እኛን ስሜታዊ የሚያደርግ ጠባይ አለው። ያቅበዘብዘናል። በሽታው ሲጠናብን ሰገራችንን መቅበራችን ትተን ምድር ላይ እንፀዳዳለን። በዚህ ጊዜ ቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ ይሰራጭና ከብቶች ሳር ሲግጡ ይገባል። ከዛም ሰዎች ጥሬ ሥጋ ሲመገቡ ይበሉታል።

ሰዎች የበሽታ መከላከል አቅማቸው ሲዳከም ስሜታዊ የሚሆኑት፣ ቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ በእኛ ሰገራችንን ለመቅበር በመዘናጋታችን ምክንያት ወደ እነርሱ ስለሚገባ ነው። ብዙ ኤች. አይ. ቪ. የያዛቸው ሰዎች ነጭናጫና ስሜታዊ የሚሆኑትና፣ ራሳቸውንም እስከ ማጥፋት የሚደርሱት ቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ የተባለው ተህዋስ በሽታቸውን የመከላከል አቅማቸው መውረዱን ተከትሎ ስለሚሰራጭባቸው ነው።

የጤና ባለሙያ ብሆን ኖሮ ጥሬ ሥጋንና ስሜታዊነትን በደንብ አጠናው ነበር። ርእሱንም "ጥሬ ሥጋና ስሜታዊነት" እለው ነበር። እንደ ማንኛውም ድመት በአናቱ ሐበሻ እንደነበረ ሰው፣ ጥሬ ሥጋን ማውገዝ አልነበረብኝም። ነገር ግን እውነት በቁራጭ ሥጋ አይለወጥም። ጥሬ ሥጋና ድራፍት የሚያዘወትሩ አሽከርካሪዎች በድፍረት ሲጋጩ የሚውሉት፣ በቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ አነሳሽነት፣ ስሜታዊ ስለሚሆኑ ጭምር መሆኑን ከመግለጽ፣ ድመት መሆኔ ሊከለክለኝ አይገባም። በድመት ፍቅር የተለከፉት አሜሪካውያን በቀር በስሜታዊነት የታወቁ ናቸው። ጮኸው ካልተናገሩ በቀር የሚደመጡ አይመስላቸውም። ስልሳ ሚሊዮን ያህሉ አሜሪካውያን ከቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ ጋር እንደሚኖሩ ስተረዳ ግን ስሜታዊነታቸው ከምን እንደመነጨ ለመረዳት አያዳግተውም። በከተሞች መስፋፋት ምክንያት እኛ

ድመቶች ሰገራችንን መቅበሪያ ከማጣታችን የተነሳ፣ ዓለም በስሜታዊነት ብትታመስ ተጠያቂዎች አይደለንም። ለብጥብጡ ሃላፊነት መውሰድ ያለበት፣ ለራሱ መቀበሪያ እንኳ ያጣው የሰው ልጅ ነው።

እኛ ድመቶች ሰገራችንን የምንቀብረው ቶክሶፕላዝማ ጎንዳይን ለመቅበር ብቻ አይደለም- እንደ ውሾች ጉረኞች ባለመሆናችን ጭምር ነው። ውሾች "እለን" ለማለትና ግዛታቸውን ለማስከበር ውጪ ሲፀዳዱ እኛ ድመቶች ግን ከጠላቶቻችን ጥቃት ራሳችንን ለመከላከል ስንል ጭምር ሰገራችንን እንቀብራለን።

ለዚህም ነው አያን ከእኔ ርቃ የሄደችው። ነገሩ ስለገባኝ አልተከተልኳትም። ወደ ኮረብታው ጥግ ሄደችና ከአንድ የእጣን ዛፍ ሥር ጫር ጫር አድርጋ ተቀመጠች። መሬቱን ስትቆፍር ያዬ ሰው፣ ነዳጅ የምታወጣ መስሎት ወገብ ዛላዋን ሰውሎ እንዳያባርራት አልሰጋሁም። ያላየሁ በመምሰል ፊቴን ወደ ግመሉ መንጋ አዞርኩ። ከደቂቃዎች በኋላ ስትመለስ ምንም እንዳልተፈጠረ ዝም ብላ አጠገቤ ቆመች።

እየመሸ በመሆኑ፣ ከሩቅ ወደሚታይ ጎጆ አመራን። እዛ ተጠግተን አድረን በነጋታው ጉዞ ለመጀመር ወሰነናል። በዚህ ሰዓት ወደ ደናን ጉዞ መጀመር አደጋ አለው። በሌሊት የሚያጋጥመንን አናውቅም። ለነገሩ እዚህም ቢሆን ሁሉ ነገር አስተማማኝ አይደለም። ድንገት በድመት መንጋ ልንከበብ እንችላለን። ያልገመትነው ዱብዳም ሊገጥመን ይችላል።



# ፴፯

ወደ ደሳሳው ጎጆ ስንጠጋ፣ የሥጋ ጥብስ አወደን። አንድ አዛውንት የተቀቀለ የግመል ሥጋ በርከት ላሉት ልጆቹ ሲያድል ነበር የደረስነው።

እኔና አያን አድፍጠን ሁኔታውን ተከታተልን። ቀስ ብዬ ጅራቴን እየቆላሁ በእሳቱ ዙሪያ ወደ ተኮለኮሉት ልጆች ተጠጋሁ። ጥቁር ከመሆኔ የተነሳ ይፈሩኝና በፍልጥ ወገቤን ሰብረው ያባርሩኛል ብዬ ሰግቼ ነበር። ከቁብ አልጣፉኝም። ውሻ ከመሆን ይልቅ ድመት መሆን የፈለኩት ለዚህ ነበር። ነጻሳ ተብዬ ከመደብደብ ብሎም ከመገደል የተረፍኩት ድመት በመሆኔ ነው።

ድምፄን አጥፍቼ ከልጆቹ ጀርባ በመቀመጥ እቁለጨለጭ ጀመር። አያንም ፈራ ተባ እያለች መጥታ አጠገቤ ቁጢጥ አለች።

በሚንበገበገው እሳት ዙሪያ የተኮለኮሉት ልጆች አባታቸው የሚሰጣቸውን የግመል ጥብስ ይሻማሉ። ተመሳሳይ ከመሆናቸው የተነሳ ባንድ ሌሊት የተወለዱ የሚመስሉት ልጆች፣ ትኩሱን አጥንት ይግጣሉ። ሶስት ከሳዋ ሴቶች ከደሳሳዋ ጎጆ ወጣ ገባ ይላሉ። ሴቶቹ ከመክሳታቸው የተነሳ ቆዳቸው ከአጥንታቸው ላይ የደረቀ ይመስላል። ከልብሶቻቸው ሾልኮ የሚታየው ቅልጥማቸው የደረቀ እንጨት መስሏል። ደማቸው የተንጠፈጠፈ ይመስል፣

አካባቢው በድርቅ በጠና በመመታቱ ረሃብና ቼነፈሩ እጥብቆ የገረፈው ቤተሰብ መሆኑን የተረዳሁት ወዲያው ነበር፡፡

አባወራው በጥልቅ ሀዘን ውስጥ ሰጥሟል፡፡ ሥጋውን በእሳቱ ዙሪያ ለተኮለኮሉት ልጆች ብቼኛ ግመሉ መሞቱን በምሬት ይናገራል፡፡ የሚጭነውና የሚያርሰው ግመሉ የደከመ ጉልበቱ ድርቁን መቋቋም አቅቶት ሞቶበት ኖሯል፡፡

አባወራው፣ ቅቅሉን ሲበላ ካቀረቀረ በኋላ ሳግ ተናነቀው፡፡ እንደ ነዳጅ ገደል ከጎደጎደው ቅንድቡ ሥር ብቅ ያሉት ዓይኖቹ፣ ቅቅሉ ላይ ሲንቀዋለሉ ከቆዩ በኋላ፣ የዕንባ ውርጭ ወደቀባቸው፡፡

በእሳቱ ዙሪያ የተሰተሩ ልጆቹን አንድ በአንድ ቃኝቶ ሲያበቃ ቅቅሉን ሳይቀምስ ተነሳና ወደ አጥሩ ጥግ ሄደ፡፡ አላስችል ብሎን እኔና አያን ተከተልነው፡፡ አባወራው አጥሩ ሥር ካለች የደረቀች ቁንጥር ሥር ተቀመጠና ስቅስቅ ብሎ ያለቅስ ጀመር፡፡ ድመት ባንሆን ኖሮ እኛም ስቅስቅ ብለን እናለቅስ ነበር፡፡ ልባችን ተነክቷል፡፡ ወደ ድመትነት የመለወጣችን አንዱ ጥቅም ይኸው ነው፡፡ የበረሃውን አስቃቂ ኑሮ በየሥርቻው እየገባን ለመመርመር ያመቻል፡፡

የድመት መንጋ አጋጥሞን የፐርጅና የሥሪያ ሥጋት ባይኖርብን ኖሮ መላ ኦጋዴንን ለማጥናት ወደ ድመትነት መለወጣችን ያመች ነበር፡፡ ሰው ሆኖ በዛ ላይ ወዘልውጥ ሆኖ በዚህ በረሃ ውስጥ መከሰትና የህዝቡን ኑባሬ ለማጥናት መሞከር መዘዙ ብዙ እንደሆነ ከቀናት በፊት ያጋጠመን ስቃይ በቂ ምስክር ነው፡፡ አያን ሰው እያለን እንደነገረችኝ፣ ወደ ኦጋዴን መጥተው ቀልጠው የቀሩ



ተመራማሪዎችና ጋዜጠኞች ብዙ ናቸው፡፡ እኛም ወደ ድመትነት ባንለወጥ ኖሮ እስካሁን እንገታችን ላለመቀላቱ ማንም እርግጠኛ መሆን አይችልም፡፡

አባወራው፣ ሞቶ ለቅቅል የበቃ ግመሉን፣ በእንባ ጠል ከተሰናበተው በኋላ ወደ ቤተሰቦቹ ተመለሰ፡፡ እኛም እግር እግሩን ተከትለን ተመለስን፡፡ መሳቅና ማልቀስ ለእንስሳት የተሰጠ ፀጋ ቢሆን ኖሮ እኛም አልቅሰን ቢወጣልን ጥሩ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ቤተሰብ ከእንግዴህ ከግመሉ ቅቅል በቀር ሌላ ምንም ጥሪት እንደሌለው ስናስብ፣ ሀዘን እንደጦር ተቀበቀበብን፡፡ እንኳን እጥንቱን ሙዳ ሥጋውን እንኳ ቢሰጡን ለመብላት አቅም የለንም፡፡



t.me/BooksandYou

# ፻፺

ኦጋዴናውያን፣

"አዳም ወደ ምድር ቢመለስ በትክክል የሚያስታውሰው ሥፍራ ኦጋዴንን ነው" የሚሉት ፍፁም ሀሰት የለበትም:: ቀንና ሌሊቱ ከመፈራረቁ በቀር በዚህ በረሃ ውስጥ የተለወጠ ነገር የለም::

የኦጋዴን የህይወት ኡደት ሁልጊዜም ተመሳሳይ ነው- መምሽትና መንጋት ብቻ:: ተመሳሳይ ምድር፣ ተመሳሳይ ሰማይ:: ድመት የላሰው ሰሃን የመሰለ ሰማይና አሸዋ የተደፋበት እርቃን ምድር:: ባደርንበት የስቃይ ጎጆ ረሃብ ምክንያት ሀዘን እንደጦር ሰፍቶ እንደያዘን ወገግ አለ። የኦጋዴን ምሥራቃዊ አድማስ ፍም መሰለ:: ፀሐይዋ የእሣተ ገሞራ ቅልጥ አለት መስላ ብቅ ብላለች:: መዓቷን ሳታወርደው ጉዞ መጀመር አለብን::

ከአደዌ ዳናን ያለው ርቀት በድመት አረማመድ ምን ያህል ሰዓት እንደሚፈጅ አላወቅንም:: ብቻ ግን በረሃብ የተጠበሰውን ጎጆ ለቀን ወጣንና ዋናውን አውራ ጎዳና ይዘን ሱክሱክ ማለት ጀመርን:: በመንገዱ ግራና ቀኝ ቸነፈር የረገጠው ምድር ተሰጥቷል:: የአሸዋ ስጥ የተሰጣበት ምንጣፍ ነው-ያገጠጠ ምድር::





መንገዱን እየገፋን ስንመጣ ጉዱም ይበልጥ እየፈጠጠ መጣ:: አካባቢው በሙሉ በቤት እንስሳት ጥንብ ተበክሏል:: አፉን ከፍቶ ጥርሱን አግጥጦ የወደቀ የግመል በድን፣ ቋጥኝ እንደተደገፈ የሞተ ፍየል፣ በሞት ላይ የሚስቅ ይመስል ጥርሱን አግጥጦ የወደቀ የአህያ አስከሬን፣ ሆዱ ከበሮ እስኪያክል የተነፋ የከብት ሬሳ....

ከፊት ለፊታችን ከነጋበት ጅብ ጋር ተገጣጠምን:: አልደነገጥንም:: ይህ ሁሉ በድን ምድር ላይ ፈስሶ እኛን ይፈልገናል ብለን አልገመትንም:: አህያ የሚያክለው ጅብ አንጋጦ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ያነፈንፋል:: ይህን ሁሉ መንገድ ስናቋርጥ አንድም አውሬ የጀመረው በድን አላማዬታችን ግን ገርሞናል:: የሁሉም እንስሳ በድን በጅብ አልተገመጠም:: የኦጋዴን ጅብ የሞተ አይበላ ይሆን? ጅቡ እኛን መከተል አለመከተሉን እየተገላመጥን እያዩን መፈርጠጣችን ተያያዝነው::

የሞት ረጃጅም ጥላዎች የወደቁበትን ምድር አቋርጠን ወደ ደናን መገሥገሣችንን ቀጥለናል:: ርምጃችን ወደ ሶምሶማ ብሎም ወደ ሩጫ ከተቀየረ ቆይቷል:: ፀሐይዋም የእሳት ላንቃዋን ከፍታ እሳት መትፋቷን ከጀመረች ቆይታለች:: ደናን ገብተን ማደር ስላለብን በነበልባሏ ውስጥ መንዝ ግዴታችን ነበር:: አስፋልቱ እንደ ብረት ምጣድ ግሏል:: አሸዋው እንደ ፍም ይፋጃል:: የድመት ጫማ የለም:: ...መቆም አይታሰብም:: ቆሞ ከመቃጠል መሮጡ ይመረጣል::

# ፴፫

የማታ ማታ ደናን መግባታችን አልቀረም። ሁለታችንም እንደ አንገት ፎጣ ተዝለፍልፈናል። እንደ ልጥ ልንቁስቁስ እንዳልን ወደ አንድ ሥጋ ቤት አመራን። የግመል ሥጋ እንደጉድ የሚበላበት ቤት ነው። ቅቅል ሲራወጥ ደረስን።

ከአንዱ ተመጋቢ ላይ አፈጠጥኩበት። አያንም ከወዲያ በኩል ካለ ማዕደኛ ላይ እየተቁለጨለጨች ነው። በካልቾ ሲጠልዛት ተመለከትኩ። ክፉኛ ከግድግዳው ጋር ስትላተም እዛው ላይ እንደ ሙጫ ተጣብቃ የምትቀር መስሎኝ ነበር። የድመት ነፍስ መች እንዲህ በቀላሉ የሚወጣ ነውና! እንደ እባብ አፈር ልሳ ተነሳች። በንዴት ጦፌ ወደሰውዬው ሄድኩና አግተመተምኩበት። በዚህ ጥቁረቴ ውስጥ ነጫጭ ረጃጅም ሰንቀጣጤዎችን ሳሳዩው ጊዜና፣ ዓይኖቹ ፈጠው በፍርሃትና በድፍረት መካከል ሆኖ ይመለከተኝ ጀመር።

"እንዲ ነችና!?" አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ። "እነዚህ ድመቶች ናቸው ወይስ ነብሮች?..."

"አቦ ሸማኔ እንዳይሆኑ ፀልይ!" አለው ከፊት ለፊት ሌላ ቅቅል የሚበላ ሰውዬ- በማፌዝ መልክ ስቆ። ነብርንና አቦ ሸማኔን ሲጠሩ ይበልጥ ወኔ ተሰማኝ። እኛ ድመቶች በመጠን እንነስ እንጂ ነብር፣ አንበሳና አቦ ሸማኔ የቅርብ ዘመዶቻችን ናቸው። ከድመቶች ሁሉ የአለምን





ሪከርድ በክብደት የያዘው ባለ ሃያ አንድ ኪሎ ግራሙ ድመት፣ ከአንድ ኮስማና ነብር አይተናነስም።

መጠናችን ይነስ እንጂ የጀርባ አጥንታችን እንደ አቦ ሸማኔ እንደ ፈለግነው የሚታዘዝ ነው። እንዲያውም መንጋጋችን ከፊት ለፊቴ ከሚያላምጠው ሰውዬ አስር እጅ ይሻላል። ምንድን ነው ይህ ሁሉ ጉራ?! እነቀው እነቀው አለኝ። ሰውዬውን ጉርንቦውን ልመዝለት እችላለሁ። እንዲያውም በአረማመድ ዘይቤአችን ከሚያላምጠው ግመልና ከቀጭኔ ጋር እንመሳሰላለን። ሙቀትን በመቋቋም ከሰውዬው በብዙ እጥፍ እንበልጣለን። የእኛን የሙቀት መቋቋም ፀጋ ፈጣሪ ቢያድለው ኖሮ ሰውዬው ኦጋዴንን ገነት ያደርገው ነበር። እንደ እርሱ ላባችን በብብታችን አይንጠፈጠፍም። ሙቀት የምናስወግደው በአፋችን ነው። ተገደን ሥጋ በል ሆነን ተፈጥረን እንጂ፣ እንደ እርሱ እርሶ ያበላውን ግመል እንመኝም ነበር። ምግቦቻችን ውስጥ ግዴታ ሃያ በመቶ ፕሮቲን መኖር አለበት። ኩሩዎች መሆናችንን ለዚህ ሰው ማን በነገረው?!

ሰውዬው ላይ እንዳፈጠጥኩ ነኝ። የምሽቱን ጨለማ ለመግፋት የበሩት መብራቶች ነጫጭ ዓይኖቼ ላይ ሲንቦገቦጉ አስፈሪነቴን ይጨምሩት ይሆናል። ሰው ከሚያይበት ብርሃን አንድ ስድስተኛውን ካገኘን እኛ ድመቶች ልቅም አድርገን ማዬት እንችላለን። ያ ማለት እኔ ስድስት ከሰውዬው ይልቅ የግመሉን ቅቅል በማዬት እጥፍ እበልጣለሁ ማለት ነው። በማሽተትስ ቢሆን!? ...ከሰውዬው ይልቅ የግመሉን የቅቅል መረቅ አስር እጅ ጠልቄ ማሽተት እችላለሁ።

ስውዬው የሚበልጠኝ በምላሱ ብቻ ነው። በማጣጣም አቅሙ። ሐበሻን በምላስ ማንም አይችለውም። ሀገሩ በሙሉ በምላስ ጅም የተሞላ ይመስል ከነገር በቀር ተግባር የለም። የሚራብበትና የሚታረዝበት፣ የጫነውንና አርሶ ያበላውን ግመል አርዶ የሚበላበት ምድር፣ በነዳጅ የተሞላ ነው። የምድሩን በረከት አውጥቶ ከመጠቀም ይልቅ በምላስ አገም ጠቀም ጦርነት አንስቶ ሀብቱን ለባዕዳን አሳልፎ ስጥቷል።

ስውዬው ጋር እንደተፋጠጥን ነን። ፈርቶኛል። ነገር ግን ፍርሃቱ እንዳይታይበት ሌላ ፍርሃት ፈርቷል። የብብቱ ጠረን ለራሱ አይድረሰው እንጂ ለእኔ መፍራቱን በብብቱ እየነገረኝ ነው። ቦቅቧቃ! ...አንበሳ ብሆን ኖሮ እሰባብረው ነበር። ለነገሩ ሰዎች ፍርሃቱን እንዳያውቁበት አንበሳ ብሆን አይጠላም። የሰው ልጅ የሚበልጠውን የመፍራት አባዜ አለበት። በሃብትም በጉልበትም የሚበልጠውን ይፈራል። የሚበልጠውን ያመልካል።

ማወቁን እጠራጠራለሁ እንጂ፣ እኛ ድመቶች በጥንታዊቷ ግብፅ እንመለክ ነበር። ባስቴት የተባለችው የግብፅ አምላክ ድመት ነበረች። በታችኛው ግብፅ ባስቴት የጦርነት አምላክ ነበረች። የላይኛውና የታችኛው ግብፅ ከመዋሃዳቸው በፊት፣ በ3100 ዓመተ ዓለም ባስቴት ትመለክ ነበር። ሐውልት ተሰርቶላታል።

ባስቴት፣ ከዚህም በተጨማሪ፣ የሴቶች ምስጢር፣ የመባዛትና የመላመድ አምላክ ነበረች። ሴቶችንና ህፃናትን ከክፉ ነገር፣ ከበሽታና ከሰይጣን ትጠብቃለች ተብሎ ይታሰብ ነበር።





የፀሐይ አምላክ የሆነው ያራ ልጅ እንደመሆኗ መጠን፣ ሁሉንም የሚያዩው ዓይን "The All Seeing Eye" የእርሷ ነው- የባስቴት- የድመቷ። የጥሩ ሽታ ምልክትም እንደሆነች ስለሚታመን በግብፅ ፒራሚዶች ላይ ተቀርፃ የምትታዩው ጭንቅላቷ የድመት፣ ሌላ አካሏ የሰው የሆነችው ባስቴት ናት። በእጇ የ'ቶ'ን ምስል ታንጠለጥላለች።

ውሻ እያለሁ ሴትን በድመት መመሰሌ ለዚህ ነበር ...ባስቴት ናት። ጭንቅላቷ የድመት አካሏ የሰው። የብዙ ሰዎች ችግር ይኸው ነው። በሰውነታቸው ውስጥ የተሸሸገ አውሬነት በብዙ ሰዎች ውስጥ አለ። ይህ የሚገለጠው ክፉ ቀን ሲያጋጥም ነው።

በህይዎቴ ውስጥ ብዙ ባስቴቶች አጋጥመውኛል- የጥቅማ ጥቅም ባስቴቶች። ሚስቴ አንዷ ነበረች። ባስቴት! ...በልጅነቴ በቤተ መቅደስ ግድግዳ ላይ ተስሎ ያየሁት የሶበድዓት ስዕል ድቅን የሚልብኝ የድሮ ሚስቴን ሳስባት ነው።

ባስቴትን ሳስብ የማይክል ጃክሰንን ሙዚቃ አስታወስኩ- "Remember The Time" የሚለውን። ጠላቴን አግብታ ለፈታችኝ ሚስቴ ማን ቢጋብዘልኝ? በፊርኦን ፊት ቆሞ የሚያቀነቅንበትና በድመት ሙኸት የሚጀምረው ተንቀሳቃሽ ምስል ድቅን አለብኝ። ፊርኦን ንግሥቲቷን ለማዝናናት ወይኑን እየተጎጨ ጥበበኞችን ይጠራል። እሳት ባፉ የሚጎርሽ ቢመጣ፣ ሰርከስ የሚያሳይ ቢመጣ ንግሥቲቷን ለማዝናናት አልተቻለም። ወደ አንበሳ እንዲጣሉ ይደረጋል። ማይክል የእስማት ጠጠሩን በትኖ ይገባና ሲያቀነቅን፣ ንግሥቲቷ በድመታዊ ድምፅ ትመስጣለች።

"Do you remember when we fell in love?
We were young and innocent then
Do you rememeber how it all began?
It just seemed like heaven?
So why did it end?
Do you remember, back in the fall?
We'd be together all day long
Do you remember us
holding hands?
In each other's eyes
We'd stare tell me
Do you remember the time?
When we fell in love
Do you remember the time?
When we first met, girl?
Do you remember the time?
When we fell in love
Do you remember the time?
Do you remember how we used to talk?
You know we'd stay on the phone
at night till dawn
Do you remember all the things we said?
Like "I love you so, I'll never let you go"

…እያለ ይቀጥላል። ባስቴትን ሳስብ ሰውዬው ላይ ማፍጠጤን ትቼው ኖሯል። ቅቅሉን ጨርሶ ሄዷል። ሳላስበው ዘፍኜለት ይሆን? የግመሉን አጥንት እንደ ጥምቀት ሐርሞኒካ ዘፍኖበት እንደሄደ የተገነዘብኩት የደቀቀውን አጥንት አስተናጋጅ መጥቶ ሲጠርገው ተመልክቼ ነው። ውርዬ አያን በወዲያ በኩል ካለው





ጠረጴዛ ላይ ወጥታ ትርፍራፊ ስትለቅም ተመለከትኩ። እኔ ወንድ ነኝ ብዬ ስፋጠጥ እርሷ የመጣችበትን አልዘነጋችም።

ወደ አያን ጠረጴዛ ብሄድ ጥሩ ሲሳይ እንደገጠማት ተመለከትኩ። እንዱ ጥሩ አፒታይት የሌለው ሰው አስተርፎት የሄደው ጥሩ ቅቅል ገጥሟታል። የድመት እመጓ አልከለከለችኝም። ተጋራኋት።

ረሃባችንን በትርፍራፊ አስታግሰን ማደሪያ እንፈልግ ጀመር። የድመት መንጋ ገጥሞን ጦርነት እንዳይታወጅብን እየተጠነቀቅን፣ ከደናን ወደ ቀብሪ ደሃር የሚወስደውን አውራ ጎዳና ይዘን ከተጓዝን በኋላ ከከተማው መውጫ አካባቢ ከሚገኝ ቤት ጣራ ላይ ወጣን። ጣራው ላይ ሆነን፣ ደናንን ቁልቁል እየተመለከትን ለማጥቃት እንደተሰናዳ ወታደር አደፈጥን።

# ፴፱

የድመት መንጋ እንዳያጋጥመን ከፍተኛ ጥንቃቄ እያደረግን ካደርን በኋላ፣ የደናን ሰማይ ከመፍካቱ በፊት ከጣራው ላይ ተነሳን። የከተማው መብራት የፀደይ አበባ መስሏል- አደይ። በመብራት የደመቀው ደናን ወገግ ሲል ጉዱ መገለጡ አይቀርም።

ሰው እያለሁ ስለደናን ብዙ አውቃለሁ። ከጎዴ እስከ ጅጅጋ በተዘረጋው አውራ ጎዳና ላይ ካሉ ከተሞች አንዷ የሆነችው ደናን፣ ወደ አሥራ አንድ ሺህ የሚጠጋ ህዝብ ይኖርባታል። በድርቅ፣ በረሃብና በወንበዴዎች እንቅስቃሴ ምክንያት የተፈናቀሉ ሰዎች ደናን ውስጥ በተሠራ ካምፕ ተከማችተው ይኖራሉ። ከዚህም በተጨማሪ ደናን የምትታወቀው በከፍተኛ ሙቀቷ ነው። ለዚህም ነው በጣልያን ወረራ ወቅት ለእሥር ቤትነት የተመረጠችው።

ደናን፣ በከፍተኛ ገሃነማዊ ሙቀቷ ምክንያት ነበር ጣሊያን በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያን ሲወር ለማሳቃያ እስር ቤትነት የመረጣት። በግራዚያኒ ላይ በተቃጣው የመግደል ሙከራ ምክንያት የጣሊያን ባንዳ ኢትዮጵያን እየነዳ ደናን አውርዶ ያጉር ነበር። በዚህ ወቅት ወደ አራት መቶ የሚጠጉ እስረኞች ሙቀቱን መቋቋም አቅቷቸው አልቀዋል። የወባ በሽታ የፈጀውም ብዙ ነው። በዛ ወቅት ደናን የሞት ደን ሆና ነበር- የእልቂት ጫካ። ከወባውና ከከፍተኛው ሙቀቱ በተጨማሪ እስረኞቹ ያለቁት፣ ተገደው ነፍሳቸውን እስኪስቱ በሚሠሩት የጉልበት ሥራ ነበር።



ደናን፣ አሁንም ድረስ ወታደራዊ ካምፕ ይገኝባታል። በዚህ የሚያልፍ መንገደኛና መኪና ሳይፈተሽ ንቅንቅ አይልም። ለነገሩ ይህ በመላው ኦጋዴን የሚደረግ የየዕለት ተግባር ነው። ኦጋዴን ውስጥ በየአሥር ኪሎ ሜትሩ የፍተሻ ኬላ ማጋጠሙ የማይቀር ጉዳይ ነው።

"ድመቶች" ስለሆንን ኬላውን ሳንፈተሽ አለፍን። ደናንን ከነአሰቃቂ ታሪኳ ወደኋላችን ትተናት ሄድን። ከደናን ቀብሪ ደሃር ለመግባት አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ያህል የሚረዝመውን መንገድ መጓዝ አለብን። ለዚህም ነው፣ ሳይነጋ ጉዞ የጀመርነው። ጉዞ እንደገና ሰው ወደ መሆን…

ከደናን ወጣ ብሎ፣ ሳጥን መሰል ደሳሳ ጎጆዎች የፈሰሱበትን መንደር አለፍነው። እንዲህ አይነት መንደር ድመት በብዛት ስለሚኖርበት የፐርጅ ሥጋታችን አይሎ ነበር። ከመንደሩ ወጣ ብሎ ከርከሮ ባዶውን መሬት ሲግጥ ተመለከትን። አለፍ ስንል ደግሞ፣ ዥግራዎች በሰልፍ አውራ ጎዳናውን አቋረጡት።

ሰው እያለሁ ሲነጋ መመልከት ያስደስተኛ ነበር። በስተምሥራቅ የሚፈካውን ሰማይ በተስፋ መመልከት ያስፈነድቀኝ ነበር። አሁን ግን ንጋቱን ሳይ፣ የገባሁበት ድመት ማልቀስ ቢችል ኖሮ ተንሰቅስቄ እንባዬን ባንዠቀዠቅኩት። የኦጋዴን ምሥራቃዊ ሰማይ በሐምራዊ ቀለም ቢፈካም፣ ንጋቱ ንጋት አይደለም። አዲሱ ቀን አዲስ ተስፋ ይዞ አይመጣም። ትናንት ዛሬ የሚደገመው እዚህ ነው- ኦጋዴን ውስጥ- ኢትዮጵያ ውስጥ። በየሸንተረሩ በየሸለቆው የሚታየው ሁሉ የጦርነት አሻራ ነው።

የቆመው የብልፅግና ምልክት ሳይሆን የተቃጠለ መድፍና ታንክ ነው።

ወደ ቀብሪ ደሃር ማራቶናችንን ቀጥለናል። የመንገዱ ርዝማኔ፣ አበበ ቢቂላን መሆንን ያስመኛል። ውሃ አልባ ወንዞችን ተሻገርን። የአሸዋ ጅረቶችን አለፍን፤ የዕንባ ጠብታ ታህል ውሃ የሌለባቸውን ወንዞች።

ወደ ቀብሪ ደሃር ስንቃረብ እሳት የለበለበው ከመሰለው በረሃ ውስጥ ምላሱን የጎለጎለ የተኩላ መንጋ ሲወጣ ተመለከትን። ተኩላ ድመት ይበላል?... ነፍሴ አውጭኝ እንክንፍ ጀመር። በድንገት እንደ አቦ ሸማኔ ተወነጨፍን።





# ፴

ከምድረ በዳ አውሬ እግሬ አውጭኝ እያመለጥን ቀብሪ ደሃር ገብተን አደርን። አልፈናቸው ከመጣን መንደር ሊባሉ ከሚችሉት አነስተኛ ከተሞች ቀብሪ ደሃር ደመቅ ያለች ከተማ ናት። ወደ ስልሳ ሺህ የሚጠጋ ህዝብ ይኖርባታል። ከወልወል ግጭት በኋላ ጣልያን ወታደሮቹን ያከማችባት የነበረች ከተማ ናት።

ከቀብሪ ደሃር ወልወል ለመዝለቅ፣ በቆራሄ፣ በገረጉቤ፣ በዋርደር አድርጎ ወልወል የሚያስገባውን መንገድ መያዝን ይጠይቃል። ወደ ምሥራቅ አንድ መቶ ስልሳ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት አለው።

ወልወል ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር ነገር የፈለገበት ሥፍራ ነው። ከግጭቱ በፊት እንግሊዝና ጣሊያን ኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን ጥቅም ለማስከበር የጋራ ስምምነት ነበራቸው። የእንግሊዝ ሶማሌ ላንድና የኢጣሊያ ሶማሌ ላንድ ግዛቶቻቸው ከኢትዮጵያ ጋር በመዋሰኑ ምክንያት አንዱ ሽምጋይ አንዱ ተሸምጋይ በመሆን ኢትዮጵያን ሲፈታተኑ ቆይተዋል። የወልወል ግጭት በይፋ የተከፈተው በ1927 ዓ.ም፣ የኢትዮጵያና የእንግሊዝ የወሰን ኮሚሽን ወልወል በደረሰ ጊዜ ነበር።

ግጭቱ በይፋ የተጀመረው፣ የኢጣሊያ ባንዳዎች የወሰን አካላይ ኮሚቴውን በማስቆማቸው ነው። የወሰን አካላይ ኮሚሽኑን አጅቦ የሄደው የኢትዮጵያ ወታደር በበኩሉ፣

የባንዳዎችን እብሪት አይቶ ቀጣው ባነፈስ፡፡ ወልወል በወቅቱ ወደ አራት መቶ የሚጠጉና እያንዳንዳቸው ሃምሳ ሜትር ያህል ጥልቀት ያላቸው የውሃ ጉድጓዶች የነበሩባት ምድር ከመሆንም በተጨማሪ፣ ለግጦሹ መሬት ቅርብ በመሆንዋ ለበረሃው ነዋሪ ተመራጭ ነበረች፡፡ አካባቢውን ለመቆጣጠርም በወቅቱ ውሃና ግጦሽ ዋናው መሣሪያ ነበሩ፡፡ ከዚህም ሌላ በኋላ የሲንክላር ኩባንያ ነዳጅ ያስሰባት የነበረች በማዕድን የበለፀገች ምድር ናት፡፡

በአንደኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ፣ ሙሶሎኒ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ካሉበት ወልወል በተጨማሪ፣ የዋቢ ሸበሌ ተፋሰስን፣ ቆራሄን፣ ቀብሪ ደሃርን፣ ገረጉቤንና ፋፋን በሙሉ እንዲያዝ ለጦር አበጋዞቹ ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ የጣልያን ባንዳዎች ግጭቱን አውሮፕላን ላይ በተጠመዱ መትረዬሶች ከመጀመራቸው ነበር የወልወል ምድር በታንክ ትርገበገብ የጀመረችው፡፡ የኢትዮጵያ ጀግኖችም በቁመህ ጠብቀኝ አሮጌ ጠብመንጃቸው ወልወል ላይ ተዋደቁ፡፡ ቁጥሩ ወደ ሶስት መቶ የሚጠጋ ባንዳ ደሙ ወልወል ላይ ሲቀዳ፣ በኢትዮጵያ በኩል ግን ዘጠና ያህል ሰው ብቻ ነበር መስዋዕት የሆነው፡፡ ከዚህ ውስጥ የወልወሉ አውሎ ነፋስ አሲ ኑር ብቻ ከመቶ በላይ ባንዳ ፈጅቷል፡፡

የቆራሄው እጥር ግራዝማች አፈወርቅ ቆራሄ ላይ መሽጎ ለጣሊያን አውሮፕላኖች አልበገር ያለውም ከዚህ በኋላ ነበር፡፡ ግራዝማች አፈወርቅ የጣሊያንን አውሮፕላን በኦርሊንከን ሲጥል ሲሞክር ቢቆስልም ቁስሉ አልተሰማውም- የተሰማው ሀገሩ የመደፈሯ ቁስል ነበር፡፡ የቆሰለ እግሩን እየጎተተ በኦርሊንከን የሀገሩን ሰማይ ይጠብቅ ጀመር፡፡ ከሃያ በላይ አውሮፕላኖች ተመላልሰው በአንድ ቀን ብቻ በንብ ሲያዘንቡ፣ አርሊንከኑ ዝም ያለው





አፈወርቅ ደሙ ተንጠፍጥፎ አልቆ፣ በእናት ሀገሩ ምድር አፈር ላይ ሲደፋ ነበር፡፡

ቀብሪ ደሃር ውስጥ ለሁለት ቀናት ያህል ረፍት ካደረግን በኋላ ወደ ደገሃቡር ጉዟችንን ቀጠልን፡፡ የኢጋዴን ጦርነት ምልክቶች አሁንም ድረስ አካባቢው ላይ ይታያሉ፡፡ በሶስተኛው ኮማንዶ ጦር ነፃ ከመውጣቷ በፊት አስረኛው ብርጌድ የተዋደቀባት ቀብሪ ደሃር የአያሌ ኢትዮጵያውያን ቀብር ናት፡፡ ወደ ኋላችን ቀረች፡፡ ከቀብሪ ደሃር - ደገሃቡር ድረስ ያለው አውራ ጎዳና ሁለት መቶ ሃያ ያህል ኪሎ ሜትር ቢሆን ነው፡፡

በመኪና ሶስት ሰዓት ያህል የሚፈጀው መንገድ ለእኛ ግን ቀናትን ፈጀብን በዚህ ሁኔታ አዲስ አበባ እንዴትና መቼ መግባት እንደምንችል አሳሳቢ እየሆነብን መጣ፡፡ በእሳር በመከራ ደገሃቡር ስንገባ፣ ገለዲድ፣ ሻይጎሽ፣ ብርቆድ፣ ሽኮችና ቢርኮት ከሚባሉ ታናናሽ መንደሮች አድረን ነበር፡፡

# ፵፩

ድመት መሆናችን ባንድ በኩል ጠቅሞናል፡፡ ይህን የምለው ምናልባት ራሴን መቀበል ግዴታዬ ስለሆነብኝ ይሆናል፡፡ አሁን ሰው አይደለሁም፡፡ ድመት ነኝ፡፡ አውሬ ነኝ፡፡ ሰው መሆን ቢያቅተኝ ቢያንስ ጥሩ አውሬ መሆን አለብኝ- መልካም ድመት፡፡ የዘመኔ ሶበድዓቶች (ግማሽ ሰዎች ግማሽ አውሬዎች) ከሁለቱ አንዱን ቢመርጡ እንዴት ጥሩ ነበር! የኔዎቹ ባስቴቶች (ድመት ጭንቅላት ሴቶች) አንዱን ቢመርጡ እንዴት መልካም ነበር! ትውልዴ አንዱን ሊመርጥ አልቻለም፡፡ አውሬነቱን በሰውነቱ ውስጥ ሸፍኖ አልቻለም፡፡ እንደ ቁምጣ ያጠረ ግንጥል ማንነቱ የአውሬነት ቀንዱን ሊሸፍንለት አልቻለም፡፡

እኔ ድመትነትን ያስመረጠኝ የገጠመኝ ችግር ነው፡፡ አያንም ድመት የሆነችው በተመሳሳይ ችግር ምክንያት ነው፡፡ ከችግሩ ለማምለጥ አውሬነትን መምረጣችን ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡ ግን በከንቱ መሞት የለብንም ስል አስባለሁ፡፡ ህልም ያለው ሰው የችግሩን ወራት እንደ አውሬ ተቆጥሮ ቢያልፍ ነውር የለውም፡፡ የትውልዴ እጣ ፈንታ ይህ ሆኗል፡፡ ለዘመናት ተተክሎ ሥር የሰደደ ችግሩ አውሬ አድርጎታል፡፡ አሳሳቢ የሆነው ሰው ለመሆን አለመጣሩ ነው፡፡ ሰውነቱን ያልፈለገው አውሬ መሆኑ ክርሱን ለጊዜውም ቢሆን ስለሞላለት ነው፡፡ ሶበድዓት እና ባስቴት ሆኖ ግማሽ ሰውነትን ግማሽ አውሬነትን የወረሰው ትውልድ ምሉዕ ሰው የሚያደርገውን መድኃኒት የሚቀምምለት አጥቷል፡፡ መድኃኒቱ እንዲገኝ የፈለገም አይመስልም፡፡ ከህመሙ ብዛት የተነሳ ፈውስ የሚገኝለት ስላልመሰለው ተስፋ ቆርጦ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን





ምንጊዜም ቢሆን መድኃኒት ትንሹ ይበቃል፡፡ ግዙፉ ዝሆን ከህመሙ የሚድነው ባንዲት ትንሽ እንክብል ነው፡፡ ህመማችን ብዙ ቢሆንም መድኃኒቱ ትንሽ ነው፡፡

እኔና አያን ድመት ከመሆናችን የጠቀመን አንድ ሶስተኛ የሆነውን የሀገራችንን ክፍል፣ ህመሙን፣ ገበናውን፣ ስቃዩን በየጎራንጉሩ ገብተን ለማዬት ስላስቻለን ነው፡፡ ማህበረሰቡን ሰው ሆኖ ጠልቆ መመርመር ከባድ ሆኗል፡፡ ለዘመናት በጦርነት አሳሩን ሲበላ ፍዳውን ሲያነጉት በመኖሩ፣ ወዘልውጥን እንደ ዓይኑ ብሌን ይከታተላል፡፡ ይጠራጠራል፡፡ በሌላ በኩል የዚህን አካባቢ ልወቅልህ የሚሉት አባይ ጠንቋይ መሰል የዘመኑ ፖለቲከኞች የችግሩ አጋፋሪዎች ናቸው፡፡ ኦጋዴንን አለም ረስቶታል፡፡ ኦጋዴንን ድመት ሆነን ኦጋዴንም አለምን ረስቷል፡፡ ኦጋዴንን ድመት ሆነን ስናቋርጥ እየተመለከትን ያለነው ይህንኑ ነው፡፡

በጀረር ወንዝ ላይ የተሰራውን ድልድይ አቋርጠን ደገሃቡርን ወደ ኋላችን ትተናት ስንሄድ ጀረር ወንዝ ውሃ አልነበረውም፡፡ ከአሸዋ ክምር በቀር ጠብታ ውሃ የለበትም፡፡

ደገሃቡር በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ወደ በርበራ ወደብ ለሚደረገው ንግድ የሲራራ ነጋዴዎች መሸጋገሪያ ነበረች፡፡ የንግድ መስመርነቷ፣ ጎሳን መሰረት እያደረገ በየጊዜው በሚነሳው ግጭትና ብጥብጥ ባይተጓጎል ኖሮ፣ እንዲህ ኮስምና አትቀርም ነበር፡፡

ከደገሃቡር ወደ ቀብሪ በያህ ጉዟችንን ቀጥለናል፡፡ እርቃናቸውን የቆሙት ኮረብቶች አውሎ ነፋስ ይጥመለመልባቸዋል፡፡

አውሎ ነፋሶቹ እንዳይወስዱን እየተጠነቀቅን፣ ወደ ቀብሪ በያህ ስንጓዝ ሰው እያለሁ እሰማው የነበረው የንዋይ ደበበን ሙዚቃ የበረሃው አውሎ ነፋስ አስታወሰኝ፡፡ ስንኞቹን ሙሉ በሙሉ ባለስታውሳቸውም በድመት ጭንቅላቴ ውስጥ እያዜምኩት ወደ ቀብሪ በያህ መንቶስቶሴን ተያያዝኩት፡፡

በበረሃው አውሎ ነፋስ
በበረሃው አውሎ ነፋስ
በፈጣኑ ባየር ፈረስ
ገና ቡሄው መስቀል ሳይደርስ
ከደጅሽ ላይ ድንገት ልድረስ፡፡

...

ጥይት ያልበገረው በጦር ያልተፈታው
ውበትሽ ማረከው ሽንጥሽ ልቤን ረታው፡፡

...

ፈጣኑ አውሎ ነፋስ የበረሃው ፈረስ
አምጥቶ ከጣለኝ እዛው ደጅሽ ድረስ
ይቀመስ ጉሽ ጠላሽ
ይበላ እንጂ ዳቦሽ

...

ከማጀት አምባሽ ቀይ አምባ
ልብ ያለው ደፍሮ ከገባ
ፍሪዳ ስንጋው ተጥሎ
እንዲያው ሲያስጎመጅ ተንጋሎ
ታናሽ ታላቅሽ የት ጋ ነው
ለቁርጥ ይመቻል ጮማ ነው
ፍሪምባ ሻኛሽ ባዋዜ
አቤት ሲጣፍጥ ያን ጊዜ
ክትፎ ከጥሬው ሲመደብ
እንዲያው ጣድ አርጎ ሰብሰብ





ሰብሰብ ሰብሰብ
ከራበው ሆዴ ሲል ገርበብ
ለብርድ አንቺን ነው መደረብ

....

በሰማይ በምድሩ እከንፍልሻለሁ
ላውዳመት ጠብቂኝ እመጣልሻለሁ
እንግዲያው ባዋጅ በገሃድ
ነፍሴ ከነፍስሽ ሲዋሃድ
ባውሎ ነፋሱ ሞገድ
ተያይዞ ነው ማበድ
ጥርሶችሽ ደስታ ሲረጩ
ፍቅር እየቀዱ ከምንጩ
ላውዳመት ሞያሽ ሲገለጥ
ክትፎው ከዶሮው ሲመረጥ
ከጓሮ ቢሆን ከጓዳም
ለወዳጅ ቢሰጥ አይጎዳም
አይጎዳም አይጎዳም
ብትሰስችም ለሆዳም
መቼም አትሸሽኝም ባዳም፡፡

..በበሃው አውሎ ነፋስ....

እንኳን በድመት በሰው ፊት እንኳ ሲዘፈን ምራቅ የሚያስውጥ የሚመስለውን ዘፈን በውስጤ እያንጎራጎርኩ መንገዴን ቀጠልኩ፡፡ በዘፈኑ ግጥም ውስጥ ያሉት የሥጋ ብልቶች የሥጋ አምሮቴን ቀስቅሰው የበረሃ ምራቄን አስጨረሱኝ፡፡ ፍሪዳው፣ ፍሪምባው፣ ሻኛው፣ ክትፎው፣ ጥሬው... የሚሉትን ቃላት ሳስብ፣ ይህ አውሎ ነፋስ ተሸክሞ ወስዶ ሥጋቤት ደጅ ላይ ቢጥለኝ ተመኘሁ፡፡ በዘፈኑ ውስጥ የሚዘፈንላትና ሽንጥና ዳሌዋ የሚያማልለው ውበታም ሴት በሥጋ ዘሮች ውስጥ ተሰወረችብኝ፡፡ ምን ላርግ?! ድመት ነኝ፡፡ ለጊዜው ሥጋ

እንጂ ግብረ ሥጋ ሊያማልለኝ አይችልም። ግብረ ሥጋ ስል የድመት መንጋው ሥጋታችን ትዝ አለኝ።

የድመት መንጋ ገጥሞን አያን እንዳትሠረር አስቀድመን የሰጋነው ስጋት እንደ ኤሌክትሪክ ነዘረኝ። አያንም ያሰብኩት በቴሌፓቲ ደርሷት ድንገት ቀጥ አለች።

"ምን ይሻላል?" አልኳት በውስጤ በዓይኔ ህሊናዬ አንድ ድመት መጥቶ ሲሰራት እየታዬኝ። መሰረሯ ብቻ አይደለም እችሩ ...ታረግዛለች። ከዛም የድመት ግልገል ትወልዳለች።

"ያንት ያለህ!"

"እስካሁን የጠበቀን ፈጣሪ ያውቃል!" አለች ጭንቀቴ በቴሌፓቲ ደርሷት። "ይልቁንስ በጊዜ ቀብሪ በያህ መግባት አለብን እንፍጠን። ይልቁንስ መፍራት ያለብን ጭራሽ የዱር ድመት እንዳያጋጥመን ነው። ታግለን እንኳ ማምለጥ አንችልም። አስገድዶ ከሰረረኝ ማርገዜ አይቀርም። ከዛ ምን እንደሚፈጠር ታውቃለህ። ሰው መሆኔን አትርሳ። ድመት ወልጄ..."

"ተይ ተይ አትጨርሺው!" ፊቴን በድመት ጣቴ ሸፈንኩ። "በኩሯን የምትበላ የድመት አራስ...."

"...ይሰውረኝ!"

"ያ ከሆነማ የሀገሬ የኢትዮጵያ ተምሳሌት ሆነሽ ማረፍሽ ነው። በኩሯን የምትገድለው ጀግናዋን የምትቀብረው፣ የሀገሬ ተምሳሌት ...ድመት"

"እያድርስ ነው። ምናለ ያ የታጠቀ መጥረቢያ አንገቴን በቀነጠሰው!"

ሩጫችን ተያያዝነው። ወደ ቀብሪ በያህ... ሰው ወደ መሆን።





# ፴፪

እንዳሰብነው አልሆነም። እንዳለምነው አልተሳካም። በደገሃቡርና በቀብሪ በያህ መካከል አራርሴ ከተባለች አነስተኛ መንደር አድረናል። ከሁለት ቀናት ጉዞ በኋላ መሆኑ ነው ቀብሪ በያህ የገባነው። እየተዳከምን ነው። በእነዚህ ቀጫጭን እግሮቻችን ተቆንጥሮ የማያልቀው መንገድ እንኳን አዲስ አበባ ጅጅጋ እንኳ በቀላሉ ሊያስገባን አልቻለም። እንዲህ በቀላሉ ሰው መሆን አልተቻለም። አውሬ ለመሆን በፍጥነት የሚሠራው አስማት ሰው ለመሆን ግን ይለግማል። በእርግጥ ወደ ሰው የሚለውጠውን አስማት አልሞከርነውም። እንሞክር ብንል እንኳ ከአስማቱ የማውቀው ጥቂት ቃላት ብቻ ነው።

"የማያዛልቅ ፀሎት ጎን ያስደቃል" እንዲሉ ላያዛልቀኝ አስማቱን ማርከስ ይሆናል ብዬ በመስጋቴ ልሞክረው አልፈለኩም።

ቀብሪ በያህ ከሃያ ሺህ የማያንስ ህዝብ የሚኖርባት ከተማ ናት። የከተማዋ ነዋሪዎች አንድ እስካሁን ካለፍናቸው የኦጋዴን ከተሞች ለየት ያለ ጠባይ አላቸው። አዲስ ነገር ለማዎቅ ካላቸው ጉጉት የተነሳ ይሁን ወይም ሌላ፣ ግልብጥ ብለው ይወጡና መንገድ ዳር ይቆማሉ።

አንዱ የዚህ ከተማ ነዋሪ ከአንድ ምግብ ቤት በር ላይ ቆሞ ሚስቱን ወደ ቤቷ እንድትሄድ ሲለምናት አይቼ ተገረምኩ። ውርዬ አያን፣ ሶማልኛውን በቴሌፓቲ ጠልፋ ተረጎመችልኝ።

"ይህን ከተማ ጥለን መሄድ አለብን!" ይላታል በምሬት። "የሴቶቹም የወንዶቹም ጠባይ ተመሳሳይ የሆነበትን ይህን ከተማ ጥለን ካልሄድን መቼም አንለወጥም። ሴቶቹ ብዙ ነገር ያምራቸዋል። ወንዶቹ ማበድ ነው የቀራችው።"

"እቅም ያለው ሶስት ሚስት አግብቶ ሁሉንም እኩል ያስተዳድራል። ምነው አንተ ባንዲት በእኔ ተማረርክሳ?!"

"ሴትን ከማስተዳደር አገር ማስተዳደር ይቀላል። ሶስት ትያለሽ እንዴ ደግሞ! አንቺን እንዲቷንም አልቻልኩም። አየሽው ይህን ድመት?!" አለ እኔን ቁልቁል እየተመለከተ። "ሴት ማለት ድመት ያያት ሥጋ ማለት ናት።"

"ያያት እንዳይጎትታት ማድረግ ደግሞ የጀግኖች ሥራ ነው። ቀናህ እንዴ እዚህ ስቆም ጊዜ?"

"እም!...'የሃምሳ ሳንቲም ሥራ ሳይሠራ የብር ከሃምሳ ምሳ ሽሮ ደረሰ' አሉ!" ሰውዬው አግምትሞ እጁን ይታጠብ ጀመር። "እዚሁ ልብላ እንጂ እንግዴህ! ነይ በይ ታጠቢ እንብላ..."

"...እሺ አዘህ ጠብቀኝ መጣሁ..." አለችው እጇን ልትታጠብ እያጎነበሰች። መታጠቢያው ከውጪ ውሃ ተሞልቶ ደረጃው ላይ የተቀመጠ ቢጫ ጀሪካን ነው። ጎኑ በአስራ ሁለት ቁጥር ሚስማር ተበስቶ ራሱ ሚስማሩ ተወትፎበታል። ለመታጠብ ሚስማሩን መንቀል፣ ለመዝጋት ደግሞ የሚስማሩ አናት ቀዳዳውን እስኪደፍነው ወደ ጀሪካኑ ሆድ መግፋት ነው። ሴትዮዋ ታጥባ ከገባች በኋላ በማስታጠቢያው ጀሪካንና በሁኔታው እየተገረምን ጉዟችንን ቀጠልን። ሰው ብሆን ኖሮ ስቄ ባላበቃሁ።





ከተብሪ በያህ መውጫ ኬላ ላይ ሰዎች ተሰልፈው አየን። ኮሌራ ስለገባ ሰው በወታደር እየተገደደ መድኃኒት ይረጫል።

ይህን ካለፍን በኋላ ከመንገድ ወጣ ብሎ የሚታይ ነገር ተመለከትንና ወዳየነው ነገር አመራን። ያየነው ነገር አስገራሚ ቤት ነው።

ቤቱ የተሠራው ከታንክ ነው። በኦጋዴን ጦርነት ወቅት በቦንብ ከጋዬ ታንክ ውስጥ ሰው ይኖርበታል። እኔና አያን በቀዳዳው አጮልቀን ነዋሪዎችን ባናይ ኖሮ፣ የሰው ልጅ ተቃጥሎ በዛገ ታንክ ውስጥ ይኖራል ብንባል በፍጹም አናምንም ነበር።

"ያንት ያለህ!" አልኩ አጮልቄ ቤተሰቡን ካዩሁ በኋላ። "ከዚህ በላይ የኦጋዴንን ሰቆቃ የሚያሳይ ምን ነገር ይገኛል?!"

"ተመልከት! ...አየህ?! ...ይህ እየሆነ ያለው ከክልሉ ዋና ከተማ ጥቂት ኪሎ ሜትሮች ወጣ ብሎ ነው። የሰው ልጅ እዚህ ውስጥ ይኖራል። አፈር በልቶት ከቆመ ታንክ ውስጥ። አይ ኢትዮጵያ!..."

"...እኔ አፈር ልብላ..." ሰው ብሆን ኖሮ አልቅሼ ይወጣልኝ ነበር። ነገር ግን እንስሳ ነኝ። የሀገሬ ፈተና አውሬ ያደረገኝ ዕንባ አልባ ሰው። እንባ አልባ ድመት። በትካዜ ተውጠን መንገዳችን ልንቀጥል ዘወር ስንል በድመት መንጋ ተከበን ራሳችንን አገኘነው። ከታንኩ አፈሙዝ የወጣ አንድ ተልባ የመሰለ ድምት እንደ መድፍ ተተኩሶ አረፈብኝ።

# ፴፫

የፈራነው ፐርጅ ከታወጀብን ወዲያ ሁለት ምርጫዎች ብቻ ነበር የነበሩን:: ጠንክሮ መዋጋት ወይም እግሬ አውጭኝ ማምለጥ። ሁለቱም ቀላል አማራጮች አልነበሩም። መዋጋትም ማምለጥም ጥበብ ይጠይቃል።

አያን ውርዬ፣ አንድ አጎዛ የመሰለ ድመት ጋር ስትፋለም አየኋት። ሙርጧን አፈር ውስጥ ቀብራ የጨበጣ ውጊያ ላይ ናት። ድመቱ ከኋላ ዞሮ ሲወጣባት እያጓራ ይዞራታል። እርሷም እንደ ጣይቱ በር እየተሽከረከረች ከነጭ አፏ ውስጥ ያሉ ጥርሶቿን አግጥጣ በደመ ነፍስ ትፋለማለች። ከሠመረለት የሚፈጠረውን ነገር መገመት ቀላል ነው። ማሰብ አልፈልግም።

እኔን ዘሎ ያነቀኝ ድመት አንገቴ ሥር ክፉኛ ወግቶኛል። የውጊያ ልምድ ባይኖረኝም በደመነፍስ ነፍሴን ለማትረፍ ተፋለምኩ። የድመት መንጋ ከቦ ያዋክበኝ ጀምሯል። አቧራው ሲጨስ ለተመለከተ የድመት ሳይሆን የአንበሳ ጦርነት የተከፈተ ይመስላል። አንዱ አንደፋድፎኝ ሲሄድ ሌላኛው ይተካብኛል።

ሲጠናብኝ እግሬ አውጭኝ ተፈተለኩ። አየር ላይ የተንሳፈፍኩ መሰለኝ። በቅፅበት ዞር ብዬ ሳይ አጎዛ የመሰለው ድመት አያን ላይ ወጥቶባታል። "ያንት ያለህ!"





ተወንጭፌ ወደ አያን ተመለስኩ። ከኋላዋ የሞት ሞቴን ተወንጭፌ ... ሙርጧን ፍለጋ ያዶረዱራል። ጆራቱን ለቀም ወጥቶ ሙርጧን ፍለጋ ያዶረዱራል። ጅራቱን ለቀም አደረኩና በጥፍሮቼ ወግቼ ከጀርባዋ ላይ ጎትቼ አወረድኩት። እርሱ ወደፊት ሲስብ አያን ጅራቷን ቆልፋ ተፈተለከች። ለቅቄው በደመ ነፍስ ተከተልኳት። ደርሶባት ይሆን? ማለቴ...

እግሬ አውጭኝ ወደ አስፋልቱ ከሮጥን በኋላ ወደ ጅጅጋ የሚወስደውን አውራ ጎዳና ይዘን ስናበቃ፣ ወደ ኋላችን ተመለከትን። የድመቱ መንጋ እየተንጋጋ እንደ ተኩላ ሲከተለን ተመለከትን። ፍጥነት ጨመርን።

ገላዬ ተቦዳድሷል። ፀጉሬ ተነጫጭቷል። ደምቻለሁ። እንዲያውም ከእኔ አያን ትሻላለች። እሷን ለመስረር እኔን ነበር ክፉኛ ያጠቁኝ። ቁስሉ ብቻ አልነበረም ችግሩ። ስጋቴ አንድ በሽታ ይዞን ሰው ሳንሆን እንዳንሞት ነበር። በዛ ላይ የድመት እድሜ አጭር ነው። በአማካይ የድመት እድሜ ከአስር እስከ አስራ አምስት አመት አይበልጥም። በታሪክ የተመዘገበው በእድሜ ዘልዛላው ድመት በሰላሳ ስምንት አመቱ ነው የሞተው። እንደ እርሱ አርጅቶ ለመሞት በኑሮው የተቀማጠለና ሐኪም የሚቀጥር ባለቤት ያስፈልጋል። እኛ ግን በበረሃ እየባዘንን ነው። በዛሬው ጦርነት በተላላፊ በሽታ አለመለከፋችን ያጠራጥራል። ይህን የምናውቀው ስንሞት ብቻ ነው። በዛ ላይ ከሰው ወደ ድመት ስንለወጥ የገባንባቸው ድመቶች እድሜ አይታወቅም። በዚህ ሁኔታ አዲስ አበባ መግባታችን ያጠራጥራል።

# ፻፬

ጅጅጋ እንደገባን ከአንድ የግመል ምግብ ቤት ደጃፍ ላይ እንደጨርቅ ተሰጣን። በተለይ እኔ ላይ በታወጀው ፐርጅ ምክንያት አካሌ በመድቀቁ የምግብ ፍላጎቴ ድራሹ ጠፍቷል። እንኳን የተጋጠ አጥንት ቀርቶ፣ ድመት በልጇ ልትሰውጠው የምትችለው ወተት በጉሮሮዬ ቢንቆረቆር እንኳ መገርገጭ የምችል አይመስለኝም።

ሆኖም "ድመት መንኩሳ አመሏን አትርሳ" የተባለችበትና መንኩሳም ፆም የሚያስገድፋት ወተት ሲያምረኝ ይቀራል። እሱን ለማግኘት የዘላን ድመት መሆንን ይጠይቃል። እኔ ግን ወተት እንደ ውሃ ከሚደፋበት ዘላን ቤት የተፈጠርኩ ድመት ሳልሆን ችግር ከሰውነት ወደ አውሬነት የለወጠኝ የአስማት ፍጥረት ነኝ። ወደ አውሬነት የለወጠኝ ድግምት እንደ ገና ወደ ሰውነት ይለወጠኝ ይሆን? እንጃ!

ወደ አውሬነት መለወጥ ድጥ ቢሆንም ወደ ሰውነት መለወጥ ማጥ ሊሆን ይችላል። እሱም ቢሆን አስማቱ ከሰራ ነው። ታናሽ መሆን ቁልቁለት ሲሆን ታላቅ መሆን ግን ዳገት ነው።

አያን ወደ ምግብ ቤቱ ገብታ ስትልቀመቀም ቆይታ ተመለሰች።



"ብስ! ብስ! አንጀትሽ ይበስብስ!" የሚሉ ድምፆች ከውስጥ የሰማሁት ለዚህ ኖሯል። የአንዱን ተመጋቢ ሰውዬ የግመል አጥንት ይዛልኝ ከች አለች። ከእኔ ጉዳት የእርሷ ጉዳት ቀላል ነው። የተናቸፍኩበት የእግር ጥፍሬና አገጩ የወላለቀ ይመስል አጥንቱን የመጋጥ አቅም የለኝም።

አጥንቱን ካፌ ጥግ አስቀምጣ፣ ብይ የመሳሰሉ "ብሉንድ" ዓይኖቿን አቁለጨለጨች። አቅም እንዳጠረኝ ገብቷት ሀዘን ዓይኖቿ ውስጥ እንደ ጉም ሲረጭ ተመለከትኩ።

"እረ ጉድ ተመልከቱ!" አለ በመጥረጊያ ወገብ ዛላዋን ብሎ ያባረራት አስተናጋጅ እኛን እየተመለከተ። "ድመትም ይታዘዘናል እንዴ?!"

"ና! በል ወደ ሥራህ ተመለስ! ወሬኛ!" አለው ነጭ ጋዋን የለበሰው ሰውዬ። ኃላፊው መሆን አለበት።

"ወቼው ጉድ! ... ሰው መተዛዘን ባቆመበት ዘመን ድመት ሲተዛዘን ማየት ያስደንቃል።" እያለ መጥረጊያውን እያወዛወዘ ገባ።

እንደ ምንም ብዬ አጥንቱ ላይ ያለውን ሥጋ መላስ ጀመርኩ። የድመት ድካም፣ እንደ ውሻ ቁስል ቶሎ እንደሚድን ተገነዘብኩ። ከደቂቃዎች ማዋዛት በኋላም ከሥጋው መንጩት ጀመርኩ። በአያን ዓይኖች ላይ የደስታ መስመሮች ሲሰመሩ ተመለከትኩ።

ከውስጥ ተመጋቢዎች በሱማልኛ ቋንቋ ሲጯጯሁ ይሰማኛል። ጫጫታቸውን ለሰማ፣ በድብድብ ሶስተኛውን

የአሰም ጦርነት የሚቀሰቅሱት ይመስለው ይሆናል። እኩል እየተነጋገሩ እኩል መደማመጣቸው ለመጤ ሰው አጃኢብ ያሰኛል።

ከዛ ሁሉ መጯጯህ በኋላ ግን ሲወጡ እየተሳሳቁ ነው።

"እብሽር!"

"መርሃባ!"

ተቃቅፎ ተሳስሞ መለያዬት።

ከሸዋ መጥቼ ድመት ለሆንኩት ለእኔ የተከበርኩ ሰው ለነበርኩት፣ ይህ ሁኔታ ቢያስቀናኝ አይገርምም። የመሃል ሀገር ሰው ዱላ ቀረሽ ንግግር ከተነጋገረ በኋላ ቀጣዩን መገመት ቀላል ነው። አስከሬን ባይቆጠር እንኳ ጥርስ ሊለቀም ይችላል።

ለነፍሳችን መያዣ እንደምንም ከተልቀመቀምን ከሰዓታት በኋላ፣ ስለቀጣዩ ጉዟችን መነጋገር ጀመርን።

"ከዚህ በኋላ በፍፁም በእግር መጓዝ የለብንም!" አለች አያን በቴሌፓቲ። "አንዱ ድመት ሊሰረኝ ይችላል።"

"አልተሰረርሽም ማለት ነው?! ፈጣሪ ሆይ ተመስገን!" እንደ ዝንጺ ከተነጠፍኩበት መሬት በደስታ ኃይል ብድግ አልኩ።

"… ያ አጎዛ የመሰለ ድመት ..ወጥቶብኝ ነበር። ግን መርጡ የብልቴን ጫፍ ነክቶ ከመመለሱ በቀር ወደ ውስጥ አልገባም።"

"የዘር ፍሬው ነክቶሽ እንዳይሆን?…"

"አይመስለኝም።"





"አንድ ሀሳብ መጥቶልኛል።" አልኳት ጥቂት ካሰብኩ በኋላ።

"ምን አይነት ሀሳብ?"

"ሰው እያለሁ አንዲት ሴት ውሻ ነበረችኝ። በየጊዜው እየወለደች ቡችሎቿን መጣል ሲታክተኝና ከፈጣሪ እንዳያጣላኝ ስል ምን አደረኩ መሰለሽ?! …የውሾቹ የስሪያ ወቅት ደርሶ ውሾቹ ግቢዬ አካባቢ ሲከማቹ አንድ መላ መጣልኝ። ወደ ነጻጅ ማደያ ሄድኩና ዝቃጭ ይዤ መጥቼ ኋላዋን ቀባኋት።"

"ጥሩ ሀሳብ ነው!" አለች አያን። "… ስለዚህ ወደ ማደያ እንሂድና ኋላዬን መለቅለቅ እንችላለን።"

"በትክክል!… በነገራችን ላይ ድመቶች ብልሆች ናቸው። ቀደምት የሰው ልጅ ጠቢባን ስነ እፅዋትን ሳይቀር ያጠኑት የድመትን ብልሃት ተጠቅመው ነው። ለምሳሌ ድመት እባብ ከነደፋት፣ ወደ ዱር ትሄድና ቅጠሏን የምትበላት እፅ አለች። ይህን የተመለከተ አንድ ጠቢብ በድብቅ ተከታትሉ ድመቷ እባብ ከነደፋት በኋላ ከምትቀምሳት እፅ ለሰው ልጅ መድኃኒት ቀምሟል።"

በቴሌፓቲ እያወራን የነዳጅ ማደያ ፍለጋ ጅጅጋን አሰስናት። ከአሸዋና ከውኃ ላስቲኮች በቀር ምንም ጠብታ ውኃ በሌለበት በቶጋ ወንዝ ላይ የተሰራውን ድልድይ አቋረጥን።

ጅጅጋ በጥንቱ ጊዜ ከሐረር እስከ ዜይላ በሚዘልቀው የንግድ መስመር፣ የሲራራ ነጋዴዎች ማረፊያ ነበረች። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ሐረርና ሀርጌሳን የሚያገናኘው አውራ ጎዳና እምብርት ናት። በቶጎ ውጫሌ በኩል ሚገባው

ኮንትሮባንድና ሽቀጥ ማራገፊያ በመሆኗ ከክልሉ ከተሞች ሁሉ ደምቃ ትታያለች። ይሁን እንጂ ፍተሻዋ አይጣል ነው።

አያን በቴሌፓቲ ተግባቦት እንዳስረዳችኝ፣ ፍተሻው የጠነከረው የመንግስት ባለስልጣናት ጅጅጋን ማዕከል አድርገው በቶጎ ውጫሌ በኩል ወደ ውጪ ሀገራት ስለሚጠፉ ነው። አንዳንዶቹ ሀገርን ዘርፈው ሲሆን ሌሎቹ ግን ሥርዓቱን ተቃውመው ነው። ይሁን እንጂ ሌሎች ከሰሜን የሚመጡ ዜጎችም በዚህ በኩል ከሀገር ይወጣሉ።

ፍተሻው የጠነከረው በእርግጥ በዚህ ምክንያት ብቻ አይደለም። ኦጋዴን በነዳጅ ምክንያት የፍጅት ቀጠና እንዳይሆን ነው። ከዚህ የተነሳ መኪና እየቆመ በጥብቅ ይፈተሻል። ወዘ ልወጥ ብቻ ሳይሆን የከተማው ነዋሪም በገባ በወጣ ቁጥር ደጃ ላይ ሳይቀር የመፈተሽ ግዴታ አለበት። አንዲት የቤት ሰራተኛ ሱቅ ደርሳ እስክትመለስ ሶስትና አራት ጊዜ ልትፈተሽ ትችላለች።

ጅጅጋ የተመሠረተችው በፊታውራሪ ተክለ ሐዋሪያት ተክለ ማርያም ነው -በ1916 ዓ.ም። ይሁን እንጂ፣ በከተማዋ እምብርት ላይ የቆመው፣ የሰይድ መሐመድ ሐውልት ነው። ሐውልቱ አስፈሪ ጎራዴውን ወደ ሰሜን ቀስሮ ሲጋር ፈረሱ ላይ ተቀምጧል።

እንግሊዞች እብዱ ሙላህ እያሉ የሚጠሩት ሰይድ መሐመድ አብደላ ሐሰን፣ በአንዳንድ ሶማሌዎች ዘንድ "የሶማሌ ብሔር አባት" እየተባለ ይጠራል። የተወለደው በቀድሞዋ የእንግሊዝ ሶማሌ ላንድ ሲሆን፣ በ1899 ዓ.ም ከእንግሊዞች ጋር ተጣላ። ይኸውም "የኤደን ሥጋ ቤት" እያሉ ከሚጠሯት በርበራ ውስጥ የስቀመጡትን የጦር



መሣሪያ ሰርቀሃል በሚል ነው። ሐሰን ይህን መሣሪያ "ደርቪሽ" የተባለ ሶማሌዎችን ሁሉ አንድ ያደርጋል ላሰው ሃይማኖት ቀመስ እንቅስቃሴው ለመለመሳቸው ተከታዮቹ አስታጥቋቸው ነበር።

ይሁንና ጥቂት መሣሪያ ይዞ፣ ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ጋር ሲገጥም ጅጅጋን ወረረ። ሰይድ መሐመድ ከወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ ከምኒልክ ጋር ብቻ አልነበረም የተጣላው ከጣልያንና እንቅስቃሴውን ካልደገፉለት ሶማሌዎችም ጭምር ነው። ከሁሉም ተጣልቶ ኦጋዴን ውስጥ ሲኳትን የኖረው ሰይድ መሐመድ፣ ለሽምግልና የተላኩ 32 ሰዎችን ሳይቀር በአንድ ጎራዴ፣ ጎርዶ ጎርዶ ካስቀረ በኋላ እንደ እብድ በመቆጠሩ ዓላማው አልተሳካለትም። የራሱ ታጣቂዎች ሳይቀር በተደጋጋሚ ጊዜ ተበትነውበታል።

ተከታዮቹን እንደገና ይሰበስባቸው የነበረው በአስገራሚ ሁኔታ ቀስቃሽ በነበሩት ግጥሞቹ ነበር። እንግሊዞች "እብዱ ሙላህ" ያሉት ለዚህ ሳይሆን አይቀርም። ከሁሉም በአንድ ጊዜ በመጣላቱ። በመጨረሻም እብዱ ሙላህ "በእንግሊዞች አቆጣጠር" በ1920 ዓ.ም በኢንፍሉዌዛ በሽታ ኦጋዴን ውስጥ በ64 አመቱ ሞቷል። ይሁን እንጂ አስከሬኑ አልተገኘም። የክልሉ መንግሥት በቅርቡ አስከሬኑን አግኝቼ ቀብሬአለሁ ቢልም፣ የሰይድ መሐመድ አስከሬን ግን የት እንደደረሰ አልታወቀም።

ሐውልቱን ስመለከት ያለቦታው እንደቆመ ከማሰቤም በተጨማሪ፣ ለአርበኝነቱ ሳይሆን ለገጣሚነቱ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ከጎራዴ ይልቅ ላባ ባለመጨበጡ አላማውን እንደሳተ ደመደምኩ።

ይልቁንስ ሐውልቱን ሳይ ያስታወሰኝ ሌሎች ኦጋዴን ላይ የተዋደቁ ጀግኖችን ነው፡፡ የወልወሉን አውሎ ነፋስ አሊ ኑርን፣ የቆራሔውን መብረቅ አፈወርቅንና የኤል- ቡሩን አጥር ኡመር ሰመተርን…ነው ያስታወሰኝ፡፡

ኡመር ሰመተር፣ ጣልያን አድዋ ላይ ድል ከተደረገ ከአርባ አመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደገና ድል ያደረገ የሶማሌ ተወላጅ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ከወልወል ግጭት በኋላ የጣልያን ወራሪ ኃይልና የኢትዮጵያ መንግሥት እርቅ ለማውረድ ባደረጉት ድርድር፣

የጣልያኑ ተደራዳሪ፣ "ኡመር ሰመተር እጁ ተይዞ ይሰጠኝ ሲል ጥያቄ በማቅረቡ ድርድሩ ሳይሳካ ይቀራል፡፡

ኡመር ሰመተር ይህን ሲሰማ የተናገረው እስከ ዛሬ ሲዘከር ይኖራል፡፡ "ከአገሬ አፈር የሚደባልቅ ቤልጅግና ጎራዴ ይገኝ እንጂ ጫት ተሸክሜ የምመጣ እንዳይመስልህ!" የሚል መልዕክት ነበር ለጣልያን የላከበት፡፡

ከአፈወርቅ ሞት በኋላ በገርለ ጉቤ፣ በቆራሔ፣ በሽላቦ፣ በኤል-ቡር እና በጅጅጋ እየተዘዋወረ ጣልያንን መውጫ መግቢያ አሳጥቷል- ኡመር ሰመተር፡፡ ከኦሮሞ፣ ከሶማሌና ከአማራ የተውጣጣ የራሱ ቅንጅታዊ ጦር ነበረው፡፡ ይህንን የጀግና ስብስብ መርቶ ኤል-ቡር ላይ በ1930 ዓ.ም የጣልያንን ስድስት ባታሊዎን ጦር፣ በሌሊት አመድ በማድረጉ ከአርባ አመት በኋላ ጣሊያን እንደገና አስክሬኑን መቁጠር ሳይችል ቀርቷል፡፡ ለወሬ ነጋሪ የተረፉለት ብቻ እግሬ አውጪኝ አምልጠዋል፡፡

ጣልያን ድል ሆኖ ነፃነት ከተመለሰ በኋላ፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ንግግሩን አትሞት ነበር- የኡመር ሠመተርን፡፡





"የሀገሬን ህዝብ የፈጀው ጠላት በጀግኖች ክንድ ተረግጦ ሲወጣ በዓይኔ ተመልክቻለሁ፡፡ የመገዛት፣ የመዋረድና የመረገጥ እድል ምን እንደሆነ ተመልክቻለሁ፡፡ እንደ ንብ ከየምሽጉ እየገቡ የሚነድፉ ኢትዮጵያውያን ዘር በመሆኔ ኮርቻለሁ፡፡ በታሪክ የሰማሁትን የአድዋ ጀግኖች ጀብዱ ለማስመስከር ልጆቻቸው በኦጋዴን የጣሊያንን አንገት ሲቆርጡ አይቻለሁ፡፡ የዚህ ህዝብ ልጅ በመሆኔ አሁንም እኮራለሁ፡፡ የማዝነው ግን መላው ሶማሌዎች ተባብረው የአንዲት ኢትዮጵያ ልጅ ሆነው ባንድ ሰንደቅ አላማ ስር ሲጠቃለሉ ሳላይ መሞቴ ነው፡፡ ከመቃብርም ውስጥ ምኞቴ ይህ ነው፡፡" ይህ ነበር የጀግናው የመጨረሻ ቃል- የኡመር ሰመተር ቃል፡፡

የሰይድ መሐመድን ሐውልት አልፌ ስሄድ የኡመር ሰመተር ጅምፅ ከኋላየ ይጠራኝ ይመስል፣ የድመት ጆሮዬን እንደ ጦር ቀስሬ ወደ ኋላ እየዞርኩ ነበር፡፡ ትውልዴ ዋናውን ፈለጉን የማይፈልግበት ወይም እንዳይፈልግ የሚዘምተው ሥርዓት ሴራ ማሳያ የሆነውን ሐውልት አልፌን ከሄድን በኋላ፣ ነዳጅ ማደያ ፍለጋችን ቀጠልን፡፡ በድመት አእምሮየ ውስጥ የተመላለሰው ሀሳብ በሙሉ ለውርዬ በቴሌፓቲ ደርሷት ኖሯል፡፡

"ትውልዱ 'እይከን' ወይም ፈለግ እንዳይኖረው ለምን እንደማይፈለግ ይገባሃል፡፡ የማያንቀሳፉት ጠላቶቻችን ሴራ እንደ ኦጋዴን ነዳጅ ተገዝቶ አያልቅም" ጠላቶቻችን ሴራ እንደ ኦጋዴን ነዳጅ ተገዝቶ አያልቅም" "ለመሀል አለች ከፊት ለፊቴ ሱክሱክ ማለቷን አቁማ፡፡ "ለመሀል ሀገር ሰው ሶማሌዎች ኢትዮጵያን የሚወዱ አይመስለውም፡፡ እውነቱ ግን ተቃራኒው ነው፡፡ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለእናት ሀገሩ የተዋደቀ ሶማሌ ስፍር ቁጥር የለውም፡፡ እንዲያውም የጦርነቱ ሁሉ ቀዳሚ ገፈት ቀማሽ ነው፡፡

"በእርግጥ ኢትዮጵያዊነቱ እንዲሸረሸር ብዙ ተሰርቶበታል። ይህም ሆኖ በረሃብ፣ በድርቅና በችነፈር አሳሩን እየበላም ሀገሩን ይወዳል። በእርግጥ መገለል አልደረሰበትም ማለት አይቻልም። የተረሳ ህዝብ ነው። በቅኝ ገዥዎች ርዝራዥ አስተሳሰብ፣ ኢትዮጵያን እንደቅኝ ገዢ ሀገር እንዲያይና በጎሳ ጦርነት እንዲታመስ ተደርጓል። ቀደም ሲል በነበረውን የማዕከላዊ መንግሥት ልል ትስስር ሰበብ አድርገው ጮሌዎቹ ራሱን ገንጥሎ እንዲያይ ሰብከውበታል። የአሁኖቹ የፖለቲካ ኃይሎች በመንግሥት ስልጣን ውስጥ ከላይ እስከታች አንድ ጎሳ ደልድለውበታል። ሌሎችን ባይተዋር አድርገዋቸዋል። ኩታ እንጂ ችሎታ ዋጋ ያጣበት ሀገር ነው። ይህ ነው ችግሩ። አድሎ በሌለው መሰረተ ልማት፣ ራሱን ባሳተፈ ችግር ፈችነትና በትምህርት ኢትዮጵያዊነቱን መኮትኮት ያሻል።"

"ልክ ብለሻል የኔ ውድ..." ማደያ ስናይ ቀጥ አልንና እርስ በእርስ ተያይተን ወደ ነዳጅ መቅጃው ገሰገስን።

አያን ደህና ዝቃጭ ያለበትን ቦታ ፈለገችና በጥፍሯ ትጭረው ጀመር።

"ደግሞ ነዳጅ ልታወጣ ነው ተብሎ ወታደር እንዳይከብሽ" አልኩ በውስጤ። ዝቃጩ ላይ ቁጭ አለችበትና ቂጧን ለቅልቃው ተነሳች። በነጭ ገላዋ ላይ የታተመው ጥቁር ቀለም ዝንጀሮ አስመስሏት ነበር ስትመለስ። ከዚህ በኋላ የስሪያ ስጋት እንደማይኖርብን ተስፋ አደረግን። ነገር ግን አሁንም እርግጠኛ መሆን አንችልም።

ዘወር አለችና ተቁለጨለጨችብኝ።

"ሞክር እስቲ... ወንድ አደለህ እንዴ? ለማለት ይሆን?" የቴሌፓቲው መልዕክት አልደረሰኝም።

የሰው ጭንቅላቴ ከድመት ጭንቅቴ እውቀት ቀድቶ በቶሎ ቢያረጋግጥልኝ ስል ተመኘሁ። መፍራቴን አይታ፣

"ይህ ዘዴም ላይከላከለኝ ይችላል። ከዚህ በኋላ በእግር ጉዞ መቀጠል የለብንም። ገብተን ሰው እንሆናለን ብለህ አታስብ።"

"ታዲያ ምን ተሻለን?"

"አውቶብስ መሳፈር አለብን።"

"ሰው ብሆን ኖሮ እስቅ ነበር። ...እንዴት ነው መሳፈር የምንችለው?"

"ሌሊት ተነስቶ፣ ከጅጅጋ - አዲስ አበባ የሚጭን አውቶቡስ አለ። ሰውን ሁሉ ጭኖ፣ የተሳፋሪ እቃ ቀርቅቦ ካበቃ በኋላ፣ እኛ ከላይ ፖርቶ መጋላው ላይ እንወጣለን።"

"ጥሩ ሀሳብ ነበር። ግን አውቶብሱ ሲበር ነፋስ ወስዶን ብንነጣጠልስ?"

"እሱ ሌላ ጉዳይ ነው። የትኛውም መፍትሔ እንከን የለሽ አይደለም። ችግሩን አውቶቡሱ ላይ ከወጣን በኋላ እናያለን። ምናልባትም አውቶብሱ እቃ የሚያለብሰው ኬንዳ ይኖራል። እዛ ውስጥ ሰርስረን እንገባለን።"

"ሴት መለኛ ናት የሚባለው ሀሰት የለበትም። ድመት ስትሆን ደግሞ ይብስባታል ልበል?"

ወደ አውቶቡስ ተራ ሄደን መሸግንና አውቶቡሱ ሌሊት እስኪነሳ መጠባበቅ ጀመርን። ጉዞ ሰው ወደ መሆን።

# ሸ፯

ከጅጅጋ ወደ አዲስ አበባ የሚሄደው አውቶቡስ እያቃሰተ የካራማራ ተራራን ዳገት በመውጣት ላይ ነው፡፡ እኔና አያን ከላይ ፖርቶ መጋላው ላይ ነን፡፡ እቃው ከተጫነ በኋላ ነበር ወደ ላይ የወጣነው፡፡ ከዛም ኬንዳው ውስጥ ተወሽቅንና ከጅጅጋ በአውቶቡስ ወጣን፡፡

ካራማራ ዳገት ላይ ሆነን፣ ጅጅጋን ወደ ኋላ ዞረን ተመለከትናት፡፡ ሌሊቱ እየነጋላት ቢሆንም መብራቶቿ ገና አልጠፉም፡፡ ተስሎንቄን መስላ ትንቦገቦጋለች፡፡ ትናንት ዴማሷ ነበርኩ፡፡ ወደ ምሥራቅ ዓይኖቻችን አዞርን፡፡

በካራማራ ተራራ አናት ላይ ጉም ይንጎማለላል፡፡ ጥቅጥቅ ደመና ለመጀመሪያ ጊዜ ስንመለከት፣ የኦጋዴን የሰቆቃ ጉዟችን እዚህ ላይ ያከተመ መሰለን፡፡

ካራማራ በኦጋዴን ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያን መክቶ ከጠላት ያዳነ ባለውለታ ተራራ ነው፡፡ በአናቱ ላይ ጉም ሳይሆን ታሪክ ይንጎማለልበታል፡፡ የሶማሊያ ወራሪ ጦር እዚህ ድረስ ተስቦ ከመጣ በኋላ ነበር በኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ካራማራ ስር አፈር ድሜ በልቶ የተመለሰው፡፡ የመግደያ ቀጠና ውስጥ መግባቱን አላወቀም ነበር፡፡ ኢትዮጵያውንን ተራራ ላይ ማሸነፍ እንደማይቻል ለማሳያነት የተላከ ይመስል፣ በኦጋዴን ለጥ ያለ በረሃ





ውስጥ ሲጋልብ የነበረው የሶማሊያ ጦር ካራማራ ላይ ቀጥ አለ፡፡የኢትዮጵያ ጦር ከጎዴ ለቆ ከወጣ በኋላ በተለያዩ የሽምቅ ተዋጊ ጦሮች እየተመታ ካራማራን በማለፍ ቆሬ ላይ ነበር የማጥቃት ውጊያውን የጀመረው፡፡

የካራማራን ዳገት አውቶቡሱ እየወጣ ሳለ ነበር የጥላሁን ገሠሠን ቀስቃሽ ዘፈን ያስታወስኩት፡፡

"...ወደ ፊት በሉለት
ይለይለት!
ወደ ፊት በሉለት
ይለይለት!
የጀግና ሰው ክብሩ
ዳር ድንበሩ!
...
የጠላትን አገጭ
በሰደፍ ለማውለቅ
ቢያስፈልግ በሳንጃ
ልቡን ለመሰንጠቅ
ወደ ፊት በሉለት
ይለይለት!
ወደ ፊት በሉለት
ይለይለት!
...
የምን ጠላ ጠላ
የምን ጠጅ ጠጂ
ጠላትን መጨረስ
ቡናርን ነው እንጂ!
ወደ ፊት በሉለት
ይለይለት!..."

ይህን ቀስቃሽ ዘፈን፣ ሠራዊቱ በራዲዮ በቀጥታ እንዲሰማ ተደረገ። ከዚያም "ወደፊት"...ተባለ። የማጥቃት ትእዛዝ በዘፈን የተላለፈለት የመጀመሪያው ሠራዊት የኢትዮጵያ ሠራዊት ሳይሆን አይቀርም።

ከዚህ በኋላ፣ ከቆሬ እስከ ካራማራ ያለው ሸለቆና ሸጥ ጥይት እንደ ቆሎ ተዘራበት። አስከሬን ተደራረበበት። ከባድ መሣሪያዎች አጋሱበት። ታንኮች አሽካኩበት። መድፎች እሳት ተፉበት፤ ሞርታሮች አጓሩበት። የስትሬላ ሚሳዬሎችና የዙ 23 መትረዬሶች የካራማራን ሰማይ አረሱት። የመትረዬስ ጥይት የሚያዘንቡ ሄሊኮፕተሮች ተንደቀደቁበት።

በዚህ የእናት ሀገር ሰማይ ላይ፣ እነ ብርጋዴር ጀነራል ለገሠ ተፈራ፣ ኮ/ል በዛብህ ጴጥሮስ፣ ኮ/ል አምሃ ደስታ፣ ኮ/ል ንጉሤ ዘርጋው፣ ብርሃኑ ውቤነህ፤ ንጉሤ ዘርጋው፣ ተጫኔ መስፍን፣ ተስፋ ደስታ፣ መስፍን ኃይሌ፣ አሸናፊ ገብረጻድቅ፣ ኃ/ሚካኤል ብሩ፣... እንደ ንብ ተናደፉበት። ሚግ 21 እና ኤፍ.5 የጦር ጀቶቻቸውን እንደ ንሥር አሞራ አከነፉበት። የሶማሊያን ወራሪ ጦር ካራማራ ላይ አይቀጡ ቅጣት ቀጡት። በዚህ ተራራ ስር በአንድ ቀን ብቻ ከሶስት መቶ በላይ አስከሬኑን አስቆጠሩት። በአየር ላየር ትንቅንቅ የጦር ሚጎቹን ወደ ነበልባልነት ቀየሩበት። ብ/ጀነራል ለገሠ ተፈራ ብቻውን አምስት የሶማሊያን ጀቶች ወደ ነበልባልነት ቀይሯል። በምድር ደግሞ የእናት ሀገር ልጆች ከጠላት ጋር በሳንጃ ተማትረዋል። የኩባ ዘማቾች ሳይቀር በካራማራ ተራራ ስር  ለቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ተዋድቀዋል።

ከዚህ በኋላ ነበር የኦጋዴን ቆንጥሮች ልብሱን ወደኋላ እየገፈፉት እግሬ አውጭኝን እስከ ሞቃዲሾ የቀጠለው።





ካራማራ የዚህ ሁሉ ቃፊር መስሎ በዝምታ ወደኋላችን ቀርቷል።

በኦጋዴን ምድር ላይ የፈሰሰውን ደምና የተከሰከሰውን አጥንት ከካራማራ በላይ ምስክር የሌለ ይመስል ጉም ጋቢውን ተሸፋፍኖ ይተክዛል። አሁንም ድረስ፣

"... ተጉዞ ተጉዞ እንደ ጆፌ አሞራ
መመለሻው ጠፋው ያገሩ ጎዳና" የሚለውን ሽለላ

የሚያግተመትም ይመስላል።

አውቶቡሱ ወደፊት ሲገሰግስ የእኔና የእያን አእምሮ ግን ከካራማራ በር ላይ ቀረ። የኦጋዴን ምድር ሰቆቃ አንቆ አስቀረን። ቻው ቻው ኦጋዴንያ!

አውቶቡሱ ባቢሌን አልፎ መጋለቡን ቀጠለ። ከጅጅጋ - ሐረር ድረስ ካለው ሰማኒያ ኪሎ ሜትር ውስጥ ሃምሳ ያህሉን ተጉዘናል ማለት ነው። ሐረር ለመግባት ገና ሰላሳ ያህል ኪሎ ሜትር ይቀረናል።

ከባቢሌ አለፍ ብሎ የቋጥታ ሸለቆ ይገኛል። "ተአምራዊዉ ሸለቆ" እየተባለ ይጠራል። የድንጋዮች ተአምር የሚታይበት ምድር ነው። በአስገራሚዎቹ የእሳተ ገሞራ ቋጥኞች ትርኢት እየተገረምን ስናልፍ፣ እኔና እያን ሰው ብንሆን ኖሮ እንተፋፈር ነበር።

ከተዛዙለት ቋጥኞች ውስጥ የወንድን ብልት መስሎ የተገተረው ይገኝበታል። የምድር ብልት ይመስላል - እንደ ጠዋት እንትን ተገትሮ ሽቅብ ሰማይን የሚያይ ቋጥኝ። የብልቱ እናት ከዘንጉ ላይ በምን ተአምር እንደቆመ የትኛውም ሳይንቲስት መተንተን የሚችል አይመስለኝም። በዘንጉ እና በእናቱ መሃል ጣት የምታክል ነገር ነች

ታላቁን ቋጥኝ ለዘመናት ሚዛኑን የጠበቀችው፡፡ እስከ ዛሬ ከርክርና ጨብጥ ያልጎበኘውን እንትን አለፍነው፡፡

ድንጋይ የፈሰሰበትን ምድር አልፈን ስናበቃ፣ አስገራሚዎቹን የተራራ ቅርጾች እያየን ወደ ሐረር ገሰገስን፡፡ አውቶብሱ ለቁርስ ሐረር ሲቆም እኔና አያንም ወጉ ይድረሰን ብለን ወረድንና ሐረር ከተማ ውስጥ መልቀምቀም ጀመርን፡፡

በታሪካዊቷ የሐረር ከተማ ውስጥ የሐረር ስንጋ ከሚበላባቸው እውቅ ሥጋ ቤቶች ካንዱ ደጅ መጥናት ቀጠልን፡፡ አንዱ ቁርጥ የሚበላ ሰውዬ እየመተረ ሲጥልልን ሰው እያለሁ ተከብሬ የጎበኘሁት ሐረር ድመት ሆኜም ፍቅሯን ባለመክልከሏ በድመት ልቤ መረቅኂት፡፡

ሰው እያለሁ የጀጎል ግንብንና የእውቁ ባለቅኔ አርተር ራምቦ መኖሪያ የነበረውን ቤት መጎብኘቴን አስታውሳለሁ፡፡ በሐረር ፍቅር ተነድፌ ወደ አዲስ አበባ መመለስ ስላቃተኝ ራስ ሆቴል ውስጥ ለበርካታ ቀናት ተቀምጫለሁ፡፡ በሆቴሉ ግድግዳ ላይ በሚገኙት የአለ ፈለገ ሰላም ስዕሎች ፍቅር ተይዤ እንደነበርም አስታውሳለሁ፡፡

አውቶብሱ ከመንቀሳቀሱ በፊት ፖርቶ መገላው ላይ እኔና አያን ወጥተን አደፈጥን፡፡

"ሰው ከሆንኩ እመለስብሻለሁ" አልኩ በውስጤ- አውቶብሱ ሐረርን ለቋት ሲወጣ ወደኋላ ዞሬ፡፡

አውቶብሱ መስከሩን ቀጥሏል- ወደ አዲስ አበባ፡፡ ከሐረር ቀጥሎ አለማያን አለፈ፡፡ ደንገጎ ዳገት ስር ወደ ቀኝ ድሬዳዋን ትቷት ወደ ቁልቢ ገሥገሠ፡፡ ከዛም ካራሚሌን፣





ቦረዳን፣ ሂርናንና ጨለንቆን አልፎ አሰበ ተፈሪ ቆመ፡፡ እኔና አያን እዚህ አልወረድንም፡፡ ካንዱ ሥጋ ቤት በር ላይ ስንቁለጨለጭ ጥሎን ይሄዳል ብለን በመስጋታችን ተሳፋሪዎች የሚቀማምሱትን ቀማምሰውና ውሃ ይዘው እስኪመለሱ የፖርቶ መጋላውን ኬንዳ ሙጥኝ ብለን ጠበቅን፡፡

አውቶብሱ ተንቀሳቀሰ፡፡ ሜኢሶን፣ አዋሽን፣ መተሃራን፣ ወለንጪቲን… ሲያልፍ ውሎ ናዝሬት እስኪገባ እኔና አያን ፖርቶ መጋላው ውስጥ እንደተሸጎጥን እንቀላፍተን ነበር፡፡

ድመት ሲተኛ መላ አካሉ እንደውሃ ፍስስ እስከሚል ነገር አለሙን ረስቶ ነው፡፡ ምሥራቃውያን የዮጋን ጥበብ ከድመት ሳይቀስሙት አይቀርም፡፡ አገር አቋራጩ አውቶቡስ ናዝሬት ላይ ጥቂት ከቆመ በኋላ፣ በፈጣኑ መንገድ በኩል ወደ አዲስ አበባ ይከንፍ ጀመር፡፡

የማታ ማታ አዲስ አበባ ገባንና መስቀል አደባባይ ላይ ተራገፍን፡፡ አብዮት አደባባይ ስንደርስ የኢጋዴን ትውስታዬ ይበልጥ በረታ፡፡ ሰኔ 18 ቀን 1969 ዓ.ም በዚህ አደባባይ የነበረውን ሰልፍ ልጅ ሆኜ ተመልክቻለሁ፡፡ ህዝባዊ ሠራዊቱ እያዜመ የነበረው ቀስቃሽ ዝማሬ አሁንም በጆሮዬ የተንቆረቆረ መሰለኝ፡፡

"…. ይህ ነው ምኞቱ
እኔ በሕይወቴ
ከራሴ በፊት ለኢትዮጵያ እናቴ…"

በብዙ ሺዎች የሚቆጠረውና፣ 'ኢትዮጵያ ራሷን ለመከላከል ቀርቶ አፍሪካን መውረር የሚችል ሠራዊት ገንብታለች' ተብላ የታማችበት ህዝባዊ ሰራዊት ሰልፍ በድመት ዓይኔ

ላይ ድቅን ብሎ አብዮት አደባባይ ላይ ጥቂት ከቆምኩ በኋላ እያንን አስከትዬ ወደ ቤቴ ከነፍኩ:: ልቤ መምታት ጀመረ:: አስማቱ ባይሰራስ? እንደገና ሰው መሆን ባንችልስ?





# ሣጌ

አዲስ አበባ እያንጎላጀች ነው:: መሽቷል:: ከቀበና ወንዝ ማዶ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤቴ ደረስን:: የሁለታችንም ልብ እየመታ ነው:: ዶፍ ዝናብ እየወረደ ነው:: ሰማዩ በመብረቅ ልባችን በሥጋት ይታረሳል::

የግቢውን አጥር ተንጠላጥለን ገባንና ከዘበኛው ቤት ጥግ ተወሸቅን:: ዝናቡ ቀስ በቀስ ጋብ አለ እንጂ አላባራም:: ግቢው ፀጥ ረጭ ብሏል:: ልጆቼ እንዴት ሆነው ይሆን? ጥያቸው ስጠፋ በናፍቆት ዓይኖቻቸው ጎድጉዶ ይሆን? ውሻ እያለሁ እንደተፈጠረው ሞቷል ብለው በሀዘን ተቆራምደው ይሆን? ... ከዘበኛው ቤት ውስጥ ድምጽ የሰማሁ መስሎኝ ጆሮዬን እንደ ጦር ቀሰርኩ::

"ወይ ድፍረት!" ይላል በተደጋጋሚ:: መሮ ነው- ዘበኛዬ:: እስከ ዛሬ ከጎኔ አልተለየም:: ድህነቱ ክብሩን አላስጣለውም::

"የድፍረትም ድፍረት እንጂ!" ቀለብ ናት- ሰራተኛዬ:: የዛሬ አራት አመት አካባቢ ከውሻነት ወደ ሰውነት ከተለወጥኩ በኋላ ልጆቼንና እነሱን ይገፍ ነበር ወደዚህኛው ቤቴ የመጣሁት:: ያኔ ሚስቴ ጓደኛዬን አግብታ ነበር የጠበቀችኝ:: ደግሞ ዛሬ ምን ተፈጥሮ ይሆን? የኔ ጉድ አያልቅም መቼም::

"እንዲያው ይቅር ይለኛል ብላ ማሰብዋ በራሱ ተአምር አይደለም?" ይላል መሮ በግርምት::

"ደፋር ናት! በጣም ደፋር ናት!" ትላለች ቀለብ:: "ያን ሁሉ በደል እንዴት ይረሳልኛል ብላ አሰበች በፈጣሪ?! ... ሰው ሁሉ ዓይኑን በጨው ማጠብ ይችልበታል! በዳይ

ሆኖ ሳለ የተበደለ መስሎ እንደሚቀርብ ሰው ልዩ ችሎታ ያለው ያለ አይመስለኝም::"

"በባሏ ላይ ያውም ጓደኛውን፣ ያውም በምድር ላይ አንደኛ ባላንጣ የሆነውን ሰው መወሽሟ ሳይቀር፣ በኋላ ደሞ ሳይሞት ሞቷል ብላ በላዩ ላይ ማግባቷ ሳያንስ፣ ... አሁን ደግሞ ሁሉን ንብረቷን ሻሽጠ አፍንጫሽን ላሽ ካላት በኋላ መምጣቷ... ከኤፍራታ በላይ በምድር ደፋር እንደሌለ ያሳያል::"

"ሁልጊዜ ይቅርታ ይደረግልኛል ብሎ እንደሚያስብ ሰው ደደብ የለም:: ደደብ ናት! ሙት መሮ... ኤፍራታ ማለት ወፍ ራስ ነገር ናት:: ያን ሁሉ ንብረቱን ሙልጭ አድርጋ በዋና ጠላቱ ካስወሰደችበት በኋላ፣ በራሱ አልጋ ላይ ከማገጠችበት በኋላ፣ ይቅርታ ሳይገባት በቀልን ለፈጣሪ ሰጥቶ ሁሉንም ትቶላት፣ ልጆቹን ይዞ ከወጣላት በኋላ፣ አሁን ያ መናጢ ሜንጦ ጉድ አድርጓት ሲሄድ ዓይኗን በጨው አጥባ ይቅር በላኝ ብላ መምጣቷ እንዴት ያለ ድፍረት ነው?"

"ጋሼ እንደገና ይቅር ካሏት ይገርመኛል! በጣም ይገርመኛል::"

ገባኝ:: ኤፍራታ ወደዚህኛው ህይወቴ መጥታለች:: ያ ክፉ ጠላቴ ሜንጦ ያላትን ሁሉ ሻሽጦ ካገር ጥሏት ጠፍቷል:: ከነመሮ በሰማሁት መረጃ መሰረት፣ 'እሰይ ደግ አደረገ' ስል በውስጤ ጮቤ ረገጥኩ:: ሰው እስክሆን ቸኮልኩ:: የድመት ፀጉሬ እስኪቆም እሳት ለበስኩ፤ እሳት ጎረስኩ:: አያንን አስከትዬ ወደ ጥናት ክፍሌ በረርኩ:: ተቆልፏል:: በየት ገብቼ ያንን ከአውሬነት ወደ ሰውነት የሚለውጠውን አስማት ባገኘሁት?





# ሻጊ

አልነጋ አለኝ:: የጥናት ቤቱ በር እስኪከፈት፣ ብይ የመሳሰሉ ዓይኖቼ ሲንከራተቱ አደሩ:: እንዴ ሰማዩን እንዴ ምድሩን ሌላ ጊዜ ደግሞ በር በሩን ስመለከት ኢደርኩና አይነጋ የለም ነጋልኝ::

አዲስ አበባ እንደለመደባት መንጫጫት ጀመረች:: ከሩቅ ካለ ቤተክርስቲያን መዝሙር ይሰማኛል::

"…. አለፍኩት ስንቱን
ማዕበሉን..."

ከመስጅድ ደግሞ አዛን::

"አላህ ወአክበር!"

ውሾች ማላዘን ጀመሩ፤ የታክሲ ወያላዎች ተሳፋሪ መጥራት ጀመሩ፤ ሥጋ ቤቶች ቢላ ማፋጨት ጀመሩ፤ ህይወት እንደገና….

ከዋናው ቤት አንዲት ሴት ስትወጣ ተመለከትኩ:: ኤፍራታ ናት:: ከስንት ጊዜ በኋላ አየኋት? ሐምራዊ የሌሊት ልብስ ለብሳለች:: ባጥንቷ መቆሟን ያየሁት የጥናት ቤቱን ለመክፈት ባጠገቤ ስታልፍ ነበር:: የሆነ ነገር ታንጎራጉራለች ምን እንደሆነ አይሰማኝም::

የጥናት ቤቱን ከከፈተች በኋላ፣ የሆነ እቃ አንጠልጥላ፣ አሁንም እንጉርጉሮውን እንደቀጠለች ተመለሰች። በንጋቱ ብርሃን ፊቷን ተመለከትኩት። መንፈሷ ተሰብሯል። ያ እንክይ ይመስል የነበረ ጉንጯ ከክሳቷ የተነሳ እንደ ባቢሎ ቋጥኝ ገጧል። ለእኔ የወረወረችው የክህደት ጦር ተመልሶ እንደወጋት በግልፅ ይታወቅባታል። ወደ ዋናው ቪላ ስትገባ ኋላዋን ተመለከትኳት። ያ ሞንዳላ የነበረ ዳሌዋ ሟሽሾ እንደ ጣፊያ አጥንቷ ላይ ተለጥፏል።

ባንድ በኩል ሀዘን በሌላ በኩል በቀል ሰንጎ ያዘኝ።

'ምን ልትሠራ መጣች? ለምን አትተወኝም? ለምን?! ለምን የራሴን ህይወት እንድኖር አትተወኝም? አንዳንድ ሰዎች የማንማርባቸው ስህተቶቻችን ናቸው። እስከሰተ ሞታቸው እንደ ጅራት የሚከተሉን ጭራዎች።' የድመት ፀጉሬ ቆመ። ወደተከፈተው በር እንደ ጥይት ተተኮስኩ። አያንም ተከተለችኝ። በቀጥታ የገሰገስኩት የአስማት ጥቅሎችን ወደማስቀምጥበት ሳጥን ነበር። ተከፍቷል። በድንጋጤ ደርቄ ቆምኩ። የአስማት ጥቅሎቼን አውጥታ ጥላቸው ይሆን? ዘልዬ ሳጥኑ ውስጥ ገባሁ።



# ሻጇ

የአስማት ጥቅሎች የሚገኙበትን ሳጥን በደመ ነፍስ ሳተረማምሰው ቆየሁ። ሳጥኑን ለምን ከፈተችው? ምናልባት የተፈረመበት ቼክ ፍለጋ ይሆናል። እርሷ ከእኔ ገንዘብ እንጂ ሌላ ምን ፈልጋ ታውቃለች? ያ የድሮ አመሏ በድግምትም በጠበልም ይለቃት አይመስለኝም። ያ ሜንጦ ጥሪት ገንዘቧን በልቷት፣እርቃኗን ጥጥሟ አስቀርቷታል። ከዛ እንኳ አለመማሯ ይገርማል። የክህደትን ጽዋ ተጎንጭታ እንኳ ከክፉ ተግባሯ አልታቀበችም። ክህደትን የመጋት እንጂ የማጣጣም አቅም ባይኖራትም፣ ያ ከሃዲ ስለካዳት ደስ ብሎኛል። ከሃዲዎች በሰፈሩት ቁና ሲሰፈሩ ከማየት የበለጠ ለተከዳ ሰው ካሳ ያለ አይመስለኝም።

በእርግጥ ኤፍራታ ከሳጥኑ መክሊት እንጂ እውቀት አለመፈለጓ ጠቅሞኛል። ጥቅሎችን አተረማምሳ ስታበቃ፣ የፈለገችውን ስታጣ ሳትቆልፈው ሄዳለች። ለእርሷ እነዚህ ጥቅሎች ተራ መጥቁሎች ናቸው።

ጥቅሎቹን ተራ በተራ በድመት ጥፍሬ እየተረተርኩ መመልከቱን ቀጠልኩ። አያን በነጭ ቅንድቧ ጉድጓድ ሥር የተቀበሩ ዓይኖቿን በልጥጣ ትመለከተኛለች። ሰው የመሆን ጉጉቷ ከእኔ ሳያይል አይቀርም። ወደ ድመት ከሚቀይረው አስማት በታች "ምልዋጡን" ተመለከትኩት። እንደገና ወደ ሰው የሚለውጠውን አስማት። ከደስታዬ

ብዛት በስሜት አስማቱን ላስኩት፡፡ አያንም በድመትኛ ፊነጨች፡፡

"... አዛሂል አዛሂል አዛሂል...." ሲል ይጀምራል አስማቱ፡፡

"...ካርናስኤል ኩርናስኤል ኪርናስኤል
አብዮስ አብዮስ አብዮስ
ማራስ ታራስ ጋማስ
ኤላስ ኤላስ ኤላስ
ሳልመን አልመን ሳሊመን
ሙኪን ላኪን አኪን
ሚጥ ሚጥ ሚጥ
እም እንስሳ ሃበ ሰብዕ
ሚጠነ እምእንስሳ ሃበ ሰብዕ
ቤቃ ሌቃ ሴቃ
ሚጠነ እምተዋርዶ ሃበ ክብር
ዮርኤል ሱራኤል ኢዙኤል
ሚጠነ እም አርዌ ሃበ ሰብዕ
በርደለጊስ በርደለጊስ በርደለጊስ
በርጀለሲስ በርጀለሲስ በርጀለሲስ
መግሪዳ አግሪዳ አግሪዳ
ሚጠነ እምአርዌ ሃበ ሰብዕ..."

የአስማት ጥቅሉን ከሳጥኑ ይዤ ከወጣሁ በኋላ ወለሉ ላይ ዘርግቼ አነበንበው ጀመር፡፡ አያን እንደ ባለፈው አልከበዳትም፡፡ ከውስጧ የፈነቀላት ሰው የመሆን ስሜት እያንዳንዱን ቃል በጥሞና እንድታይ አደረጋት፡፡ ሰው የመሆን ጥማት... በአፊ እንስሳ ታነበንብ ጀመር፡፡



# ፵፱

ከውጪ እንደገና ዶፍ ዝናብ ይወርዳል፡፡ የመብረቁ ብልጭታ በመስኮት በኩል ሲገባ ነበልባል የሚለቅብን ይመስላል፡፡ አስማቱን በደጋገምነው ቁጥር ነጎድጓዱ እያየለ መጣ፡፡ ምድሩ በነጎድጓዱ ሲርገበገብ ሰማዩ በመብረቅ ሲናጥ እኔና አያን ሰው የመሆን ምጣችን ቀጠለ፡፡ ምጣችን ጠና፡፡ ሰው የመሆን ምጥ፡፡

አያን አስማቱን እያጠናች ሳለ፣ ትውልዱ በሙሉ ይህን አስማት ቢያውቀው ስል ተመኘሁ፡፡ ሰው የሚያደርገውን አስማት፡፡ በውስጡ የሸሸገውን እውሬነት የሚያስወጣለትን አስማት፡፡ የሰው መልክ የነሳውን የተሸፈነ አውሬነት የሚነቅልለትን አስማት፡፡ ሰውነቱን ያረከሰውን አውሬነት ያቃባውን መንፈስ እርቃን የሚያወጣለትን አስማት፡፡

ባስቴት... ድመት ራስ ሴት... ወይ ድመትነቷን ወይ ሴትነቷን የሚያረጋግጥላትን አስማት... ሰበድዓት... ወይ ሰውነቱን ወይ እባብነቱን እንዲነጥል የሚያደርገውን አስማት... ትውልዱ ቢያውቀው ምን አለበት?

ሰባኪው ... እንዲህ ብሎ ቢሰብክስ?

"ባስቴት ሆይ ... ጭንቅላትሽን የሞላውን አውሬነትሽን ተይ!... ሰበድዓት ሆይ ... ግማሽ አውሬነትህን ጣል!... ሰው ሁን! አውሬው ሆይ ትውልዱን ጥለህ ውጣ! ... የታፈረውን የተከበረውን ኢትዮጵያዊ ሰው ወደ አውሬነት የቀየርህ መንፈስ ውጣ! ... በሥላሴ ስም ውጣ! በጌታ ስም ውጣ! ስለ አሳህ ብለህ ውጣ!..."

... ጉርምርምታው ምድርን ሲያንቀጠቅጥ መብረቁ ሰማዩን ሲንጥ እኔና እያን አስማቱን መድገማችንን ቀጥለን ነበር።

".... ዬናዌ አርዌ አክሴ
ጰራቅሊስ፣ ቴርናስ፣ ኢክናስ
ሚጥ እምአርዌ ሃበ ሰብዕ
ሚጥ እምግባረ እንስሳ ሃበ ምግባረ ሰብዕ..."

በዚህ ቅፅበት የጥናት ክፍሉን የሚያርበደብድ ንውፅውፅታ ተፈጠረ። መብረቅ የወደቀ ይመስል አካባቢው ድብልቅልቁ ወጣ። ወጀቡ ጣሪያውን ሲነቅለው ደረሰ። የአስማት ጥቅሉ ወደላይ ተንሳፈፈ። ሁለታችንንም የማናውቀው ኃይል አየር ላይ አንሳፎ ከመጽሀፍ መደርደሪያው ጋር አጋጨን። የማስታውሰው በአያሌ መጻህፍት የተሞላው መደርደሪያ ወድቆ፣ ወለሉ በመጻህፍት ሲሞላ ነው። ከዚህ በኋላ የሆነውን ሁሉ አላስታውስም።





# ፶

ከሰዓታት በኋላ ካለሁበት ልዩ ዓለም ውስጥ ነቃሁ። የተጫነኝን የመፃህፍት ክምር ፊነቃቅዬ ተነሳሁ። መለመላዬን ነበርኩ- ዕርቃኔን። አላመንኩም። ወደ ሰውነት ተለውጫለሁ። በስስት ገላዬን ዳሰስኩት። እንደገና ወደራሴ ተመልሻለሁ- ወደ ዲዲሞስ ዶሬ (ይቅርታ ወደ ዶክተር ዲዲሞስ ዶሬ)።

እርቃኔን ነኝ፤ ልክ በገነት ውስጥ ክብሩን እንደተገፈፈው አዳም መለመላዬን ቆሜአለሁ ሀፍረተ ሥጋዬን በሁለት እጆቼ ከድኜ እያንን መፈለግ ጀመርኩ። እርሷም እንደገና ወደ ሰውነት ተለውጣ ይሆን? ልቤ ይመታ ጀመር።

ከስንት ጊዜ በኋላ የልቤን ምት አዳመጥኩት በሞቴ?... በወጣትነቴ ፍቅር ሲይዘኝ ነበር እንዲህ ልቤ መምታቱን የማስታውሰው። ያሁኑን አያርገውና ያኔ የልብ ምት ነበረኝ። ዛሬ ካልደከመኝ በቀር ፍፁም የልብ ምት የለኝም። ለካስ የልብ ምትም ይናፍቃል። ትክክለኛ ስሜት፣ ትክክለኛ የራስ ጠረን፤ የሚወዱት ሰው ጠረን ለካስ እንዲህ ይናፍቃል። ስንቱ የልብ ምቱ ቀዝቅዞ ይሆን? ስንቱ የራሱን ጠረን በትኖ ይሆን?

ወለሉ ላይ የተዘረገፈውን የመጽሐፍ ናዳ እየፈለስኩ እያንን ማሰስ ጀመርኩ። የለችም።

ተጣራሁ።
"እያን! ..." የራሴ የድምጽ ማሚቶ በባዶው የጥናት ቤት ውስጥ አስተጋባ።

"… እያን! …" የሰማዩ ጉርምርምታ እና ንውፅውፅታ ተከተለ። የእያን ድምፅ ግን የውሃ ሽታ ሆነ።

"እያን! … እያን…. እያን!…" ደጋግሜ በኃይል ተጣራሁ።

ከደቃቂዎች በኋላ የሚያቃስት ድምፅ ሰማሁ፤ ከወዲያኛው የግድግዳ ጥግ ነው። በፍጥነት ሄድኩ። እያን እርቃኗን ቆማለች።

"ሰው ሆንኩ!…. ተለወጥኩ!… ዳንኩ!… ይህን ማመን አልችልም!…." ድምፅዋ ይንቀጠቀጣል፤ ሰውነቷ ይንዘፈዘፋል። አቀፍኳት። ትኩስ እንባዋ በደረቴ ላይ ሲንፎለፎል ታወቀኝ።

"አሁንም ድረስ አንገቴ ላይ ሊያርፍ የነበረው ፋስ እየታየኝ ነው። በህይወት አለሁ እርግጠኛ ነህ?…"

"አዎ አለሽ… በህይወት አለሽ እያን ውዴ …."

"እርግጠኛ ነህ?…. "

"አዎ እርግጠኛ ነኝ! ከፈለግሽ ራስሽን በመስታውት ታይዋለሽ።"

" መ… መስታውት የታለ?…."

"ቆይ ልብስ ላምጣልሽ…"

ወጥቼ ወደ ዘበኛው ቤት ሮጥኩ። በዝናቡ ውስጥ እርቃኔን ሲያየኝ ሰይጣን የመጣ መስሎት መደንገጡ የማይቀር ነው። የዘበኛውን ቤት ጠገግ ተጠልዬ ተጣራሁ።

"መሮ! … መሮ!….. መሮ!…."

"አቤት!" አለ መሮ ፎክሮ ከተነሳ በኋላ። "ማነው?!"

"እኔ ነኝ መሮ.. ዲዲሞስ ነኝ።"



"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ!…" መሮ በሩን ከመከፈቱ በፊት ሰይጣን የጠራው መስሎት ጸሎት አደረገ።

"እውነት ከሆን ደግመህ ተናገር!"

"እውነት ነው መሮ… እኔ ዶክተር ዲዲሞስ ዶራ ነኝ።"

ጥቂት አዳመጠና፤

"በስመ አብ በል!" አለ።

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!" ያዘዘኝን ፈፀምኩ።

መሮ በዝግታ በሩን ከፈተና እያማተበ ታዛውን ግራና ቀኝ ተመለከተ።

"መሮ … እንዴት ነህ?!"

ባትሪውን ተግ! አድርጎ አበራብኝ።

"ጋሼ … እረ ምን ጉድ ነው?!"

"አትደንግጥ! …"

"ምነው እርቃንዎን?! … ጋሽዬ እረ ምኑን ነው ምመለከተው? ሰአሊ ለነ ቅድስት… ማን ዘረፈዎ …" ፊቱን ወደኋላ አዙሮ የለበሰውን ብርድ ልብስ አቀበለኝ።

"ወደቤት ግባና ልብስ አምጣልኝ።" አልኩት በሰጠኝ ብርድ ልብስ እርቃኔን ተግኜ ሳበቃ። እየሮጠ ወደ ትልቁ ቤት ገባና ከደቂቃዎች በኋላ ልብስ ይዞልኝ ተመለሰ። እንደገና ያመጣልኝን ነጭ ልብስ ለባብሼ ከጨረስኩ በኋላ ሌላ ልብስ እንዲያመጣልኝ ወደ ትልቁ ቤት ላኩት። አሁንም ከደቂቃዎች ቆይታ በኋላ ሌላ ሙሉ ልብስ ይዞልኝ መጣ። ይህኛው ለእያን ነበር። ወደ ጥናት ክፍሉ ወሰድኩት።

የወንድ ልብስ ቢሆንም ሙሉው ሱፍ በአያን ቁመና ላይ ሂዶ ልክክ አለ። እንዲያውም አማረባት።
ፈገግ አለችና፤

"እንደገና ሰው ሆንኩ ማለት ነው?" አለች ያችን የኦጋዴን ነጭ ጥርሷን እያሳየችኝ። "በፍጹም ላምን አልችልም! እንዴት ላምን እችላለሁ?! ... ራሴን የሆንኩ ስላልመሰለኝ መላ አካሌን ስነካካ ነበር፤ ቃላት ይህን ያህል ኃይል ያላቸው አይመስለኝም ነበር። አውሬም ሰውም የሚያደርጉት ቃላት መሆናቸውን ለማመን በእኔ ህይወት ውስጥ ማለፍን ይጠይቃል።"

"ይገባኛል ይህ እውነት በእኔ ህይወት ውስጥ ተደግሟል" አልኳት። "ቃላት አውሬም ሰውም ያደርጋሉ።"

"እኔ'ምልህ..." አለች እየተቁለጨለጨለች። "ዘበኞቹ ሲያነሷት የነበረችው ሴት... ሚስትህ ናት? ማ... ማለቴ ይቅርታ ልትጠይቅህ መጥታ ነው?...ማ... ማለቴ ይቅርታ ልታደርግላት ነው?..."

"በፍጹም ይቅርታ ላደርግላት አልችልም።"

"ለምን?..." ጠልቀው በሚመረምሩ ዓይኖቿ ጠልቃ ተመለከተችኝ።

"ምክንያቱም ከዚህ ቀደም ይቅርታ አድርጌላታለሁ። ታሪካችንን በዝርዝር አጫውቼሻለሁ። ያንን መድገም አይጠበቅብኝም።" ይህንን ስንነጋገር ምድሩን ያጨላለመው ዝናብ እያባራ ነበር። ጀገጀጉ አበቃ።

ወጥቼ አዲሱን ቀን ሰማዩ ላይ ፈለግሁት። ወገግ ብሏል፤ ፈገግ ብሏል፤ ከኋላዬ እጅ ሲነካኝ ተሰማኝ ዞርኩ። በእንባ ከተሞሉ ዓይኖች ጋር ተገጣጠምኩ።

"ይቅር ባለኝ! ይህን ስል እያፈርኩ ነው። ይህን ስል በፀፀት ውስጤ እየታመሰ ነው። ላንተ የማይገባውን ሁሉ





አድርጌብሃለሁ! ጠላትህን አግብቼብሃለሁ..." ኤፍራታ ናት። ተንበረከከች።

አያን ከጥናት ክፍሉ ስትወጣ ተመለከትኳት። ነጭ ሱፍ ለብሳ ሳቢሳ መስላለች። ሱፍ ሴት ላይ እንዲህ ያምራል እንዴ? የለበሰችው ነጭ ልብስ ንፅህናዋን ለማሳየት ቃፊር የቆመ ይመስል መልአክ አስመስሏታል።

የኤፍራታ ቀንድ ግንባሯ ላይ ሲቆም ተመለከትኩ።

"ይህቺ ደግሞ ማን ናት?!" ከተንበረከከችበት ፈጥና ተነሳች።

"ማንስ ብትሆን? ..." በለሆሳስ መለስኩላት። "ይህ አንቺን አይመለከትም!"

"አይደረግም!"

"ተደርጓል! ላገባት ነው። ሠርጋችን በቅርቡ ይደገሳል። ከፈለግሽ መገኘት ትችያለሽ፤ ተጠርተሻል።"

አያን ፈገግ አለች፤ ኤፍራታ እሳት ለበሰች።

"እንቃታለሁ! የባሌን ልብስ አውልቂ አንቺ ስድ!"

"ከፈታሽኝ አራት አመታት ተቆጥረዋል! አይደለም እንዴ?"

"እንግዲያውስ በትዳር ላይ ትዳር በመመስረትሽ ወንጀለኛ ነሽ።"

"አይደለሁም!... ሞተህ ነበር።"

"መቼ ቀብረሽኝና ነው?"

"ባልቀብርህም ሞተህ ነበር።"

"አልሞትኩም! ሞተሽ የነበርሽው አንቺ ነሽ። በምድር ላይ የሚጠላኝንና፣ በህብቴ ብቻ ምራቁን ሲውጥ የኖረውን ጓደኛዬን አግብተሽ ነበር የጠበቅሽኝ! ይህ ሀገር የሚያውቀው ሀቅ ነው። የእኔ ስህተት በስህተት አንቺን



t.me/BooksandYou

አስመግደሌ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ከመግደል የበለጠ በቀል ነው! ይገባሻል አይደል?...ስለዚህ የሞትሽው አንቺ እንጂ እኔ አይደለሁም።... እኔ አንቺን ብሆን ኖር እኔን ፍለጋ አልመጣም ነበር። ሌላው ይቅርና ልጆችሽን እንኳ ዘወር ብሎ ያላሰበ ልብሽ ዛሬ ምን ተፈጠረና ነው እኔን ፍለጋ የመጣሽው? ... የቀረችኝን ልብ ልትርባት! ተይኝ! ከህይወቴ ውጭልኝ!" በዚህ ሰዓት ድምጼን የሰሙት ልጆቼ እየተንደረደሩ ደረጃውን ሲወርዱ ተመለከትኩ።

"አባዬ!... አባዬ!..." ነፍሳቸው በደስታ ሲቃ ልትመነጠቅ ምንም አልቀራት።

"አባዬ አለ! አልሞተም!..."

መላእክትን ይመስላሉ። ተንበርክኬ፣ እጆን ከፍቼ ጠበኳቸው። ተስገብግበው አቀፉኝ። አንገታቸው ስር የማውቃትን፣ ማንም ኬሚስት ሊቀምማት የማይችል ጠረናቸውን ማግኙት።

"እማዬ እኮ ሞቷል ብላን ነበር።"

"እርሷ ሁሌም እንደዚህ ነው የምትለው። እናንተን ትቼ ሳለመሞት ብዬ ብዙ ችግር አልፌ ነው የመጣሁላችሁ። ህልም ያለው ሰው በከንቱ አይሞትም። ህልሞቼ እናንተ ናችሁ።"

"አባዬ ... ከዚህ በኋላ ትተኸን አትሄድም አደል?" አለች ሴቷ ልጄ ጥብቅ አድርጋ አቅፋኝ።

"በፍፁም ትቻችሁ አልሄድም። ለሥራ እንደሄድኩ ታውቃላችሁ። አይደለም እንዴ?... ብርድ ነው ግቡ። በኋላ የማጫውታች ብዙ ነገር አለኝ። ግቡ።" ልጆቼ የእኔና የእርሷን ጭቅጭቅ እንዲሰሙ አልፈለኩም።



# ፵፩

ኤፍራታ ግቢውን ባንድ እግሩ ታቆመው ጀመር።

"ስሚ አንቺ ወፍ ዘራሽ! አሁኑኑ ግቢዬን ለቀሽ ውጪልኝ!" ኤፍራታ ተንጨረጨረች።

"ያንቺ ግቢ አይደለም!" ደሜ ፈላ። "ሄጂና ከዛ አውሬ ብብት ሥር ተወሸቂ። እኔ በአንቺ ዘንድ ሞቻለሁ። በምድር ላይ የለሁም።"

"እሱም የለም።" አለች እያነፈረቀች።

"ጥሎሽ ሄደ? ጠገበሽ?... የእጅሽን ነው ያገኘሽው!... ሁሉንም ሰምቻለሁ። ሜንጦ ውበትሽንና ሀብትሽን አሟጦ ጥሎሽ ሄዷል።መራራውንና የዘገየውን ፅዋሽን አስጎንጭቶሽ ክዶሽ ላይመለስ ሄዷል።"

"እባክህን እንደዚህ አትበል..." ትንሰቀሰቅ ጀመር። "እባክህ ይቅር በለኝ።"

"ያኔ.... አንቺ ብትሆኚ ኖሮ ለማንም የማታደርጊውን ይቅርታ አድርጌልሻለሁ። ያ ይቅርታ ለአንቺም ለሜንጦም አይገባችሁም ነበር። በልጆቼ እናት ላይ እጄን አላነሳም ብዬ እንጂ እንደ ሥራሽ ቢሆን ኖሮ በምድር ላይ መኖር አልነበረብሽም ነበር። ያን ሁሉ በደል በልጆቼ ፊት ነው የፈፀምሽብኝ።"

"አሁን የድሮዋ ኤፍራታ አይደለሁም! ሁሉንም ነገር የማስተካክልበት እድል ልትሰጠኝ ይገባል። እሱን አብረን ስንኖር የምታየው ይሆናል።"

"በፍፁም አብረን አንኖርም!"

"እባክህ ይቅር በለኝ?!" ኤፍራታ እግሬ ስር እንደገና ተንበረከከች።

"ይቅርታ አድርግላት የልጆችህ እናት ናት" አለች አያን ወደ ግቢው በር እየተራመደች:: "ችግርህ ልሆን እዚህ ድረስ አልመጣሁም:: ወደ ሰውነቴ መመለሴ በቂ ነው::" የእንባ ሳግ እየተናነቃት መሆኑን ከድምፅዋ አወጣጥ ተረዳሁ::

ኤፍራታን በተንበረከከችበት ትቻት ወደ አያን ሮጥኩ:: የግቢውን በር ከመክፈቷ በፊት ደረስኩባትና እጇን ለቀም አድርጌ ወደ እኔ አዞርኳት:: ጉንጯ በእንባ ዳክሯል::

"ውስጤ ነግሮኝ ነበር:: ውስጤን ማዳመጥ አቅቶኝ ነው" አለች እንባዋን እየሞዠቀች:: "ሚስትህ አንተን የመሰለ ሰው መጣሏ ቆጭቷት አንድ ቀን ወዳንተ እንደምትመለስ አስቤ ነበር:: ይህን እያሰብኩ እንኳ አፍቅሬህ ነበር:: ቁስሌን ሁሉ የምትጠግንልኝ መድኃኒቴ አንተ እንደ ሆንክ አስቤ ነበር:: ሳላስበው ነው:: በደንብ አላሰብኩበትም:: ፍቅር እንደ ውሃ ሙላት እያሳሳቀ ነው የወሰደኝ:: ተሳስቻለሁ::"

"አልተሳሳትሽም:: እኔም አፍቅሬሻለሁ:: ሰውም አውሬም ሆነሽ ከእኔ ጋር ብዙ መከራ አሳልፈሻል:: አዲስ አበባ ገብተን ሰው ከሆንን በኋላ እንደማገባሽ ድመት ሆኜ እንኳ እያሰብኩ ነበር::"

"በፍፁም አይሆንም:: ...ለልጆችህ ስትል ይቅርታ አድርግላትና ከእርሷ ጋር ኑር::"

"አላደርገውም! ልጆቼን አንቺም እናት እንደ ምትሆኛቸው አምናለሁ:: ልጆቼም ቢሆኑ አድገዋል:: አራት አመት ሙሉ እናትም አባትም ሆኜ አሳድጌአቸዋለሁ:: ያኔ ዞር ብላ አላየቻቸውም:: ለምን አሁን እንደመጣች ታውቂያለሽ?" አልኳት እንደገና በጉንጯ ላይ የሚፈስ እንባዋን እየጠረኩ:: "አሁን ወደ እኔ





የመጣችው፣ እኔን ትታ ያገባችው ጓደኛዬ የነበረው፣ ጉያዬ ውስጥ ተወሽቆ ምርጥ ጠላቴ የነበረው ሜንጦ፣ ሀብቷን ሁሉ ሽጦ ውበቷን ሁሉ አሟጦ ጥሏት ስለሄደ ብቻ ነው:: አልደብቅሽም:: እርሱ እያለ እኔን መርጣ እንደገና ብትመጣ ኖሮ በደሌን ለፈጣሪ ሰጥቼ እቀበላት ነበር:: አሁን ግን እንደዛ አይደለም::"

"ትክክል ነህ!" የሚል ድምፅ ከኋላዬ ሰማሁና ዞርኩ:: ራሷ ኤፍራታ ነበረች:: የሆነ ብልቃጥ ነገር በቀኝ እጇ ይዛለች:: "ያኔ ያደረክልኝ ይቅርታ ራሱ የማይገባኝ ነበር:: አሁን የምፈልገው..." ድምፅዋ ተንቀጠቀጠ:: "አሁን የምፈልገው ፍፁም ይቅርታ እንድታደርግልኝ ብቻ ነው:: የበደልኩህ በደል የአንተን ቀርቶ የእኔንም አጥንት ዘልቆ እየተሰማኝ ነው:: ሜንጦ ንብረቴን በሙሉ ወስዶታል:: እርቃኔን ቀርቻለሁ:: ሃብቴን ብቻ አይደለም የወሰደብኝ:: የአንተንም ፍቅር ነጥቆኛል:: የሚወድህን ሰው ከማጣት በላይ ማጣት የለም:: ማጣትህ ዘልቆ የሚሰማህ የሚወድህንና የምትወደውን ሰው ያጣህለት ነው:: ልክ ነህ:: ከዚህ በላይ ላቆስልህ አይገባም:: እውነቱን ልንገርህ?" አለችና እጇን ስባ ሆዷ ላይ አደረገችው::

"ምንድን ነው?"

"ከሜንጦ አርግዣለሁ:: ከእባብ ባረግዝ ይሻለኝ ነበር:: እንዲህ ሆኜ ነው ጥሎኝ የሄደው:: የእርሱን ዲቃላ መቼም አልወልድም::" የያዘቻውን ብልቃጥ ከመ ቅፅበት ወደ አፏ አስጠጋችውና ኸረው አድርጋ ጠጣችው::

"ምንድን ነው?" ሳላስበው ጮህኩ:: ልጆቼም እንደገና እየተሯሯጡ መጡ::

"ይቅር በለኝ! እባክህ ይቅር በለኝ!" ስትል ቆየችና እጄን እንደያዘችኝ እጥፍጥፍ ብላ ወደቀች::

"እማዬ!" ልጆቹ ተጯጯሁ። ቀለብና መሮ እየሮጡ መጥተው ለማንሳት አገዙኝ።

"ኤፍራታ!" ሁሉ ነገር ዞረብኝ። "ጨካኝ ነሽ! ለልጆችሽ እንኳ መኖር ነበረብሽ… ጨካኝ ነሽ! … ጨ …. እሺ ይቅር ብዬሻለሁ። ይ…ቅ…ር…ታ…" ከመሮ ጋር ተጋግዘን መኪናዬ ውስጥ አስገብተናት ወደ ሐኪም ቤት በረርኩ።

----------* --------------* ----------

ድካማችን ከንቱ ነበር። ሐኪሙ ህይወቷ ማለፉን የነገረን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ነበር። አምርሬ አለቀስኩ። በቀብሯ ሰዓት ሳይቀር ለያዥ ለገናዥ አስቸገርኩ። የኤፍራታ የሕይወት መቅኖ ከንቱ መሆኑ ብቻ አልነበረም ያስለቀሰኝ። ምንም ቢሆን የልጆቼ እናት ናት። የልጆቼን እንባም መቋቋም አልቻልኩም። በደሏ ሁሉ እንደ እርሷው በድን ሆኗል። ሞቷል።

በኤፍራታ ቀብር ላይ፣ አያን ሳትቀር አምርራ ስታለቅስ አይቻለሁ። ታሪካችንን የሚያውቅ ሰው ሁሉ ቀብሯ ላይ ያላለቀሰ አልነበረም።

----------* --------------* ----------

አያን፣ የኤፍራታን ሰማኒያ እስካወጣ ድረስ እያፅናናችኝ አብራኝ ከረመች። ልጆቼ አልጠሏትም። እንዲያውም ቀስ በቀስ ወደዋታል። ትምህርት ቤት የማመላለሱ ሥራም የእርሷ ነበር።

ከኤፍራታ ሰማኒያ አንድ ሳምንት በኋላ፣ በአንዲት ብሩህ ጠዋት ፀሐይ እየሞኩ ስቆዝም፤

"ወደ ኦጋዴን መሄዴ ነው።" የሚል ድምፅ ከጀርባዬ ሰማሁ። ዞርኩ። አያን ሻንጣዋን ሸክፋ ለመሄድ ተነስታ ነበር። አፌ ደረቀ።

"ም--- ም ---- ምን?"





"ተሸናፊ መሆን አልፈልግም። አንተ የተፅናናህ ይመስለኛል። እዛ ግን ብዙ ፅናት የሚጠይቅ ሥራ አለብኝ። የአቅሜን ያህል ያንን አካባቢ ለመለወጥ እታገላለሁ።"

"አይሆንም!" ተከተልኳት።

"ቀብሬ ኦጋዴን ውስጥ ይሆናል። የዚያ ህዝብ ሕይወት መለወጥ አለበት። በዛ በረሃ ውስጥ አንዲት ጠብታ እንኳ መሆን አለብኝ።"

"አያን!" እጇን ያዝኳት። "እኔም ካንቺ አልለይም። ቀጣዩ ሕይወቴ ስለ ኦጋዴን ማጥናትና ማስተማር ነው። አብረን ሄደንም የዛን አካባቢ ስቆቃ ለዓለም ማሳወቅ ነው። ታላቁ የለውጥ መሣሪያ ትምህርት ቤት እናቋቁማለን። ትምህርት ነው። የቻልነውን ያህል ለለውጡ እንታገላለን። ከዛ በፊት ግን…." ወደ ቤት ሮጬ ገባሁና አስቀድሜ አዘጋጅቼላት የነበረውን ስጦታ ይዤ ተመለስኩ። ልጆቼንም አንድ ምስጢር ነግሬ ይዣቸው መጥቻለሁ። ከአልማዝ በነገርኳቸው መሠረት በግራና በቀኙዋ ቆሙ። ከአልማዝ ፈርጡ የሚንቦገቦገውን ቀለበት በጣቷ ላይ የተሠራውንና ሳስገባ ዕንባዋን መቋቋም አቅቷት ነበር።

"እነዚህን ከኦጋዴን ድምፆች የተረፉ ልጆቼንም ተረከቢኝ! ሰጥቼሻለሁ!" ሁለቱም ተጠመጠሙባት። ዕንባዋን አበሱላት። በደስታ ሲቃ ተውጣ አቀፈችኝ። ከልጆቼ ጋር አቀፍናት።

----------* --------------* ----------

አስተያየተዎን ከዚህ በሚከተለው አድራሻ ቢልኩ ለደራሲው ይደርስልዎታል።

E-mil:- ramatohara@gmail.com



"ከአገሬ አፈር የሚያባልቅ ቤልጅግና ነራዶ ይገኙ እንጂ
ሚት ተሸከሚ የምመጣ እንዳይመስልህ!"

እዮር ሰማተር

• ...በእግራቸው ሥር ተሽሎከሎቴ ገቡ፡፡ እመሃላቸው ወፍራም ግንድ ተጋድሚል፡፡ በግንዱ ላይ ደማሞ ያእያንኤንገት አርፏል፡፡ የሚያብለጨልጭ ሩስ የያዘ ፈርጣማ ወንበዴ መፍለጫውን እንቱ ላይ ሰማሰረፍ የአለቃውን ትዕዛዝ በመጠበቅ ላይ ነው፡፡

• ...ህፃን በወታደሮች እጅ ወደቀች፡፡ በአስቃቂ ሁኔታ ተደፍራ ባመጨረሻም ተገደላ፤ በጎዴ ጎዳና ላይ ሰዓይን የሚዘገንን በድና ለመቀጣሚነት ተጣለ፡፡ ያቺ የዋቢ ወንዝ ዳር አበባ የምስለች ውቧ ህፃን ፈራረሰች፡፡ እስከተፈራርስ ድረስ በድኗን ለመቅበር የደፈረ እንኳ አልነበረም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ለኢትዮጵያ መንግሥት እንደምትሰልል በመጠርጠሯ ነው፡፡

• ...ነዋሪዎች የጦርነት ቀጠና የሆነችውን ከተማ ለቀው ሲወጡ ድመቶች የወዳደቀውን አስከሬን ቀመሱ፡፡ ስደተኞች ሲመለሱ ከተማዋ በድመት መንጋ ተወራ ጠበቀቻቸው፡፡ ድመቶች የሰው ሥጋ ለምደው ነበር፡፡ የቤታቸው ድመት ወደ አውሬነት ተቀይሮ ጠበቃቸው። ልጆቻቸውን፣ ወተት እጠጥተው ያሳደጓቸው ድመቶቻቸው ነጠቋቸው፡፡ የእኔም እናት ህፃን ልጇ ጠፍቶባት ስትፈልግ ስንብታ ይህን ወሬ ትሰማና የቤቷን ታዛ ስታስስ ትንንሽ የህፃን አጥንቶች ታገኛለች፡፡ ልጇን ድመቶች ተቀራምተውት ነበር፡፡ ልጇን ድመት እንደበላባት ሲገባት በቁሟ ተዝለፍልፋ ወደቀች፡፡ አልተነሳችም፡፡

• ...ኦጋዴን ውስጥ በነዳጅ ቁፋሮ ላይ የተሰማሩት ፔሽኮ፣ ኒው ኤጅ፣ ሳውዝ ዌስት ኢነርጂ፣ ፓሊግሩፕ ኮርፓሬሽን እና ዣንግያን የተባሉት ኩባንያዎች ቢሆኑም፣ ዣንግያን የተባለው የቻይና ኩባንያ ግን በተፈፀመበት አሰቃቂ ጥቃት ጥሎ ወጥቶ እንደነበር ይታወቃል፡፡

• ..."ነዳጁም ይወጣል! ደሙም ይፈስል!..."

ሶስተኛው ሰው

199 ብር

t.me/BooksandYou